## የጎልማሶች ሰንበት ትምህርት፡የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያ
## መደበኛ እትም

# በክርስቶስ አንድ መሆን

የትምህርቱ አዘጋጆች ፡ ዴኒስ ፎርቲን

ዘካሊዎ አሰረስ እንደተረጎመው

ይህ የጎልማሶች ሰንበት ትምህርት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያ የሚዘጋጀው በሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን ዋና መስሪያ ቤት በሆነው በጀነራል ኮንፍረንስ ውስጥ ሆኖ፤ የጎልማሶች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያን በሚያዘጋጀው ቢሮ ነው፡፡ መምሪያዎቹ የሚዘጋጁት የጀነራል ኮንፈረንስ አስተዳደር ኮሚቴ ንዑስ ኮሚቴ በሆነውና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያዎችን በሚያሳትመው የሰንበት ትምህርት ሕትመት ቦርድ ነው፡፡ የታተመው መምሪያ በውስጡ ዓለም አቀፋዊ የሆነ የምዘና ኮሚቴ ሀሳቦችንና የሰንበት ትምህርት ሕትመት ቦርድን ማረጋገጫ ስለሚያንጸባርቅ የአዘጋጁን (የአዘጋጆችን) ሀሳብ ብቻ የሚወክል አይደለም፡፡ በተለየ ካልተጠቀሰ በቀር በዚህ ሰንበት ትምህርት ጥቅም ላይ የዋሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በሙሉ የተወሰዱት ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው፡፡

በኢትዮጵያ አድቬንቲስት ማተሚያ ቤት ታተመ

4ኛ ሩብ ዓመት

ከ ከመስከረም 19 - ታህሳስ 19 2011 ዓ.ም

# ማውጫ

| አርዕስት | ቀን | ገጽ |
| --- | --- | --- |
| 1. ፍጥረት እና ውድቀት | ከመስከረም 19 - 25 | 5 |
| 2. የመለያየት መንስዔዎች | መስከረም 26 - ጥቅምት 2 | 14 |
| 3. "ሁሉም አንድ እንዲሆኑ" | ከጥቅምት 3 - 9 | 24 |
| 4. የኅብረት ቁልፉ | ከጥቅምት 10 - 16 | 33 |
| 5. በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን የተስተዋለው ኅብረት ተሞክሮ | ከጥቅምት 17 – 23 | 42 |
| 6. የኅብረት ገጽታዎች | ከጥቅምት 24 – 30 | 51 |
| 7. ግጭቶች ሲከሰቱ | ከሕዳር 1 – 7 | 60 |
| 8. በእምነት ውስጥ ያለ አንድነት | ከሕዳር 8 - 14 | 68 |
| 9. እጅግ የላቀው አሳማኝ ማስረጃ | ከሕዳር 15 – 21 | 76 |
| 10. ሕብረት እና የፈረሱ ግንኙነቶች | ከሕዳር 22 – 28 | 85 |
| 11. አንድነት በአምልኮ ውስጥ | ከሕዳር 29 - ታህሳስ 5 | 94 |
| 12. የቤተ ክርስቲያን ድርጅትና አንድነት | ከታህሳስ 6 – 12 | 103 |
| 13. አንድነትን ወደ ቀደመ ንጽህናው መመለስ | ከታህሳስ 13 – 19 | 112 |

# መግቢያ

ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤተሰቦች አገልግሎት የሚሰጡባት፣ ቃሉን የሚያጠኑባትና ሥግደት የሚያቀርቡባት ስፍራ ናት፡፡ የሱስን እንደ መሪዋ እና ቤዛዋ የምትመለከተው ቤተ ክርስቲያን መልካሙን የደኅንነት የምስራች ለመላው ሰብዓዊ ዘር እንድታደርስ ተጠርታለች፡፡

የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን መሰረታዊ እምነቶች በቅደም ተከተል በቀረቡበት ተራ ቁጥር 12 በከፊል የሚከተለውን ሀሳብ እናገኛለን "ቤተ ክርስቲያን የየሱስ ክርስቶስን ጌትነትና አዳኝነት አምነው የተቀበሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች አካል ናት፡፡ በአንድነት አምልኮ እንድናደርግ፣ ኅብረት እንድንፈጥር፣ ቃሉን እንድናስተምር፣ የጌታ እራት መታሰቢያን እንድናከብር፣ ለመላው ሰብዓዊ ዘር አገልግሎት እንድንሰጥና ወንጌልን ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ በማወጅ ከብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝቦች ጋር ቅብብሎሽ እንድንፈጥር እነሆ ከዓለም ተጠርተናል፡፡"—Seventh-day Adventists Believe (Boise, Idaho: Pacific Press© Publishing Association, 2005) p. 163.

በነገራችን ላይ፤ ቤተ ክርስቲያን ስንል ምን ማለታችን ነው? የቤተ ክርስቲያን ሰው ማን ነው? የእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ለቤተ ክርስቲያን በምንሰጠው ፍቺ ላይ ይወሰናል፡፡

በእርግጥ ቤተ ክርስቲያን ጌታን የሚታዘዙ፣ ለአምልኮና ለአገልግሎት በአንድነት የሚሰበሰቡ በየሱስ የሚያምኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፡፡ እነዚህ ወገኖች በመኖሪያ ቤት ወይም ከፍ ባለ የጉባዔ አዳራሽ በአንድነት ይሰባሰባሉ (ሮሜ 16፡10-11)፡ ፡ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን ስንል ክርስቲያኖች የሚሰበሰቡበትን ሕንፃ ማለታችንም ነው፡፡ ሆኖም ይሄኛው ፍቺ እምብዛም አያስኬድም፡፡ ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን የተሰኘው ቃል ቀጥተኛ ተዛምዶ ከምዕመኑ እንጂ ከሕንፃው ባለመሆኑ ነው፡፡

ቤተ ክርስቲያን በአንድ መልክአ ምድር የሚገኙ የተወሰኑ አማኞችን የምትወክልበት ሁኔታ አልፎ አልፎ በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ተንጸባርቆአል፡፡ ይህን ተከትሎ ጳውሎስ ለገላትያ ቤተ ክርስቲያን ሲጽፍ በዚያ ክልል ብዛት ባላቸው ከተሞች እና ቀበሌዎች ይገኙ የነበሩ ምዕመናንን ጠቅሶአል (ገላ. 1፡2፣ 1ጴጥ. 1፡1)፡፡ አንዳንዴ ቤተ ክርስቲያን--የአንድ ኃይማኖታዊ አስተምህሮ ተከታዮች ወይም እምነታቸውንና የያዙትን ቅርስ የሚወክል የራሳቸው የሆነ የተለየ መጠሪያ ያላቸው ሕዝቦች የሚል አንደምታ አለው፡፡

ሆኖም እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው ፍቺዎች በሙሉ ምሉዕ ናቸው ለማለት አያስደፍርም፡፡ ቤተ ክርስቲያን በምድር ዙሪያ የሚገኙ የእግዚአብሔር ሕዝቦች

ናቸው፡፡ ምንም እንኳ ክርስቶስ በተለያዩ ኃይማኖታዊ ተቋማት ታማኞች ቢኖሩትም (አብዛኞቹ በመጨረሻው ቀውስ ወቅት የእግዚአብሔርን ትሩፋን ይቀላቀላሉ /ራእ. 18፡1-4/)

በዚህ ሩብ ዓመት ትኩረታችንን በሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን ላይ በማድረግ በክርስቶስ አንድ መሆን ለእኛ ያለውን አንደምታ እንመለከታለን፡፡

የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን መሰረታዊ እምነቶች በቅደም ተከተል በቀረቡበት ተራ ቁጥር 14 የሚከተለውን እናገኛለን “ቤተ ክርስቲያን ከእያንዳንዱ ዜጋ፣ ወገን፣ ቋንቋ እና ሕዝብ የተውጣጡ አያሌ አባላት ያሏት አንድ አካል ናት፡፡ እኛ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረቶች እንደ መሆናችን የዘር፣ የባህል፣ የትምህርት፣ የብሔር ወይም ከፍታ፣ ዝቅታ፣ ሀብታም፣ ደሃ፣ ወንድ፣ ሴት--መሃላችን ገብቶ ሊከፋፍለን አይገባም፡፡ እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ ከራሱና እያንዳንዳችንን ከሌላው ጋር ወደ ሕብረት ባመጣን በክርስቶስ እኩል ነን፡፡ ያለ አድሎ እና ያለ ገደብ እናገለግላለን--እንገለገልማለን፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ በተገለጠው በየሱስ ክርስቶስ አንድ ዓይነት እምነት እና ተስፋ እየተጋራን እንደ አንድ አካል ወደ ሁሉም በመድረስ እንመሰክራለን፡፡ የዚህ ኅብረት ምንጩ ልጆቹ አድርጎ የተቀበለን የሕያው እግዚአብሔር አንድነት ነው፡፡”— Seventh-day Adventist Believe, p. 201.

በቀደሙት ጊዜያት፣ ዛሬም ሆነ እስከ ጊዜው መጨረሻ በዚህ ኅብረት ላይ ተግዳሮት መኖሩ እሙን እንደመሆኑ፤ እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት--በአማኞች ኅብረት ርዕሰ ነጥብ ዙሪያ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎችን ማቅረብ የዚህ ተያያዥነት ያለው ትምህርት ዓላማ ነው፡፡ በክርስቶስ አንድ ሆነን እንዴት መኖር እንዳለብን አስመልክቶ በመጽሐፍ ቅዱስ አያሌ ብርሃኖችና መመሪያዎች ተሰጥተውናል፡፡ እነዚህ የተሰጠንን ኅብረት በቤተ ክርስቲያን ገልጠን እንድናሳይ የሚያስችሉን ብርሃኖች እና መመሪያዎች የዚህ ሩብ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን ትኩረት ይሆናሉ፡፡

የዚህ ትምህርት አዘጋጅ የሆኑት ዴኒስ ፎርቲን በቤሪን ስፕሪንግስ ሚቺጋን ዩኒቨርሲቲ፤ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ነገረ መለኮት የትምህርት ክፍል ፕሮፌሰር ናቸው፡፡ ዴኒስ በጎርጎሮሳውያኑ አቆጣጠር 1994 ይህን ተቋም ከተቀላቀሉ በኋላ የሥነ መለኮት የትምህርት ክፍል የማስተርስ መርኀ ግብር ዳይሬክተር፣ እንዲሁም ቀደም ሲል ረዳት ዲን እስከ ቅርብ ጊዜ ደግሞ (2006 - 2013) ዋና ዲን ሆነው አገልግለዋል፡፡

## 1ኛ ትምህርት ከመስከረም 19 - 25

# ፍጥረት እና ውድቀት

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ዘፍ. 1:26, 27፣ 1ዮሐ. 4:7-8፣ 16፣ ዘፍ. 3:16–19፣ ዘፍ. 11:1–9፣ ገላ. 3:29፣ ዘዳ. 7:6–11፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ**፡- "ወደ ውጪም አውጥቶ፣ 'ቀና ብለህ ወደ ሰማይ ተመልከት፤ እስቲ መቁጠር ከቻልህ፣ ከዋክብቱን ቁጠራቸው፤ ዘርህም እንዲሁ ይበዛል' አለው፡፡ አብራም እግዚአብሔርን አመነ፤ እርሱም ጽቅ አድርጎ ቆጠረለት" (ዘፍ. 15፡5-6)፡፡

የእግዚአብሔር ሕዝቦች ታሪክ በሰብዓዊው ፍጥረትና በአሳዛኙ የኃጢአት ውድቀት ይጀምራል፡፡ የቤተ ክርስቲያናዊውን ኅብረት ተፈጥሮ ለማስተዋል የሚደረግ ማንኛውም ዓይነት ሙከራ ከቀደመው አምላካዊ የፍጥረት ዕቅድ እና ከውድቀት በኋላ ባስፈለገው ወደ መጀመሪያው ንጽህና የመመለስ ተግባር ሊጀምር የግድ ይሆናል፡፡

ሰብዓዊው ፍጡር በአንድ ቤተሰብነት እንዲጸና የእግዚአብሔር ሀሳብ መሆኑን የመጀመሪያዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎች ይፋ ያደርጉልናል፡፡ የመለያየትና የመከፋፈል ሥር እንዲሰድና ያለመታዘዝ ውጤት አብልጦ እንዲንሰራፋ መንስዔው ኃጢአት ብቻ ነው፡፡ አዳምና ሔዋን ከተከለከለው ዛፍ ፍሬ ከበሉ በኋላ (ዘፍ. 3፡ 11) እግዚአብሔር ለመጀመሪያ ጊዜ ሲገናኛቸው የተስተዋለው መስተጋብር ለዚህ መለያየት ፍንጭ ይሆነናል (ዘፍ. 3፡11)፡፡ በመሆኑም ይህን ኅብረት ወደ ቀደመው ሁኔታ መመለስ የደኅንነት እቅድ ከሚፈጽማቸው ተግባራት መካከል አንዱና ወሳኙ ነው፡፡

የእግዚአብሔር ሕዝቦች አባት ተብሎ የሚጠራው አብርሃም በአምላካዊው የደኅንነት እቅድ ቁልፍ ሚና መጫወት የቻለ ሰው ነበር፡፡ አብርሃም የ "ጽድቅ በእምነት" (ሮሜ 4፡1-5) ታላቅ ምሳሌ ሆኖ በመጽሐፍ ቅዱስ የቀረበ ሲሆን፤ ይህ እምነት የእግዚአብሔር ሕዝቦችን እርስ በርስ ብሎም ከራሱ ከጌታ ጋር በአንድ ያስተሳስራል፡፡ እግዚአብሔር የቀደመውን ኅብረት ለመመለስና ለጠፋው ሰብዓዊ ዘር ያለውን አምላካዊ ፈቃድ ለማሳወቅ በሕዝቡ አማካይነት ይሠራል፡፡

**እሁድ** **መስከረም 20**

## ፍቅር፡ እንደ ኅብረት መሰረት

በዘፍጥረት መጽሐፍ ምዕ. 1 እና 2 የፍጥረትን ታሪክ አማክሎ የሚፈሰው ግልጽ መልእክት በፍጥረት ሣምንት መጨረሻ ገቢራዊ ከሆነው አጠቃላይ ትዕይንት ጋር ስምምነትና ውህደት አለው፡፡ እግዚአብሔር በመጨረሻ ላይ የተናገራቸው ቃላት “እጅግ መልካም ነበረ” (ዘፍ. 1፡31) የሚሉ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ አባባሉ እግዚአብሔር ይህን ዓለም እና የሚኖሩባትን ሰዎች ፈጥሮ ሲጨርስ የተስተዋለውን ሥነ ውበት የሚያንጸባርቅ ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ዓይነት ክፉ ወይም ተቃርኖ በስፍራው አለመኖሩን ጭምር አመላካች ነበር፡፡ የቀደመው የእግዚአብሔር የፍጥረት ዓላማ እያንዳንዱ የእጁ ሥራ እርስ በርስ ተስማምቶና ተደጋግፎ አብሮ የሚኖርበትን ብልሃት ያካተተ ነበር፡፡ ምድር ለሰብዓዊው ቤተሰብ ውብ ሆና ተፈጥራ ነበር፡፡ ሁሉም ነገር ፍጹምና የከበረውን የፈጣሪ ማንነት የሚያሳይ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ለዓለም የነበረው የቀደመ ሀሳብ እና ዓላማ ለዛ ያለውን ስምምነት፣ አንድነትና ፍቅር የተላበሰ ነበር፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዘፍ. 1፡26-27፡፡ ሰብዓዊው ፍጡር በዘፍ. ምዕ. 1 እና 2 ከቀረቡት ሌሎች ፍጥረታት ይልቅ ተወዳዳሪ የማይገኝለትና ድንቅ ስለመሆኑ ጥቅሶቹ ምን ያስተምሩናል?

---

---

የዘፍጥረት መጽሐፍ እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ መፍጠሩን ይነግረናል፡፡ ስለ ሌሎች ፍጥረታት ያልተባለውን ያህል ስለ ሰው አፈጣጠር መነገሩን እንመለከታለን፡፡ “እግዚአብሔር ‘ሰውን በመልካችን፣ በአምሳላችን እንሥራ ... አለ፡፡’ ስለዚህ እግዚአብሔር ሰውን በራሱ መልክ ፈጠረው፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፡፡” (ዘፍ. 1፡26-27)፡፡ ምንም እንኳ የነገረ መለኮት ምሑራን በዚህ መልክ ትክክለኛ ተፈጥሮ እና በራሱ በእግዚአብሔር ባህሪ ዙሪያ ለብዙ ምዕተ ዓመታት ቢሞግቱም፤ አብዛኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የእግዚአብሔርን ባህሪ የሚያቀርቡት ፍቅር መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ 1ዮሐ. 4፡7-8፣ 16፡፡ እኛ መጀመሪያ እንዴት እንደተፈጠርን ማስተዋል እንድንችል ጥቅሶቹ በምን መልኩ ይረዱናል? ሁናቴው በፍጥረት ወቅት የምናገኘውን የቀደመ ኅብረት እንዴት ሊነካ ይችላል?

---

እግዚአብሔር ፍቅር ነው፡፡ እንዲሁም የሰው ልጆች ማፍቀር የሚችሉ ፍጥረቶች እንደ መሆናቸው (የተቀሩት የምድር ፍጥረታት የዚህ ጸጋ ተቋዳሽ አይደሉም) በአምላካዊው አምሳል መፈጠር ማለት ማፍቀር መቻልን ማካተቱ የግድ ይሆናል፡ ፡ ይሁንና ፍቅር ከሌሎች ጋር ባለ ግንኙነት ብቻ ሊፈጠር ይችላል፡፡ ስለዚህ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ማንኛውም ፍጡር ይህን ባህሪ--ማለትም ማፍቀር የመቻልንና በጥልቅ የመውደድ ችሎታን ማካተቱ የግድ ይሆናል፡፡

## ሰኞ

## መስከረም 21

## የውድቀት መዘዝ

ውድቀትን ተከትሎ የመጣው ጦስ እንዲህ በዋዛ ተዘርዝሮ የሚያበቃ አይደለም፡፡ የአዳምና ሔዋን አለመታዘዝ በሁሉም ሕይወት ባላቸው ፍጥረታት መካከል በነበረው ስምምነት ላይ መቃቃር ፈጠረ፡፡ እንደውም ይባስ ብሎ ዛሬ ድረስ በሰው ልጆች መሃል አለመስማማት፣ ብጥብጥ፣ አለመግባባትና ክፍፍል እንዲጠነሰስ መንስዔ ለመሆን በቃ፡ ፡ አዳምና ሔዋን ለደረሰባቸው ውድቀት አንዱ በሌላው ላይ በማመካኘት ሳይውል ሳያድር ወዲያውኑ፣ እርስ በርሳቸውም ሆነ ከሌላው ጋር የነበራቸውን ውህደት አጡ (ዘፍ. 3፡12-13)፡፡ ከዚያን ጊዜ ወዲህ ነገሮች እየከፉ ሄዱ፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዘፍ. 3፡16-19፣ 4፡1-15፡፡ እግዚአብሔር በፈጠረው ለዛ እና ስምምነት በነበረው ዓለም ኃጢአት ስላስከተለው ውጤትና ተጽእኖ ምን ይነግሩናል?

---

የአዳም አለመታዘዝ በሂደት መላውን የእግዚአብሔር ፍጥረታት በማወክ ለአያሌ ያልተጠበቁ ክስተቶች መዘዝ ለመሆን በቃ፡፡ ራሱ ተፈጥሮአዊው ዓለም ሳይቀር ኃጢአት ያስከተለውን የሥቃይ መዘዝ መቅመሱን ተያያዘው፡፡ ሁለቱ ወንድማማቾች እርስ በርሳቸው ሊዋደዱና አንዱ ለሌላው አለኝታ ሊሆን ሲገባ፤ ነገር ግን አንደኛው የእግዚአብሔርን ሌላው ደግሞ እግዚአብሔር ያስቀመጠውን የአምልኮ መንገድ ሳይሆን የግሉን ራስ ወዳድ አምልኮ በመከተሉ ባይተዋር ሆኑ፡፡ ይህ ባይተዋርነት ጸብ ብሎም ሞት አስከተለ፡፡ ይሁን እንጂ በቃየን የተስተዋለው ድርጊት ባብዛኛው ያነጣጠረው በወንድሙ አቤል ላይ ሳይሆን በራሱ በእግዚአብሔር ላይ ነበረ፡፡ ቃየን በእግዚአብሔር ላይ ብርቱ የቁጣ ስሜት ተሰማው (ዘፍ. 4፡5)፡፡ ይህ ቁጣው ደግሞ በአቤል ላይ የበቀል በትር እንዲሰነዝር መራው፡፡ በዚህም አለመታዘዝ በሰብዓዊው የእርስ በርስ ግንኙነት ላይ መቃቃር ፈጠረ፡፡

“እግዚአብሔር አምላክ የሰው ዐመፅ በምድር ላይ የበዛና የልቡም ሐሳብ ዘወትር ወደ ክፋት ብቻ ያዘነበለ መሆኑን ተመለከተ፡፡” (ዘፍ. 6፡5)፡፡ ውሎ አድሮ ይህ የክፋት ተግባር ለጥፋት ውሃ እና ለቀደመው የእግዚአብሔር ፍጥረት ውድመት መንስኤ

የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት ጀመረ፡፡ ሆኖም ግን በሰብዓዊው ፍጡር ተስፋ ያልቆረጠው እግዚአብሔር በኖኅ እና ቤተሰቡ አማካይነት የሰብዓዊውን ዘር ቅሪት በምድር ከማትረፍ ወደ ኋላ አላለም፡፡

ከጥፋት ውሃ በኋላ እግዚአብሔር ለኖኅና ቤተሰቡ ቃል ገባ፡፡ በዝናብ ወቅት በሰማይ የሚወጣው ቀስተ ደመና ሰብዓዊውን ፍጡር ስለ አምላካዊው ጥበቃና እንክብካቤ፣ ደግነትና ምኅረት ዘወትር የሚያስታውስ ምልክት ሆነ (ዘፍ. 9፡12-21)፡፡ እግዚአብሔር ከኖኅ ጋር ቃል ኪዳን በማድረግ ለእርሱና ለቃሉ ሙሉ ለሙሉ ታማኝ የሆነ አንድ ሰብዓዊ ቤተሰብ የመመስረት ቅድመ እቅዱን ዳግም አዋቀረ፡፡

*ኃጢአት መለያየት የሚያመጣባቸው መንገዶች ምንድን ናቸው? ምርጫዎችዎ በሰዎች መሃል ስምምነትና አንድነት ለማምጣት እገዛ ያደርጉ ዘንድ አሁን የሚመርጧቸው ምርጫዎች ምን ሊሆኑ ይገባል?*

**ማክሰኞ** **መስከረም 22**

## ከፍ ያለው ኅብረት ማጣትና መለያየት

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዘፍ. 11፡1-9፡፡ ኅብረት የማጣቱና የመለያየቱ ችግር ይበልጥ እንዲከፋ ያደረገ ምን ዓይነት ነገር ተከሰተ?

________________________________________

________________________________________

ከጥፋት ውሃ በኋላ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱት ቀጣይ ክስተቶች የባቤል ግንብ ግንባታ፣ የቋንቋዎች መደበላለቅ እና እስከዚያ ጊዜ ድረስ አንድ ቋንቋ ይናገሩ የነበሩ ሰዎች በምድር መበተን ነበር፡፡ ምናልባት አንዳንዶቹ የኖኅ ዝርያዎች በጤግሮስ እና ኤፍራጥስ ወንዞች መካከል በነበረው መልክአ ምድር ውበትና በዐፈሩ ለምነት በመሳብ በያኔዋ ሰናዖር (በዛሬው ደቡባዊ ኢራቅ) ዘፍ. 11፡2--ለመክተም እና ግዙፉን የባቤል ግንብ ለመገንባት ወሰኑ፡፡

የአርኪዎሎጂ ጥናት እንደሚያሳየው ሜሶፖታሚያ በቀደመው ዘመን ከፍተኛውን የሕዝብ ብዛት የያዘ ክልል ነበር፡፡ ከነዋሪዎች መካከል ሱመራውያን አንዱ ሲሆኑ እነዚህ ሕዝቦች በሸክላ ገበታ ላይ የጽሑፍ ጥበብን በመፍጠር ተመስክሮላቸዋል፡፡ በጥሩ ሁኔታ የታነጹ ቤቶችን ይገነቡ የነበሩት ሱመራውያን ጌጣጌጦችን፣ የእጅ መሣሪያዎችን እና የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን በመሥራትም እንዲሁ የተካኑ ነበሩ፡፡ ለተለያዩ አማልክት የተሠሩ ልቀው ይታዩ የነበሩ ብዛት ያላቸው ቤተ አምልኮዎች በቁፋሮ ተገኝተዋል፡፡

በሰናዖር ምድር ሰፍረው የነበሩት የኖኅ ዝርያዎች ብዙም ሳይቆዩ እግዚአብሔር ዓለምን ዳግመኛ በውሃ እንደማያጠፋ ለኖኅ የገባለትን ቃል ዘነጉ፡፡ የባቤልን ግንብ

መገንባት ወጣ ላለው ዕውቀትና ችሎታቸው መታሰቢያ ቅርሳቸው ነበር፡፡ ይህን ፕሮጀክት እንዲጀምሩ የገፋፋቸው ምክንያትና ምኞት ለምድራዊው ዝና እና ለስማቸው መጠሪያ የሚሆን ሀውልት ማቆም ነበር (ዘፍ. 11፡4)፡፡ "በመለኮታዊ ዓላማው መሠረት ሰዎች በእውነተኛ ኃይማኖት ትስስር አንድነታቸውን መጠበቅ ነበረባቸው፡፡ ጣዖት አምልኮና ከአንድ በላይ አምላክ የማምለክ አባዜ ይህን ውስጣዊ መንፈሳዊ ትስስር ሲበጥስ፤ የኃይማኖት አንድነትን ብቻ ሳይሆን የወንድማማችነትንም መንፈስ አጡ፡፡ በእንደ ባቤል ግንብ ፕሮጀክት ዓይነት ውጪያዊ ኅብረት በመመስረት የጠፋውን ውስጣዊ አንድነት ለማምጣት የሚደረግ ጥረት ፈጽሞ የስኬት ባለቤት ሊያደርግ አይችልም፡፡"—The SDA Bible Commentary, vol.1, pp. 284, 285.

የአዳምና ሔዋን ውድቀት የሰብዓዊውን ዘር ኅብረት እና የቀደመውን አምላካዊ ዕቅድ እንዳይሆን በማድረጉ፤ በአምልኮ ዙሪያ ውዥንብርና ግራ መጋባት ተፈጠረ፣ ክፋትና ምግባረ ብልሹነትም በምድር ዙሪያ ተሰራጨ፡፡ የሰብዓዊው መለያየት ወደ ብዙ ባህሎች፣ ቋንቋዎችና ዝርያዎች በመስረጹ እነሆ ዛሬ ድረስ በሕዝቦች መሃል ያለ ግንኙነት ከልብ ሳይሆን ከአንገት በላይ ሆነ፡፡

*በቤተ ክርስቲያን ሳይቀር በመለያየት እየጎዱን ያሉ የብሔር፣ የባህልና የቋንቋ ደዌዎችን በተጨባጭ ለመፈወስ የሚያስችሉን ቅደም ተከተሎች ምንድን ናቸው?*

**ረቡዕ** **መስከረም 23**

## አብርሃም፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች አባት

ሦስቱ የዓለም ታላላቅ ኃይማኖት የሆኑት ይሁዲ፣ ክርስትና እና እስልምና አብርሃምን እንደ አባት ይመለከቱታል፡፡ ለክርስቲያኖች ይህ አንድነት ከመንፈሳዊ ግንኙነት ጋር በአንድ የተሳሰረ ነው፡፡ አብርሃም የትውልድ አገሩን ሜሶፖታሚያን ለቅቆ እንዲወጣ ጥሪ ሲቀርብለት "በምድር የሚኖሩ ሕዝቦች በአንተ አማካይነት ይባረካሉ" (ዘፍ. 12፡3፣ ዘፍ. 18፡18፣ 22፡18)) የሚል ተስፋ ተሰጥቶት ነበር፡፡ ይህ በረከት የመጣው በየሱስ አማካይነት ነበር፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዕብ. 11፡8-19፣ ሮሜ 4፡1-3፣ ገላ. 3፡29፡፡ ጥቅሶቹ የትኞቹን የአብርሃም ኃይማኖታዊ አላባዎች ይጠቅሳሉ? ደግሞም ከዛሬው የክርስትና ኅብረት ጽንሰ ሃሳብ ጋር እንዴት ይዛመዳሉ? የክርስትና አንድነት ዋነኛ አካል ምን መሆን እንዳለበት መገንዘብ እንችል ዘንድ ከመልእክቶቹ ምን እናገኛለን?

_______________

_______________

አብርሃም እንደ የኃይማኖት አባትነቱ ለክርስቲያናዊ ኅብረት አስኳል የሆኑ መሰረታዊ አላባዎችን ይሰጠናል፡፡ በመጀመሪያ--አብርሃም መታዘዝን ተለማመደ "አብርሃም

ርስት አድርጎ ወደሚቀበለው ስፍራ እንዲሄድ በተጠራ ጊዜ በእምነት ታዘዘ፤ ወዴት እንደሚሄድ ባያውቅም፣ እሺ ብሎ ሄደ” (ዕብ. 11፡8)፡፡ በሁለተኛ ደረጃ--በአምላካዊው ኪዳን ላይ ተስፋ አደረገ፡፡ “በባዕድ አገር እንዳለ መጻተኛ በተስፋይቱ ምድር በእምነት ተቀመጠ፤ የተስፋውን ቃል አብረውት እንደሚወርሱት እንደ ይስሐቅና እንደ ያዕቆብ በድንኳን ኖረ፤ ምክንያቱም መሠረት ያላትን፣ እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ ይጠባበቅ ነበር” (ዕብ. 11፡9-10)፡፡ ሦስተኛ--እግዚአብሔር አንድ ቀን ልጅ እንደሚሰጠውና የአብራኩ ፍሬዎች እንደ ሰማይ ከዋክብት እንደሚበዙ አመነ፡፡ ለዚህ በሰጠው ምላሽ መሰረት እግዚአብሔር በእምነት አጸደቀው (ሮሜ 4፡1-3)፡፡ አራተኛ--በአምላካዊው የደኅንነት እቅድ የሚታመን ሰው ሆነ፡፡ አብርሃም ልጁን ይስሐቅ በሞሪያ ተራራ እንዲሰዋለት እግዚአብሔር ሲጠይቀው እጅግ ከፍ ያለውን የእምነት ፈተና ተፈተነ (ዘፍ. 22፡1–19፣ ዕብ. 11፡17–19)፡፡

ብሉይ ኪዳን አብርሃምን የእግዚአብሔር ወዳጅ አድርጎ ይገልጸዋል (2ዜና 20፡7፣ ኢሳ. 41፡8)፡፡ የእምነት ሕይወቱ፣ ጽኑ መታዘዙና በእግዚአብሔር ኪዳን ላይ የነበረው ልበ ሙሉነት እነሆ ለዛሬው የክርስትና ሕይወታችን ምሳሌ አድርጎታል፡፡

*በቀጣዮቹ ጥቂት ቀናት ስለሚወስዷቸው እርምጃዎችና ከአንደበትዎ ስለሚወጡ ቃላት አሰብ ያድርጉ፡፡ ማንኛውም የሚናገሩትም ሆነ የሚያደርጉት ነገር እምነትዎን በተጨባጭ ማንጸባረቅ የሚችለው እንዴት ነው?*

## ሐሙስ — መስከረም 24

## የእግዚአብሔር የተመረጡ ሕዝቦች

እግዚአብሔር አብርሃም አገልጋዩ እንዲሆን በመጥራት እርሱን በዚህ ዓለም የሚወክለውን ሕዝብ ለራሱ መረጠ፡፡ ይህ ጥሪ እና ምርጫ የእግዚአብሔር ፍቅር እና ጸጋ ነበር፡፡ ሰብዓዊው ውድቀት አስከፊ ውድመትና መለያየት ካስከተለ በኋላ እግዚአብሔር ለእስራኤል ያቀረበው ጥሪ መላው ሰብዓዊ ዘር ወደ ቀደመው ንጽህና የሚመለስበት የአምላካዊው እቅድ ማዕከል ነበር፡፡ እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደዚህ ንጽህና ለመምራት የሠራውን ሥራ ማጥናት ቅዱስ ታሪክ ሲሆን፤ የዚያ ዕቅድ ዐቢይ አካል ደግሞ ባለ ኪዳኑ የእስራኤል ሕዝብ ነበር፡፡

በዘዳግም ምዕራፍ 7 ቁጥር 6 እና 11 መሠረት እግዚአብሔር እስራኤልን ሕዝቤ ብሎ የጠራው ለምንድን ነው? ይህን ከአብርሃም ዘር የሆነ ሕዝብ የራሱ አድርጎ የመረጠው ለምንድን ነው?

እግዚአብሔር ለሰብዓዊው ዘር ያለው ፍቅር እስራኤልን እንደ ራሱ ሕዝብ የመምረጡ ማዕከል ነው፡፡ እግዚአብሔር አምላካዊውን ዕውቀት በሕዝቦቹ ውስጥ ለማኖርና የሰብዓዊውን ዘር መቤዠት እውን ለማድረግ ሲል ከአብርሃም እና ከእርሱ ትውልድ ጋር ኪዳን ገባ (መዝ. 67፡2)፡፡ ይህም ሆኖ እግዚአብሔር እስራኤልን እንዲመርጥ ያደረገው እጅግ የላቀ ፍቅሩ ነው፡፡ የአብርሃም ትውልድ የማይገባው የነበረውን አምላካዊ ፍቅር የራሱ ለማድረግ የሚያስችል አንድም የሚመካበት ነገር አልነበረውም፡፡ "እግዚአብሔር እናንተን የወደዳችሁና የመረጣችሁ ከሌሎች ሕዝቦች በቁጥር ስለ በዛችሁ አይደለም፤ ቁጥራችሁማ ከሕዝቦች ሁሉ እጅግ አነስተኛ ነበር" ዘዳ. 7፡7)፡፡

እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመምረጥ ጥቅም ላይ የሚያውላቸው እሴቶች ለሰብዓዊው መስፈርት እንግዳና የተገላቢጦሽ ናቸው፡፡ ሰዎች መሪዎችን ለመምረጥ ኃያልነትን፣ ችሎታንና በራስ መተማመንን ሲመለከቱ እግዚአብሔር ግን ጠንካራውና ብርቱው እንዲያገለግለው አይመርጥም፡፡ ይልቁንም ደካማነቱንና ከንቱነቱን የተረዳውን ይመርጣል፤ ይኸውም ማንም በራሱ እንዳይመካ ነው (1ቆሮ. 1፡26-31)፡፡

ሆኖም በእርሱ የተመረጡ ወገኖች ተሰጥቶአቸው የነበረውን ልዩ መብትና ጥቅም እንመልከት፡፡ "እስራኤል ሕዝቡ የተመሰገነና የተከበረ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር ምኞት ነበር፡፡ እያንዳንዱ መንፈሳዊ ጥቅም ለእነርሱ ተሰጥቶ ነበር፡፡ ለራሱ ተወካይ ሊያደርጋቸው የሚችለውን ስምሙ የባሕሪ ቅርጽ እንዲይዙ ከማድረግ ውጪ አንዳች የከለከላቸው ነገር አልነበረም፡፡

"ለእግዚአብሔር ሕግ መታዘዛቸው በዓለም ሕዝቦች ፊት አስደናቂ ብልጽግና ያጎናጽፉቸው ነበር፡፡ በእያንዳንዱ የሙያ ዘርፍ ጥበብና ችሎታ ሊሰጣቸው የሚችል እርሱ የዘወትር መምህራቸው እንደመሆኑ ለሕጉ በመታዘዛቸው ሞገስ ይሆናቸውና ከፍ ከፍ ያደርጋቸው ነበር፡፡ እርሱን ከታዘዙ ሌሎች ሕዝቦችን ያጠቁ ከነበሩ በሽታዎች ይጠበቁ ነበር፡፡ በጥልቅ የማሰብ ችሎታም ይባረኩ ነበር፡፡

"የእግዚአብሔር ክብር፣ ግርማ እና ኃይል በብልጽግናቸው ሁሉ ይገለጥ ነበር፡፡ የካኅናት መንግሥትና መኳንንት እንዲሆኑ ተጠሩ፡፡ እስራኤላውያን በምድር ታላቅ ሕዝብ ሊያደርጋቸው የሚችል እያንዳንዱ ስጦታ ተበርክቶላቸው ነበር፡፡"—Ellen G. White, Christ's Object Lessons, p. 288.

እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች--እግዚአብሔር ለጥንቶቹ እስራኤላውያን እና ለእኛ ባደረገው ነገርና ባቀረበው ጥሪ መሀል ምን ዓይነት መመሳሰሎችን ማግኘት እንችላለን? መልስዎን በሰንበት ጥናት ክፍለ ጊዜ ይዘው ይቅረቡ፡፡

## ዓርብ

## መስከረም 25

ተጨማሪ ሀሳብ፡ Ellen G. White, “The Creation,” pp. 44–51, and “The Call of Abraham,” pp. 125–131, in Patriarchs and Prophets.

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር የነበረው የቀደመ ዓላማ በተመሳሳይ በቤተሰብ እና በሰንበት ተቋማት ምስረታም ተንጸባርቆአል፡፡ የሱስ በማር. 2፡27-28 በግልጽ እንዳመለከተው የሰንበት እረፍት የተዘጋጀበት የቀደመ ዓላማ ለመላው ሰብዓዊ ዘር ጥቅም ሲባል ነው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ የሰንበት ዩኒቨርስ አቀፍ ተፈጥሮ በራሱ በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ ተገልጧል፡፡ እግዚአብሔር ሰባተኛውን ቀን ከሌሎቹ የሣምንቱ ቀናት የለየው እስራኤልን እንደ ኪዳን ሕዝቡ ከመጥራቱ በፊት ብቻ ሳይሆን ኃጢአት በምድር ከመታወቁ አስቀድሞም ጭምር ነበር፡፡ ሰው ሁሉ ሰባተኛውን ቀን ቢጠብቅ፤ ዕለቱ ኅብረት የሚያመጣ ብርቱ ኃይል በሆነ ነበር፡፡ የአዳምና ሔዋን ትውልድ ከእግዚአብሔር አምላክ ጋር እንዲሁም እርስ በርስ ያላቸውን ኅብረት እንዲያስታውሱ ታቅዶ የተሰጠ የእረፍት ቀን ነበር፡፡ “በኤደን ገነት የተቋቋሙት ሰንበት እና ቤተሰብ በአምላካዊው ዓላማ እንዳይፈቱ ሆነው በአንድ ተገምደዋል፡፡ ከሌሎቹ የሣምንቱ ቀናት ይልቅ በዚህ ዕለት በበለጠ የኤደንን ሕይወት መኖር ይቻለናል፡ ፡ አባወራው እንደ ቤቱ ካኅን እንዲሁም እናትና አባት እንደ ልጆቻቸው መምህርና ጓደኛ ሆነው የቤተሰብ አባላት በሥራ፣ በጥናት፣ በአምልኮና በመዝናናት ጊዜአቸውን አንድ ላይ ያሳልፉ ዘንድ የእግዚአብሔር እቅድ ነበር፡፡”—Ellen G. White, Child Guidance, p. 535.

### የመወያያ ጥያቄዎች፡

1. በዘፍጥረት መጽሐፍ የሔዋን ከአዳም የጎን አካል መሠራት በባልና ሚስት መካከል ሊኖር ስለሚገባው የጠበቀ ትስስር ምን ይገልጽልናል? በሁለት የትዳር ተጓዳኞች መካከል ሊኖር የሚገባው የጠበቀ ትስስር በተመሳሳይ በሕዝቡ መሃል እንዲኖር የሚመኘው አምላክ፤ ይህን ጥምረት በመላው የመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች በምሳሌ የሚያቀርበው ለምንድን ነው?

2. ምንም እንኳ የሰብዓዊው ዘር በቋንቋና በብሔር መከፋፈል የቀደመው አምላካዊ ዕቅድ አካል አለመሆኑን የባቤል ግንብ ታሪክ ቢነግረንም፤ እነዚህን ተፈጥሮአዊ መለያየቶች አስንቀን መገኘት የምንችለው እንዴት ነው? ቤተ ክርስቲያን የብዙ ሕዝቦችና ቋንቋዎች ስብጥር ብትሆንም፤ ዛሬም ኅብረትና ስምምነትን መለማመድ የምትችለው እንዴት ነው?

3. በጥንቷ እስራኤል እና እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስትነታችን በእኛ መጠራት መካከል ያሉ አንዳንድ መመሳሰሎች ምንድን ናቸው? ከሁሉ በላይ ለክርስቶስ መለኮታዊ ጥሪ ታማኝ እንድንሆን ከሚረዱን ነገሮች ምን እንማራለን?

*ማጠቃለያ፡ የሰዎች ተስማምቶና እንደ አንድ ቤተሰብ ሆኖ መኖር በፍጥረት ወቅት የነበረ የቀደመ አምላካዊ እቅድ ነው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን አለመታዘዝ የእግዚአብሔርን እቅድ አፋለሰ፡፡ ሆኖም እግዚአብሔር በክርስቶስ ብቻ የሚገኘውን ወደ ቀደመው ንጽህና የመመለስ ኪዳን መጠበቅ የሚችልበትን ሕዝብ ለማቋቋም አብርሃምን ጠራ፡፡*

# 2ኛ ትምህርት መስከረም 26 - ጥቅምት 2

## የመለያየት መንስዔዎች

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ዘዳ. 28:1–14፤ ኤር. 3:14–18፤ መሳፍ. 17:6 ፤ 1ነገሥ. 12:1–16፤ 1ቆሮ. 1:10–17፤ ሐዋ. 20:25–31፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ :-**“ ‘የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፤ ቅዱሱንም ማወቅ ማስተዋል ነው’ ” (ምሳ. 9:10)

የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን እንዲታዘዝ የሚጠይቅ ተደጋጋሚ ጥሪ በብሉይ ኪዳን ነቢያት ይቀርብ ነበር፡፡ አለመታዘዝና ቸልተኝነት ወደ ክህደትና መከፋፈል መምራቱ ዕሙን ነው፡፡ ኃጢአት በተፈጥሮው ከሚያስከትለው ውጤት እነርሱን ለመታደግና በብዙ ባዕዳን ሕዝቦች መሃል ለመቀደስ ሲባል ለአምላካዊው ሕጎች መታዘዛቸው የግድ ነበር፡፡ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መከተሉ በአንድ ልብ እንዲሆን ከማስቻሉ በተጨማሪ፤ ጎብረታቸው ዙሪያ ገባውን ሰንጎ የያዘውንና ጥሶ ሊገባ የሚዳዳውን የአረማውያን አምልኮ ልምድ እንዲቋቋሙ የሚያስችል መፍትሔ ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ዓላማ እስራኤል የተቀደሰና በዙሪያው ለነበሩ ሕዝቦች ምስክር እንዲሆን ነበር፡፡

ጌታ ዕብራውያንን ከምድረ ግብፅ ከታደገ በኋላ ሙሴ እንዲህ ብሏቸው ነበር፡ “ገብታችሁ በምትወርሷት ምድር፣ እንድትፈጽሟቸው እግዚአብሔር አምላኬ ባዘዘኝ መሠረት ሥርዐትንና ሕግን አስተምሬአችኋለሁ፡፡ በጥንቃቄ ጠብቋቸው፤ ስለ እነዚህ ሥርዐቶች ሁሉ ለሚሰሙና፣ ‘በእውነቱ ይህ ታላቅ ሕዝብ የቱን ያህል ጥበበኛና አስተዋይ ነው’ ለሚሉ ሕዝቦች ይህ ጥበባችሁንና ማስተዋላችሁን ይገልጣልና” (ዘዳ. 4፡5-6)፡፡

እነዚህ ሕዝቦች ለእግዚአብሔር ታማኝ ቢሆኑ ኖሮ አብልጠው መባረካቸውና ለሌሎችም በረከት መሆናቸው እምብዛም አያጠያይቅም፡፡ በተቃራኒው ታማኝነትን ማጉደል ከብዙ በጥቂቱ ለመጠነ ሰፊ ችግርና መለያየት ይዳርጋል፡፡

**እሁድ** **መስከረም 27**

## “ከዳተኛይቱ እስራኤል ሆይ፤ ተመለሽ”

በአለመታዘዝና ሥርዓተ አልበኝነት በተሞላው የእስራኤል ሕዝብ ታሪክ፤ አንዴ ታማኝ ሆነው ወደ እርሱ ሲመለሱ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከቀድሞው በባሰ ሲያምጹና ሲወዛገቡ በተደጋጋሚ ተስተውሎአል፡፡ ይህ ሁኔታ ሰርክ ሲታይ የኖረ ሐቅ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች አምላካዊውን ፈቃድ ዘወትር በንቃት በተከተሉ ቁጥር የሰላምና ህይወት በረከት ይበዛላቸው ነበር፡፡ በተቃራኒው ሲያምጹና የገዛ ፈቃዳቸውን ሲከተሉ ህይወታቸው ከአምላካዊው ረድኤት የራቀና በጦርነት ብሎም በግጭት የተሞላ ይሆን ነበር፡፡ እስራኤል ወደ ተስፋይቱ ምድር ከመግባቱ አስቀድሞ ይህ ሊሆን እንደሚችል የተነበየው ጌታ ለህልውናቸው አደገኛ የሆነውን ውጤት እንዴት ማስቀረት እንደሚችሉ መፍትሔውን ሰጥቶአቸው ነበር፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዘዳ. 28፡1-14፡፡ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር በታማኝነት ቢጸና ኖሮ ምን ዓይነት በረከቶች መቀበል ይችል ነበር?

____________________________________________

____________________________________________

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ኤር. 3፡14-18፡፡ እግዚአብሔር እስራኤላውያን ንስሐ እንዲገቡና ወደ እርሱ እንዲመለሱ ካቀረበው ጥሪ ምን እንማራለን? ጌታ ለሕዝቡ ስላለው ፍቅር እና ትዕግሥት ምን ይነግረናል?

____________________________________________

____________________________________________

ሕዝቡ አመጸኛ፣ ከኅብረት አፈንጋጭና ጣኦት አምላኪ ቢሆንም እግዚአብሔር ግን አፍቃሪ፣ መሐሪና ቸር ሆኖ የቀረበበት የኤርምያስ መጽሐፍ እጅግ ያስገርማል፡፡ ሕዝቡ ንስሐ ገብቶ ከስህተት መንገዱ እንዲመለስ እግዚአብሔር ዘወትር ግብዣውን ያቀርባል፡፡ አዲስ ንጽህናና ተስፋ እንደሚሰጠን በተደጋጋሚ ቃል ገብቶናልና፡፡

“ ‘ከዳተኛይቱ እስራኤል ሆይ፤ ተመለሽ’ ይላል እግዚአብሔር፣ ‘እኔ መሐሪ ስለሆንሁ፣ ከእንግዲህ በቁጣ ዐይን አላይሽም’ ይላል እግዚአብሔር፡፡ ‘ለዘላለም አልቆጣም፡፡ በአምላክሽ በእግዚአብሔር ላይ በማመጽሽ፣ ክብርሽንም ለእንግዶች አማልክት፣ በየለምለሙ ዛፍ ስር አሳልፈሽ በመስጠት፣ ለእኔ ባለመታዘዝሽ በደለኛ መሆንሽን ይህን አንድ ነገር ብቻ እመኚ ’ ይላል እግዚአብሔር፡፡” (ኤር. 3፡ 12-13)፡፡

እነዚህ በኤርምያስ የተነገሩ ቃላት ለሕዝቡ የቀረቡት የእግዚአብሔር ቃል ሙሉ ለሙሉ ችላ በተባለበት ወቅት ነበር፡፡ ምንም እንኳ በንጉሥ ኢዮስያስ ዘመን አንዳንድ የተሐድሶ እንቅስቃሴዎች ቢጀመሩም፤ ብዙዎች እግዚአብሔርን በታማኝነት መታዘዛቸውን እንዲቀጥሉ የሚያስችል መንፈሳዊ ግፊት አልተሰማቸውም ነበር፡፡ መተላለፋቸው፣ በጦኦት አምልኮ መውደቃቸውና ራስ ወዳድ ህይወታቸው ለመንፈሳዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ዳርጎአቸው ነበር፡፡ እነዚህ ሕዝቦች አምላካዊውን ፈቃድ ከማድረግ ባፈገፈጉ ቁጥር የወደፊቱ ነገር በእጅጉ አስጊ ገጽታ የተላበሰ ይሆን ነበር፡፡ ሆኖም እግዚአብሔር በኤርምያስ አማካይነት እንዴት እንደተማጸናቸው በነቢዩ መልእክት እንመለከታለን፡፡ የተሻለውን የወደፊት ማንነት ያቀደላቸው ይህ ጌታ ዳግመኛ ወደ ብልጽግና፣ ወደ መንፈሳዊ ኅብረት እና የተሟላ ጤንነት ሊመልሳቸው ናፈቀ፡፡ ሆኖም ይህ እውን መሆን የሚችለው እውነተኛውን እምነት ተከትሎ በሚመጣው እውነት ውስጥ በእምነት መኖር እስከ ቻሉ ድረስ ብቻ ነበር፡፡

*በመታዘዝ እና አለመታዘዝ መሃል ያለው ልዩነት በግል ሕይወትዎ ያለው ትርጉም ምን ይመስላል?*

## ሰኞ

## መስከረም 28

## ለራስ መልካም መስሎ የሚታየውን ማድረግ

የጌታን ፈቃድ ያልተከተሉ አያሌ እስራኤላውያን ድርጊታቸው ያስከፈላቸውን ብርቱ ዋጋ የመጽሐፈ መሳፍንት ታሪኮች ያሳዩናል፡፡ እስራኤላውያን ከነዓን ገብተው ብዙም ሳይቆዩ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ዙሪያቸውን ከከበቧቸው አጎራባች ሕዝቦች የሐሰት አማልክት ጋር ማቆራኘት ጀመሩ--ይህ ደግሞ በትክክል እንዳታደርጉ የተባሉት ነገር ነበር፡፡ የሚያሳዝነው እነዚህ ሕዝቦች የገጠማቸው ችግር በዚህ ብቻ የሚያበቃ አልነበረም፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ መሳ. 17፡6፣ 21፡25፡፡ በእግዚአብሔር ሕዝቦች መሃል ይበልጥ ይነሱ ስለነበሩ ችግሮች ጥቅሶቹ ምን ያስተምሩናል? በእግዚአብሔር ሕዝቦች መካከል ይከሰቱ በነበሩ የመከፋፈል መንስዔዎች ዙሪያ ተነጋገሩ፡፡

---

---

የሕዝቡ አንድነት የተመሰረተው ለጌታ ታማኝ ለመሆን በነበራቸው ቁርጠኝነት ይኸውም ከእግዚአብሔር ጋር በገቡት ኪዳን ነበር፡፡ እስራኤላውያን በተለይ ማንነታቸው በአጎራባች ሕዝቦች ተጽእኖ ስር እንዲወድቅ በፈቀዱና እያንዳንዱ ሰው

ለራሱ መልካም መስሎ የታየውን ባደረገ ቁጥር ወደ ጥፋት ጎዳና ማዘንበሉ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ እኛ ሁላችን በኃጢአት የወደቅን ከመሆናችን አኳያ በየግላችን ይበጃል ያልነውን አካሄድና የየልባችንን ዝንባሌ እንድንከተል ብንተው፤ እንድንራመድበት እግዚአብሔር ከጠራን መንገድ ስተን መጥፋታችን ዕሙን ነው፡፡

እስራኤላውያን በመስፍኖች ይተዳደሩ በነበሩበት ወቅት ስለነበረው መንፈሳዊ እና ማህበራዊ ሁኔታዎች የሚከተሉት ጥቅሶች ምን ይነግሩናል?

መሳ. 2:11–13_______________________________________

መሳ. 3:5–7________________________________________

"ያለመታዘዝን ውጤት ሙሴ ለሕዝቡ እንዲነግር ጌታ አስተምሮት ነበር፡፡ የእግዚአብሔርን ሕግ ለመታዘዝ ሲቃወሙ ራሳቸውን የሕይወት ባለቤት ከሆነው ጌታ ስለሚነጥሉ፤ አምላካዊው በረከት ወደ እነርሱ ለመድረስ ይሳነዋል፡፡ አልፎ አልፎ እነዚህ ማስጠንቀቂያዎች ሲከበሩና በጥንቃቄ ሲስተዋሉ በአይሁዳውያን ላይ ይፈሱ የነበሩ በረከቶች ከእነርሱ አልፈው ለሌሎችም አጎራባች ሕዝቦች ይተርፉ ነበር፡፡ ሆኖም የእነዚህ ሕዝቦች አብዛኛው ታሪክ እግዚአብሔርን የመርሳት እና በምድር የእርሱ ተወካይ ሆነው ከፍ ባለ ማዕረግ ለመሰየም የተሰጣቸውን ልዩ መብትና ጥቅም የዘነጋ፣ ከማየትም የተጋረደ ነበር፡፡ በእርሱ የተጠየቁትን አገልግሎት በመንፈግ በአምላካቸው ላይ ስርቆት ፈጸሙ፡፡ ለሌሎች መልካም ኃይማኖታዊ አመራር ከመስጠትና ምሳሌ ከመሆን ተሰናከሉ፡፡ በባልንጀራዎቻቸውም ላይ ተመሳሳይ ስርቆት ፈጸሙ፡፡ መጋቢዎች ሆነው የተሾሙበትን የወይን ተክል ፍሬ ለራሳቸው ለመውሰድ ተመኙ፡፡ ክፉ ምኞታቸውና ስግብግብነታቸው በአረማውያን ሳይቀር የተናቁ አደረጋቸው፡፡ በዚህም አረማዊው ዓለም የእግዚአብሔርን ባህሪ እና የመንግሥቱ መሰረት የሆነውን ሕግ በተሳሳተ መንገድ የሚተረጉምበትን ምክንያት አገኘ፡፡"—Ellen G. White, Prophets and Kings, pp. 20, 21.

እንደ ቤተ ክርስቲያን የገዛ ድርጊቶቻችን ዙሪያችን ባሉ ባልንጀሮቻችን ላይ ተጽእኖ ማሳደር የሚችሉት እንዴት ነው? የእነዚህን ሰዎች ልብ በአዎንታዊ መንገድ ለመንካት የሚያስችል ምን ዓይነት ቅመም በሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች ውስጥ መመልከት ይችላሉ?

መሳ. 2: 11-13 _______________________________________

መሳ. 3: 5-7 ________________________________________

**ማክሰኞ** **መስከረም 29**

## የዕብራውያን መከፋፈል

የክህደት መንገድ እና አስከፊ መዘዙ በአንድ ጀንበር እውን አልሆነም፡፡ ይልቁንም ለምዕተ ዓመታት የተከማቹ የተሳሳቱ ምርጫዎች በመጨረሻ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ አስደንጋጭና አስፈሪ ጦስ ይዘው ከተፍ አሉ፡፡

የንጉሥ ሮብዓምን ታሪክ በ1ኛ ነገሥ. 12፡1-16 ይመልከቱ፡፡ በእግዚአብሔር ሕዝቦች መሃል እንዲህ ያለው አስፈሪ መከፋፈል እንዲከሰት ምክንያት የሆነው ነገር ምን ነበር?

________________________________________

________________________________________

"እግዚአብሔር ለእስራኤል የነበረውን በጎ ፈቃድ ሮብዓምም ሆነ እነዚያ ልምድ የለሽ፣ አብሮ አደግ--ወጣት አማካሪዎቹ አስተውለው ቢሆን ኖሮ፤ በመንግሥታዊው አስተዳደር ተሐድሶ እንዲመጣ ሕዝቡ ላቀረበው ጥያቄ ጆሮዎቻቸውን በሰጡ ነበር፡፡ ሆኖም ሴኬም ላይ በተደረገው ጉባዔ አግኝተውት በነበረው ዕድል መንስኤን ከውጤት መለየት ስለተሳናቸው ከፍተኛ ቁጥር ባለው ሕዝብ ላይ ሊኖራቸው ይገባ የነበረው ተጽእኖ እስከ ወዲያኛው ደካማ ሆኖ ቀረ፡፡ በሰለሞን የንግሥና ዘመን የነበረው ጭቆና ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግና በዚያ ላይ ሌላ ግፍ የማከል ቁርጠኝነት እግዚአብሔር ለእስራኤል ከነበረው ዕቅድ ጋር በቀጥታ የሚጋጭ ነበር፡፡ ሕዝቡም በእነርሱ ላይ ጥርጣሬ እንዲያድርበት የሚያደርግ ከበቂ በላይ ምክንያት ማግኘት ቻለ፡፡ ንጉሡና በእርሱ የተመረጡ አማካሪዎቹ ሥልጣንን እንዲህ ጥበብና ርኅራኄ በጎደለው መንገድ ለመለማመድ መሞከራቸው፤ በሥልጣን መታበይንና በደረጃ ትምክህት ማድረግን ገልጦ አሳየ፡፡"—Ellen G. White, Prophets and Kings, p. 90.

ትክክለኛ ውሳኔዎችን ለመወሰን ጥበብ የሚያሻ ስለመሆኑ የሚከተሉት ሀሳቦች ምን ይነግሩናል? የእውነተኛ ጥበብ ምንጩ ወዴት ነው?

ምሳ. 4:1–9________________________________

ምሳ. 9:10 ________________________________

ያዕ. 1:5 ________________________________

በሕዝቡ ላይ ተጭኖ የነበረውን ቀንበር ይበልጥ የማከበድ ውሳኔ ላይ የደረሰው ችኩሉና ጥበብ የጎደለው የሮብዓም ታሪክ በእስራኤል መንግሥት ህልውና አሳዛኙ ክስተት ነው፡፡ ንጉሡ ከሁለት የተለያዩ አማካሪ ቡድኖች ምክር ለማግኘት ሞክሮ ነበር፡፡ ሆኖም ይህ የአብሮ አደጎቹንና ልምድ የሌላቸውን ወጣቶች እንጭጭ ሐሳብ

የመከተሉ የመጨረሻ ውሳኔው አባቱ ሰሎሞንም ሆነ አያቱ ዳዊት ላለፉት 80 ዓመታት በገነቧት አገር ላይ ብርቱ ውድመት አስከተለ፡፡ ከአባቱ ይልቅ እርሱን የበረታ አድርጎ በማቅረብ ሕዝቡን ለማስፈራራት የተቀበለው ይህ ምክር በእርግጥም የሞኝ ነበር፡፡ ሕዝቡ ተጭኖበት የነበረው ቀንበር እንዲነሳለት ለጠየቀው ተማጽኖ የድጋፍ ስሜት አሳይቶ ሥራ ላይ ማዋል፤ ንጉሡ የሚከተለው የአመራር ዓይነት ሊሆን አይገባም የሚለው የወጣት አማካሪዎቹ እምነት ነበር፡፡ በዚህ ፋንታ አምባ ገነን እና ጨካኝ አድርጎ ራሱን ለሕዝቡ ማቅረብ ይኖርበታል ብለው ተናገሩ፡፡ በመጨረሻ ሮብዓም ደካማን የሚያጠቃና የሕዝቡ አመኔታና ታማኝነት የማይገባው አድርጎ ራሱን አቀረበ፡፡ ይህን ተከትሎ የእግዚአብሔር ዓላማ ያልነበረውና ሊሆን የማይገባው መከፋፈል በእግዚአብሔር ሕዝቦች መሃል ተፈጠረ፡፡

**ረቡዕ** **መስከረም 30**

## በቆሮንቶስ የተከሰተው መከፋፈል

በእግዚአብሔር ሕዝቦች መሃል ይደርስ የነበረው የመከፋፈልና ኅብረት የማጣት ችግር በአዲስ ኪዳንም ሳያባራ አሳዛኝ ክስተት እንደሆነ ቀጠለ፡፡ ለምሳሌ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የጻፋቸው የመጀመሪያዎቹ አራት ምዕራፎች በአማኞች መሃል ሕብረት እንዲኖር ይማጸናሉ፡፡ በኤፌሶን እያለ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ስለ ተፈጠሩ የተለያዩ መከፋፈሎች የሰማው ጳውሎስ ስለ ቤተ ክርስቲያን ኅብረት አስፈላጊነትና መለያየት መወገድ ብዕሩን ማንሳት ይጀምራል፡፡ የዚህ መጥፎ ሁኔታ እየተስፋፋ መሄድ በእጅጉ ያሳሰበው ሐዋርያው፤ ለችግሩ የመፍትሔ ምክረ ሐሳብ ለመለገስ የተቻለውን ለማድረግ ሲጥር ይስተዋላል፡፡

በ 1ቆሮ. 1፡10-17 መሰረት በአማኞች መካከል መከፋፈልና ጠብ እንዲፈጠር መንስኤ የሆነው ነገር ምን ሊባል ይችላል?

______________________________________________

______________________________________________

ከቀሎዔ ቤተሰቦች አንዱ በአማኞች መካከል ስለነበረው መከፋፈልና ክርክር ለጳውሎስ ሲነግረው፤ በቆሮንቶስ የነበሩ ወንድምና እህቶች ጉዳይ ሐዋርያውን አብልጦ ያሳስበው ጀመር፡፡ ሐዋርያው በመልእክቱ መግቢያ የተጠቀማቸው ቃላት ጉዳዩ ምን ያህል እንዳሳሰበው ያሳያሉ፡፡ “ወንድሞች ሆይ፤ በመካከላችሁ መለያየት እንዳይኖር፣ አንድ ልብ፣ አንድ ሐሳብ እንዲኖራችሁ፤ እርስ በርሳችሁም እንድትስማሙ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችኋለሁ” (1ቆሮ. 1፡10) ይህ የመፍትሔ ሀሳብ እንደ ክርስቲያን ዘወትር በአንድ ልብ መመላለስ እንደሚኖርባቸው የሚያስታውስ ነበር፡፡ በመካከላቸው አለመግባባትና መከፋፈል እንዲፈጠር ያደረገው ነገር ምንም ይሁን ምን ጳውሎስ እንዲቆም ፈልጎአል፡፡

ሰዎች የቱንም ያህል ችሎታና ስጦታ ሊኖራቸው ቢችልና ለአገልግሎት ቢጠሩ እንኳ፤ ክርስቲያኖች የተጠሩት ክርስቶስን እንዲከተሉ መሆኑን ጳውሎስ የቆሮንቶስ አማኞችን ሲያስታውስ እንመለከታለን፡፡ አማኞች ጎራ ከፍለው የፈጠሩት መለያየት የክርስቶስ ፈቃድ አለመሆኑን ለነገ ሳይል ቁርጥ አድርጎ ነግሮአቸዋል፡፡ የክርስትና ሕብረት አስኳል ክርስቶስ እና እርሱ በመስቀል ላይ የፈጸመው የመሥዋዕትነቱ እውነታ መሆኑንም ጭምር ተናግሮአል (1ቆሮ. 1፡13)፡፡

አንድ ሰው የቱንም ያህል "የከበረ" መንፈሳዊ ነገር ባለቤት፣ መካሪና ተቆጪ፣ ሰባኪና መሪ ሊሆን ቢችል--የክርስትና ኅብረት ምንጭ እውነታው የሚገኘው በሌላ በማንም ሳይሆን በየሱስ ክርስቶስና በእርሱ በተሰቀለው ብቻ ነው፡፡ እኛ ሁላችን በመስቀሉ ግርጌ በተመሳሳይ ደረጃ እንገኛለን፡፡ ጥምቀታችን እርሱ ብቻ ከኃጢአታችን ሊያነጻን በሚችለው በየሱስ ነው፡፡ ይህም ቢሆን በክርስቶስ የሚኖረንን ኅብረት ለማምጣት በተጨባጭ የመሥራት ግዴታ ተጥሎብናል፡፡ በመሆኑም እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስትነታችን የእምነትና የተልዕኮ አንድነታችን ብቻውን ዋስትና ሊሆነን እንደማይችል ይህ አበክሮ ይነግረናል፡፡ የክርስቶስ ፍቅርና ጌትነት አንድ ካላረገን በቀር መከፋፈልና አለመግባባት የዛሬውን የቤተ ክርስቲያናችንን ኅብረት ሊያመነምን ይችላል፡፡

*ጳውሎስ በመልእክቱ ያስቀመጣቸውን አደጋዎች ማስወገድ የምንችለው እንዴት ነው? ከክርስቶስ ውጪ ለማንኛውም ሰው ማሳየት በሚገባን ታማኝነት ዙሪያ ዘወትር ጥንቁቅ መሆን ያለብን ለምንድን ነው?*

**ጥቅምት 1**

## ሐሙስ

## "ነጣቂ ተኩላዎች . . ሰርገው" ይገባሉ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሐዋ. 20፡25-31፡፡ ጳውሎስ የኤፌሶንን ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ያስጠነቀቀበት ጉዳይ ምን ነበር? ይህ እንዳይሆን ለመግታት ምን ማድረግ ነበረባቸው?

---

---

---

በአገልግሎት ዘመኑ ተደጋጋሚ ተቃውሞ ይደርስበት የነበረው ጳውሎስ የየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ንጽህና ጠብቆ ማቆየት ቀላል ሊሆን እንደማይችል ያውቅ ነበር፡፡ ሐዋርያው ከኤፌሶን ሽማግሌዎች ጋር በነበረው የስንብት ቃል በሕዝቅኤል ከጉበኛው ወይም ጠባቂው ምሳሌ (ሕዝ. 33፡1-6) በማንሳት የወንጌል ንጽህና የተጠበቀ እንዲሆን የማድረግ ኃላፊነት እነርሱም እንዳለባቸው ሲነግራቸው ይስተዋላል፡፡ ታማኝ እረኝነት በወቅቱ አገልግሎት ይሰጡ ከነበሩት አሥራ ስድስቱም ጉባዔዎች ይጠበቅ ነበር፡፡

ስለ ሐሰተኛ መምህራን "ነጣቂ ተኩላዎች" (ሐዋ. 20፡29) በሚል በጳውሎስ የቀረበው አገላለጽ የሱስ የበግ ለምድ ለብሰው በመካከላችሁ ለመግባት ከሚያሸምቁ ሐሰተኛ ነቢያት ተጠንቀቁ (ማቴ. 7፡15) ብሎ የተናገረውን ያስታውሰናል፡፡ ጳውሎስ ይህን ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ብዙም ሳይቆይ ሐሰተኛ መምህራን ተከስተው ሐዋርያው በእስያ ባቋቋማቸው አብያተ ክርስቲያናት አማኞች ላይ ነጠቃ መፈጸም ጀመሩ፡፡ ጳወሎስ ለእስያ አብያተ ክርስቲያናት ከሰጣቸው ማስጠንቀቂያዎች መሃል አንዳንዶቹ በኤፌ. 5፡6-14 እና ቆላ. 2፡8 ላይ ተጠቅሰዋል፡፡

እንዲሁም ጳውሎስ በሁለተኛው የጢሞቴዎስ መልእክቱ በቤተ ክርስቲያን ሊከሰቱ በሚችሉ የስህተት ትምህርቶችና ክሕደቶች ዙሪያ በኤፌሶን ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት የነበረውን ጢሞቴዎስ ሲያስጠነቅቅ ይስተዋላል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ 2ጢሞቴ. 2፡14-19፤ 3፡12-17፡፡ ጢሞቴዎስ የሐሰተኛ መምህራንን ሴራ ተቃውሞና የቤተ ክርስቲያንን አንድነት አስጠብቆ ማቆየት በሚችልበት ዘዴ ዙሪያ ሐዋርያው ምን አለው?

---

---

በመጀመሪያ ጢሞቴዎስ "የእውነትን ቃል በትክክል እንደሚያስረዳ" (2ጢሞቴ. 2፡15) አገልጋይ የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ ነበረበት፡፡ እነዚህን ከንቱ ውዝግቦችና መላ ምቶች ማርከስ የሚቻለው በእግዚአብሔር የተሰጡትን አስተምህሮዎች በትክክል በማስተዋልና በማስረዳት ነው፡፡ ማንም ሰው በተሳሳተ ትርጓሜ ተሰናክሎ በየሱስ ላይ ሊኖረው የሚገባውን እምነት እንዳያጣ መከላከል ይቻል ዘንድ፤ ማንኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ከአጠቃላዩ ሥዕል ተቃርኖ እንዳይኖረው ለአምላካዊው እውነት ትክክለኛውን ፍቺ መስጠት የግድ ይሆናል፡፡ ከጉዳዩ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸው አከራካሪ ነጥቦች በእግዚአብሔር ቃል መርኅ ሥር እንዲገዙ ሲደረጉ አማኞች በክርስቶስ ድል አድራጊውን ሕይወት ለመምራት የተዘጋጁ ይሆናሉ፡፡ ጳውሎስ ለራሱ ለጢሞቴዎስ የሰጠው ሁለተኛው ምክረ ሀሳብ "እግዚአብሔርን ከማያስከብር ከንቱ ልፍለፋ ራቅ" (2ጢሞቴ. 2፡16) የሚል ነበር፡፡ ጢሞቴዎስ የከበረና ታማኝ አገልጋይ መሆን የሚሻ ከሆነ፤ ረብ የለሽና መላ ምት ርዕሰ ጉዳዮችን ከአስተምህሮው ማራቅ ነበረበት፡፡ እንደነዚህ ዓይነቶቹ እሰጣ ገባዎች አብልጠው ከአምላካዊው ጽንሰ ሀሳብ ከማራቅ ውጪ የአማኙን እምነት አያንጹም (2ጢሞቴ. 2፡16)፡፡ እግዚአብሔርን ወደ መምሰልና ወደ ስምምነት ሊመራን የሚችል አንድ ነገር--እውነት ብቻ ነው፡፡ ጢሞቴዎስ እነዚህን ስህተቶች ማስወገድ የግድ የሆነበትና በምዕመኑም ላይ ብርቱ ግፊት ያደረገበት ምክንያት ትምህርቱ እንደማይሽር ቁስል በቤተ ክርስቲያን ሰርጎ

በመግባቱ ነበር (2ጢሞቴ. 2፥17)፡፡ ወደ ድምዳሜ ስንመጣ--የቤተ ክርስቲያንን ኅብረት አደጋ ላይ ሊጥል የሚችለው የሐሰት ትምህርት ማርከሻ የእግዚአብሔርን ቃል መታዘዝ ሆኖ እናገኘዋለን (2ጢሞቴ. 3፥14-17)፡፡

በተመሳሳይ የሐሰት ትምህርታቸውን ተጠቅመው በመካከላችን መለያየት ሊያመጡ ከሚችሉ የበግ ለምድ የለበሱ ነጣቂ ተኩላዎች መጠበቅ የምንችለው እንዴት ነው?

## ዓርብ

ጥቅምት 2

*ተጨማሪ ሀሳብ፡ Ellen G. White, “The Rending of the Kingdom,” pp. 87–98, in Prophets and Kings; “A Message of Warning and Entreaty,” pp. 298–308, in The Acts of the Apostles.*

“ጌታ የመረጣቸው አገልጋዮቹ እንዴት ለዛ ያለው አንድነት ማምጣት እንዳለባቸው ይማሩ ዘንድ ምኞቱ ነው፡፡ አንዳንዶች በእነርሱና በሌሎች አገልጋዮች ስጦታዎች መሃል ያለውን ልዩነት እጅግ አግዝፈው በማሰብ ፋይዳ ያለውን ኅብረት ለመፍጠር አዳጋች አድርገው ያስባሉ፡፡ ነገር ግን አማኞች የእውነትን ብርሃን ሊያደርሷቸው የሚገቡ በተለያየ የአዕምሮ ሁናቴ የሚገኙ--ማለትም መልእክቱ እንደተመሰከረላቸው የሚቃወሙ መኖራቸውን ሲያስታውሱ፤ ከወትሮው ለየት ባለ አግባብና አቀራረብ እነዚህን አፈንጋጭ ልቦች ለአምላካዊው እውነት ለመክፈት መሥራት እንደሚችሉ ያስተውላሉ፡፡ በዚህም ከሌሎች ጋር በኅብረት ለመሥራት የሚያስችላቸውን ጥረት ለማድረግ ተስፋ ያደርጋሉ፡፡ መክሊቶቻቸው የቱንም ያህል ብዝሃነት ቢኖራቸውም ነገር ግን በአንድ መንፈስ ቁጥጥር ሥር የዋሉ ይሆናሉ፡፡ እያንዳንዱ ከአንደበታቸው የሚወጣ ቃልም ሆነ ድርጊት ደግነትንና ፍቅርን የሚገልጽ ይሆናል፡፡ እያንዳንዱ ሠራተኛ ታማኝ ሆኖ የተመደበበትን ስፍራ ሲሞላ ክርስቶስ ለተከታዮቹ ኅብረት የጸለየው ጸሎት ምላሽ ያገኛል፡፡ እነዚህ ወገኖች የእርሱ ደቀ መዛሙርት መሆናቸውንም ዓለም ይገነዘባል፡፡—Ellen G. White, Gospel Workers, p. 483.

### መወያያ ጥያቄዎች፥

1. በአንድ ሰው “ዐይን” ትክክል የሆነውን ነገር የማድረግ ተገቢነት ጥያቄ አዲስ የፍልስፍና ሀሳብ አይደለም፡፡ ማዕከላዊነትን፣ የዕውቀት መጀመሪያ ወይም የግብረገብን ገዢነት ጽንሰ ሃሳብ አልቀበል የሚለው ድኅረ ሥልጣኔ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ወደሚያስጠነቅቀው ሕገ ጠል ግርግር የሚወስደውን መንገድ የመጥረግ ኃይል አለው፡፡ እኛ እንደ ክርስቲያንነታችን ብሎም በአጠቃላይ እንደ ቤተ ክርስቲያን ከእንዲህ ያለው ፈታኝ ሁኔታ ጋር መጋጠም የምንችለው እንዴት ነው?

2. የንጉሥ ሮብዓምን እና የእስራኤልን መከፋፈል ታሪክ አሰላስሉ (1ነገሥ. 12) ዛሬስ ለእኛ ምን ትምህርት እናገኛለን?

3. በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሁከት፣ ጥልና መከፋፈል እንዳይነሳ ለመከላከል የቤተ ክርስቲያን አባላትና መሪዎች ምን ማድረግ ይኖርባቸዋል? እነዚህ ጉዳዮች በፍጥነት እያደጉ ከመሄዳቸው አስቀድሞ እንዲገቱ ማድረግ ምን ያህል አስፈላጊ ነው?

እኛም እንደ አንዳንዶቹ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አባላት በወጥመድ እንዳንወድቅ-- እንደ ቤተ ክርስቲያን አባልነታችን እንዴት መጠንቀቅ ይኖርብናል?

4. በምሳ. 6፡16-19 በአለመስማማት ዙሪያ የቀረበውን መልእክት ዐውድ ያጥኑ፡ ፡ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንዎ ሊከሰት የሚችልን ጸብና መለያየት ለማስቀረት ከዚህ ምን ዓይነት ትምህርት ያገኛሉ?

*ማጠቃለያ፡* በመጽሐፍ ቅዱስ ወደ መከፋፈል የሚመሩ ሁኔታዎች ተጠቅሰው እንመለከታለን፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በታማኝ መታዘዝ ሲመላለሱ የመከፋፈል አደጋዎች በእጅጉ ቀንሰው ነበር፡፡ በመሳፍንቶች ዘመን የተስተዋሉትም ሆኑ በሮብዓም ንግሥና ወቅት የታየው መጥፎ ውሳኔ የመከፋፈልን በራፍ ወለል አርገው ከፈቱ፡፡ በአዲስ ኪዳን ዘመንም የመከፋፈል ዕድል ያለ እንደመሆኑ፤ በመካከላችን ሊከሰቱ የሚችሉ መከፋፈሎችንና መለያየቶችን መከላከል የሚቻልበት ምርጥ መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል ማስተዋልና ለመታዘዝ የሚደረግ ቅዱስ ቁርጠኝነት ናቸው፡፡

# 3ኛ ትምህርት ከጥቅምት 3 - 9

## “ሁሉም አንድ እንዲሆኑ”

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ዮሐ. 17:1–26፤ 1ዮሐ. 5:19፤ ዮሐ. 13:18–30፤ ዮሐ. 5:20–23፤ ማር. 9:38–41፤ ራእ. 18:4፤ 1ዮሐ. 2:3–6፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ :-**“ ‘የእነርሱን ትምህርት ተቀብለው በእኔ ለሚያምኑ ጭምር እንጂ ለእነዚህ ብቻ አልጸልይም፤ ይህም፣ አባት ሆይ፤ አንተ በእኔ፣ እኔም በአንተ እንዳለሁ ሁሉም አንድ እንዲሆኑ፣ እንዲሁም አንተ እኔን እንደ ላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፣ እነርሱም በእኛ እንዲሆኑ ነው፡፡” (ዮሐ. 17፡ 20-21)፡፡

በየሱስ ላይ ሊደርስ የተቃረበው ክህደትና ሞት ከወዲሁ ያስከተለበትን ጭንቀትና በአድማሱ አጥልቶ የነበረውን አስፈሪ ድባብ የዮሐንስ ወንጌል ያስቃኘናል፡፡ አልፎ አልፎ “የሊቀ ካኅናት ጸሎት” (ዮሐ. 17) በሚል የሚታወቁትንና የየሱስ የመጨረሻ ቃላት የሆኑትን አስደማሚ መመሪያዎች በአምስቱ ወሳኝ ምዕራፎች (ዮሐ. 13-17) እናገኛቸዋለን፡፡

“በአንዴ ሁለቱንም--ማለትም ካኅን እና የመሥዋዕት በግ በመሆን በዚህ ጸሎት ራሱን ቀድሶና ቤዛ አድርጎ መስጠቱ ለጌታችን ገጣሚ ክብርና ማዕረግ ነው፡፡ በተመሳሳይ ይህ የቅድስና ጸሎት የተደረገው ቤዛ ስለ ሆናቸው በሰገነት ስለ ነበሩት ደቀ መዛሙርት እና የኋላ ኋላ በእነርሱ ምስክርነት ወደ እምነት ለሚመጡ ሁሉ ነበር፡፡”—F. F. Bruce, The Gospel of John (Grand Rapids: Eerdmans, 1983), p. 328.

የዚህ ጸሎት ዋንኛ ክፍል--በደቀ መዛሙርቱ እና በወደፊቶቹ በአዳዲስ አማኞች መሃል ሊኖር የሚገባ ኅብረት ምን ያህል የሱስን እንደሚያሳስበው ያሳየ ነበር፡፡ “‘ስለ ሰጠኸኝና የአንተ ስለሆኑት እንጂ ለዓለም አልጸልይም፡፡ የእኔ የሆነው ሁሉ የአንተ ነው፤ የአንተ የሆነውም ሁሉ የእኔ ነው፤ በእነርሱም ከብሬአለሁ’” (ዮሐ. 17፡9-10) ይህ የየሱስ ጸሎት ቁልፍ ጭብጥ ነበር፡፡

ለዚህ ጸሎት ጥንቃቄ የተሞላው ትኩረት ሳንሰጥ በክርስቶስ አንድ የመሆኑ የቤተ ክርስቲያን ኅብረት የተሟላና ፋይዳ ያለው ውይይት ሊኖረው አይችልም፡፡ የሱስ ስለ ምን ጸለየ? ስለ ማን ጸለየ? የእርሱ ጸሎት ዛሬ ለእኛ ምን ትርጉም አለው?

**እሁድ**

**ጥቅምት 4**

## የሱስ ስለ ራሱ መጸለዩ

የሱስ እንደ ሊቀ ካኅንነቱ የጸለየው ጸሎት በሦስት ይከፈላል፡፡ በመጀመሪያ ለራሱ መጸለዩ (ዮሐ. 17፡1-5)፣ በሁለተኛ ደረጃ ለደቀ መዛሙርቱ ያደረገው ጸሎት (ዮሐ. 17፡6-19)፣ ሦስተኛው ደግሞ በእርሱ ለሚያምኑ የወደፊት አማኞች የጸለየው ጸሎት ናቸው (ዮሐ. 17፡20-26)፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዮሐ. 17፡1-5፡፡ የጸሎቱ ይዘት ምንድን ነው? ለእኛ ያለው ትርጉምስ ምን ይመስላል?

________________________________________________

________________________________________________

የሱስ በመጀመሪያ ለራሱ ይማልዳል፡፡ በዚሁ በዮሐንስ ወንጌል ቀደምት መልእክቶች የሱስ ጊዜው ገና አለመድረሱን ሲናገር እንመለከታለን (ዮሐ. 2፡4፣ 7፡30፣ 8፡20)፡፡ አሁን ግን ለኃጢአት መሥዋዕት የሚሆንባት ያቺ ሰዓት መቃረቧን ያወቀው የየሱስ ምድራዊ ህይወት ትዕይንት ከፍጻሜ ደርሶ ነበር፡፡ ሰብዓዊነትን ወስዶ የመጣበትን ምድራዊ ተልዕኮ በድል ለማጠናቀቅ ብርቱ ጥንካሬ ያስፈልገዋል፡፡ እነሆ ጊዜው የጸሎት ነው፡፡

የሱስ በአስጨናቂው የመስቀል ጎዳና ማለፉ ግዴታ ቢሆንበት እንኳ የአባቱን ፈቃድ በማድረግ እርሱን ከማክበር ወደ ኋላ አይልም ነበር፡፡ የሱስ የመስቀል ላይ መሥዋዕትነቱን መቀበሉ በተለምዶ እንደሚባለው "ዕጣ ፈንታው" ወይም "የአርባ ቀን ዕድሉ" ሳይሆን--እውነታው አብ የሰጠውን ሥልጣን በተግባር የሚለማመድበት ነበር፡፡ የሱስ ሰብዓዊውን ሥጋ ለመልበስ ምክንያት የሆነውን ተልዕኮ በሙሉ ፈቃደኝነት በማሳካት ይኸውም ለዓለም ኃጢአት የመሥዋዕት ሞት በመሞት አባቱን አከበረ እንጂ የሰማዕት ሞት አልሞተም፡፡

በዮሐ. 17፡3 መሰረት የዘላለም ሕይወት ምን ማለት ነው? እግዚአብሔርን ማወቅ ስንል ፍቺው ምንድን ነው?

________________________________________________

________________________________________________

የዘላለም ሕይወት ጽንሰ ሃሳብ እግዚአብሔርን በግል በማወቃችን ላይ የተመሰረተ ነው ሲል የሱስ በቀዳሚና በዋነኝነት ይነግረናል፡፡ ደኅንነት የሚገኘው በሥራ ወይም በዕውቀት ሳይሆን የሱስ በመስቀል ላይ ካደረገልን ነገር አኳያ ጌታን የማወቅ ተሞክሮ ነው፡፡ ይህ ዕውቀት ከአብ ጋር ባለን የግል ግንኙነት ይማከላል፡፡ ዕውቀትን በጭብጥና ዝርዝር በሆኑ ጉዳዮች መገደብ ሰብዓዊ ዝንባሌአችን ቢሆንም፤ ነገር ግን የሱስ እዚህ ላይ ጥልቀት ያለውንና አብልጦ እርካታ ሊያመጣ የሚችለውን ይኸውም

ከእግዚአብሔር ጋር ግላዊ ግንኙነት መፍጠርን ኢላማ ሲያደርግ ይታያል፡፡ ሌላኛው የመጀመሪያው የየሱስ ምጽአት ዓላማ ሰብዓዊው ፍጡር የእግዚአብሔርን ማንነት ለማወቅ ለሚያደርገው ፍተሻ ይበልጥ ትርጉም ወዳለውና የሚያድን ዕውቀት መምራት ነው፡፡ ይህ ዕውቀት ወደ እርስ በርስ ኅብረት መምራቱ ዕሙን ነው፡፡

*ስለ እግዚአብሔር በማወቅና እርሱን በግል በማወቅ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ እንዲመጡ የረዱዎት ምን ዓይነት ተሞክሮዎች አሉዎት?*

**ሰኞ** **ጥቅምት 5**

## የሱስ ስለ ለደቀ መዛሙርቱ መጸለዩ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዮሐ. 17፡9-19፡፡ የሱስ በተለይ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በተያያዘ ምን ብሎ እየጸለየ ነው?

---

---

የሱስ በመቀጠል የጸለየው ለደቀ መዛሙርቱ ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ ያ የቀደመ የጌታ አብሮነት በማከተሙ፤ በእርሱ ላይ የነበራቸውን እምነት ሊያሳጡ የሚችሉ የከፉ አደጋዎች ከፊታቸው ባሉት ቀናት ተደቅነው ነበር፡፡ በዚህ የተነሳ ለአብ ጥበቃና ጥንቃቄ አሳልፎ ሰጣቸው፡፡

ደቀ መዛሙርቱ ከዓለም ይጠበቁ ዘንድ የሱስ ስለ እነርሱ ጸለየ እንጂ ስለ ዓለም አልጸለየም፤ ምክንያቱም ዓለም የአብን ፈቃድ እንደሚቃወም ያውቃል (1ዮሐ. 5፡19)፡፡ ነገር ግን ይህ ዓለም ደቀ መዛሙርቱ አገልግሎት የሚሰጡበት አውድማ እንደመሆኑ በውስጡ ካለው ክፉ ሁሉ እንዲጠበቁ ጸለየ፡፡ የሱስ በዓለም ያሉ ፍጥረቶቹ ሁኔታ ግድ ስላለው የአዳኝነቱን ስፍራ ወሰደ፡፡ የወንጌል ስርጭት ወደ ዓለም ወጥተው መልካሙን የምስራች ከሚሰብኩ ወገኖች ጋር በጥብቅ የተሳሰረ በመሆኑ፤ ክፉው እንዳያሸንፋቸው ስለ እነርሱ መማለድ አስፈለገው (ማቴ. 6፡13)፡፡

የሆነው ሆኖ ከየሱስ ደቀ መዛሙርት መካከል አንዱ ሽንፈት አገኘው፡፡ ከዚያ ምሽት ቀደም ብሎ ከመካከላቸው አንዱ ሊክደው (አሳልፎ ሊሰጠው) መወሰኑን የሱስ ጠቅሶ ነበር (ዮሐ. 13፡18-30)፡፡ ምንም እንኳ የሱስ ብሉይ ኪዳን ስለ ይሁዳ ክህደት የተነገረውን ትንቢት ቢጠቅስም (መዝ. 41፡9) ይሁዳ የዕጣ ፈንታ ሰለባ አልነበረም፡፡ በዚያ የመጨረሻ የጌታ እራት አገልግሎት የሱስ የፍቅርና የወዳጅነት ስሜት አሳይቶት ነበር (ዮሐ. 13፡26-30)፡፡ "በፋሲካ የጌታ ራት የሱስ ክህደት ሊፈጽምበት የተሰናዳውን ደቀ መዝሙር ሃሳብ በመግለጥ መለኮታዊ ባህሪውን አሳየ፡፡ በደግነት የተሞላው የሱስ ይሁዳን በደቀ መዝሙርነት ተቀብሎ የአገልግሎቱ አካል አደረገው፡፡ ሆኖም

የመጨረሻው የፍቅር ተማጽኖ ተገቢውን ከበሬታና ተቀባይነት ማግኘት ሳይችል ቀረ፡ ፡"—Ellen G. White, The Desire of Ages, p. 720.

ቀደም ሲል እንደ ተከሰተው ክፉ ቅናትና ምቀኝነት ደቀ መዛሙርቱን ሊከፋፍል እንደሚችል ያውቅ የነበረው ጌታ በመካከላቸው ኅብረት እንዲኖር ጸለየ፡፡ "ቅዱስ አባት ሆይ፤ እኛ አንድ እንደ ሆንን፣ እነርሱም አንድ እንዲሆኑ በሰጠኸኝ በስምህ ጠብቃቸው" (ዮሐ. 17፡11)፡፡ እንዲህ ያለው ኅብረት ከሰብዓዊው ሥራ ውጤት በላይ በመሆኑ፤ የመለኮታዊው ጸጋ ስጦታ ውጤት ብቻ ይሆናል፡፡ አንድነታቸው በአብና በወልድ ኅብረት ላይ መመስረቱ ለወደፊቱ ውጤታማ አገልግሎት ወሳኝ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡

በእውነት መቀደሳቸው ወይም መባረካቸው ሌላው ለአገልግሎት ወሳኙ ነጥብ ነው፡፡ በደቀ መዛሙርቱ ልብ ውስጥ የሚተገበረው የአምላካዊው ጸጋ ሥራ የተለወጡ ሰዎች ያደርጋቸዋል፡፡ የእግዚአብሔርን እውነት የመመስከር አገልግሎት እስከ ሰጡ ድረስ፤ እነርሱ ራሳቸው በዚያ እውነት መለወጣቸው የግድ ይሆናል፡፡

*"ከዚህ ዓለም" አለመሆን ማለት ምን ማለት ነው? የዕለት ከዕለት ህይወታችንም ሆነ የአኗኗር ዘይቤአችን "ከዚህ ዓለም" አለመሆናችንን ማሳየት የሚችለው እንዴት ነው?*

**ማክሰኞ** **ጥቅምት 6**

## "በእኔ ለሚያምኑ"

የሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ከጸለየ በኋላ የልመናውን ይዘት በማስፋት እንዲህ ብሎአል፡ "የእነርሱን ትምህርት ተቀብለው በእኔ ለሚያምኑ ጭምር እንጂ ለእነዚህ ብቻ አልጸልይም" (ዮሐ. 17፡20)፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዮሐ. 17፡20-26፡፡ የሱስ ውሎ አድሮ በወንጌል መልእክት ለሚያምኑ ወገኖች የነበረው ምኞት ምን ነበር? የዚህ ጸሎት ፍጻሜ ማግኘት ወሳኝ የሆነው ለምንድን ነው?

---

---

አብ እና ወልድ አንድ እንደሆኑ ሁሉ የወደፊቶቹም አማኞች አንድ ይሆኑ ዘንድ የሱስ ጸለየ፡፡ የሱስ የአብን እና ወልድን አንድነት አስመልክቶ የጠቃቀሳቸውን ጥቂት ነጥቦች በዮሐንስ ወንጌል እናገኛለን፡፡ አብም ሆነ ወልድ ማንኛውንም ተግባር የሚያከናውኑት በተናጥል ሳይሆን ሁሌም በአንድነት ነው (ዮሐ. 5፡20-23)፡፡ አብ ልጁን ለዓለም አሳልፎ እስከ መስጠት ፈቃደኛ መሆኑ እና ወልድ ህይወቱን ለመስጠት እሺታውን መግለጹ ለወደቀው ሰብዓዊ ዘር ያላቸውን የማይነጣጠል ፍቅር ያሳያል (ዮሐ. 3፡16፣ 10፡15)፡፡

የሱስ በዚህ ጸሎቱ በአብ እና በወልድ መካከል ያለውን የፍቅርና የዓላማ እንድነት ይጠቅሳል፡ "'እርስ በርሳችሁ ብትዋደዱ፣ ሰዎች ሁሉ የእኔ ደቀ መዛሙርት እንደሆናችሁ በዚህ ያውቃሉ' " (ዮሐ. 13፡35)፡፡ ከአብም ሆነ ከወልድ ጋር የሚኖርን አንድነት በፍቅር ገልጾ ማሳየት ለታዛቢው የማይታበል ማረጋገጫ ይሆናል፡፡ "እውነተኛ ልባዊ አንድነታቸውን የሚገልጸው ተግባራቸው፤ ለወንጌል እውነት አሳማኝ ምስክርነት መስጠቱ የግድ ይሆናል"—Andreas J. Köstenberger, John, Baker Exegetical Commentary on the New Testament (Grand Rapids: Baker Academic, 2004), p. 498. ይህ እንግዲህ የየሱስን አዳኝነት ዓለም የሚያውቅበት መንገድ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ይህ የሱስ የጸለየለት አንድነት በሰዎች የማይታይና የተሰወረ መሆን አይችልም፡፡ ዓለም በእግዚአብሔር ሕዝቦች መሃል ፍቅርና አንድነት ማየት ሳይችል የወንጌልን እውነትነት እንዴት አምኖ መቀበል ይሆንለታል?

"እግዚአብሔር በዘላለማዊው እውነት መድረክ በፍጹም አንድነት የሚቆሙ ሕዝቦችን እየመራ ነው... ሕዝቦቹ ሁሉ ወደ እምነት አንድነት ይመጡ ዘንድ አምላካዊው እቅድ ነው፡፡ ክርስቶስ ራሱን በመስቀል ላይ መሥዋዕት አድርጎ ከመስጠቱ ጥቂት ቀደም ብሎ እርሱ ከአብ ጋር አንድ እንደሆነ ደቀ መዛሙርቱም አንድ እንዲሆኑ ጸለየ፡፡ ክርስቶስ በአብ የተላከ አዳኝ መሆኑን ዓለም ማመን ነበረበት፡፡ 'የእነርሱን ትምህርት ተቀብለው በእኔ ለሚያምኑ ጭምር እንጂ ለእነዚህ ብቻ አልጸልይም'--የተሰኘው ይህ በእጅጉ ልብ የሚነካና ወደር የማይገኝለት ጸሎት ዘመናትን ተሻግሮ እነሆ ከእኛም ጊዜ ደርሶአል፡፡

"የክርስቶስ ተከታዮች ለዚህ ጸሎት በሕይወታቸው ምላሽ የመስጠት ብርቱ ኃላፊነት ወድቆባቸዋል"—Ellen G. White, Testimonies for the Church, vol. 4, p. 17.

*በዚህ ስፍራ የቀረበው ዓይነት ኅብረት ላይ ለመድረስ በግል ሕይወታችንና በቤተ ክርስቲያን ምን እያደረግን እንገኛለን? ቤተ ክርስቲያናችን ወደሚፈለገው ኅብረት እንድታመራ ፍላጎታችን ከሆነ እያንዳንዳችን ለዓለም የምትን መሆናችን ወሳኝ የሆነው ለምንድን ነው?*

**ጥቅምት 7**

**ረቡዕ**

## ኅብረት በክርስቲያኖች መሃል

የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ማር. 9፡38-41፣ ዮሐ. 10፡16፡፡ ማነው እውነተኛ የየሱስ ተከታይ በሚል ለሚነሳው ጥያቄ ከእኛ በላይ ላሳር ለተሰኘው ምላሽ እና ቅጽበታዊ ፍረጃ አግባብነት ዙሪያ የሱስ ለደቀ መዝሙሩ ዮሐንስ ከሰጠው ምላሽ ምን እንማራለን?

ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች የሱስ በዮሐ. 17 የጸለየውን ጸሎት በቀጥታ ከቤተ ክርስቲያናቸው ኅብረት ጋር ገጣሚ አድርገው የማስተዋል አካሄድ ይከተላሉ፡፡ የሦስቱን መላእክት መልእክት ለዓለም በማካፈል ተልዕኮአችንን ከዳር ለማድረስ እንደ ቤተ ክርስቲያን አንድ ልንሆን ይገባል፡፡ ሆኖም እዚህ ላይ መጠኑ ቢያንስም ሞጋች ሃሳብ አለ፡፡

ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ስለሚኖረን ኅብረትስ? የሱስ የጸለየውን ጸሎት ከእነርሱ ጋር ከሚኖረን ኅብረት ብርሃን አኳያ እንዴት እናዛምደዋለን ነው?

ልክ እንደኛ ሁሉ እግዚአብሔር በሌሎች ቤተ ክርስቲያኖችም ታማኝ ሕዝቦች እንዳሉት እናምናለን፡፡ በተጨማሪ እግዚአብሔር በባቢሎን ሳይቀር ታማኞች እንዳሉት መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስቀምጥልናል፡፡ "'ሕዝቤ ሆይ፤ በኃጢአቷ እንዳትተባበሩ፣ ከመቅሰፍቷም እንዳትካፈሉ፣ ከእርሷ ውጡ' " (ራእ. 18፡4)፡፡

በተመሳሳይ የክርስቶስ ተከታዮች ነን በሚሉ ታላቅ የክህደት ተግባር እንደሚፈጸም ከራእይ መጽሐፍ እንረዳለን፡፡ ይህን ተከትሎ አያሌ ሐሰተኛ ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው ብሎም ከመንግሥት ጋር በሚፈጥሩት ኅብረት በራእ. 13፡1-17 የተገለጸው ስደት ገቢራዊ ወደ መሆን ይመጣል፡፡ በዚህ የተነሳ አድቬንቲስቶች እንደ አለማቀፉ የአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት የሚቀርቡላቸውን የኅብረታችን አካል ሁኑ ጥሪ የሚመለከቱት ሁሌም በጥንቃቄ ነው፡፡

ነገሩ እንዲህ ከሆነ ከሌሎች የክርስትና ድርጅቶች ጋር አግባብ መፍጠር የምንችለው እንዴት ነው? ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች አብያተ ክርስያናት ጋር አብራ በምትሠራቸው ሥራዎች ዙሪያ ኤለን ጂ. ኋይት የሚከተለውን ጽፋለች፡፡ "ሰብዓዊው ወኪል የገዛ ፈቃዱን ለእግዚአብሔር ሲያስገዛ መንፈስ ቅዱስ ግለሰቡ የሚያገለግላቸውን ወገኖች ልብ ይነካል፡፡ እንደ Women's Christian Temperance Union የመሳሰሉትን ኅብረቶች መራቅም ሆነ መተው እንደሌለብን ተመልክቻለሁ፡፡ ከእነርሱ ጋር በምንፈጥረው ኅብረት ከሚያሰክር መጠጥም ሆነ በአካላችን ላይ ጉዳት ከሚያደርሱ ልል ልማዶች ሙሉ ለሙሉ ተጠብቀንና በሰንበት ርዕሰ ጉዳይ ላይ ያለንን አቋም ጠብቀን፤ መሻትን በመግዛት ዙሪያ ያላቸውን አቋም ማድነቅ እንችላለን፡፡ መሻትን በመግዛት ዙሪያ ለሚነሱ ጥያቄዎች በራችንን ከፍተን ከእኛ ጋር ኅብረት ፈጥረው የሚሠሩበትን ግብዣ በማቅረብ ጽኑ እገዛቸውን ማግኘት እንችላለን፡፡ እነዚህ ወገኖች እንዲህ ያለውን ኅብረት ከእኛ ጋር ሲፈጥሩ አዳዲስ እውነቶችን ይሰማሉ፡፡ መንፈስ ቅዱስም እነዚህን ልቦች የማነቃቃት ሥራ ለመሥራት ይጠባበቃል፡፡"—Welfare Ministry, p. 163.

ምንም እንኳ ጸሐፊዋ በአንድ ወቅት ስለ ነበረ ኅብረት እየተናገረች ቢሆንም ነገር ግን ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር በሚኖረን ዝምድና በተለይም በአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ጥያቄዎች ዙሪያ ልንከተላቸው የሚገቡ መርኅዎችን ትሰጣለች፡፡ አብረን ልንሠራ

የምንችልባቸው ነጥቦች፡--(1) የጋራ ፍላጎት ማሳደር በሚችሉ ማኅበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ (2) የእምነታችን እሴቶችና ልምምዶች ሳይጣሱ እንዲጠበቁ አጽንኦት በመስጠት (3) የተባረክንባቸውን የከበሩ እውነቶች ለሌሎች በማካፈል ይህን "ኅብረት" ጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል፡፡

**ሐሙስ** **ጥቅምት 8**

## በፍቅር የምንጋራው አንድ እምነት

ዘላለማዊ ሕይወት ማለት እግዚአብሔርን ማወቅ ነው--ሲል የሱስ በዮሐ. 17:3 ተናግሮአል፡፡ ለመሆኑ እግዚአብሔርን ማወቅ ምን ማለት ነው? እግዚአብሔርን ማወቃችንን በየቀኑ ሕይወታችን የምናሳየውስ እንዴት ነው?

ከመቼውም የዓለም ታሪክ በላቀ ሥልጡን እንደሆነ የሚናገረው የዘመናችን ማኅበረሰብ ራሱን ለሕግ ታዛዥ ዜጋ አድርጎ ሲያቀርብ ቢስተዋልም--ነገር ግን በእግዚአብሔር የተጣለበትን አምላካዊ ትእዛዛት የመጠበቅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግዴታውን ከመወጣት ይልቅ ጉዳዩን ዝቅ አድርጎ ሲመለከት ይስተዋላል፡፡ እንደውም አንዳንዶች ትእዛዛቱ በእግዚአብሔር ጸጋ ተወግደዋል ሲሉ ይሞግታሉ፡፡ ሆኖም ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ አይደለም፡፡ "ትእዛዛቱን መጠበቅ እግዚአብሔርን የማወቃችን መሰረት ሳይሆን እግዚአብሔርን/ የሱስን የማወቃችንና እርሱን የመውደዳችን ምልክት ነው፡፡ ስለዚህ በእግዚአብሔር ላይ ያለን ዕውቀት በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ወደ ተግባር የሚመራን ጭምር ነው፡፡"—Ekkehardt Mueller, The Letters of John (Nampa, Idaho: Pacific Press, 2009), p. 39. የሱስ ራሱ ስለዚህ ጉዳይ አጽንኦት ሰጥቶ ሲናገር "ብትወዱኝ ትእዛዜን ትጠብቃላችሁ፡፡" "የሚወደኝ ትእዛዜን ተቀብሎ የሚጠብቅ ነው" ይላል (ዮሐ. 14፡15፣ 21)፡፡ "እግዚአብሔርን ስንወድና ትእዛዛቱን ስንፈጽም የእግዚአብሔርን ልጆች እንደምንወድ በዚህ እናውቃለን፤ እግዚአብሔርን መውደድ ትእዛዛቱን መፈጸም ነውና፡፡ ትእዛዛቱም ከባድ አይደሉም፡፡" (1ዮሐ. 5፡2-3)፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዮሐ. 13፡34-35፡፡ የሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸው አዲስ ትእዛዝ ምን ነበር? ይህ በየሱስ ተከታዮች መካከል ከሚኖር ኅብረት ጽንሰ ሀሳብ ጋር የሚዛመደው እንዴት ነው?

ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ በሚል የቀረበው ትእዛዝ እግዚአብሔር ለሙሴ

የሰጠው ትእዛዛት አካል እንደ መሆኑ በራሱ አዲስ አልነበረም (ዘሌዋ. 19፡18)፡፡ አዲስ የሆነው እርሱ እንደ ወደዳቸው ደቀ መዛሙርቱም እርስ በርሳቸው እንዲዋደዱ የሰጣቸው ትእዛዝ ነበር፡፡ ራስን መሥዋዕት አድርጎ እስከ መስጠት የደረሰው የየሱስ ፍቅር ምሳሌ ለክርስቲያኑ ማኅበረሰብ በዓይነቱ አዲስ ሥነ ምግባራዊ አስተምህሮ ነበር፡፡

እንዴት ያለ እጹብ ድንቅ ሥርዓት ከፊታችን ተዘርግቶአል! የየሱስ ሕይወት--ፍቅር በተግባር የተገለጸበት ትዕይንት ነው፡፡ አጠቃላዩ የጸጋ ሥራ ራስን የመካድና መሥዋዕት አድርጎ የማቅረብ የማያቋርጥ የፍቅር አገልግሎት ጥረት ነው፡፡ የክርስቶስ ሕይወት ስለ ሌሎች መልካም ሲባል የማያቋርጥ ፍቅርና ራስን መሥዋዕት ማድረግ የተገለጸበት መሆኑን መረዳት እንችላለን፡፡ በክርስቶስ ላይ መነሳሳት የፈጠረው መርኅ በሕዝቦቹ የእርስ በርስ ግንኙነትም ላይ መነሳሳት ሊፈጥር የተገባ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ፍቅር በመካከላችን አንድነት እንዲኖር መንስዔ ከመሆኑ ባሻገር ለዓለም ብርቱ ምስክር መሆኑ አንድና ሁለት የለውም፡፡

*የሱስ የገለጠው ዓይነት ራስን መሥዋዕት አድርጎ የመስጠትን ፍቅር በተመሳሳይ ለሌሎች ገልጦ ማሳየትን መማር የምንችለው እንዴት ነው?*

## ዓርብ

## ጥቅምት 9

*ተጨማሪ ሀሳብ፡-- Ellen G. White, "God's Law Immutable," pp. 443–446, in The Great Controversy. Read the articles "Denominations, Relations to Other," pp. 763, 764, and "Roman Catholic Church," p. 1110, in The Ellen G. White Encyclopedia.*

"ምንም እንኳ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን የአያሌ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖች ባለቤት ዓለማቀፍ ተቋም ብትሆንም ነገር ግን አድቬንቲስቶች እንደ ብቸኛዋ ሁለንተናዊ ዩኒቨርስ አቀፍ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አይመለከቷትም፡፡ ለዚህ መንስዔው ዩኒቨርስ አቀፏ ሁለንተናዊ ቤተ ክርስቲያን ከማንኛውም የክርስትና ተቋም እጅግ የገዘፈ ባህሪ በመላበሷ ነው፡፡ ዩኒቨርስ አቀፏ በየሱስ የሚያምኑትንና እርሱን የሚከተሉትን ወገኖች በአንድ የምትይዝ እንደ መሆኗ ስፋትና መጠኗ የሚታይ፣ የማይታይም ነው፡፡ ይህ በዓይነቱ ልዩ የሆነ ሥነ መለኮታዊ ጉዳይ በራእይ መጽሐፍ አሳዛኝ በሆነ ሁኔታ የተገለጸውንና በክርስቲያኖች መካከል ገቢራዊ የሆነውን ክህደት ከግምት ካስገባ ወደ ጡዘት ሊያመራ ይችላል፡፡ በበጉ፣ በሙሽራው፣ በቅድስት ከተማ ወይም በአዲሲቱ የሩሳሌም (ራእ. 21፣22) የተመሰለችውና በራእ. 12 የምናገኛት ጉድፍ ዐልባዋ ንጽሕት ቤተ ክርስቲያን ከራእ. 17 ታላቂቷ 'አመንዝራ' ከተማ ባቢሎን ጋር በንጽጽር ቀርባለች፡፡ ለምሳሌ ዩኒቨርስ አቀፏ ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ በገሃድ የመታየት ሁኔታ ቢገጥማትም--ነገር ግን ይህችኑ ቤተ ክርስቲያን መካከለኛው ክፍለ ዘመን ላይ ማየት እጅግ ውስብስብና አስቸጋሪ ሆኖ

እናገኘዋለን፡፡

“ስለዚህ አድቬንቲስቶች የእውነተኛዋን የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ጽንሰ ሃሳብ በራሳቸው ኃይማኖታዊ ተቋም ብቻ አይወስኑም ወይም ከሌሎች የክርስትና ኃይማኖታዊ ተቋሞች ጋር በቀጥታ አያያይዙም፡፡ እውነተኛዋ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን እርሱን በእውነት የሚያምኑትን ወገኖች ታካትታለች፡፡ እግዚአብሔር እነዚህን ወገኖች ያውቃቸዋል፡፡ በሌላ በኩል አድቬንቲስቶች ራሳቸውን በራእ. 12፡17 እንዲሁም ከምዕራፍ 12-14 የተጠቀሱት የእግዚአብሔር የመጨረሻው ዘመን ትሩፋን አድርገው ያምናሉ፡፡ ትሩፋኑ አካባቢያዊም ሆነ ዩኒቨርስ አቀፍ ባህሪ የተላበሱ ናቸው፡፡”— Ekkehardt Mueller, “The Universality of the Church in the New Testament,” in Ángel Manuel Rodríguez, ed., and Message, Mission, and Unity of the Church (Silver Spring, Md.: Biblical Research Institute, General Conference of Seventh-day Adventists, 2013), p. 37.

## የመወያያ ጥያቄዎች፥

1. የሱስ በዮሐ. 17 የጸለየው ጸሎት ፍጻሜ ማግኘት ለቤተ ክርስቲያናችን እጅግ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? ለመጀመሪያው ክፍለ ዘመኗ ቤተ ክርስቲያን አንድነት የነበረው ፍላጎትስ ስለ ዛሬዋ ምን ያሳየናል?

2. አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንዎ ከማኅበራዊ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር አብራ የምትሠራባቸው አጋጣሚዎች ተፈጥረዋል? የተገኘው ስኬት ምን ይመስላል? አመቺ ሁናቴዎች በተገኙ ቁጥር በተሰጡን እውነቶች ላይ ሳንደራደር አብረናቸው መሥራት የምንችለው እንዴት ነው?

3. በመቀጠል የቀረበው በታላቁ ተጋድሎ መጽሐፍ የምናገኘው መልእክት አንደምታ ምንድን ነው? ይህ በመካከላችን በተጨባጭ እንዲኖር ማድረግ የምንችለው እንዴት ነው? “የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከቃሉ የሚንጸባረቀውን ብርሃን የሚቀበሉ ከሆነ ክርስቶስ ለእነርሱ የጸለየው የአንድነት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ፡፡ ይኸውም ሐዋርያው እንዲህ ሲል የገለጸው ነው ‘በሰላም ማሰሪያ የመንፈስ አንድነት... አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ አንድ ጌታ፣ አንድ እምነትና አንድ ጥምቀት አለ’ (ኤፌ. 4፡3-5)፡፡ ”—Ellen G. White, The Great Controversy, p. 379.

*ማጠቃለያ*፡--በዮሐ. 17 የቀረበው የየሱስ የሊቀ ካኅናት ጸሎት ዛሬም የቤተ ክርስቲያን አንድነት ጌታን ግድ እንደሚለው አስታዋሽ ነው፡፡ ጸሎቱን ጸሎታችን በማድረግ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያለንን እምነት ለማጠናከር መጣር ይኖርብናል፡፡ እንዲሁም ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር የቱንም ዓይነት የሥነ መለኮታዊ አስተምህሮ ልዩነቶች ቢኖሩንም፤ ግንኙነታችን ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የሚለውን መርኅ መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡

# ፋኛ ትምህርት ከጥቅምት 10 - 16

## የኅብረት ቁልፉ

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ኤፌ. 1:3–14፣ ገላ. 4:7፣ ኤፌ. 2:11–22፣ 4:1–6፣ 11፣ ማቴ. 20:25–28፣ ኤፌ. 5:15–6:9፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ :-**"በክርስቶስ ያቀደውንም የፈቃዱን ምስጢር እንደ በጎ ሐሳቡ እንድናውቅ አደረገ፡፡ በዘመን ፍጻሜ ይሆን ዘንድ ያለው ሐሳቡ በሰማይም በምድርም ያሉትን ነገሮች ሁሉ ራስ በሆነው በክርስቶስ ሥር ለመጠቅለል ነው፡፡" (ኤፌ. 1፡9-10)፡፡

የእስያ አካል በሆነችው የዛሬዋ የቱርክ ግዛት ማለትም በሜዲቴራንያን፣ በኤጅየን እና በጥቁር ባሕር መካከል ትገኝ የነበረችው ኤፌሶን በሐዋርያት ዘመን ዋንኛ የንግድ ማዕከል ከመሆኗ በተጨማሪ ብርቱ ተጽእኖም ነበራት፡፡ በዚያ ማለትም በኤፌሶን የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ከአይሁዳውያን፣ ከአሕዛብ እና ከልዩ ልዩ ታሪካዊ ዳራ ከመጡ ማኅበረሰቦች የተውጣጡ አማኞች ነበሯት፡፡ በዚህ የተነሳ አባላት በክርስቶስ ባይሆኑና እንደ ክርስቶስ አካልነታቸው ኅብረት ባይፈጥሩ ከዘመኑ ዓለም አስተሳሰብ አኳያ ወደ ውዝግብ ሊያመሩ ይችሉ ነበር፡፡ በመሆኑም የክርስቶስ ተከታዮች አንድነት ጉዳይ ጳውሎስን በእጅጉ ያሳሰበው እንደ ነበር ለኤፌሶን ሰዎች ከላከው ደብዳቤ መረዳት እንችላለን፡፡ ጳውሎስ ስለ ኅበረት የነበረው ጽንሰ ሃሳብ ሁለት ገጽታዎች ሲኖሩት አንደኛው፡--የቤተ ክርስቲያን ኅብረት ይኸውም አይሁዶችና አሕዛብ በክርስቶስ አንድ አካል ወደ መሆን የመጡበት፡፡ ሁለተኛው፡--የአጽናፈ ሰማይ (ዩኒቨርስ) ኅብረት ይኸውም በሰማይና በምድር ሁሉም ነገሮች በስተ መጨረሻ በክርስቶስ የሚያገኙት አንድነት ናቸው፡፡

የዚህ ኅብረት ምንጩ ክርስቶስ ነው፡፡ "በክርስቶስ" ወይም "ከክርስቶስ ጋር" የሚለው አገላለጽ በዚህ መልእክት እጅግ ተደጋግሞ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን--እግዚአብሔር በየሱስ ክርስቶስ ሕይወት፣ ሞት እና ትንሣኤ ለእኛ ብሎም ለመላው አጽናፈ ሰማይ የፈጸመውን ለማሳየት ነው፡፡ በደኅንነት እቅድ የመጨረሻው የእግዚአብሔር ዓላማ ሁሉም ነገር በክርስቶስ አማካይነት ዳግመኛ ኅብረት እንዲፈጥር ማድረግ ነው፡፡ ይህ ኅብረት በሙላት ደምቆ የሚታየው በምድር ታሪክ መጨረሻ ነው፡፡

እሁድ

**ጥቅምት 11**

## በክርስቶስ የሚገኙ በረከቶች

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡--ኤፌ. 1፡3-14፡፡ እንደ ጳውሎስ አባባል እዚህ ላይ በክርስቶስ የተሰጠን ነገር ምንድን ነው?

---

---

የየሱስ ተከታዮች ለእግዚአብሔር ምስጋና የምናቀርብበት አያሌ ምክንያቶች አሉን፡፡ በክርስቶስ አማካይነት ወንዶችና ሴቶች ልጆቹ አድርጎ ተቀብሎን ሲያበቃ የዚህ ዓለም ወኪሎቹ አደርጎ መረጠን፡፡ ጳውሎስ በክርስቶስ አማካይነት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ለመግለጽ አያሌ ሥዕላዊ ማሳያዎችን ጥቅም ላይ ሲያውል ይስተዋላል፡፡ ከእነዚህ ምስሎች መካከል እኛን እንደ ልጆቹ መቀበሉን የሚያሳየውና በኅብረት ላይ ትኩረት የሚያደርገው የዚህ ትምህርት ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡ እኛ በክርስቶስ አማካይነት የልጅነት ማዕረግ አግኝተን የእግዚአብሔር ቤተሰብ አካል ለመሆን በቅተናል፡፡ ደግሞም እግዚአብሔር ከእስራኤል ልጆች ጋር ገብቶ የነበረው ኪዳን ለዚህ ቤተሰባዊ ገጽታ በማመሳከሪያነት መቅረብ ይችላል፡፡ የሱስን እንደ መሲህ የተቀበሉ አሕዛብም እንዲሁ ለእስራኤል የተገባው ኪዳን ወራሽ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናቸውን ከጳውሎስ መልእክት ዐውድ መመልከት እንችላለን (ሮሜ 8፡17፣ ገላ. 4፡7)፡፡ ከክርስቶስ ጋር ኅብረት የመፍጠርና በክርስቶስ የመሆን ጥቅም ለሁሉም የክርስትና ኅብረት ወሳኝና መሰረታዊ ነው፡፡ መላው ሰብዓዊ ዘር ከክርስቶስ ጋር ኅብረት እንዲፈጥር ማድረግ የእግዚአብሔር ምኞት መሆኑን ከጥቅሱ መገንዘብ እንችላለን፡፡ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ እኛ ሁላችን በእኩል ዐይን በእርሱ የተወደድን፣ የከበረ ዋጋና እንክብካቤ የተቸረን ልጆቹ ነን፡፡

አስቀድሞ ወሰነን (ኤፌ. 1፡5፣ 11) በሚል የቀረበው ይህ የጳውሎስ መልእክት ክፍል በአንዳንዶች ላይ ግርታ ሲፈጥር ይስተዋላል፡፡ አባባሉ እግዚአብሔር እኛ እንድንድን በመምረጥ ኪዳን እንደ ገባ ሁሉ ሌሎችም እንዲጠፉ መርጦአል የሚል አንደምታ ያለው ይመስላል፡፡ ነገር ግን ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ አይደለም፡፡ ይልቁንም እግዚአብሔር መላው ሰብዓዊ ዘር የሚድንበትን የደኅንነትን ዕቅድ ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ አዘጋጀ፡፡ “በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድርስ ዓለምን ወዶአልና” (ዮሐ. 3፡16፣ 1ጢሞቴ. 2፡6፣ 2ጴጥ. 3፡9)፡፡ ምንም እንኳ እግዚአብሔር ያቀረበውን የደኅንነት እቅድ ማን እንደሚቀበልና እንደማይቀበል አስቀድሞ ሊያውቅ ቢችልም ነገር ግን ጉዳዩ በአንድ ሰው የግል ውሳኔ ላይ አስቀድሞ ከመወሰን ጋር ፍጹም ግንኙነት

የለውም፡፡ ክርስቶስ ለእኛ ባደረገው ነገር ምክንያት እነሆ ደኅንነት ለመላው ሰብዓዊ ፍጡር ተሰጠ፡፡ ጥያቄው፡ ለዚህ ግብዣ ምላሽ የምንሰጠው እንዴት ነው? የሚል ይሆናል፡፡ እግዚአብሔር ማንንም ለማዳን ከፍላጎት ውጪ አያስገድድም፡፡

“ምንም እንኳ ሰዎች አምላካዊውን ሕግ ቢተላለፉም ባለመታዘዛቸው ጠንቅ እንዳይጠፉ፤ ይልቁንም ለእነርሱ ቤዛ እና ዋስ በሚሆነው ክርስቶስ ላይ በሚኖራቸው እምነት የእግዚአብሔር የተመረጡ ሕዝቦች ይሆኑ ዘንድ በሰማያዊው ጉባዔ እቅድ ወጣ፡፡ እግዚአብሔር አምላክ እርሱን ደስ እንደሚያሰኘው እንደ በጎ ፈቃዱ በራሱ በየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ልጆቹ አድርጎ በመቀበል አስቀድሞ ወሰነን፡፡ እነሆ ሰው ሁሉ ይድን ዘንድ አምላካዊው ፈቃድ ነው፡፡ ለአብነት ያህል የሰብዓዊውን ዕዳ ለመክፈል እግዚአብሔር አንድያ ልጁን የኃጢአት መሥዋዕት አድርጎ ሰጥቶአል፡፡ ሰዎች የሚጠፉት በክርስቶስ የሱስ በኩል የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ለመጠራት በመቃወማቸው ነው፡፡”— Ellen G. White Comments, The SDA Bible Commentary, vol. 6, p. 1114.

## ሰኞ ጥቅምት 12

### ግድግዳውን ማፍረስ

በሕዝቦች መካከል ከሚስተዋሉ ጥልቅ ልዩነቶች አንዳንዶቹ ዘርን፣ ብሔርንና ኃይማኖትን ያማከሉ ናቸው፡፡ ዛሬ ብዛት ባላቸው ሕዝቦች የነዋሪ መታወቂያ ወረቀት ላይ የግለሰቡ ብሔር ወይም ኃይማኖት ተጠቅሶ እንመለከታለን፡፡ ተደጋግሞ እንደሚስተዋለው እነዚህ ልዩነቶች ከሰዎች የዕለት ከዕለት ልዩ መብቶች ወይም ገደቦች ጋር ብርቱ ቁርኝት አላቸው፡፡ ታዲያ በአካባቢው ጦርነት ወይም ግጭቶች ሲቀሰቀሱ እነዚህ የልዩነትና የማንነት መገለጫ ጠቋሚዎች የጭቆና፣ የመድልዎ፣ የሁከትና ብጥብጥ አቀጣጣይ ይሆናሉ፡፡

ጳውሎስ በኤፌ. 2፡11-22 መልእክቱ ለክርስቲያኑ ማኅበረሰብ የተሻለ ጎዳና ያመላክታል፡፡ በክርስቶስ ያለን አንድነት በልዩነቶቻችችን ላይ ተጽእኖ ማሳደር የሚችለው እንዴት ነው? በየሱስ የመስቀል ላይ ሞት የፈራረሰው ነገር ምን ነበር?

____________________________________________

____________________________________________

የኤፌሶን ሰዎች በክርስቶስ የእግዚአብሔርን ጸጋ ከመቀበላቸው አስቀድሞ ሕይወታቸው ምን ይመስል እንደ ነበር እንዲያስታውሱ ጳውሎስ ይጋብዛቸዋል፡፡ የብሔር፣ የባህልና የኃይማኖት ልዩነቶች በማኅበረሰቡ መሃል ጥላቻና ግጭት አስከትለው ነበር፡፡ ሆኖም ሁላችንም በክርስቶስ አንድ አዳኝና ጌታ ያለን ሕዝቦች

መሆናችን በእርግጥም መልካም የምስራች ነው፡፡ እኛ ሁላችን የእግዚአብሔር ሕዝቦች ነን፡፡ “አሁን ግን እናንተ ቀድሞ ርቃችሁ የነበራችሁ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም አማካይነት ቀርባችኋል” (ኤፌ. 2፡13)፡፡

በየሩሳሌም የነበረችው የጥንቷ ቤተ መቅደስ ቅጥር ለአይሁዳውያን ብቻ አገልግሎት እንዲሰጥ ሆኖ በግድግዳ ተለይቶ ነበር፡፡ ይህ ቅጥር ከአይሁድ ዝርያ ውጪ የነበሩ ባዕዳን አልፈው በመሄድ የሥቃይና ቸነፈር ሰለባ እንዳይሆኑ የሚከለክል ጽሑፍ ነበረው፡፡ ጳውሎስ ከወንጌል ጉዞዎቹ መልስ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ ይህን ሕገ ደንብ ጥሰሃል ተብሎ ተከስሶ ነበር፡፡ ጳውሎስ ተይዞ የታሰረው የኤፌሶኑን ሰው ጥሮፊሞስ (ሐዋ. 21፡29) የአይሁድ ቅጥር ወደ ሆነው ቤተ መቅደስ አስገብቶአል በሚል ነበር፡፡ ጳውሎስ በዚህ መልእክቱ፡ ክርስቶስ “ሁለቱን አንድ ያደረገ፣ የሚለያየውንም የጥል ግድግዳ ያፈረሰ ሰላማችን እርሱ ነውና” (ኤፌ. 2፡14) ሲል ይሞግታል፡፡

በክርስቶስ ያሉ አማኞች የአብርሃም ዝርያዎች እንደመሆናቸው የልብ መገረዝን ይቀበላሉ፡፡ እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው አካላዊው ግርዘት አማኞች በክርስቶስ የሚቀበሉትን መንፈሳዊ መገረዝ ያመላክት ነበር (ዘዳ. 10፡16)፡፡ “በእርሱ ሆናችሁ በእጁ ባልተደረገ መገረዝ ተገረዛችሁ፤ በክርስቶስም መገረዝ የሥጋን ኃጢአታዊ ባሕርይ አስወገዳችሁ” (ቆላ. 2፡11)፡፡

*ጥቅሶቹን በድጋሚ አንብቡ፡ (ኤፌ. 2፡11-22)፡፡ ይህን የጳውሎስ መልእክት በቤተ ክርስቲያናችን በተጨባጭ እያስተዋልን ያለንበት ሁናቴ ምን ይመስላል? አሁን ድረስ ያሉ ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው?*

**ማክሰኞ** **ጥቅምት 13**

## ኅብረት በአንድ አካል ውስጥ

ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈው መልእክት ጭብጥ ላይ የተመረኮዘውን እውነታ አቅርቦላቸዋል፡፡ በአይሁዳውያን እና በአሕዛብ፣ የተለያየ ባህል በነበራቸው ሕዝቦች እና ዝርያ ታሪካዊ ዳራ መካከል የነበረው ኅብረት መሰረተ ቢስ አፈ ታሪክ ሳይሆን ለተቀበልነው ጥሪ የሚገባ ኑሮ እንድንኖር የቀረበልን ተማጽኖ ነው (ኤፌ. 4፡1)፡፡

በኤፌ. 4፡1-3 መሰረት ክርስቲያኖች በክርስቶስ ለቀረበላቸው ጥሪ ያለ ነቀፌታ መራመድ የሚችሉት እንዴት ነው?

---

---

በክርስቲያኖች ህይወት የሚተገበሩት የእነዚህ በጎ ምግባሮችና ጸጋዎች ተጨባጭ ውጤት “በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ” (ኤፌ. 4፡3) እንድንተጋ

ይረዱናል፡፡ እነዚህ ሁሉ መለያ ባህሪያት የተመሰረቱት በፍቅር ላይ ነው (1ቆሮ. 13፡ 1-7)፡፡ ፍቅርን በንቃትና በተጨባጭ መለማመድ በክርስቲያን ብሎም በሌሎች ወንድም እህቶች መካከል የሚኖር ግንኙነት ተጠብቆ እንዲቆይ ይረዳል፤ ሰላምና ኅብረት እንዲነቃቃም ያደርጋል፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚኖር ኅብረት ከወትሮ በተለየ የእግዚአብሔርን ፍቅር በመግለጽ ለሌሎች ምስክር ይሆናል፡፡ በተለይ ጠብ፣ ሁከት፣ መከፋፈልና ጦርነት በሚነሳበት ወቅት ቤተ ክርስቲያን ምስክር እንድትሆን ተጠርታለች፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ኤፌ. 4፡4-6፡፡ በእነዚህ ሦስት ቁጥሮች ወሳኝ የሆነው ጭብጥ ምንድን ነው?

____________________________________________

____________________________________________

ጳውሎስ በዚህ ምዕራፍ የመጀሪያ ቁጥሮች ላይ በቤተ ክርስቲያን ኅብረት ላይ ያለውን ጥልቅ ፍላጎት ሲገልጽ ይስተዋላል፡፡ በኅብረት ዙሪያ ልባዊ ምክር በመስጠት መልእክቱን የሚጀምረው ጳውሎስ (ኤፌ. 4፡1-3) አማኞችን የሚያስተሳስሩ ሰባት መሰረታዊ ነጥቦችን በማስከተል ጽሑፉን ይቀጥላል (ኤፌ. 4፡4-6)፡፡ ከሞላ ጎደል በአማኞች ውስጥ ያለው ይሄው ኅብረት (ኤፌ. 4፡4-6) ምዕመናን ያለማሰለስ የሚያሳድጉትና የሚንከባከቡት (ኤፌ. 4፡1-3) የተቻላቸውን ብርቱ ጥረት የሚያደርጉበትና የሚረባረቡበት የመጨረሻ ግብ ነው (ኤፌ. 4፡13)፡፡

"ሐዋርያው ለወንድሞቹ ያቀረበላቸውን የእውነት ኃይል በሕይወታቸው ገልጠው እንዲያሳዩ አደፋፍሯቸዋል፡፡ እነዚህ ወገኖች በታማኝነትና በእርጋታ፣ በትዕግሥትና በፍቅር የክርስቶስን ጸባይና የማዳኑን በረከቶች ማሳየት ነበረባቸው፡፡ አንድ አካል፣ አንድ መንፈስ፣ አንድ ጌታ፣ አንድ እምነት አለ፡፡ አማኞች እንደ ክርስቶስ አካልነታቸው በተመሳሳይ መንፈስና ተስፋ ብሩህ ኃይል የተሞሉ ናቸው፡፡

"በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚከሰቱ መከፋፈሎች የክርስቶስን ኃይማኖት በዓለም ፊት ውርደት ላይ በመጣል የእውነት ጠላቶች አካሄዳቸውን ተገቢ አስመስለው ለማቅረብ ዕድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ የጳውሎስ ትእዛዞችና መመሪያዎች በእርሱ ዘመን ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን ብቻ አልተጻፉም፡፡ ይልቁንም መልእክቶቹ ለእኛ ዘመን እንዲደርሱ የእግዚአብሔር እቅድ ነበር፡፡ በሰላም ማሰሪያ ውስጥ ኅብረታችንን ለመጠበቅ ምን እያደረግን ነው?"—Ellen G. White, Testimonies for the Church, vol. 5, p. 239.

በተጠሩበት ለመራመድዎ እግጠኛ ለመሆን ዛሬ ምርጫዎ ምን ሊሆን ይገባል?

ረቡዕ

## ጥቅምት 14

# የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ኅብረት

"ነገር ግን ክርስቶስ በወሰነው መጠን ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጥቶናል" (ኤፌ. 4፡7)፡፡ መዳን ለተቀበሉት ሁሉ የተሰጠ ስጦታ ቢሆንም አንዳንድ መንፈሳዊ ስጦታዎች ለተለየ ዓላማ ለተወሰኑ ሰዎች ይሰጣሉ፡፡

ጥቅሱን ያንብቡ፡ ኤፌ. 4፡11፡፡ እግዚአብሔር ምን ዓይነት የአመራር ስጦታ ለቤተ ክርስቲያን ይሰጣል?

---

በኤፌ. 4፡12 መሰረት እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የተለየ የአመራር ስጦታ ሲሰጥ ዓላማው ምንድን ነው? እነዚህ ስጦታዎች እርስ በርሳቸው እንዴት ይዛመዳሉ?

---

ሁሉም ክርስቲያኖች የወንጌል ሠራተኞችና የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው፡፡ በማቴ. 28፡19-20 ክርስቲያኖች ለአገልግሎት ወጥተው ሕዝቦችን ደቀ መዝሙሮቹ እንዲያደርጉ፣ እንዲያጠምቁ፣ እንዲያስተምሩ ክርስቶስ ተልዕኮ ሰጥቶአቸዋል፡፡ የወንጌል ሥራ የተሰጠው እንደ መጋቢዎችና ወንጌላውያን ላሉ ጥቂት ዕድለኞች ብቻ ሳይሆን የክርስቶስን ስም ለተሸከሙ ሁሉ ነው፡፡ ማንም አማኝ ወንጌልን ከማሰራጨት ራሱን ነፃ ሊያደርግ እንደማይችል ሁሉ--የትኛውም የቤተ ክርስቲያን መሪ ለእርሱ ብቻ የተነጠለ አገልግሎት እንዳለው መናገር አይችልም፡፡ የሥነ አመራር መንፈሳዊ ስጦታዎች ቤተ ክርስቲያንን የማነጽ የተለየ ሥራ ይሠራሉ፡፡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአማኞች መካከል ኅብረትን ለማጠናከርና ለማደርጀት አጥብቀው ይፈለጋሉ፡፡

የጳውሎስ ሥነ አመራር ስጦታ ዝርዝሮች የእግዚአብሔር ሕዝቦች ወደ ጠፉት እንዲደርሱ የሚያስችል ሚና እንዳላቸውም ይነግሩናል፡፡ የክርስቶስን አካል የማነጹ አገልግሎት የሰመረና ስኬታማ እንዲሆን እርዳታ መስጠት በተለይ በዚያው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተጠሩ ጥቂቶች ኃላፊነት ነው፡፡ "ይህም የሚሆነው ሁላችንም የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኘው አንድነት በመምጣትና ሙሉ ሰው በመሆን፣ በክርስቶስ ወዳለው ፍጹምነት ደረጃ እስከምንደርስ ነው፡፡" (ኤፌ. 4፡13)፡፡ አገልግሎታችን የክርስቶስን ምሳሌ በተከተለ ሥነ አመራር መራመድ ይኖርበታል፡፡ የሱስ ሌሎችን ሊያገለግል እንጂ ሊገለገል እንዳልመጣ ሁሉ (ማቴ. 20፡ 25-28) እኛም የእርሱን ፈለግ በመከተል ልንወጣ ይገባል፡፡

ሰዎች በገዛ ራሳቸው ሀሳብ የመምራትና ለማንም ተጠያቂ ያለመሆን ጠንካራ ዝንባሌ አላቸው፡፡ የምዕራቡ ማኅበረሰብ ደግሞ በተለይ የዚህ ወረርሽኝ ተጠቂ ነው፡፡ ሆኖም በዚህ ምድር አንድም ክርስቲያን ብቻውን አለመሆኑን የሚያስታውሰን ጳውሎስ፤

በጋራ ጉዞአችን እርስ በርስ እንድንበረታታ እገዛ የሚያደርጉልንን መንፈሳዊ መሪዎች በአማኝ ማኅበረሰብ ውስጥ እንደምንፈጥር ይነግረናል፡፡ እኛ ሁላችን፣ በአንድነት የክርስቶስ አካል ክፍል ነን፡፡

ምን ዓይነት መንፈሳዊ ስጦታዎች አሎት? ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንዎ ኅብረት እንዴት እየተጠቀሙባቸው ይገኛሉ?

**ሐሙስ**

**ጥቅምት 15**

## ክርስቶስን ያማከለው ሰብዓዊ ግንኙነት

ክርስትና ግንኙነቶችን መሰረት ያደረገ ኃይማኖት ሲሆን፤ ይኸው ግንኙነት ደግሞ ከእግዚአብሔር እና እርስ በርስ ከሰዎች ጋር ያለን ግንኙነት ያማከለ ነው፡፡ አንድ ሰው ከሌሎች ጋር የረባ ግንኙነት ሳይኖረው ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዳለው ቢያስብ ትርጉም የለውም፡፡ ክርስትና አንዳች በሌለበት ወና ውስጥ መኖር አይችልም፡፡ ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈው መልእክቱ የሚያነሳቸው የኅብረት መርኅዎች ከሌሎች ጋር ለሚኖሩን ግንኙነቶች ገጣሚ ናቸው፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ኤፌ. 5፡15-21፡፡ በቁ. 21 ጳውሎስ ምን እያለን ነው? በመታዘዝና በኅብረት መሃል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?

____________________________________________

____________________________________________

ጳውሎስ አንዱ ለሌላው የሚሸነፍና እሺ ባይ እንዲሆን የሰጠው ልባዊ ምክር “በመንፈስ ተሞሉ” (ኤፌ. 5፡18) ከሚለው ሀረግ ጋር ትስስር አለው፡፡ ሰዎች እርስ በርሳቸው የሚያሳዩት ትህትና በመንፈስ የመሞላት አንዱ መገለጫ ነው፡፡ ጉዳዩ ለሰዎች ከሚኖረን ቀናነትና በጎ አመለካከት ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ በእርግጥ ይህ የሰብዓዊው ተፈጥሮ ባህሪ ሳይሆን፤ በልባችን የሚኖረው መንፈስ ውጤት ነው፡፡ ይህ በክርስቶስ የምናገኘው የአንድነት ሰንሰለት ከዚያው ከአንድ ባሕር የሚቀዳው መንፈስ ስጦታ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር--ውስጣዊ ጥሩነት የሆነው ትህትናና መታዘዝ ለክርስቶስ ብሎም ለመሥዋዕትነቱ ያለንን አክብሮት ይገልጻል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ኤፌ. 5፡22-6፤ 9፡፡ ይህ በቤትም ሆነ በሥራ ቦታ በክርስቶስ አማኙ የሚስተዋለው ትህትና በሰብዓዊ ግንኙነታችን ላይ ምን ዓይነት ተጽእኖ ይኖረዋል?

____________________________________________

____________________________________________

የቤተ ክርስቲያን ኅብረት በመጠኑም ቢሆን በቤተሰብ ላይ ባለ አንድነት መተማመን ያደርጋል፡፡ በባልና ሚስት መሃል ሊኖር የሚገባ አንድነት፣ ፍቅር እና መከባበር ክርስቶስ

ራሱን አሳልፎ እስከ መስጠት ቤተ ክርስቲያንን የመውደዱን ምሳሌ ሊከተል እንደሚገባ ሐዋርያው ጳውሎስ አጽንኦት ይሰጣል፡፡ ስለዚህ በክርስቶስ የተስተዋለው አክብሮት በቤት ውስጥ፣ በቤተ ክርስቲያን፣ በባሎች እንዲሁም በሚስቶች መሃል መታየቱ የግድ ይሆናል፡፡ ይህ የክርስቶስ ባህሪ የሆነው ጥሩነት በልጆች እና በወላጆች፣ በሠራተኞች እና በአለቆች መካከል በጉልህ ሊታይ ይገባል፡፡ በቤታችን ሊሰፍን የሚገባው ለዛ ያለው ስምምነትና ሰላም በቤተ ክርስቲያን ህይወትም ሊሰፍን የተገባ ነው፡፡

*ለቤተሰብዎ አባል ወይም ለሥራ ባልደረባዎ እንዴት ዓይነት አቀራረብ ሊኖርዎ እንደሚገባ አስመልክቶ ለዛሬ ከቀረቡት ጥቅሶች ምን ዓይነት መርኅዎችን መውሰድ ይችላሉ?*

## ዓርብ

## ጥቅምት 16

*ተጨማሪ ሀሳብ*: *Ellen G. White, "The Spirit of Unity," pp. 179–188, in Testimonies for the Church, vol. 9.*

"ክርስቶስ በዜግነት፣ በማዕረግ ወይም በኃይማኖታዊ ጉዳዮች ዙሪያ የማበላለጥ እውቅና አልሰጠም፡፡ ጸሐፍትና ፈሪሳውያን መላውን የሰማይ ስጦታ ከተቀረው ዓለም የእግዚአብሔር ቤተሰብ በመነጠል ለብሔራዊ ጥቅማቸው ብቻ ለማዋል ተመኝተው ነበር፡፡ ክርስቶስ ግን እያንዳንዱን የመለያየት ግድግዳ ሊያፈራርስ መጣ፡፡ የአምላካዊው ምህረት ስጦታና ፍቅር ወደ ሳንባችን እንደምንስበው አየር፣ ማለዳ እንደምትፈነጥቀው የጸሐይ ጮራ ወይም ምድሪቱን እንደሚያረሰርሰው ካፊያ ነፃ መሆኑን ሊያሳየን መጣ፡፡

"የክርስቶስ ሕይወት አይሁድ እና አሕዛብ፣ ነፃ ሰዎችና ግዞተኞች በጋራ ወንድማማችነት የተቆራኙበትንና በእግዚአብሔር ፊት እኩል የሚሆኑበትን ከኅብረተሰባዊ ክፍፍል የጸዳ ኃይማኖት መሰረተ፡፡ የትኛውም ሕገ ደንብን ወይም መመሪያን የተከተለ ጥያቄ በእንቅስቃሴዎቹ ላይ ተጽእኖ አላሳደረም፡፡ በጎረቤቶቹና በሩቅ እንግዶች፣ በጓደኞቹና በጠላቶቹ መሃል አንዳችም ልዩነት አላደረገም፡፡ ወደ ልቡ የሚሳበው የሕይወትን ውሃ የተጠማው ነፍስ ነበር፡፡"—Ellen G. White, Testimonies for the Church, vol. 9, pp. 190, 191.

### የመወያያ ጥያቄዎች፡

1. የሚከተለውን ሃሳብ ያሰላስሉ፡ "መላው የእግዚአብሔር ልጆች እውነትን አጥብቀው እንዲይዙ የሚያወሳው አምላካዊው እቅድ ግልጽና ቀላል በሆነ አቀራረብ በኤፌሶን አራተኛው ምዕራፍ ላይ ተገልጾአል፡፡ የቤተ ክርስቲያኑ ኅብረት ተጠብቆ የሚኖርበትና አባላት ጤናማውን ኃይማኖታዊ ተሞክሮ ለዓለም እንዲገልጹ የሚያስችለው ዘዴ ግልጽ በሆነ ቋንቋ በዚህ ስፍራ ቀርቦአል፡፡"—Ellen G. White Comments, The

SDA Bible Commentary, vol. 6, p. 1117. በኤፌ. 4 የቤተ ክርስቲያን ኅብረትን የሚጠቁሙ ምን ዓይነት ነጥቦችን ይመለከታሉ? ኅብረቱ የሰመረ እንዲሆን በምን መልኩ የበኩልዎን እገዛ ማበርከት ይችላሉ?

2. ትህትና እና የአንተ ትብስ፣ አንቺ ትብሽ አስፈላጊነት የቤተ ክርስቲያን ኅብረት ጥያቄ አስኳል ነው፡፡ ለመሆኑ ያለ እነዚህ ባህሪያት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድነት ሊኖር የሚችለው እንዴት ነው? የምንታበይ፣ በአመለካከታችንና በአቋማችን ከእኔ በላይ ላሳር የምንል ከሆንና ሌሎችን ለማድመጥ ፈቃደኞች ካልሆን ኅብረት የማምጣት ዕድላችን የመነመነ ነው፡፡ ለመሆኑ ይህን ትህትና እና ቅንነት መማር የምንችለው እንዴት ነው?

3. ሁሌም በሁሉም ነገር ባንስማማም እንኳ አንድነት ሊኖረን የሚችለው እንዴት ነው?

*ማጠቃለያ፡* ጳውሎስ ለኤፌሶች ሰዎች በላከው በዚህ ደብዳቤው "በክርስቶስ መሆን" ምን ማለት እንደሆነ አስመልክቶ አያሌ ምክረ ሀሳቦችን ለሕዝበ ክርስቲያኑ ይለግሳል፡ ፡ በየሱስ የሚገኘው ደኅንነት ህይወትን በተጨባጭ ይለውጣል፡፡ በቤተ ክርስቲያን ያሉ ወንድም እህቶችን ጨምሮ ሁሉም ዓይነት ሰብዓዊ ግንኙነቶቻችን በሕይወታችን መለወጥ የሚያገኙት በክርስቶስ ኃይል ነው፡፡ በመካከላችን ኅብረት ይኖር ዘንድ ይህ መለወጣችን እጅግ ወሳኝ ነው፡፡

# 5ኛ ትምህርት ከጥቅምት 17 – 23

## በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን የተስተዋለው ኅብረት ተሞክሮ

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ሐዋ. 1:12–14. ሐዋ. 2:5–13 ራእ. 14:12 ፣ሐዋ. 2:42–47. ሐዋ. 4:32–37. ሐዋ. 5:1–11፣ 2ቆሮ. 9:8–15፡፡

**<u>መታሰቢያ ጥቅስ :-</u>**“እነርሱም በሐዋርያት ትምህርት በኅብረት፣ እንጀራውንም በመቁረስና በጸሎት ይተጉ ነበር” (ሐዋ. 2፥42)፡፡

የቤተ ክርስቲያን ኅብረት እውነት የሆነውን የሱስ የማካፈል መንፈሳዊ ውጤት ነው፡፡ “መንገዱ እኔ ነኝ፣ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ፣ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም፡፡” (ዮሐ. 14፥6)፡፡ ጠንካራ አንድነት ያላቸው ኅብረቶች በጋራ መንፈሳዊ ጉዞ ተሞክሮ የተቀረጹ ናቸው፡፡ የሚለራይት እንቅስቃሴ ዘመኖቹ ቀደምት አድቬንቲስቶች የእንዲህ ያለው ተሞክሮ ባለቤቶች ነበሩ፡፡ እነዚህ ወገኖች በጎርጎሮሳውያኑ ቀመር 1844 ላይ ደርሶባቸው ለነበረው ተስፋ አስቆራጭ ክስተት ትክክለኛውን ማብራሪያ እስኪያገኙ የጋራ ተሞክሮአቸው ልቦቻቸውን በአንድ ማስተሳሰር ችለው ነበር፡፡ ይህ ተሞክሮ ለሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን ውልደት እንዲሁም ከዳግም ምጽአቱ አስቀድሞ ስላለው ፍርድ እና ተዛማጅ እውነቶች መንስዔ ለመሆን በቃ፡፡

የሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ በተስተዋለው የደቀ መዛሙርቱ ተሞክሮ የተለያየ የኋላ ታሪክ በነበራቸው አማኞች መካከል ኅብረትና ስምምነት በመፍጠሩ ረገድ-- የእግዚአብሔር ቃል፣ ጸሎት እና የአማኞች ኅብረት ብርቱ ኃይል እንዳለው ማሳያ ምስክር ነበር፡፡ ይህ የቀደመ ተሞክሮ እነሆ ዛሬም መተግበር ይችላል፡፡

“የክርስትና ኅብረት ከፍላሉ ጉባዔዎች እጅግ አስፈላጊ ቅመም በመሆኑ የአምልኮአቸው አካል እንዲሆን አጥብቄ ላበረታታ እወዳለሁ... አማኙ ከሌሎች አማኞችና ከጌታ የሱስ ክርስቶስ ጋር መንፈሳዊ ትስስር ለመፍጠር የሚያስችለው ከዚህ ውጪ ሌላ ምንም ምትክ የለውም... የሱስ ክርስቶስ ሁሌም ቢሆን በመጀመሪያ አንድን ነፍስ ወደ ራሱ ያመጣል፡፡ በመቀጠል አካሉ በሆነው ቤተ ክርስቲያን አማካይነት ከሌሎች አማኞች ጋር ኅብረት እንዲፈጥር ያደርጋል፡፡”*—Robert G. Rayburn, O Come, Let Us Worship (Grand Rapids: Baker Book House, 1980), p. 91.*

**እሁድ** **ጥቅምት 18**

## መዘጋጃዎቹ ቀናት

የሱስ በመስቀል ለኃጢአታችን ቤዛ ከመሆኑ አስቀድሞ በነበሩት የመጨረሻዎቹ ሰዓታት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በነበረው ቆይታ ብቻቸውን እንደማይተዋቸው ቃል ገባላቸው፡፡ የአገልግሎታቸው አካል የሆነው ሌላው አጽናኝ መንፈስ ቅዱስ ይላክላቸዋል፡፡ መንፈስ የሱስ ነግሮአቸውና አድርጓቸው የነበሩ አያሌ ነገሮችን እንዲያስታውሱና (ዮሐ. 14፡26) ተጨማሪ አዳዲስ እውነቶችን እንዲረዱ ይመራቸዋል (ዮሐ. 16፡13)፡፡ የሱስ ወደ ሰማይ ሊያርግ በነረበት ዕለትም እንዲሁ አስቀድሞ የሰጣቸውን ተስፋ አድሶ ነበር፡፡ “‘እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ... መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በሚወርድበት ጊዜ ኀይልን ትቀበላላችሁ” (ሐዋ. 1፡5፣8)፡፡ ደቀ መዛሙርት በየሩሳሌም፣ በይሁዳ፣ በሰማርያ ብሎም እስከ ምድር ጫፍ ምስክር ለመሆን የሚያስችላቸው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይሰጣቸዋል (ሐዋ. 1፡8)፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሐዋ. 1፡12-14፡፡ በእነዚህ አሥር ቀናት ውስጥ ደቀ መዛሙርት ምን አደረጉ?

________________________________________________________________

________________________________________________________________

እነዚህ አሥር ቀናት እጅግ በተጋጋለ ስሜት ብርቱ መንፈሳዊ ዝግጅት የተደረገባቸው ጊዜያቶች እንደነበሩ ለመገመት እንችላለን፡፡ ደቀ መዛሙርት በአንድነት ተሰባስበው የቀደሙትን የየሱስ ተግባራት፣ አስተምህሮዎችና ታምራቶች እያሰላሰሉ “በአንድ ልብ ሆነው ያለማቋረጥ ተግተው ይጸልዩ ነበር” (ሐዋ. 1፡14)፡፡

“ደቀ መዛሙርት በእውነተኛ ንስሐ ልቦቻቸውን ትሑት አድርገውና አለማመናቸውን ተናዝዘው የሱስ የሰጣቸውን ተስፋ ፍጻሜ እየተጠባበቁ ነበር፡፡ ክርስቶስ ከመሞቱ አስቀድሞ ለእነርሱ የተናገራቸውን ቃላት ማስታወስ ሲጀምሩ ፍቺያቸውን ይበልጥ በሙላት አስተዋሉ፡፡ ተዘንግተዋቸው የነበሩ እውነቶች ዳግመኛ በአእምሮአቸው አንቃጨሉ፡፡ አንዱ አስታውሶ ሲናገር ሌላውም ያንኑ ይደግም ነበር፡፡ በአዳኙ ላይ ስለ ነበራቸው የተሳሳተ አስተሳሰብ ራሳቸውን ተቹ፡፡ የአስደናቂ ሕይወቱ ትዕይንት እንደ ወታደራዊ ሰልፍ በፈርጅ በፈርጅ ሆኖ በፊታቸው አለፈ፡፡ ውብ የሆነውን የክርስቶስ ጸባይ ብቻ በሕይወታቸው መመስከር ቢችሉ--ንጹህና ቅዱስ የሆነውን ሕይወቱን እያሰላሰሉ አምልኮ ሲያደርጉ፣ የቱንም ዓይነት ልፋት ወይም መሥዋዕትነት የገዘፈ ሊሆንባቸው እንደማይችል ተሰማቸው፡፡ ያለፉትን ሦስት ዓመታት ዳግም ሊያገኟቸው ቢችሉ እንዴት በተለየ ይመላለሱባቸው እንደነበርና ለጌታቸው ያላቸው ፍቅር ምን ያህል ጥልቅ እንደሆነ ሊያሳዩ በጣሩ ነበር፡፡ ከአንደበቶቻቸው በወጡ የስንፍና ቃላት ወይም ባሳዩት ያለማመን ድርጊት ምን ያህል እንደ ጎዱት እያሰቡ ከልባቸው ተጸጸቱ፡፡

ሆኖም ይቅር መባላቸውን ሲያስቡ መጽናናት አገኙ፡፡ ከዚህ በኋላ በተቻላቸው እርሱን በዓለም ፊት በጀግንነት እየመሰከሩ ሥርየት ያመጣላቸውን አዳኝ ለመካስ ቁርጥ ሃሳብ አደረጉ… ልዩነቶቻቸውን በሙሉ በማስወገድና ምኞቶቻቸውን በላቀው ነገር ላይ በማዋል በክርስትና ኅብረት ተቀራረቡ፡፡”—Ellen G. White, The Acts of the Apostles, pp. 36, 37.

*ከእምነትዎ ጋር በተያያዘ ምን ዓይነት ነገሮችን ማድረግ ይችላሉ? የወደፊቱን በተሻለ ተስፋ የተሞላ ማድረግ ይቻል ዘንድ ባለፈው ከተጸጸቱባቸው ነገሮች ምን መማር ይችላሉ?*

**ሰኞ** **ጥቅምት 19**

## ከባቤል ወደ በዓለ ኀምሳ

የየሱስን ዕርገት ተከትሎ ገቢራዊ የሆኑት መንፈሳዊ ዝግጅት የተደረገባቸው ቀናት በበዓለ ኀምሳው ትዕይንቶች ድምዳሜ አገኙ፡፡ የመጀመሪያው ጥቅስ እንደሚነግረን መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ ከመውረዱ አስቀድሞ በዚያው ዕለት “ሁሉም በአንድነት በአንድ ስፍራ ተሰብስበው ነበር” (ሐዋ. 2፡1)፡፡

በብሉይ ኪዳን እያንዳንዱ እስራኤላዊ ተባዕት እንዲካፈልባቸው ከሚጠየቁ ሦስት አበይት በዓላት መካከል በዓለ ኀምሳ ሁለተኛውን ይይዛል፡፡ በግሪክኛ ጴንጤቆስጤ በሚል ስያሜ የሚታወቀው ይህ በዓል የሚውለው ፋሲካ በተከበረ በኀምሳኛው ቀን ላይ ነበር፡፡ በበዓሉ ላይ ዕብራውያን በበጋው ወቅት ከሚያፈሩት ፍራፍሬዎች በኩር የሆኑትን በምስጋና ስጦታ ለእግዚአብሔር ያቀርባሉ፡፡

በተጨማሪ በየሱስ ዘመን በነበረው የበዓለ ኀምሳ አከባበር አሥርቱ ትእዛዛት በሲና ተራራ ለሙሴ የተሰጡበትን በመታሰቢያነት ያካትት ነበር (ዘፀ. 19፡1)፡፡ በመሆኑም የእግዚአብሔር ሕግ አስፈላጊነት የክርስትና መልእክት ጥቅል አካል ሆኖ መቀጠሉን መመልከት እንችላለን፡፡ የሱስን አስመልክቶ የእግዚአብሔርን ሕግ ለጣሰ እያንዳንዱ ተነሳሒ (ንስሐ የሚገባ) የእርሱ ሞት አምላካዊውን ይቅርታ ያሰጣል፡፡ ከዚህ አኳያ ስለ መጨረሻዎቹ ቀናት ከሚነግሩን ወሳኝ ጥቅሶች አንዱ ስለ ሕጉ እና ስለ ወንጌል የሚከተለውን ቢል እምብዛም ሊያስገርም አይችልም፡ “የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁና ለኢየሱስም ታማኝ ሆነው በትዕግሥት የሚጸኑ ቅዱሳን የሚታወቁት በዚህ ነው” (ራእ. 14፡22)፡፡

ሙሴ በሲና ተራራ አሥርቱን ትእዛዛት በተቀበለ ጊዜ (ዘፀ. 19፡16-25፣ ዕብ. 12፡18) ከሆነው በተመሳሳይ በጴንጤቆጤ ወቅትም በእጅጉ ያልተለመዱ ድንቅ ክስተቶች ገቢራዊ ሆነዋል፡፡ “ድንገትም እንደ ብርቱ ዐውሎ ነፋስ ያለ ድምፅ ከሰማይ መጥቶ ተቀምጠው የነበሩበትን ቤት እንዳለ ሞላው፡፡ የእሳት ምላሶች የሚመስሉም ታዩአቸው፤ ተከፋፍለውም በእያንዳንዳቸው ላይ ዐረፉ፡፡ ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ

ተሞሉ፤ መንፈስም እንዲናገሩ በሰጣቸው መጠን በሌሎች ቋንቋዎች ይናገሩ ጀመር፡፡ ” ሐዋ. 2፡2-4)፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሐዋ. 2፡5-13፡፡ የዚህ አስደናቂ ክስተት አንደምታው ምንድን ነው?

---

---

በዓለ ኀምሳ ወይም ጴንጤቆስጤ ስለ ጌታ ቸሮታና በጎነት ምስጋና የሚቀርብበት የደስታ በዓል ነው፡፡ ምናልባት ያልፈላ የወይን ጠጅ ጠጥተዋል የሚል ክስ በሐዋርያቱ ላይ የቀረበበት ምክንያት ይኸው ሊሆን ይችላል (ሐዋ. 2፡13-15)፡፡ ሐዋርያት በተለያዩ ቋንቋዎች በመናገርና በመደመጥ ባሳዩት ታምራት የእግዚአብሔር ኃይል በተለየ መታየት ቻለ፡፡ በዘመኑ ልዕለ ኃያል በነበረው ሮም ስር ይገዙ ከነበሩ ልዩ ልዩ አገራት በዓሉን ለማክበር በየሩሳሌም የተሰባሰቡ አይሁዳውያን ስለ መሲሁ የሱስ የተሰጠውን መልእክት በገዛ ቋንቋቸው ለመስማት ቻሉ፡፡

በባቤል ግንብ ከተጀመረው የቋንቋ መደበላለቅ አንስቶ ሰብዓዊው ዘር በተለያዩ ብሔሮች ተከፋፍሎ መኖሩን ቢቀጥልም፤ ነገር ግን ለጌታ ቸሮታና በጎነት ምስጋና በሚቀርብበት በጴጥጤቆስጤ በዓል ከወትሮው እጅግ በተለየና ባልተለመደ መልኩ የቀደመውን ሰብዓዊ መበታተን ዳግም ማስተሳሰር ተቻለ፡፡ የጸጋው ታምራት ሰብዓዊውን ቤተሰብ ዳግም ማስተሳሰር ጀመረ፡፡ በዓለማቀፍ ደረጃ የተስተዋለው የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ኅብረት በባቤል ጠፍቶ የነበረውን ዳግም በማደስ የመንግሥቱን ተፈጥሮ የሚመሰክር ሆነ፡፡

## ማክሰኞ — ጥቅምት 20

## የአማኞች ኅብረት

ጴጥሮስ ለሕዝቡ ያቀረበውን ስብከትና በንስሐ እንዲመለሱ የመንገሩን ተማጽኖ ተከትሎ በምላሹ ሦስት ሺ ያህል ሰዎች የሱስን እንደ መሲህ ተቀበሉ፡፡ እግዚአብሔር ለእስራኤል የገባው የብሉይ ኪዳን ተስፋ ፍጻሜ መሆኑንም አመኑ፡፡ በእነዚያ ሁሉ ሰዎች ልብ ውስጥ ጌታ እየሠራ ነበር፡፡ በተለያዩ ሩቅ አገራት ይኖሩ የነበሩ ብዙዎች የየሱስን ዝና ሰምተው ስለ ነበር እርሱን ለማየት ተስፋ በማድረግ ወደ የሩሳሌም ተጉዘዋል፡፡ ምናልባት አንዳንዶች የሱስን ሊያዩና የእግዚአብሔርን አዳኝነት መልእክት ሊሰሙ ቢችሉም ነገር ግን ተከታዮቹ ለመሆን አልወሰኑም ነበር፡፡ በጴንጤቆስጤ በዓል ላይ እግዚአብሔር በደቀ መዛሙርቱ ሕይወት በታምር ጣልቃ ገብቶ ለየሱስ ትንሣኤ በምስክርነት ተጠቀመባቸው፡፡ አሁን ሰዎች በየሱስ ስም የኃጢአት ይቅርታ ማግኘት እንደሚችሉ ያውቃሉ (ሐዋ. 2፡38)፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሐዋ. 2፡42-47፡፡ እነዚህ የመጀመሪያዎቹ የየሱስ ተከታይ አማኝ ማኅበረሰብ ክርስቲያኖች ምን ዓይነት እንቅስቃሴ ነበራቸው? ለመሆኑ ይህን አስደናቂ ኅብረት ምን ፈጠረው?

---

---

ይህ የሐዋርያው አስተምህሮ የተቀሰመበትና አዲሱ አማኝ ማኅበረሰብ ተካፋይ የሆነበት የመጀመሪያ እንቅስቃሴ በዓይነቱ የተለየ ነበር፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊው መመሪያ በአዳዲስ አማኞች መሃል የተዋጣለት መንፈሳዊ ዕድገት ለማምጣት የሚያስችል ቁልፍ መሣሪያ ነው፡፡ የሱስ "ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው" (ማቴ. 28፡ 20) ሲል ለደቀ መዛሙርቱ ተልዕኮ ሰጥቶአል፡፡ ይህ አዲስ ማኅበረሰብ በቂ ጊዜ ወስዶ በደቀ መዛሙርቱ አማካይነት ስለ የሱስ ይማር ነበር፡፡ እነዚህ ወገኖች የቀደሙትን የዕብራውያን መልእክቶች ፍጻሜ በሚያመላክቱት የሐዋርያት ጽሑፎች በቀረበው መሰረት ስለ የሱስ ህይወት፣ አገልግሎት፣ አስተምህሮ፣ ታምራቶች፣ ተምሳሌታዊ ንግግሮችና ስብከቶች ለመስማት እንደቻሉ ይታመናል፡፡

በተጨማሪ በየዕለቱ ተገናኝተው እየጸለዩና እንጀራ እየቆረሱ በደስታ ይመገቡ ነበር፡፡ በእርግጥ "እንጀራ እየቆረሱ" የተሰኘው አባባል ቀጥተኛ ትስስር ከጌታ ራት ጋር ይሁን ወይም በአንድ ላይ ማዕድ ከመቅረብ--ብዙም ግልጽ አይደለም (ሐዋ. 2፡46)፡፡ በወቅቱ የአምልኮአቸው ማዕከል በመሆን አገልግሎት ትሰጥ በነበረችው በየሩሳሌሟ ቤተ መቅደስ እና በቤታቸው ያደርጉ የነበረው መደበኛ አብሮነት የተጠቀሰውን በዓይነቱ አዲስ አማኝ ማኅበረሰብ አንድነት በትክክል ይገልጻል፡፡ የጠለቀ ወዳጅነት ተጋርተዋል፡፡ በአንድ ላይ ይጸልዩና ይመገቡ ነበር፡፡ ጸሎት የክርስትና ኅብረት በጣም አስፈላጊ አላባ እንደመሆኑ፤ የመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገት ወሳኝ መሰረታዊ ክፍል ነው፡፡ ይህ አዲስ ማኅበረሰብ በቂ የአምልኮ ጊዜ ይወስድ ነበር፡፡ እያንዳንዱ እንቅስቃሴ በጽናት ገቢራዊ ይሆን እንደ ነበር ከመልእክቱ እናነባለን፡፡

ይህ በጽናት የተሞላ ኅብረት በየሩሳሌም ከነበሩ ሌሎች ወንድሞች ጋር መልካም ግንኙነት እንዲፈጠር መነቃቃት አመጣ፡፡ "በሕዝቡ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው" (ሐዋ. 2፡47) በሚል የተገለጹት አዳዲሶቹ አማኞች በሕይወታቸው የታየው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ዙሪያቸውን በነበሩ ወገኖች ላይ ብርቱ ተጽእኖ ማሳደሩና የሱስ በእርግጥ መሲህ ለመሆኑ ምስክርነታቸው አያጠራጥርም፡፡

ከላይ በምሳሌ ከተገለጸው አንድነት፣ ኅብረትና ምስክርነት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንዎ ምን መማር ትችላለች?

ረቡዕ

## ጥቅምት 21

## ለጋስነት እና ስስት

የየሱስ ተከታዮች በጴንጤቆስጤ ማግስት ከተለማመዷቸው ተፈጥሮአዊ ፈጣን ዕድገቶች አንዱ የእርስ በርስ መረዳዳት መሆኑን ሉቃስ ይነግረናል፡፡ "ያመኑ ሁሉ በአንድነት ነበሩ፤ ያላቸውንም ሁሉ በጋራ አደረጉ፡፡ ሀብታቸውንና ንብረታቸውንም እየሸጡ ለእያንዳንዱ ሰው የሚያስፈልገውን ያህል ይሰጡት ነበር" (ሐዋ. 2፡44-45)፡፡

ይህ እያንዳንዱ ያፈራውን በጋራ የመጠቀም አካሄድ ኅብረቱ የሚጠይቀው መስፈርት ሳይሆን ያ የተለማመዱት ኅብረት ያመጣው በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የፍቅር ውጤት ነበር፡፡ በተጨማሪ የኅብረታቸው ጽኑ መገለጫ ነበር፡፡ ይህ የአማኞች ማኅበራዊ አኗኗር ለተወሰኑ ጊዜያት የቀጠለ ሲሆን በዚህ ዙሪያ ተጨማሪ ዝርዝሮች በሐዋ. ምዕ. 4እና 5 ቀርቧል፡፡ በተጨማሪ ቀጥሎ እንደምናየው በሌሎች የአዲስ ኪዳን መልእክቶች የሚገኝም ጭብጥ ነው፡፡

በርናባስን ለመጀመሪያ ጊዜ የምንተዋወቀው በዚህ ዐውደ ጽሑፍ ነው፡፡ ግለሰቡ የግል ርስት የነበረው ሀብታም እንደነበር መገመት ይቻላል፡፡ ንብረቱ ለክርስቲያን ኅብረት ጥቅም እንዲውል በማሰብ ሸጠና ገንዘቡን ወደ ሐዋርያት አመጣ (ሐዋ. 4፡ 36-37)፡፡ በርናባስ እንደ ምሳሌ ልንከተለው የሚገባ ሰው ሆኖ ቀርቦአል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሐዋ. 4፡32-37፣ 5፡1-11፡፡ የበርናባስን ባህሪና አመለካከት ከሐናንያ እና ባለቤቱ ሰጲራ ጋር ያስተያዩ፡፡ ባልና ሚስቱ ምን ነካቸው?

እነዚህ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን በግልጽ ከመዋሸታቸው በተጨማሪ ስስትና ክፉ ምኞት ተንጸባርቆባቸዋል፡፡ ምናልባት ራስ ወዳድነትንና ስስትን ያህል የአማኞችን ኅብረትና ወንድማዊ ፍቅር በፍጥነት ሊያጠፋ የሚችል ኃጢአት የለም፡፡ የበርናባስ ድርጊት ለጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ኅብረት በአዎንታዊ ሲታይ፤ በተቃራኒው ሐናንያ እና ሰጲራ ግን በአሉታዊ ምሳሌነት ይነሳሉ፡፡ ሉቃስ የሕብረቱ አካል የነበሩትን ከመልካም ምግባር አፈንጋጭ ሰዎች ታሪክ በመናገር ረገድ ሐቀኛ ነው፡፡

ከአስርቱ ትእዛዛት አንዱ የሆነውና ስለ ክፉ ምኞት የሚናገረው የመጨረሻው ትእዛዝ (ዘጸ. 20፡1-17) ከሌሎቹ የተለየ ነው፡፡ ሌሎቹ ትእዛዞች እግዚአብሔር ለሰብዓዊው ፍጡር ያለውን ፈቃድ ፊት ለፊት ስለ መተላለፍ ሲናገሩ፤ የመጨረሻው ትእዛዝ ግን በልብ ውስጥ ስለ ተደበቀው ነገር ያወሳል፡፡ የክፉ ምኞት ኃጢአት ድርጊታዊ ሳይሆን ይልቁንም የአስተሳሰብ ሂደት ነው፡፡ ክፉ ምኞት እና ባልደረባው ራስ ወዳድነት በዐይን የሚታይ ኃጢአት ሳይሆን ኃጢአተኛው ሰብዓዊ ፍጡር የሚገኝበት ሁናቴ

ነው፡፡ ይህ ኃጢአት ገሃድ መውጣት የሚችለው እንደ ሐናንያ እና ሰጲራ ዓይነቱ ራስ ወዳድ ድርጊት ብቻ ነው፡፡ በዚህም የመጨረሻው ትእዛዝ በሁሉም ትእዛዞች የተኮነኑ ድርጊቶች የሚገለጹበት የክፉው ሁሉ ተግባር ሥር መሆኑን መመልከት ይቻላል፡፡ ይህ ክፉ ምኞት በቀላሉ በሰይጣን ተጽእኖ ስር የሚወድቁበትን በር በመክፈት እግዚአብሔርን ወደ መዋሸት መራቸው፡፡ ሁኔታው ይሁዳን ከነዳው ክፉ ምኞት የተለየ አልነበረም፡፡

*ክፉውን ምኞት ወይም ስስትን ከሕይወታችን መንቀል የምንችልባቸው መንገዶች ምንድን ናቸው? ላለን ነገር ምስጋና እና ውዳሴ ማቅረብ የዚህ ክፉ ነገር ማርከሻ ኃይል የሆነው ለምንድን ነው?*

**ሐሙስ** **ጥቅምት 22**

## ድኾችን ማሰብ

አንዱ የነበረውን ለሌሎች የሚያካፍልበት ማኅበራዊ አኗኗር የቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ኅብረት ተጨባጭ መገለጫ ነበር፡፡ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች የተገለጸው የልግስና ተግባር ኋላ ላይ ጳውሎስ በመቄዶንያ እና አንጾኪያ ያቋቋማቸው ቤተ ክርስቲያኖች በየሩሳሌም ለነበሩ ድኾች የድርሻቸውን እንዲያበረክቱ ግብዣ ሲያቀርብላቸው እንደ ቀጠለ እንመለከታለን (ሐዋ. 11:27–30፣ ገላ. 2:10፣ ሮሜ 15:26፣ 1ቆሮ. 16:1–4)፡፡ ስጦታው በአብዛኛው አሕዛብ አማኞችን ያቀፉ እነዚያ አብያተ ክርስቲያናት በየሩሳሌም ለነበሩ አይሁድ ወንድም እህቶች የነበራቸውን ጥንቃቄና ፍቅር በተጨባጭ ገልጦ ማሳየት የቻለ ሆነ፡፡ አማኞች የባህልና የብሔር ልዩነቶች ቢኖሯቸውም በክርስቶስ አንድ አካል ፈጥረው የከበረውን አንድ ወንጌል ይጋሩ ነበር፡፡ ይህ በችግር ከነበሩ ወገኖች ጋር ተካፍሎ የማደር ተግባር ቀድሞውኑ በቤተ ክርስቲያን የነበረውን ኅብረት መግለጥ ብቻ ሳይሆን ኅብረቱን ጽኑ መሰረት ላይ የሚያቆምም ነበር፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ 2ቆሮ. 9፡8-15፡፡ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የተገለጠው ለጋስነት ውጤቱ ምን ይሆናል አለ?

---

---

በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን የተስተዋለው ኅብረት ዛሬም ምን መሠራት እንደሚኖርበት ያሳየ ነው፡፡ በአማኞች መሃል ዓለማቀፋዊ ቁርጠኝነት ባይኖር ኅብረት መምጣት ባልቻለ ነበር፡፡ የጥንቱ የአማኞች ኅብረት መሪዎች--ከክርስቶስ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማሳደግ የአገልግሎታቸው አካል አድርገው ተመልክተውት ነበር፡፡ በባልና ሚስት እንዲሁም በልጆች መሃል ያለ ፍቅር በቁርጠኝነት በየቀኑ እንዲጎለብት እንደሚደረግ ሁሉ በአማኞች መካከል ያለውም ኅብረት ተመሳሳይ ነው፡፡ በክርስቶስ ያለን ኅብረት በብዙ መንገዶች የሚደፋፈር ብሎም በጉልህ የሚታይ ጭምር ነው፡፡

በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ይህን አንድነት ያዳበሩ የታወቁ አላባዎች፡ ጸሎት፣ አምልኮ፣ ኅብረት፣ የጋራ ራዕይ እና የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት ናቸው፡፡ እነዚህ ወገኖች ያስተዋሉት ወንጌልን ለዓለም የመስበክ ተልዕኮአቸውን ብቻ አልነበረም፡ ፡ ይልቁንም አንዱ ለሌላው የፍቅርና እንክብካቤ ኃላፊነት እንዳለበትም ተረድተው ነበር፡፡ ኅብረታቸው በገዛ አጥቢያቸው ያደርግ በነበረው የለጋስነት ተግባር ድጋፍ ሰጭነቱን ገልጦ ማሳየት የቻለ ብቻ ሳይሆን፤ ከራሳቸው አልፎ በብዙ ርቀት የሚገኙ የቤተ ክርስቲያን ማኅበረሰቦችንም ያካተተ ነበር፡፡

"ቸርነታቸው የእግዚአብሔርን ጸጋ በከንቱ ላለመቀበላቸው ምስክር መሆን ችሎ ነበር፡፡ እንዲህ ያለው ለጋስነት በመንፈስ ከመቀደስ ውጪ ሌላ ምን ሊያፈራ ይችላል? ይህ በአመኑትም ሆነ በአላመኑት ዐይን የጸጋው ታምራት ነበር፡፡"—Ellen G. White, The Acts of the Apostles, p. 344.

እርስዎና ቤተ ክርስቲያንዎ ለሌሎች ለጋስ የመሆንን ጥቅም የተለማመዳችሁበት መንገድ ምን ይመስላል? ማለትም--የቸርነት እጆቻቸውን ለሌሎች የሚዘረጉ ምን ዓይነት በረከት ይወርድላቸዋል?

## ዓርብ

## ጥቅምት 23

*ተጨማሪ ጥናት*: *Ellen G. White, "Pentecost," pp. 35–46, in 3 The Acts of the Apostles.*

"ይህ የአማኞች የለጋስነት ተግባር [ሐዋ. 2:44-45፣ 4:32–35] የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ውጤት ነበር፡፡ በወንጌል ኃይል የተለወጡ ወገኖች 'በአንድ ልብ እና በአንድ መንፈስ ነበሩ፡፡' የተልዕኮው ስኬት ለሁሉም መሰጠቱ--አንድ ሁሉንም በጋራ የሳበና የተቆጣጠረ ነገር ነበር፡፡ ይህን ተከትሎ ስስትም ሆነ ምቀኝነት በህይወታቸው ቦታ አልነበረውም፡፡ ለወንድማቸውና ለዓላማቸው የነበራቸው ፍቅር ለገንዘብና ለቁሳዊው ነገር ከነበራቸው የላቀ ነበር፡፡ ከምድራዊው ሀብት ይልቅ ለነፍሳት ከፍ ያለ ዋጋ ለመስጠታቸው ሥራዎቻቸው ምስክር ነበሩ፡፡

"የእግዚአብሔር መንፈስ ሕይወታችንን ሲመራ የሚከሰተው ይኸው ነው፡፡ ልባቸው በክርስቶስ ፍቅር የተሞላ ወገኖች በእርሱ ጉስቁልና እኛ ባለጸጎች እንድንሆን ስለ እኛ የደኸየውን ጌታ ምሳሌ ይከተላሉ፡፡ ገንዘብ፣ ጊዜ፣ ተጽእኖ--ከእግዚአብሔር እጅ የተቀበሏቸው ስጦታዎች በሙሉ የወንጌልን ሥራ ለማፋጠን ብቻ ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ በዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን እንደሚታየው አባላት ምድራዊውን ብልጭልጭ ነገር ከመውደድ ይልቅ መንፈስ ቅዱስ በሚሰጣቸው ኃይል ባልንጀራቸው ወንጌል የሚሰማበትን መሥዋዕትነት ለመክፈል ፈቃደኞች ሲሆኑ፤ በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን እንደ ሆነው በአምላካዊው ቃል የታወጁት እውነቶች በአድማጭ ልብ ብርቱ ተጽእኖ ያገኛሉ፡፡"—Ellen G. White, The Acts of the Apostles, pp. 70, 71.

## የመወያያ ጥያቄዎች፣

1. የቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ለተለማመደችው ኅብረት መምጣት መንስዔ በመሆን እገዛ ያደረጉትን ነጥቦች ከዚህ ሣምንት ትምህርት ያንብቡ፡፡ እኛ ዛሬ እንደ ቤተ ክርስቲያን ተመሳሳይ ተግባራት መፈጸም የምንችለው እንዴት ነው? በዚያን ወቅት በነበሩ አማኞች መሃል የተተገበሩ እኛን ግን የሚጎድሉን ነገሮች ምንድን ናቸው?

2. እነዚያ የቀደሙ የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያኖች ከእነርሱ እጅግ ርቀው በየሩሳሌም ይኖሩ ለነበሩ ድኾች እርዳታ ማድረጋቸው ለእኛ ምን ምሳሌ ይተውልናል? ሌሎች ማኅበራዊ ጉዳዮችን በተመለከተስ? አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖች ድህነትን በመቅረፍና ሌሎች መሰረታዊ ነገሮችን በማቅረብ ረገድ ማኅበረሰብ አቀፍ ተግባራቶች ማከናወን የሚችሉት እንዴት ነው?

3. ከአሳዛኙ የሐናንያ እና ሰጲራ ታሪክ ልንቀስም የምንችላቸው አንዳንድ ትምህርቶች ምንድን ናቸው? የእነዚህን ሁለት ሰዎች ሞት ስለ ሰሙ ሲጠቀስ “ታላቅ ፍርሐት ያዛቸው” (ሐዋ. 5፡5) በሚል የቀረበው ሀረግ አስፈላጊነት ምኑ ላይ ነው?

## ማጠቃለያ፡

የየሱስ ደቀ መዛሙርት በታላቅ ኃይል እንደሚፈስ ተስፋ ለተሰጠው መንፈስ ቅዱስ ራሳቸውን በማዘጋጀታቸው የቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ፈጣን ዕድገት ማስመዝገብ ቻለች፡፡ በእነርሱ የተስተዋለው ኅብረትና የጋራ መታመን መንፈስ ቅዱስ ልባቸውን በበዓለ ኀምሳ ቀን ለማዘጋጀት እንዲጠቀምባቸው ምክንያት ነበሩ፡፡ አንዱ ለሌላው ያሳይ ከነበረው ቸርነት እና ከተመዘገበው ፈጣን የቤተ ክርስቲያን ዕድገት አኳያ መንፈስ ቅዱስ ከበዓለ ኀምሳ በኋላም ይህን አዲስ አማኝ ማኅበረሰብ የመለወጥ ሥራውን ቀጠለ፡፡

# 6ኛ ትምህርት ከጥቅምት 24 - 30

## የኅብረት ገጽታዎች

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ 1ጴጥ. 2:9፣ ዘፀ. 19:5-6፣ ኤፌ. 2:19–22፣ 1ቆሮ. 3:16-17፣ 1ቆሮ. 12:12–26፣ ዮሐ. 10:1–11፣ መዝ. 23፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ :-**"አካል ብዙ ብልቶች ቢኖሩትም አንድ አካል ነው፤ ነገር ግን ብልቶች ብዙ ቢሆኑም አካል አንድ ነው፡፡ ክርስቶስም እንዲሁ ነው፡፡" (1ቆሮ. 12፡12)፡፡

መጽሐፍ ቅዱስን ያጠና ማንም ሰው መጽሐፉ በምስሎችና ምልክቶች የተሞላ መሆኑን እና እነዚህ ትዕይንቶች ደግሞ ከራሳቸው ይልቅ ወደ ገዘፉ ተጨባጭ ሐቆች እንደሚያመለክቱ ይረዳል፡፡ ለአብነት ያህል መላው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የመሥዋዕት ሥርዓቶች የሱስን እና አጠቃላይ የደኅንነት እቅድ የሆነውን እውነት አመላካች ተምሳሌቶች ናቸው፡፡

ሌሎች አያሌ ምስሎች በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆን እንደውም አንዳንዴ በጣም መሰረታዊ የሆኑት እንደ ውሃ፣ እሳት እና ነፋስ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ነገሮች እንደየ ጽሑፉ ዐውድ የመንፈሳዊው እና ሥነ መለኮታዊው እውነት ገጽታ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የሱስ በሚከተለው ንግግሩ "ነፋስ ወደሚወስደው ይነፍሳል፤ ድምፁንም ትሰማለህ፤ ነገር ግን ከየት እንደ መጣ፣ ወዴት እንደሚሄድም አታውቅም፤ ከመንፈስም የተወለደ ሁሉ እንዲህ ነው" (ዮሐ. 3፡8) በማለት ነፋስን በመንፈስ ቅዱስ ተምሳሌትነት ሲያቀርብ ይታያል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በዓለም ፊት ተገልጦ እንዲታይ ጥሪ የሚያቀርበውን ቤተ ክርስቲያናዊ ኅብረት ይፋ ለማድረግ ብዛት ያላቸውን ምስሎች ይጠቀማል፡፡ ምንም እንኳ እያንዳዱ ግለሰባዊ ምልከታ በራሱ የተሟላ ሊሆን ባይችልም፤ ይልቁንም እነዚህ ምስሎች ጠቅለል አድርገው ስለ ቤተ ክርስቲያን ኅብረት ብዙ ነገሮችን ይገልጻሉ፡፡ ለአብነት ያህል፡--ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር ስላላት ግንኙነት፣ አባላት እርስ በርሳቸው ስለሚኖራቸው ግንኙነቶችና በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያን ከማኅበረሰቡ ጋር የሚኖራት ግንኙነቶች አንኳር የሚባሉት ናቸው፡፡

የዚህ ሣምንት ትምህርታችን በአንዳንድ ገጽታዎች ላይ ምልከታ በማድረግ በክርስቶስ ያለንን ኅብረት እንዴት እንደሚገልጹልን እናያለን፡፡

**እሁድ** **ጥቅምት 25**

## የእግዚአብሔር ሕዝብ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ 1ጴጥ. 2፡9፣ ዘፀ. 19፡5-6፣ ዘዳ. 4፡20፣ 7፡6፡፡ ጥቅሶቹ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በተለየ ስላላቸው ክብር ምን ይላሉ?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

ቤተ ክርስቲያን ስንል ጉዳዩ በቀጥታ የሚያያዘው ከሕንፃው ሳይሆን ከሕዝብ (ከምዕመን) ጋር ቢሆንም፤ አሁንም ሕዝብ ስንል ማንኛውንም ሕዝብ ማለታችን አይደለም፡፡ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን እንደ አባታቸውና አዳኛቸው የተቀበሉ፣ በክርስቶስ የተዋጁና እርሱን የሚታዘዙ የእግዚአብሔር ንብረት ሕዝቦች ናቸው፡፡ ይህ ገጽታ የደኅንነት እቅድ ከወጣበት ጊዜ አንስቶ እግዚአብሔር በምድር ላይ ሕዝቦች እንዳሉት እና በብሉይ ኪዳኗ እስራኤል ብሎም በአዲስ ኪዳኗ ቤተ ክርስቲያን መካከል የተሳሰረ ቀጣይነት ለመኖሩ አጽንኦት ይሰጣል፡፡ እግዚአብሔር ከአዳም ጊዜ አንስቶ ከውሃ ጥፋት በፊትና በኋላ ከነበሩ አባቶች እንዲሁም ከአብርሃም ጋር ኪዳን ገባ፡ ፡ ይኸውም ሕዝቡ በዚህ ዓለም የአምላካዊው ፍቅር፣ ምህረትና ፍትሕ ተወካይ እንዲሆን ነው፡፡

የእግዚአብሔር ሕዝቦች “የተመረጠ ትውልድ”፣ “የንጉሥ ካህናት”፣ “ቅዱስ ሕዝብ” ተብለው ይጠራሉ፡፡ እነዚህ መጠሪያዎች የሕዝቡን ለተለየ ዓላማ መጠራት ይጠቁማሉ፡ “እናንተ ግን ከጨለማ ወደ አስደናቂ ብርሃኑ የጠራችሁን የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ እንድታውጁ” ነው (1ጴጥ. 2፡9)፡፡ በተጨማሪ አባባሉ በዘፀ. 34፡6-7 የቀረበውን የእግዚአብሔርን በምሕረት የተሞላ ባህሪ ያስተጋባል፡ “ቤተ ክርስቲያን አባሎቿ በሕይወታቸው የከበረውን አምላካዊ ባህሪ እንዲያንጸባርቁና መልካምነቱንና ምኅረቱን ለሰዎች ሁሉ ያውጁ ዘንድ እግዚአብሔር የገዛ ርስቱ አድርጎ ገዛት”—The SDA Bible Commentary, vol. 7, p. 562.

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዘዳ. 7፡6-8፡፡ እግዚአብሔር የአብርሃምን ትውልድ የገዛ ሕዝቡ አድርጎ እንዲመርጥ የገፋፋው ነገር ምንድን ነው? ይህ ዛሬም ሊሠራ የሚችለው እንዴት ነው?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

ዛሬ “ቅዱስ ሕዝብ” (ሌላው የቤተ ክርስቲያን ገጽታ?) የሚለው መጠሪያ የሚውለው ለየትኛው አገር ሕዝብ ነው ብለን ራሳችንን ልንጠይቅ ብንችልም መልሱ--የለም ነው፡፡ ሁሉም ብሔሮች እና ብሔረሰቦች የእግዚአብሔር ፍቅር እና ጸጋ የማይገባቸው ናቸው፡ ፡ ምንም እንኳ ቅዱስ ሕዝቦቹ እንድንሆን አምላካዊው ቃል ጥሪ ቢያደርግልንም

የእስራኤል መመረጥና መመስረት እውን የሆነው ከገዛ ፍቅሩ የተነሳ እንጂ ከሰብዓዊው ፍጡር በመልካም ሥራ አለመሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች መመስረት እርሱ ለፍጡሮቹ ያለውን ፍቅር ያመላክታል፡፡ ሕዝቦቹ ኃጢአት ሠርተው በአገር ደረጃ ክህደት ቢፈጽሙም፤ እግዚአብሔር ግን ለአብርሃምና ሕዝቡን ለሚያድነው ለዘሩ ፍሬ ለክርስቶስ የገባውን ኪዳን ጠበቀ፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች የተመረጡት ከጸጋው የተነሳ እንደመሆኑ የመዳናቸውም መንስኤ ይሄው ነው፡፡ ይህ ጭብጥ ተራ የሆነው ትውልዳችን ከማይገባው አምላካዊ ጸጋ ጋር የፈጠረውን ትስስር ያስታውሰናል፡፡

*"የእግዚአብሔር ሕዝቦች" ብንሆንም እንኳ ደኅንነታችን ክርስቶስ ለእኛ ያደረገው ነገር ውጤት እንጂ እኛ ለራሳችን ማድረግ የምንችለው ነገር ያለመሆኑን የተቀደሰ እውነታ ሁልጊዜ ከፊታችን እንደጠበቀን መጓዝ ያለብን ለምንድን ነው?*

**ሰኞ** **ጥቅምት 26**

## የእግዚአብሔር ቤተሰብ

በአዲስ ኪዳን የተገለጸው ሌላው የእግዚአብሔር ሕዝቦች ገጽታ አምላካዊው ቤት ወይም ቤተሰብ ነው፡፡ በዐለቶች እና ግንቦች የተመሰለው ዘይቤአዊ አነጋገር በቤተክርስቲያን ለሚስተዋል የረቀቀ እና እርስ በርስ የመረዳዳት ሰብዓዊ ተፈጥሮ አጽንኦት ይሰጣል፡፡ ጴጥሮስ ክርስቲያኖችን "ሕያዋን ድንጋዮች" (1ጴጥ. 2፡5) በማለት ይጠቅሳል፡፡ ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር ጽናትንና ጥብቅነትን ይገልጻል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ኤፌ. 2፡19-22፡፡ ጳውሎስ በመልእክቱ ጎላ አድርጎ የገለጻቸው ሃሳቦች ምንድን ናቸው? ይህ ምስል በቤተክርስቲያን ውስጥ ስላለው አንድነት ምን ይነግረናል?

---

---

በዚህ ጥቅስ ጳውሎስ ሁለቱን የቤተ ክርስቲያን ገጽታዎች በአንድ ያጣምራል፡ አንደኛው ግዑዙ ቤት ወይም ህንፃ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ሰብዓዊው ቤተሰብ ነው፡፡

አንድ ድንጋይ በራሱ በጣም የከበረ ባይሆንም ከሌሎች ድንጋዮች ጋር ሲተሳሰር ግን ብርቱ ውሸንፍር መቋቋም የሚችል ግንብ ይሆናል፡፡ ማንም ክርስቲያን ብቻውን ብርቱ ሊሆን አይችልም፤ ይልቁንም ከእግዚአብሔር ቤተሰብ ጋር ሊዛመድና ኅብረት ሊፈጥር ይገባል፡፡ አንድ ሕንፃ ጽኑ ሆኖ እንዲቆም ከተፈለገ በጠንካራ መሰረት ላይ ማረፉ የግድ ይሆናል፡፡ መሰረቱ የሱስ ክርስቶስ ሲሆን እርሱም የእግዚአብሔር ቤት "የማዕዘን ድንጋይ" ነው (1ቆሮ. 3፡11)፡፡ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን የአገልግሎቷ የማዕዘን ድንጋይ ከማድረግ የምትገታ ከሆነ ሕልውናዋን ታጣለች፡፡ ቤተ ክርስቲያን--የየሱስ ሕይወት፣ ሞት፣ ትንሳዔ፣ እርገት እና ዳግም ምጽአት ናት፡፡

ቤተ ክርስቲያን ኅብረት ፈጥረው መልካሙን የየሱስ የምሥራች ለዓለም የሚያካፍሉ አማኝ ማኅበረሰቦችን ቅርጽ ትፈጥራለች፡፡ የቤተ ክርስቲያን አጀንዳ የሱስ እና የሱስ ብቻ ነው፡--ማንነቱ፣ ለእኛ ያደረገልንና እያደረገልን ያለው ነገር፣ እርሱን እንደ ጌታ እና እንደ አዳኝ የሚቀበል ማንኛውም ሰው የሚሰጠው ስጦታ...፡፡ የቤተሰብ ገጽታም እንዲሁ ጥልቅ ትርጉም አለው፡፡ ይህኛው የሚያርፈው በራሳቸው በሰዎች የእርስ በርስ ግንኙነት ላይ ነው፡፡ አባት፣ እናት፣ ወንድም፣ እህት የተለመደው የቤተሰብ ገጽታ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ በቤተሰብ አባላት መካከል ያለ ትስስር ጠንካራ እንደ መሆኑ አንዱ ለሌላው ያለው ታማኝነት ውጪያዊውን ግንኙነት ያስንቃል፡፡ ታማኝነት ትልቁ የኅብረት ክፍል እንደመሆኑ--ለመሆኑ ታማኝነት የጎደለው የቱንም ዓይነት ኅብረት ሊኖር የሚችለው እንዴት ነው?

ይህ ገጽታ ከቤተ ክርስቲያን ጋር እንዴት ይዛመዳል? የቤተ ክርስቲያን አባላትም እንዲሁ የአንዱ ትልቅ ቤተሰብ አካል ናቸው፡፡ እኛ እርስ በርስ የተሳሰርነው እንደ ሰብዓዊ ፍጡርነታችን የሁላችንም አባት በሆነው አዳም ብቻ ሳይሆን ሁለተኛው አዳም ከሆነው ከየሱስ ጋር "በአዲስ ልደት" ተሞክሮ በመዛመዳችን ነው፡፡ በዚህ የተነሳ የእርስ በርስ ኅብረት የፈጠርነው በኃይማኖታዊ እውነቶች ብቻ ሳይሆን ከየሱስ ባገኘነው አዲስ ሕይወት የተለወጥን በመሆናችን ጭምር ነው፡፡

የሚያሳዝነው ሁሉም ሰው ከገዛ ቤተሰቡ ጋር ድንቅ የሚባል ዓይነት ተሞክሮ የለውም፡፡ በዚህ የተነሳ ይህ ገጽታ ለእነርሱ እምብዛም ትርጉም ላይሰጥ ይችላል፡፡ ታዲያ እንደ ቤተ ክርስቲያን እነዚህ ወገኖች ኖሯቸው የማያውቀው ዓይነት ቤተሰብ መሆን የምንችለው እንዴት ነው?

**ማክሰኞ** **ጥቅምት 27**

## የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ

ሌላው ጳውሎስ ከህንፃ ጋር በተቀራኘ ጥቅም ላይ ያዋለው ዘይቤአዊ አነጋገር የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ወይም መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ይህ ውድ እና የከበረ ዋጋ ያለው ሕንፃ አንዱ ገጽታ ነው፡፡ ጳውሎስ በ1ቆሮ. 6፡19 ሰብዓዊውን አካል ከመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ጋር ሲያመሳክር በ1ቆሮ. 3፡16-17 ደግሞ ይህንኑ ምስል ከእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ጋር በማገናዘብ ያቀርባል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ 1ቆሮ. 3፡16-17፡፡ ቤተ ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ናት ሲል ምን ማለቱ ነው? በቁ. 17 ስለ ምን እያስጠነቀቀ ነው?

---

---

ጳውሎስ ስለ ቤተ ክርስቲያን ባወሳበት በዚህ ጽሑፍ ስለ ግዑዙ ሕንፃ ወይም የእግዚአብሔር ማደሪያ ቤተ መቅደስ እየተናገረ እንዳልነበር ግልጽ ነው፡፡ ይህ

ዘይቤአዊ አነጋገር ለአንድ ዓላማ የተስማማ ኅብረት ስላለው አካል--ይኸውም የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ኅብረት የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መሆኑንና እርሱ በመንፈስ በመካከላቸው እንደሚያድር ይናገራል፡፡

እንደ ጳውሎስ ከሆነ እግዚአብሔር በክርስትና ኅብረት መሃል ያድራል፡፡ ሆኖም ይህን ኅብረት ለማጥፋት የሚሞክር ማንም ሰው አምላካዊውን ፍርድ ተከትሎ የሚመጣውን ውጤት ይቀበላል፡፡ የአማኞች አንድነት--የዚህ ኅብረት እና የእግዚአብሔር በዚህ መቅደስ መገኘት አስኳል ነው፡፡ ምንም እንኳ ይህ ጥቅስ የአንድን ሰው አካላዊ ሁኔታ ከመንከባከብና ከመጠበቅ አኳያ አልፎ አልፎ ጥቅም ላይ ሲውል ቢስተዋልም (ክርስቲያኖች ይህን ማድረግ ቢጠበቅባቸውም) ጳውሎስ በተለይ እያነሳ የነበረው ነጥብ ግን ይህ አልነበረም፡፡ ይልቁንም መልእክቱ የቤተ ክርስቲያንን ኅብረት የሚያፈርሱትን ያስጠነቅቃል፡፡

ከዚህ ቀደም ባለው ምዕራፍ ጳውሎስ ለአንድነት ፈታኝ ያላቸውን ነጥቦች በማንሳት ይሞግታል፡ “በመካከላችሁ ቅናትና ክርክር” መከፋፈል አለ (1ቆሮ. 3፡3)፡፡ እነዚህ አመልና ባህሪዎች የእግዚአብሔርን በቤተ መቅደሱ መገኘት የሚያገልሉ ደንበኛ የክርስትና አንድነት ስጋቶች ናቸው፡፡ በሌላ አነጋገር በቤተ ክርስቲያን የሚነሱ ግጭቶች የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ማፍረስ ይችላሉ፡፡

ግጭቶች በቤተ ክርስቲያን ሲቀሰቀሱ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የሰጠው ምክረ ሃሳብ ዛሬም በሥራ ላይ መዋል የሚችል ነው፡፡ “ወንድሞች ሆይ፤ በመካከላችሁ መለያት እንዳይኖር፣ አንድ ልብ፣ አንድ ሐሳብ እንዲኖራችሁ፤ እርስ በርሳችሁም እንድትስማሙ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችኋለሁ” (1ቆሮ. 1፡10)፡፡

*በጳውሎስ ዘመን የነበረችው ቤተ ክርስቲያን የገጠሟት ችግሮች--ቅናት፣ ክርክርና መከፋፈል ብቻ አልነበሩም፡፡ እነዚህን ችግሮች እኛም ብንሆን ዛሬ እንጋራቸዋለን፡፡ አንድነታችን ሥጋት ላይ እንዳይወድቅ በእነዚህ ችግሮች ዙሪያ ለመሥራት በመሻቱ ረገድ የእያንዳንዳችን ሚና ምንድን ነው?*

**ረቡዕ** **ጥቅምት 28**

## የክርስቶስ አካል

ምናልባት ቤተ ክርስቲያንን በመወከል ስለ ተለያዩ ብልቶች ጠንከር ባለ መንገድ የሚናገረው በጣም ታዋቂው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምስል ወይም ገጽታ የክርስቶስ አካል ነው፡፡ “አካል ብዙ ብልቶች ቢኖሩትም አንድ አካል ነው፤ ነገር ግን ብልቶች ብዙ ቢሆኑም አካል አንድ ነው፡፡ ክርስቶስም እንዲሁ ነው... እንግዲህ እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ፤ እያንዳንዳችሁም የአካሉ ብልቶች ናችሁ” (1ቆሮ. 12፡12፣ 27)፡፡

አንዱ አካል የተገነባው ከብዙ ልዩ ልዩ ብልቶች እንደ መሆኑ እያንዳንዱ ብልት የራሱ የሆነ የተለያየ ተግባርና ኃላፊነት አለው፡፡ የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ሁኔታም ከዚህ ተመሳሳይ ነው፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፣ 1ቆሮ. 12፣12-26፡፡ ለመሆኑ ይህ ብዙ ብልቶች ያሉት አንድ አካላዊ ገጽታ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንዎ መተግበር የሚችለው እንዴት ነው? ዓለማቀፍ አደረጃጀት ላላቸው እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን ባሉ ተቋሞች መተግበር የሚችለውስ እንዴት ነው?

---

---

እውነተኛ የክርስቲያን አንድነት የሚመጣው በጥላቻና በንቀት ውስጥ ሳይሆን ከዚያ በጸዳ ብዝሐነት ነው የሚል ሀሳብ የያዘው በ1ቆሮ. ምዕ. 2 የምናገኘው የጳውሎስ አስተምህሮ ጥልቀት ያለው ተጨባጭ እውነታ ይዞአል፡፡ የዚህ የተለያየ ማንነት መገለጫ የሆነው ብዝሐነት ምንጩ መንፈስ ቅዱስ በመሆኑ መደነቅ የለብንም፡፡ ሰብዓዊው ብልቶች አስገራሚ አንድነት ብቻ ሳይሆን አስገራሚ ልዩነትም እንዳላቸው ሁሉ በዚህ ብዝሐነት ውስጥ የክርስቶስን ምሉዕነትና ባለጸግነት የሚገልጸው የክርስቶስ አካል ነው፡፡

ይህ ገጽታ እንደ ቤተ ክርስቲያን እኛን በቀጥታ ይናገራል፡፡ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን ባለፉት ጥቂት አሥርተ ዓመታት ተስፈንጣሪ የሚባሉ ዕድገቶችን አስመዝግባለች፡፡ ቤተ ክርስቲያኒቱ ከተለያዩ ታሪካዊ ዳራዎች፣ ባሕሎችና አካባቢዎች የተውጣጡ አማኞችን ማቀፏ እሙን ቢሆንም፤ የብሔር፣ የዘር፣ የባህል፣ የትምህርት እና የዕድሜ ልዩነቶች በክርስቶስ ያለንን አንድነት እንዲከፋፍሉ መፍቀድ የለብንም፡፡ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ይህን ብዝሐነት የአንድነት ምንጭ አድርጎ ካረቀው በልዩነቶቹ ውስጥ ሁላችንም የክርስቶስ መሆናችን ተገልጦ የሚታይ ይሆናል፡፡

ከላይ እንደ ተመከትነው እያንዳንዳችን ማንም ብንሆን ወይም ከየትም ብንመጣ ሁላችንም ከመስቀሉ ግርጌ እኩል ነን፡፡ በዙሪያችን ያለው ዓለም አብልጦ በተበጣጠሰ ቁጥር ቤተ ክርስቲያን በብዝሐነት ውስጥ ወዳለው አንድነት መድረስ እንደሚቻል ማሳየቷ የግድ ይሆናል፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች የወንጌልን ፈዋሽና አስታራቂ ኃይል ገልጦ የማሳየት ክህሎት አላቸው፡፡

ጳውሎስ እንዴት ወደዚህ አንድነት መድረስ እንደሚቻል ይነግረናል፡፡

ክርስቶስ አካሉ ለሆነችውና አዳኟ ለሆናት ቤተ ክርስቲያን ራስ... ነውና" (ኤፌ. 5፣ 23)፡፡ "እርሱ አካሉ የሆነችው የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው" (ቆላ. 1፣18)፡፡ እያንዳንዱ አማኝ ከክርስቶስ ጋር በመንፈስ በመገናኘቱ መላው አካል ከአንድ ማዕድ ይቆርሳል፡፡ እንዲህ ከሆነ የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት፣ ያወቅነውን እውነት መታዘዝ እንዲሁም በክርስቶስ አካል አንድነት የምንጋራውን የአምልኮና የጸሎት ተሞክሮ አስፈላጊነት እንደ ተጋነነ ነገር መቁጠር አንችልም፡፡

ሐሙስ

## ጥቅምት 29

# በጎች እና እረኛ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዮሐ. 10፡1-11፡፡ ከዚህ ስለ ቤተ ክርስቲያን ከቀረበ ምሳሌያዊ አነጋገር ስለ አንድነት የሚናገሩት የትኞቹ ናቸው? በተጨማሪ መዝ. 23 ያንብቡ፡፡

---

---

በዘመናዊዎቹ ትላልቅ ከተሞች የትኛውንም ዓይነት የከብት እርባታ ሥራ መመልከት አይቻልም፡፡ ዛሬ በበግ እና በእረኛ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያውቁ ጥቂት ቢሆኑም ነገር ግን የሱስ ይህን ምሳሌያዊ አነጋገር ሲጠቀም ሰዎች ምን ለማለት እንደፈለገ ያስተውላሉ፡፡ የሱስ "መልካም እረኛ እኔ ነኝ" ብሎ እንደተናገረ ይህን አባባል ተቀብለውና አድንቀው ወዲያውኑ "እግዚአብሔር እረኛዬ ነው" ከሚለው መዝ. 23፡1 ጋር ያመሳክራሉ፡፡ እዚህ ላይ የምናገኘው ምስል ወይም ገጽታ ግልጽ ብቻ ሳይሆን ጉልህና ደማቅ ነው፡፡ በጥንታዊው የመካከለኛው ምስራቅ ባህል እረኞች ስለ በጎቻቸው ማንኛውንም ፈታኝ ሁኔታ በመጋፈጥ ረገድ የታወቁ ነበሩ፡፡ እረኝነት ስለ አምላካዊው ባህሪና ከሕዝቡ ጋር ያለውን ግንኙነት ለመግለጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅም ላይ ከዋሉ እጅግ ከበሬታ ካላቸው ገጽታዎች መካከል አንዱ ነው፡፡

በበጎች መልክ የቀረቡት የእግዚአብሔር ሕዝቦች ገጽታ አስደናቂ ነው፡፡ የበጎች ገራምነትና ራሳቸውን ከክፉ መከላከል አለመቻል አንዱ መሳጭ ተፈጥሮአቸው መሆኑን ተከትሎ ከክፉ ከለላና ምሪት ለማግኘት በመልካም እረኛ ላይ መተማመን ያደርጋሉ፡፡ በጎች ብልጠት የጎደላቸው ሆነው ይታያሉ፡፡ በአንዳንድ አጋጣሚ በጎች የሚጠፉበት ሁናቴ ሲከሰት እረኛው የገቡበት ገብቶ መልሶ ወደ በረቱ ያመጣቸዋል፡፡ ግልገል በጎች በእቅፍ መያዝን ጨምሮ ልዩ ጥንቃቄ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ለበጎች ተገቢውን ጥንቃቄ ለማድረግ ትዕግሥትና የሚፈልጉትን መረዳት ያሻል፡፡ ይህ በብዙ መንገድ ቤተ ክርስቲያንን የሚወክል ፍጹም ምስል ይሰጠናል፡፡ የቤተ ክርስቲያን አባል ከመንጋው እረኛ ጋር በሚኖረው ግንኙነት የተትረፈረፈ ጥቅም ከማግኘት ውጪ ሊያስፈራው የሚገባ አንዳች ነገር አይኖርም፡፡

በግ የእረኛውን ድምፅ የመስማቱን አስፈላጊነት አስመልክቶ የሱስ በዚህ ምሳሌያዊ አነጋገሩ አጽንኦት ሰጥቶአል፡፡ እንደ ሁናቴው ጥቂት መንጎችን በአንድ ጉረኖ ወይም አጥር ባለው የበጎች መዋያ በማኖር ከክፉ መጠበቅ ይቻላል፡፡ ታዲያ ኋላ ላይ መለየት የሚችሉት እንዴት ነው? እረኛው ማድረግ የሚኖርበት በጉሮኖው በራፍ ቆሞ መጣራት ነው፡፡ በጎቹ ድምፁን አውቀው ወደ እርሱ ይመጣሉ፡፡ "የራሱ የሆኑትንም ሁሉ ካወጣ በኋላ ፊት ፊታቸው ይሄዳል፤ በጎቹም ድምፁን ስለሚያውቁ ይከተሉታል" (ዮሐ. 10፡4)፡፡ ለቤተ ክርስቲያን የእረኛውን ድምፅ መስማት ወሳኝ ነው፡፡ በእርግጥ

የእግዚአብሔር ሕዝቦች አንድነትና ደኅንነት ከእርሱ ጋር ባላቸው ቅርበት ይወሰናል፡፡ ድምፁን ሰምተው ከመታዘዛቸውም ጋር ቀጥተኛ ትስስር አለው፡፡

*ባጠቃላይ ሰዎች እንደ በግ መታየቱን አይፈልጉም፡፡ ሆኖም በግን ያማከለው ምሳሌያዊ አነጋገር ለእኛ ተገቢና ገጣሚ የሆነው ለምንድን ነው? እዚህ ላይ የምናገኘው ምስል እረኛ እንደሚያስፈልገንና ድምፁን መታዘዝ ተገቢ መሆኑን የሚነግረን እንዴት ነው?*

## ዓርብ

## ጥቅምት 30

ተጨማሪ ሀሳብ፡ Ellen G. White, “The Divine Shepherd,” pp. 476–484, in The Desire of Ages; “The Church on Earth,” pp. 240–243, in Counsels for the Church.

“ቤተ ክርስቲያንን በማነጽና በማሳደግ የእግዚአብሔር አብ፣ የክርስቶስና የመንፈስ ቅዱስ ወሳኝ ተግባራትን ተከትሎ የአማኞች መተባበርና አንድነት ወሳኝ ሚና አላቸው:: የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ቤተ መቅደስ የሚለውን ዘይቤአዊ አነጋገር ከየሩሳሌም ቤተ መቅደስ እና ከዘመን አይሽሬው የግሪክና ሮማውያን ውሁድ ኪነ ሕንፃ ጥበብ ዐውድ አማኞች የቤተ ክርስቲያንን ቅድስና በዐይነ ሕሊናቸው እንዲስሉ አድርገው አቅርበዋል፡፡ በዘመናት የተስተዋለው የአብያተ ክርስቲያናቱ ኪነ ሕንፃ እምብዛም የማይለዋወጥ ተጽእኖ ያሳረፈ ይመስላል፡፡ ዘይቤያዊው አነጋገር ከሥነ ሕይወታዊው ምሳሌ ጥምረት እና ከሥነ ሕንፃ አኳያ ጥቅም ላይ መዋሉ ጉዳዩን ይበልጥ አጉልቶታል፡፡ ከብዙ ድካምና ትዕግሥት በኋላ ‘የተጠናቀቀውን ሕንፃ ከመመልከት ይልቅ የግንባታ ታሪኩን ሂደት በዐይነ ህሊናችን ለመሳል እንገፋፋለን፡፡’ ቤተ ክርስቲያን ‘የሕያው እግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ’ (2ቆሮ. 6፡16) ሕይወትና ታሪክ በትህትና የምትገልጽበት በዓይነቱ ልዩ የሆነ አስደናቂ መብትና ሥልጣን ተሰጥቶአታል፡፡ ”—John McVay, “Biblical Metaphors for the Church: Building Blocks for Ecclesiology,” in Ángel Manuel Rodríguez, ed., Message, Mission, and Unity of the Church (Hagerstown, Md.: Review and Herald®, 2013), p. 52.

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. ስለ መጽሐፍ ቅዱሳዊው የቤተ ክርስቲያን ገጽታ ወይም ምስል አሰብ ያድርጉ፡፡ በአብዛኛው የሚወዱት የትኛውን ዓይነት ነው? ለምን? ቤተ ክርስቲያን የተገለጸችባቸው አንዳንድ ዘይቤአዊ አነጋገሮች በሚከተሉት ጥቅሶች ይገኛሉ፡ -1ጢሞቴ. 3:15፣ 2ጢሞቴ. 2:3–5፣ 1ጴጥ. 2:9፡፡ ዘይቤአዊ አነጋገሮቹ ስለ ቤተ ክርስቲያን ሌላ ምን ያስተምራሉ?

2. “እግዚአብሔር ህዝቦቹ በጠበቀ የክርስቲያን ኅብረት ቁርኝት ውስጥ እንዲኖሩ ይፈልጋል፡፡ በወንድሞቻችን ላይ የሚኖረን መተማመን ለቤተ ክርስቲያን ብልጽግና አስፈላጊ ነው፡፡ ኃይማኖታዊ ቀውስ ሲፈጠር በሕብረት መቆምና መወሰን ጠቃሚ ነው፡፡ በግዴለሽነት የሚወሰድ አንድ እርምጃ እና አስተዋይነት የጎደለው አንድ ድርጊት--ቤተ ክርስቲያን ለዓመታት እንዳታገግም የሚያደርግ አስቸጋሪ ሁናቴ ውስጥ ሊከት ይችላል፡፡”—Ellen G. White, Testimonies for the Church, vol. 3, p. 446. ለቤተ ክርስቲያን ኅብረት ምን ያህል በጥንቃቄ ዘብ መቆም እንዳለብን አስመልክቶ ይህ ማስጠንቀቂያ ምን ሊያስተምረን ይገባል? እያንዳንዳችን ለዚህ የተቀደሰ ዓላማ ያለን ሚና ምን ይመስላል?

3. “የእግዚአብሔር ሕዝቦች” ብንሆንም የመዳናችን መመኪያ የእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ እንደሆነ በእሑዱ ጥናታችን በአጽንኦት ቀርቦአል፡፡ ለነገሩ “የእግዚአብሔር ሕዝቦች” ተብለን እንድንጠራ ባለ ልዩ መብት ያደረገን በእርሱ መልካም ሥራና የመስቀል ላይ መሥዋዕትነቱ ማመናችንና መመካታችን መሆኑ አከራካሪ ሊሆን ይችላል? ለምን?

*ማጠቃለያ፡--አዲስ ኪዳን የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ተፈጥሮ እና ተልዕኮ ለመግለጽ የተለያዩ ዘይቤዎችን ይጠቀማል፡፡ ከሁሉም በላይ እነዚህ ዘይቤዎች እግዚአብሔር ሕዝቦቹን በጥንቃቄ እንደሚያይና እንደሚጠብቅ ያስተምሩናል፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች አንዱ ከሌላው ጋር በብዙ ኅብር የተገመዱ መሆናቸውንና አንዳችን ለሌላው እንድንሠራ የተጠራንበትን ሥራ መሥራት እንዳለብን እነዚሁ ምስሎች በተጨማሪ ያስተምሩናል፡፡*

# 7ኛ ትምህርት ከኅዳር 1 - 7

## ግጭቶች ሲከሰቱ

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ሐዋ. 6፡1–6፤ ሐዋ. 10፡1–23፤ ማቴ. 5፡17–20፤ ሐዋ. 11፡3–24፤ ሐዋ. 15፡1–22፤ አሞጽ 9፡11-12፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ :-**“ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁላችሁ ክርስቶስን ለብሳችሁታልና፡፡ በአይሁድና በግሪክ፣ በባሪያና በነጻ ሰው፣ በወንድና በሴት መካከል ልዩነት የለም፤ ሁላችሁም በክርስቶስ አንድ ናችሁ፡፡” (ገላ. 3፡27-28)፡፡

በማናቸውም ክርስቲያን ማኅበረሰብ ውስጥ አስቸጋሪ ከሚባሉ ተግባራት መካከል አንዱ የአመለካከት ልዩነት ሲፈጠር ከቤተ ክርስቲያን ማንነትና ተልዕኮ አኳያ አንድነትን ጠብቆ ማቆየት ነው፡፡ ልዩነቶች በከረሩ ቁጥር አስከፊ መዘዞች ሊከተሉ ይችላሉ፡፡

የዛሬዎቹ ክርስቲያን ማኅበረሰቦች በአዲስ ኪዳን ከምንመለከታቸው የተለዩ አይደሉም፡፡ ሰዎች ያው ሰዎች እንደመሆናቸው አንኳር በሚባሉ ነጥቦች ዙሪያ ልዩነቶች ይከሰታሉ፡፡ በዕውቀት ላይ ባልተመሰረቱ የሀሳብ ልዩነቶች እንዲሁም ቁልፍ በሚባሉ የብሉይ ኪዳን ታሪኮችና ልምዶች አተረጓጎም መንስኤ በቀደሙት ክርስቲያኖች መካከል ሙግት ነበር፡፡ ደግ አሳቢዎቹና አስተዋይ ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ምሪትና በአምላካዊው ቃል ኃይል ለውጥረቶቹ መፍትሔ ለማግኘት ጥረት ባያደረጉ ኖሮ ግጭቶቹ ቤተ ክርስቲያንን ገና በእንጭጩ ሊያጠፏት በቻሉ ነበር፡፡

ከጥቂት ሳምንታት በፊት የቀደመችው ቤተ ክርስቲያን የጉባዔን ኅብረት የተለማመደችበትን መንገድ አጥንተናል፡፡ በዚህ ሳምንት ይህችው ቤተ ክርስቲያን አንድነቷን በማመንመን ሕልውናዋን አደጋ ላይ ሊጥሉ የነበሩ ወስጣዊ ግጭቶችን እንዴት እንደፈታች እንመለከታለን፡፡ ግጭቶቹ ምን ነበሩ? እንዴት መፈታት ቻሉ? ከእነዚህ ተሞክሮዎች ዛሬ ምን መማር እንችላለን?

**እሁድ** **ኅዳር 2**

## ኅሳን ያማከለ ጭፍን ጥላቻ

ጥቅሱን ያንብቡ፡ ሐዋ. 6፡1። በየዕለቱ ለመበለቶች ይደረግ በነበረው ምግብ የማደል ሥራ በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን የተነሳው ማጉረምረም ምክንያቱ ምን ነበር?

---

---

አንዳንድ የቀደሙ ክርስቲያኖች ከግሪክ በመጡ አይሁድ መበለቶች ላይ በነበራቸው ጭፍን ጥላቻ የተነሳ ከዕብራውያን ወገኖቻቸው ያነሰ ምግብ ያድሏቸው ነበር። ይህ በገሃድ የታየ አድልዎ በቀደሙት አማኝ ማኅበረሰብ መካከል መሰነጣጠቅ ፈጠረ። በወቅቱ በተጨባጭ አድልዎ ስለመኖሩ ወይም ስለ አለመኖሩ ጥቅሱ የሚለው ነገር ባይኖርም ነገር ግን አንዳንዶች ችግሩ አለ ብለው እንደሚያምኑ ብቻ ይገልጻል። ይህ ውዝግብ የቀደመችውን ቤተ ክርስቲያን አንድነት ሥጋት ላይ ጥሎ ነበር። በቤተ ክርስቲያን የኅሳ ልዩነት ፈጥኖ መታየቱ አብልጦ ትኩረትን ይስባል።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሐዋ. 6፡2-6። ይህን የተሳሳተ ግንዛቤ ለመፍታት በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን የተወሰዱ ቀለል ያሉ እርምጃዎች ምን ነበሩ?

---

---

---

የቀደመችው ቤተ ክርስቲያን በፍጥነት ማደግ በሐዋርያት ላይ የማያባራ ከባድ ሸክም አስከትሎ ነበር። በተለምዶ "ዲያቆናት" በሚል የሚታወቁት (ምንም እንኳ አዲስ ኪዳን እንዲህ ብሎ ባይጠራም) የእነዚህ ሰባት ሰዎች መሾም በየሩሳሌም የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን ውጥረት በመቀየር ብዙዎች በአገልግሎት የሚሳተፉበትን በር ከፈተ።

ሐዋርያት ግሪክኛ ተናጋሪ አማኞች ያቀረቡትን ቅሬታ በጥንቃቄ ካዳመጡ በኋላ መፍትሔ እንዲፈልጉ ጠየቋቸው። ለሐዋርያት ረዳት የሚሆኑ ሰባት ሰዎችን የመምረጡን ኃላፊነት ለዚሁ ቡድን መተዋቸውን ተከትሎ ግሪክ ተናጋሪ ሰባት ደቀ መዝሙሮችን በዕጩነት አቀረቡ። ተመራጮች "በመንፈስ ቅዱስና በጥበብ የተሞሉ ለመሆናቸው የተመሰከረላቸው" (ሐዋ. 6፡3) መሆን ነበረባቸው። እስከዚያን ጊዜ ድረስ ወንጌልን የመስበክና ለመበለቶች ምግብ የማደል ኃላፊነትን አካትቶ የነበረው የሐዋርያት አገልግሎት ለሁለት ቡድን ተከፍሎ የነበረ ሲሆን፤ እያንዳንዱ አገልግሎት ወንጌልን ለማወጅ እኩል ዋጋ ነበረው። ሉቃስ ቃሉን የሚሰብኩትን ሐዋርያትና ምግብ የሚያድሉ (ሐዋ. 6፡1) ዲያቆኖችን ለመጥቀስ የሚጠቀመው "አገልግሎት" /ዲያኮኒያ/ (ሐዋ. 6፡4) የተሰኘውን ተመሳሳይ ቃል ነው።

መሪዎች ለችግሩ መፍትሔ ፍለጋ ከአማኞች ብዙዎቹን በአንድ ላይ ከመሰብሰባቸው ተጨባጭ ሁኔታ ምን ዓይነት ቁም ነገር ይመለከታሉ? (ሐዋ. 6፥2)

ሰኞ

ኅዳር 3

## የአሕዛብ መለወጥ

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ራሱን የቻለ ታላቅ ክስተት የሆነው የአሕዛብ ወደ የሱስ ክርስቶስ ወንጌል መለወጥ፤ በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ህይወት፣ ሕልውናና ተልዕኮ የውዝግብ መንስዔና ሥጋት መሆን የሚችል ነበር፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሐዋ. 10፥1-23፡፡ አሕዛብ ወንጌልን እንዲቀበሉ በማዘጋጀቱ ረገድ መንፈስ ቅዱስ በብዙዎች ልብ እየሠራ እንደ ነበር በምንባቡ የሚጠቁሙን ነጥቦች የትኞቹ ናቸው?

---

---

ጴጥሮስ በዚህ በተመለከተው ራእይ በጣም ግራ ተጋብቶ እንደነበር እሙን ነው፡፡ ለዚህ ምክንያቱ እንደ ታማኝ አይሁድነቱ በሕጉ መሰረት ንጹህ ያልሆነ ወይም ርኩስ ምግብ ፈጽሞ ተመግቦ ባለማወቁ ነው (ዘሌዋ. 11፣ ሕዝ. 4፥14፣ ዳን. 1፥18)፡፡ ሆኖም የዚህ ራእይ ዓላማ ከምግብ ጋር የተያያዘ ሳይሆን፤ ለወንጌል ስርጭት ጋሬጣ በነበረው በአይሁዳውያንና አሕዛብ መካከል ስለ ተገነባው ግድግዳ ነበር፡፡ እነዚህ ግድግዳዎች እንደ ዛሬው ሁሉ በጥንቱም ዓለም ተስፋፍተው ነበር፡፡

በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት የመጨረሻዎቹ አሥርተ ዓመታት የነበረው ክርስትና በተጨባጭ የተገነባው በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተተነበየውን መሲህ የግል አዳኛቸው አድርገው በተቀበሉ አይሁዳውያን ነበር፡፡ እነዚህ የቀደሙ የየሱስ ተከታዮች በተማሩት መሰረት ሕጉን የሚታዘዙ ታማኝ አይሁዳውያን ነበሩ፡፡ የየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የብሉይ ኪዳኖቹ ትእዛዛት እንደፋቁ ወይም እንደሻሩ አድርጎ አልተመለከተም (ማቴ. 5፥ 17-20)፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሐዋ. 10፥28-29፣ 34-35፡፡ ጴጥሮስ በኢዮጴ የተቀበለውን ራእይ ፍቺ እንዴት ነበር ያስተዋለው? እንዲህ ዓይነቱን ትርጓሜ እንዲሰጥ ምን ገፋፋው?

---

---

አሕዛብ የክርስትናን ኅብረት የሚቀበሉበትን መንገድ መንፈስ ቅዱስ አዘጋጅቶ እንደ ነበር በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እንመለከታለን፡፡ ደግሞም አሕዛብ በቅድሚያ መገረዝ ወይም ወደ ይሁዲነት መለወጥ ሳያስፈልጋቸው ይህን ማድረግ የሚችሉ ሆኑ፡፡ በጴንጤቆስጤ ቀን በየሱስ ተከታዮች ላይ የፈሰሰው ተመሳሳይ መንፈስ በቆርኔሌዎስና

በቤተሰቦቹ ላይ መፍሰሱ ይህ በእርግጥ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ጴጥሮስና ባልደረቦቹን አሳምኖ ነበር (ሐዋ. 10፡44-47)፡፡ መንፈስ ቅዱስ ለአይሁዳውያን እንደ ተሰጠ ሁሉ ለአሕዛብም መፍሰስ የሚችል ከሆነ፤ የሱስን እንደ መሲህ ለመቀበል መገረዝ እንደ ቅደመ ሁኔታ አለመጠየቁ ግልጽ ሆነ፡፡ ይህ ድምዳሜ በቀደምት ክርስቲያኖች መሃል ለተከሰተው ብርቱ ሥነ መለኮታዊ ውዝግብ መንስኤ ለመሆን በቅቶ ነበር፡፡

**ማክሰኞ** **ኅዳር 4**

## በመንፈስ መመራት

በቂሳርያ በነበረው ቆርኔሌዎስ ላይ የሆነው ነገር ብዙም ሳይቆይ ዜናው በየሩሳሌም ይኖሩ ወደ ነበሩ ክርስቲያን ማኅበረሰብ ጆሮ በመድረሱ ጴጥሮስ ስለ ጉዳዩ ማብራሪያ እንዲሰጥ ተጠየቀ፡፡ በወቅቱ ጴጥሮስ ባደረገው ነገር አማኞች ተበሳጭተዋል፡፡ ምክንያቱም አይሁዳውያን የሙሴን ሕግ በሚረዱት መሰረት ታማኝ አይሁዶች ከአሕዛብ ጋር እንዲመገቡ አይፈቀድላቸውም ነበር (ሐዋ. 11፡3)፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሐዋ. 11፡4-18፡፡ ጴጥሮስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራና በዚህ ክስተት ስለነበረው የመሪነት ሚና ምን ዓይነት ማብራሪያ ሰጠ? የሆነውን በመግለጹ ረገድ የነጥቡ ዋንኛ ሃሳብ ምን ነበር?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

ምንም እንኳ አንዳንዶች በጴጥሮስ ድርጊት ሕጋዊነት ዙሪያና አሕዛብን ለማጥመቅ እንዴት ውሳኔ ላይ እንደ ደረሰ ጥያቄ አንስተው የነበረ ቢሆንም ጴጥሮስ ግን ለዚህ ሁሉ በቂ ምስክር ነበረው፡፡ በጴንጤቆስጤ የተገለጠላቸው ያው መንፈስ ቅዱስ በተመሳሳይ መንገድ ተገልጦ ስላረጋገጠለት (ሐዋ. 11፡12) በዚህ ጉዳይ የተስተዋለው የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አልነበረም፡፡ "ይህን በሰሙ ጊዜም የሚሉትን አጥተው እንዲህ እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ፤ 'ይህማ ከሆነ፣ አሕዛብም ወደ ሕይወት ይመጡ ዘንድ፣ እግዚአብሔር ንስሐን ሰጥቷዋል ማለት ነዋ'" (ሐዋ. 11፡18)፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሐዋ. 11፡19-24፡፡ በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ሕይወት በመቀጠል ምን ተስተዋለ?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

በቆርኔሌዎስና ቤተሰቡ የተፈጸመው ይህ ያልተለመደ ድርጊት በተለይ ለእነርሱ ብቻ የሆነ እንጂ ለሌላው አሕዛብ ሊደገም እንደማይችል አድርገው በየሩሳሌም የነበሩ አንዳንዶች ያስቡ ነበር፡፡ ሆኖም ይህ አስተሳሰብ የመንፈስ ቅዱስ እቅድ አልነበረም፡

፡ ከእስጢፋኖስ ሞት (ሐዋ. 8፡1) በኋላ በየሱስ ደቀ መዛሙርት ላይ የደረሰውን ስደት ተከትሎ ከየሩሳሌምና ይሁዳ አልፈው ወደ ሰማርያ፣ ፊንቄ፣ ቆጵሮስና አንጾኪያ ተበተኑ፡፡ እጅግ ብዙ ሕዝብ የሱስን የግል አዳኙ አድርጎ ተቀበለ፡፡ የሱስ ይህ እንደሚሆን አስቀድሞ ተንብዮአል (ሐዋ. 1፡8)፡፡ አሕዛብ በአስደናቂና በከፍተኛ መጠን ወደ ክርስትና ከመግባታቸው አኳያ ራሳችንን በቀደምት አማኝ አይሁዳውያን ቦታ ብናስቀምጥ፤ ለነበሩ ተግዳሮቶች ምላሽ መስጠት ቀላል እንዳልነበር ለመረዳት አንቸገርም፡፡

*በቤተ ክርስቲያንና በመልዕክታችን ዙሪያ ጠባብ አመለካከት በማስተናገድ ምስክርነታችንን ሊያሰናክል ከሚችል ሁኔታ መገታት የምንችለው እንዴት ነው?*

**ረቡዕ** **ኅዳር 5**

## የየሩሳሌም ጉባዔ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሐዋ. 15፡1-2፣ ገላ. 2፡11–14፡፡ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ጽኑ ውዝግብ የፈጠሩ ሁለት ጉዳዮች ምንድን ናቸው?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

የቀደሙት ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን አንድነት ዙሪያ የተጋፈጡት አደገኛ ሁኔታ በተጨባጭ የደረሰ ክስተት ነበር፡፡ አንዳንድ አይሁድ ክርስቲያኖች ደኅንነት ለእግዚአብሔር የኪዳኑ ሕዝቦች ብቻ እንደተወሰነ በማሰብ መገረዝን እንደ አንድ የኃይማኖቱ መስፈርት ይመለከቱ ነበር፡፡ ከታማኝ የአይሁድ ዘይቤዎች አንዱ ከአሕዛብ ጋር ምንም ዓይነት ንክኪ አለማድረግ--ከተደረገ ግን ደኅንነታቸው እንደሚረክስ ያስቡ ነበር፡፡

አይሁዳውያን ከአሕዛብ ጋር ባላቸው ግንኙነት ጥብቅ ወግና ልማድ ነበራቸው፡፡ ሐዋርያት የየሱስ ተከታይ ለመሆን ምኞት ወዳደረባቸው አሕዛብ መድረስ ሲጀምሩ እነዚህ ወጎች ለአዲሱ የክርስቲያን ማኅበረሰብ እንቅፋት ሆኑ፡፡ አስቀድሞ በብሉይ ኪዳን እንደ ተተነበየው መሲህ የእግዚአብሔር የኪዳኑ ሕዝቦች አዳኝ በመሆኑ አሕዛብ መዳን የሚፈልጉ ከሆነ በመጀመሪያ የአይሁድን እምነት ተቀብለው ሲያበቁ፤ በመቀጠል ከአይሁዳውያን ጋር የኪዳኑን ሕግ መከተል አልነበረባቸውምን?

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሐዋ. 15፡3-22፡፡ በየሩሳሌም ጉባዔ የቀረቡት አንዳንድ ጠንከር ያሉ ጉዳዮች ምን ነበሩ?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ይህ ከግርዘት እና ከአሕዛብ ጋር በሚኖር ግንኙነት ዙሪያ በቀጥታ ከብሉይን ኪዳን ታሪክ አተረጓጎም የተወሰደ ጠንከር ያለ ጉዳይ ስር የሰደደ ውዝግብ አስነስቶ ነበር፡ ፡ ሐዋርያት፣ ሽማግሌዎችና ከአንጾኪያ የመጡ ልዑካን በአንድ ላይ ለውይይት ቢቀመጡም ንግግራቸው ያለምንም መፍትሔ ረጅም ጊዜ የወሰደ ይመስላል፡፡

ከዚያም ጴጥሮስ፣ በርናባስና ጳውሎስ ንግግር አደረጉ፡፡ ጴጥሮስ በንግግሩ እግዚአብሔር ወደ አሕዛብ የሚደርሱበት መንገድ የቀየሰበትን ራእይ እንደ ሰጠው በማውሳት ከመንፈስ ቅዱስ ያገኘውንም ስጦታ ጠቀሰ፡፡ ጳውሎስና በርናባስም እንዲሁ እግዚአብሔር በእነርሱ በኩል ለአሕዛብ ያደረገውን ታሪክ አካፈሉ፡፡ በውጤቱም የብዙዎች ዐይኖች ለዚህ አዲስ እውነት ተከፈቱ፡፡ "'እኛም የዳንነው ልክ እንደ እነርሱ በጌታ በየሱስ ጸጋ መሆኑን እናምናለን' " (ሐዋ. 15፡11) ሲል ጴጥሮስ ተናገረ፡፡

ለብዙ ምዕተ ዓመታት ተጠብቆ የቆየ ወግና ልማድ እነሆ ወንጌል በፈነጠቀው ብርሃን ተገፈፈ፡፡

ለረጅም ጊዜ ውስጥዎ ተጠብቆ የቆየ ኃይማኖታዊ አስተምህሮን የተረዱበትን መንገድ የቀየሩበት አጋጣሚ አለ? በኃይማኖታዊ አስተምህሮው በነበሮት አረዳድ ዳግመኛ ጥያቄ ሊኖርዎ ቢችል ከበፊቱ ልምድዎ ምን ተምረዋል?

**ሐሙስ** **ኅዳር 6**

## አስቸጋሪ የመፍትሔ ሀሳብ

በአንጾኪያ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ተወካዮችን ወደ የሩሳሌም ለመላክና ለግጭታቸው የተሻለ መፍትሔ ለማግኘት የተወሰነ መተማመን ደረጃ ላይ መድረስ ነበረባት፡፡ ሆኖም በሐዋርያትና በሽማግሌዎች መካከል ሰዓታት የፈጀ ውይይት ከተደረገ በኋላ ጉባዔውን እንደ መራ የሚታመነው የየሱስ ወንድም ያዕቆብ መደረግ በሚኖርበት ጉዳይ ላይ ውሳኔ አሳለፈ (ሐዋ. 15፡13-20)፡፡ አሕዛብ ክርስቲያን ለመሆን መገረዝን ጨምሮ ሁሉንም ዓይነት ወግና ልማዶች በመታዘዝ ወደ ይሁዲነት መለወጥ እንደማያስፈልጋቸው ጉባዔው ግልጽ ውሳኔ አሳለፈ፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ አሞጽ. 9፡11-12፣ ኤር. 12፡14-16፡፡ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ስለ እስራኤላውያን አጎራባች አገሮች ምን ዓይነት ትንቢት ተናግረው ነበር?

________________________________________

________________________________________

ያዕቆብ ከአሞጽ 9 በመጥቀስ በሚያቀርበው መረጃ ስለ ሕዝቦች መዳን በሌሎች የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች የቀረቡ ማመሳከሪያዎችን እንመለከታለን፡፡ በእስራኤል ምስክርነትና ተሞክሮ መላውን ዓለም ማዳን አምላካዊው እቅድ ነበር፡፡ በእርግጥ እግዚአብሔር ለአብርሃም ያቀረበው ጥሪ እርሱንና የእርሱን ትውልድ ተጠቅሞ ሁሉንም ሕዝብ

መባረኩን ያካትታል (ዘፍ. 12፡1-3)፡፡ አሕዛብን አስመልክቶ መንፈስ ቅዱስ የሰጠው ምሪት--የጴጥሮስ፣ የበርናባስና የጳውሎስ አገልግሎት እንዲሁም የአያሌ አሕዛብ ወደ ክርስትና መለወጥ በዋዛ ሊታለፍ የማይችል ሐቅ ነው፡፡ እነዚህ ምስክርነቶች አብዛኞቹ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ፍጻሜ እያገኙ መምጣታቸውን በየሩሳሌም የነበሩ ክርስቲያን ማኅበረሰብ መሪዎች መገንዘብ እንዲችሉ ረድተዋቸው ነበር፡፡ በእርግጥ እስራኤላውያን ከአሕዛብ ጋር በሚኖራቸው መስተጋብር የሚመሩባቸውን ሕጎችና መመሪያዎች ራሱ እግዚአብሔር አስቀድሞ ሰጥቶአቸው ነበር (ዘሌዋ. 17፡ 18)፡፡ ያዕቆብም ቢሆን ወደ ውሳኔ ሲደርስ እነዚሁኑ ሕጎች ጠቅሷል (ሐዋ. 15፡29)፡፡ አሕዛብ አምላካዊውን ሕዝቦች ተቀላቅለው በየሱስ ደኅንነት እንዲያገኙ እግዚአብሔር ጥሪ እያቀረበ እንደ ነበር ለእያንዳንዳቸው ግልጽ ሆነላቸው፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ከዚያ በፊት ያልተመለከቷቸውን ወሳኝ እውነቶች በመግለጥ በአምላካዊ ቃል ላይ ጥልቅ ማስተዋል ሰጣቸው፡፡

በየሩሳሌም ለተደረሰው ውሳኔ የአንጾኪያ አማኞች የሰጡትን ምላሽ ሐዋ. 15፡30-35 እንደሚከተለው ይነግረናል፡ "ሕዝቡም ካነበቡት በኋላ አበረታች በሆነው ቃሉ ደስ ተሰኙ" (ሐዋ. 15፡31)፡፡

የቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ራሷን ለአምላካዊ ቃል በማስገዛት በመንፈስ ቅዱስ ምሪት እንዴት በፍቅር፣ በአንድነትና በመታመን በአንድነቷ ላይ ያንዣበበውን ቀውስ እንደ ቀለበሰች በዚህ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በቀረበው ብርቱ ምሳሌ እንመለከታለን፡፡

*ሌሎች እያሉ ያሉትን ነገር ልንሰማ የማንፈልግ ቢሆንም እንኳ ነገር ግን የሚባለውን መስማትና ልክ ሊሆኑ እንደሚችሉም ከግምት ማስገባት ለእኛ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ከዚህ ምን እንማራለን?*

## ዓርብ ኅዳር 7

ተጨማሪ ሀሳብ፡ Ellen G. White, "A Seeker for Truth," pp. 131–142; "Jew and Gentile," pp. 188–200, in The Acts of the Apostles.

"ከተለያዩ ስፍራዎች የተመረጠውና በዚህ ጉዳይ ላይ ውሳኔ የሰጠው ጉባዔ የአይሁድና የአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናትን በማዋቀር ግንባር ቀደም ከሆኑ ሐዋርያትና መምህራን የተውጣጣ ልዑክ ነበር፡፡ የየሩሳሌም ሽማግሌዎች፣ ከአንጾኪያ የመጡ ረዳት ኃላፊዎችና ብርቱ ተጽእኖ የነበራቸው ቤተ ክርስቲያኖች የጉባዔው አካል ነበሩ፡፡ ጉባዔው ብሩህ በሆነ የውሳኔ ዐውድ እና በመለኮታዊው ፈቃድ ላይ በተመሰረተ የቤተ ክርስቲያን ልዕልና የተመራ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ራሱ መንፈስ ቅዱስን ለአሕዛብ በመስጠት በዚህ ዙሪያ ላነሱት ጥያቄ መልስ መስጠቱን በውይይታቸው መጨረሻ መመልከት ቻሉ፡፡ የእነርሱ ድርሻ የመንፈስን ምሪት መከተል እንደሆነ አስተዋሉ፡፡

"ሁሉም የክርስትና አካል በዚህ ጥያቄ ላይ ድምፅ እንዲሰጥ አልተጠራም፡፡

ሐዋርያትና ሽማግሌዎች፣ ተጽእኖ አሳዳሪዎች እንዲሁም ፍትሕና ርትዕ አዋቂዎች በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ተቀባይነት ያገኘውን ይህን ሕገ ደንብ አረቀቁ፡፡ ይሁን እንጂ በውሳኔው ሁሉም ደስተኞች አልነበሩም፡፡ በራሳቸው አስተሳሰብ ይመሩ የነበሩ ግትር አስተሳሰብ አራማጅ አንጃዎች በሀሳቡ አልተስማሙም ነበር፡፡ የእነዚህ ሰዎች ሃሳብ በራሳቸው ኃላፊነት በሥራው መሳተፍ ነበር፡፡ ማጉረምረም የበዛበት፣ ስህተት ፈላጊና ልል ባህሪ ይስተዋልባቸው የነበሩ እነዚህ ሰዎች አዳዲስ እቅዶችን እየነደፉ እግዚአብሔር የወንጌልን መልእክት እንዲያስተምሩ የሾማቸውን ወገኖች አገልግሎት ወደ ኋላ ለመጎተት ይጥሩ ነበር፡፡ ቤተ ክርስቲያን በዚያ ጊዜ ከገጠሟት እንቅፋቶች አንስቶ እስከ ዘመን መጨረሻ ተመሳሳይ ሳንካዎች አይለዩአትም፡፡”—Ellen G. White, The Acts of the Apostles, pp. 196, 197.

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. ግጭቶች በሚነሱ ጊዜ በዚህ ሣምንት ከተመለከትናቸው ግጭቶችን የመፍቻ ዘዴዎች የትኞቹን ቅደም ተከተሎች ለቤተ ክርስቲያን ማኅበረሰብዎ መተግበር ይቻላል? ምንም እንኳ ቤተ ክርስቲያን ካስተናገደቻቸው ጉዳዮች አንዱ ሥነ መለኮታዊ እንደመሆኑ የቤተ ክርስቲያን አንድነት ከባሕል፣ ከፖለቲካ ወይም ከጎሳ ጋር በተያያዘ ሥጋት ሲገጥመው ከእነዚህ ተሞክሮዎች ምን እንማራለን? ከላይ ከተመለከትናቸው መሃል የትኞቹን መርኆዎች ልናወጣ እንችላለን?

2. ከላይ የቀረበውን የኤለን ኋይት ጽሑፍ ደግመው ይመልከቱ፡፡ ምንም እንኳ ውሳኔውን ተከትሎ የተገኘው ውጤት አመርቂ ቢሆንም አንዳንዶች ግን አልረኩም ነበር፡፡ ከዚህ አሳዛኝ እውነታ ምን ዓይነት ትምህርት እናገኛለን?

*ማጠቃለያ*: የቀደመችው ቤተ ክርስቲያን አውዳሚ ውጤት ሊያስከትሉባት በሚችሉ ብዛት ያላቸው ውስጣዊ ውዝግቦች ተወጥራ ነበር፡፡ ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ስትመራና ራስዋን ለእግዚአብሔር ቃል ስታስገዛ እነዚህን ውዝግቦች ማስወገድና ከመከፋፈል መመለስ እንደምትችል ተመልክተናል፡፡

# ፀኛ ትምህርት ከኅዳር 8 - 14

## በእምነት ውስጥ ያለ አንድነት

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ሐዋ. 4:8-12፣ ሐዋ. 1:11፣ ማቴ. 25:1-13፣ ዕብ. 9:11-12፣ ዘፀ. 20:8-11፣ 1ቆሮ. 15:51-54፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ :-**"'ድነት በሌላ በማንም አይገኝም፤ እንድንበት ዘንድ ለሰዎች የተሰጠ ከዚህ ስም በስተቀር ሌላ ስም ከሰማይ በታች የለምና'" (ሐዋ. 4፡12)፡፡

ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች በ1888 ዓ.ም. በአንዳንድ ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ዙሪያ ብርቱ ሙግት አድርገው ነበር፡፡ መጋቢዎችና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በዳን. 7 ስለሚገኙት አሥሩ ቀንዶች ትንቢት ምንነት እንዲሁም በገላ. 3፡24 በቀረበው ሕግ ዙሪያ በሚከራከሩበት ወቅት አንዱ ለሌላው የነበረው በጥላቻ የተሞላ አመለካከት ኅብረታቸውንና ጓደኝነታቸውን ብሎም የቤተ ክርስቲያንን አንድነትና ተልዕኮ ማጥፋቱን የተገነዘቡ ጥቂቶች ብቻ ነበሩ፡፡

በሁኔታው አብልጣ ያዘነችው ኤለን ጂ. ኋይት በውይይቱ ተሳታፊ የሆኑት ሁሉ ከየሱስ ጋር ያላቸውን ግንኙነት በጥንቃቄ እንዲያስቡበት እና በተለይ ደግሞ በሃሳብ በማንስማማ ጊዜ ለየሱስ የሚኖረን ፍቅር እንዴት በባህሪያችን መታየት እንደሚኖርበት ታበረታታ ነበር፡፡ በተጨማሪም ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አባላት በእያንንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ተመሳሳይ አቋም እንዲይዝ መጠበቅ የለብንም ስትል ተናግራለች፡፡ ሆኖም መሰረታዊ የሆኑትን የአድቬንቲስት እምነቶች በማስተዋል ረገድ ግን አንድነት ሊኖረን እንደሚገባ አጽንኦት ትሰጣለች (Ellen G. White, Counsels to Writers and Editors, pp. 28-32)፡፡ በዚህ ሣምንት አድቬንቲስት የሚያሰኙንንና አንድነታችንን የሚቀርጹ አንዳንድ መሰረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎችን እንመለከታለን፡፡

**እሁድ** **ኅዳር 9**

## መዳን በየሱስ

ምንም እንኳ እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስትነታችን ከሌሎች የክርስትና አካላት ጋር አንድነት ለመፍጠር የሚያስችሉንን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነጥቦች ብንጋራም፤ ኃይማኖታዊ አስተምህሮአችን በክርስትናው ዓለም ማንም እያወጀው የማይገኘውን የተለየ እውነት ይዞአል፡፡ እነዚህ እውነቶች እኛን የመጨረሻዎቹ የእግዚአብሔር ትሩፋን አድርገው ይገልጹናል፡፡
ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሐዋ. 4፡8-12፣ 10፡43፡፡ ከደኅንነት ዕቅድ አኳያ ባለው ማስተዋል ጴጥሮስ ስለ የሱስ ክርስቶስ ምን ዓይነት አጽንኦት ይሰጣል?

____________________________________________________

____________________________________________________

እግዚአብሔር በክርስቶስ ዓለምን ከራሱ ጋር ማስታረቁን (2ቆሮ. 5፡19) ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ነግሯቸዋል፡፡ የክርስቶስ ሞት በኃጢአት ጥልቅ ሸለቆ እና በሞት ላይ ድልድይ በመሥራት እነሆ ከአብ ጋር አስታረቀን፡፡ ክርስቲያኖች የሱስ በዚህ ምድር ለመፈጸም የመጣውን የሞቱን፣ የትንሣኤውንና የአስታራቂነቱን ፍቺ ለምዕተ ዓመታት ያጤኑት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ የእርቅ ሂደት ሥርየት በሚል ይታወቃል፡ ፡ ሥርየት የተሰኘው ቃል አንዱ አማኝ ከሌላው ጋር ባለው ግንኙነት በአንድ ልብና በአንድ ሃሳብ መሆንን ይወክላል፡፡ መለያየትና መከፋፈል በሚከሰትበት ወቅት ይህ ኅብር የእርቅ ውጤት ይሆናል፡፡ የቤተ ክርስቲያን ኅብረት የዚህ እርቅ ስጦታ ነው፡፡

የሚከተሉት ጥቅሶች ስለ የሱስ ሞትና ትንሣኤ ምን ያስተምሩናል?

ሮሜ. 3:24-25________________________________________

1ዮሐ. 2:2____________________________________________

1ዮሐ. 4:9-10________________________________________

1ጴጥ. 2:21-24________________________________________

ምንም እንኳ በክርስቶስ ሞት እና ትንሣኤ ላይ ያለንን እምነት ከሌሎች የክርስትና አካላት ጋር በተመሳሳይ ብንጋራም፤ ነገር ግን እኛ የምናውጀው የሦስቱ መላእክት መልእክት ክፍል ከሆነው (ራእ. 14፡6-13) "ከዘላለማዊው ወንጌል" ዐውድ ነው (ራእ. 14፡6)፡፡ እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስትነታችን ከሌሎች የክርስትና አካላት በተለየ ለእነዚህ መልእክቶች አጽንኦት እንሰጣለን፡፡

*የክርስቶስ ሞት ተጨባጭ እውነታና ትንሣኤ የሚያስገኘውን ተስፋ ሁሌም ከፊትዎ ጠብቀው መዳዝን መማር የሚችሉት እንዴት ነው?*

ሰኞ ኅዳር 10

## የክርስቶስ ዳግም ምጽአት

በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኙ ሁሉም ትንቢቶች እና የተስፋ ቃሎች በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ወቅት ፍጻሜ እንደሚያገኙ ተስፋ የሚያደርጉት ሐዋርያትና የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ክስተቱን "የተባረከ ተስፋችን" (ቲቶ 2፡13) ሲሉ ይጠሩታል፡፡ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች የእምነታቸው አካል የሆነውን ዳግም ምጽአት ዛሬም አጽንተው ይዘዋል፡፡ ለነገሩ "አድቬንቲስት" የተሰኘው ስማችን ራሱ ይህንኑ በሚገባ ይገልጻል፡፡ ክርስቶስን የሚወዱ ክርስቲያኖች በሙሉ ጌታን ፊት ለፊት እያዩ አምልኮ የሚያቀርቡባትን ያቺን ዕለት በታላቅ ጉጉት ይጠባበቃሉ፡፡ እስከዚያው ግን የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ተስፋ የእግዚአብሔርን ሕዝቦች በአንድ እንዳስተሳሰረ ይኖራል፡፡

የሚከተሉት ጥቅሶች ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ሁናቴ ምን ያስተምራሉ? ዳግም ምጽአቱን ከሚጠቁሙ አንዳንድ እሳቤዎች የሚለዩት እንዴት ነው? ሐዋ. 1፡11፣ ማቴ. 24፡26-27፣ ራእ. 1፡7፣ 1ተሰ. 4፡13-18፣ ራእ. 19፡11-16፡፡

---

---

የሱስ የዳኑ ሕዝቦቹን ሊዋጅ ዳግም እንደሚገለጥ መጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ ያረጋግጥልናል፡፡ የሱስ ራሱ "ያን ቀንና ሰዓት ግን ከአብ በስተቀር የሰማይ መላእክት ቢሆኑ፣ ወልድም ቢሆን ማንም አያውቀውም፡፡" በማለት በዚህ ጊዜ ይሆናል ብሎ መናገር እንደማይቻል ይጠቁማል፡፡ የሱስ ክርስቶስ ዳግም የሚገለጥበትን ጊዜ የማናውቅ ብቻ ሳንሆን አታውቁትም ተብሎ ተነግሮናል፡፡

ቤተ ክርስቲያን ዳግም ምጽአቱን በምትጠባበቅበት ወቅት ሊኖራት የሚችለውን ተሞክሮ ለማሳየት የሱስ በአገልግሎቱ መጨረሻ አካባቢ የዐሥሩን ልጃገረዶች ምሳሌ (ማቴ. 25፡1-13) ተናግሮአል፡፡ እነዚህ በሁለት ቡድን የተከፈሉ ልጃገረዶች ዳግም ምጽአቱን እንጠባበቃለን ብለው የሚያምኑ ሁለት ዓይነት አማኞችን ይወክላሉ፡፡ ምንም እንኳ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የነበሩ ልዩነቶች እምብዛም ባይታዩም ነገር ግን የየሱስ ምጽአት በዘገየ ጊዜ ልዩነቶቻቸው በገሃድ ጎልተው መውጣት ችለው ነበር፡፡ መዘግየት ቢኖርም ነገር ግን አንደኛው ቡድን ተስፋውን አለምልሞና ተጨማሪ መንፈሳዊ ዝግጅቶችም አድርጎ ነበር፡፡ የአምላካዊውን ተስፋ ፍጻሜ የሚያሳይ ተጨባጭ ማስረጃ ባይኖርም እንኳ ክርስቲያናዊው ተሞክሮ ስሜታዊ ደስታ ላይ መመስረት የለበትም፡፡ ይልቁንም ባለማቋረጥ በእግዚአብሔር ጸጋ እየታመኑ መኖር እንደሚገባ የሱስ ይህን ምሳሌያዊ አነጋገር ተጠቅሞ ደቀ መዛሙርቱን ለማስተማር ተስፋ አድርጎአል፡፡ ተግተን እንድንጠባበቅና በማናቸውም ቢዜ ለዳግም ምጽአቱ

ዝግጁ ሆነን እንድንገኝ የሱስ ዛሬም ግብዣውን ያቀርብልናል፡፡

ምንም እንኳ "ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት" የሚለው ስማችን ዳግም ምጽአቱ ምን ያህል ለእኛ ወሳኝ እንደሆነ ቢመሰክርም ነገር ግን ይኸው ተጨባጭ እውነታ ከፊታችን መሆኑን እያስተዋልንና እየተጠባበቅን ምን ያህል በግል እንመላለሳለን? ዓመታት ባለፉ ቁጥር የሱስ በዐሥሩ ልጃገረዶች ምሳሌያዊ አነጋገር የሰጠውን ማስጠንቀቂያ ሳንስት መጠበቅ የምንችለው እንዴት ነው?

**ማክሰኞ** **ኅዳር 11**

## የየሱስ የሰማያዊው መቅደስ አገልግሎት

ሙሴ ለአምላካዊው ማደሪያ የሚሆን የመገናኛ ድንኳን ወይም ቤተ መቅደስ እንዲሠራ እግዚአብሔር አዞት እንደ ነበር በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ እናነባለን (ዘፀ. 25፡8)፡፡ በመገናኛ ድንኳኑ አገልግሎት አማካይነት የእስራኤል ሕዝቦች የደኅንነትን እቅድ ይማሩ ነበር፡፡ ይህ ከቦታ ቦታ እንዲንቀሳቀስ ሆኖ የተሠራ መገናኛ ድንኳን ቆየት ብሎ፣ በንጉሥ ሰለሞን ዘመን ውብ በሆነ ቤተ መቅደስ ተቀየረ (1ነገሥ. 5-8)፡፡ መገናኛ ድንኳኑም ሆነ ቤተ መቅደሱ የተሠሩት ከሰማያዊው መቅደስ ንድፍ አኳያ ነበር (ዘፀ. 25፡9፣ 40)፡፡

በሰማይ ዋንኛው የእግዚአብሔር መኖሪያ ቤተ መቅደስ መኖሩን በመላው የመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች ተጠቅሶ እንመለከታለን፡፡ ምድራዊው የቤተ መቅደስ አገልግሎት የደኅንነትን እቅድና የየሱስን ሰማያዊ ክኅነት አገልግሎት በጨረፍታ የምናይበት ነው፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዕብ. 8፡6፣ 9፡11-12፣ 23-28፣ 1ዮሐ. 1፡9-2፡2፡፡ ጥቅሶቹ ስለ የሱስ የክኅነት አገልግሎት ምን ያስተምሩናል?

________________________________________________________________

________________________________________________________________

ሰማያዊው ቤተ መቅደስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ካረገ አንስቶ ስለ ደኅንነታችን የካኅንነት አገልግሎቱን እየሰጠ የሚገኝበት ስፍራ ነው (ዕብ. 7፡25)፡፡ "እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበልና በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ፣ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ" (ዕብ. 4፡16)፡፡

በምድራዊው የመገናኛ ድንኳን ካኅኑ አገልግሎት የሚሰጥባቸው ሁለት ክፍሎች ነበሩ፡፡ የመጀመሪያው ዕለታዊውን አገልግሎት የሚሰጥበት ቀዳሚው ቅዱስ ክፍል ሲሆን ሁለተኛው በዓመት አንድ ጊዜ አገልግሎት የሚሰጥበት ቅድስተ ቅዱሳን ነበር፡፡ በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱስ በሁለት ምዕራፍ ስለ ተከፈሉት ስለ እነዚህ የየሱስ ሰማያዊ አገልግሎቶች ይገልጻል፡፡ የተቀደሰው የየሱስ ሰማያዊ አገልግሎት--ማማለድን፣

ይቅርታን፣ እርቅንና ወደ ቀድሞው ንጽሕና መመለስን አካቶአል፡፡ ንስሐ የሚገቡ ኃጢአተኞች በየሱስ አማላጅነት በቀላሉ ወደ አብ መቅረብ ይችላሉ (1ዮሐ. 2፡1)፡፡ የሱስ ከ1844 አንስቶ በሰማያዊው ቅድስተ ቅዱሳን እየሰጠ የሚገኘው አገልግሎት በዓመት አንድ ጊዜ በሥርየት ቀን ይደረግ ከነበረው የፍርድና ማንጻት ገጽታዎች ጋር የተሳሰረ ነው (ዘሌዋ. 16)፡፡ ደግሞም የቤተ መቅደሱ የማንጻት አገልግሎት በፈሰሰው የየሱስ ደም ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በክርስቶስ መልካም ተግባራት የኃጢአት መገኛ መወገድንና በአምላካዊው መንግሥት ሥር ከሚተዳደረው ዩኒቨርስ ጋር የሚፈጠረውን ፍጹም እርቅና ስምምነት ያሳየው በዚህ ዕለት የተፈጸመው የሥርየት ተግባር በመጨረሻ የሚመጣውን አስቀድሞ ያመላከተ ነበር፡፡ የዚህ የባለ ሁለት ገጽታ ኃይማኖታዊ አስተምህሮ አገልግሎት አጠቃላዩን የደኅንነት ዕቅድ በማስተዋሉ ረገድ በዓይነቱ ልዩ የሆነ የአድቬንቲስት አስተዋጾ ነው፡፡

ረቡዕ　　　　　　　　　　ኅዳር 12

## ሰንበት

ሌላው ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች የሚያምኑትና ጠብቀው የያዙት የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ሰባተኛ ቀን ሰንበት ነው፡፡ ሰንበት በአማኞች መሃል አንድነትና ኅብረት የሚያመጣ ቁልፍ ኃይማኖታዊ አስተምህሮ ነው፡፡ በክርስትናው ዓለም ከጥቂቶች በቀር በብቸኝነት ይህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ እንከተላለን፡፡

ሰንበት ከፍጥረት ጊዜ አንስቶ እግዚአብሔር ለሰብዓዊው ፍጡር የሰጠው ስጦታ ነው (ዘፍ. 2፡1-3)፡፡ በፍጥረት መጨረሻ በዕለቱ ገቢራዊ በሆኑ ሦስት መለኮታዊ ድርጊቶች ሰንበት ተቋቋመ፡ (1) እግዚአብሔር በሰንበት ዐረፈ (2) ቀኑን ባረከው (3) ቀደሰው፡፡ እነዚህ ሦስት ድርጊቶች ሰብዓዊው ዘር ሰማያዊውን ሐቅ በምድር እንዲለማመድና የእግዚአብሔርን የስድስት ቀን የፍጥረት ሥራ እውነት አጽንቶ እንዲይዝ በማስቻል ሰንበትን የተለየ አምላካዊ ስጦታ አድርገው አቋቋሙ፡፡ ሰንበት እግዚአብሔር ሕዝቦቹን በተለየ ሁናቴ የሚገናኝበት ዕለት ነው፡፡

በመቀጠል የቀረቡ ጥቅሶቹ ሰንበት ለሰብዓዊው ፍጡር ስላለው ትርጉም ምን ያስተምሩናል? ዘፀ. 20:8-11፣ ዘዳ. 5:12-15፣ ሕዝ. 20:12-20፡፡

____________________________________________________________

ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች የየሱስን ምሳሌ ለመከተል ባለን ጽኑ ምኞት (ሉቃ. 4፡16) ሰባተኛውን ቀን ሰንበት እናከብራለን፡፡ የሱስ በሰንበት ቀን የነበረው ተሳትፎ ዕለቱን የእረፍትና የአምልኮ አድርጎ ማጽደቁን ያመለክታል፡፡ ክርስቶስ ሰንበትን ከማክበርና በዕለቱ ደስ ከመሰኘት የሚመጡ አካላዊና መንፈሳዊ ፈውሶችን ወርድና ስፋት ለማስተማር ሲል አንዳንድ ታምራቶችን በሰንበት ቀን ያደርግ ነበር (ሉቃ. 13፡10-17)፡፡

የሱስ ሰንበትን አለመሻሩን ያስተዋሉ ሐዋርያትና የቀደሙ ክርስቲያኖችም በተመሳሳይ ዕለቱን ይጠብቁና አምልኮ ያደርጉ ነበር (ሐዋ. 13:14፣ 42፣ 44፣ 16:13፣ 17:2፣ 18:4).

ሌላው ውብ የሰንበት ገጽታ ከኃጢአት ነፃ የመሆናችን ምልክት መሆኑ ነው፡፡ ሰንበት እግዚአብሔር እስራኤላውያን ሕዝቦቹን ከግብፅ ባርነት ወደ ተስፋይቱ ከነዓን ዕረፍት ያስገባበት አዳኝነቱን የሚያስታውሱበት ዕለት ነው (ዘዳ. 5፡12-15)፡፡ ምንም እንኳ እስራኤላውያን በተደጋጋሚ ይፈጽሙ በነበረው አለመታዘዝና ጣኦት አምልኮ ጠንቅ ሙሉ ለሙሉ ወደ ተስፋው ምድር ባይገቡም እርሱ ግን ዛሬም "የሰንበት ዕረፍት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ገና ቀርቶለታል" (ዕብ. 4፡9) ሲል ይነግረናል፡፡ ወደዚያ ዕረፍት ለመግባት የሚመኙ ሁሉ የሱስ በሚሰጠው ደኅንነት በሚገኝ እምነት ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ለኃጢአታችን ይቅርታ ለማግኘትና የዘላለማዊ ሕይወት ባለቤት ለመሆን የምንመካው በሥራችን ሳይሆን በዚሁ በእርሱ መልካም ሥራ ብቻ ከመሆኑ አኳያ በሰንበት ማረፍ ይህን በክርስቶስ የማረፍ መንፈሳዊ ተምሳሌት ይዞአል (ዕብ. 4፡10፣ ማቴ. 11፡28-30)፡፡

*ክርስቶስ ለሕዝቡ የሚመኘውን አንድነትና ኅብረት በተጨባጭ እንዲለማመዱ ሰንበት የረዳዎት እንዴት ነው?*

## ሐሙስ ኅዳር 13

## ሞት እና ትንሳኤ

በፍጥረት ወቅት "እግዚአብሔር አምላክ ከምድር ዐፈር ወስዶ ሰውን አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ሆነ" (ዘፍ. 2፡7)፡፡ ይህ ሰው የተፈጠረበት ታሪክ እግዚአብሔር የሕይወት ምንጭ መሆኑን ያሳያል፡፡ ለመሆኑ ሕያውነት ወይም አለመሞት የዚህ ሕይወት ውስጠ ባህሪያዊ ገጽታ ነው? እግዚአብሔር ብቻ ሕያው መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (1ጢሞቴ. 6፡16)፡፡ ሕያውነት ሰብዓዊው ፍጡር ሲወለድ በስጦታ አልተሰጠውም፡፡ ሰብዓዊው ፍጡር ከእግዚአብሔር በተቃራኒ ሟች ነው፡፡ አምላካዊው ቃል "ለጥቂት ጊዜ ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንፋሎት ናችሁ" (ያዕ. 4፡14) በማለት ሰብዓዊውን ሕይወት ይገልጸዋል፡፡ ሰው በሚሞት ጊዜ ፍጹም ራሱን በማያውቅበት ጥልቅ የእንቅልፍ ሁናቴ ውስጥ ይወድቃል (መክ. 9:5-6፣ 10፣ መዝ. 146:4፣ መዝ. 115:17፣ ዮሐ. 11:11-15)፡፡

ምንም እንኳ ሰብዓዊው ፍጡር ሟች እና ለሞት የሚዳረግ ሆኖ ወደዚህ ምድር ቢመጣም፤ ነገር ግን የሱስ ክርስቶስን የሕያውነት ምንጭ አድርጎ የሚያስቀምጠው መጽሐፍ ቅዱስ በእርሱ የማዳን ኃይል ለሚያምኑ ሁሉ የሕያውነትን ተስፋ እንደሚሰጥ ይነግረናል፡፡ "የእግዚአብሔር ስጦታ ግን በጌታችን በክርስቶስ ኢየሱስ የዘላለም ሕይወት ነው" (ሮሜ 6፡23)፡፡ "አሁን ግን ሞትን ደምስሶ በወንጌል አማካይነት ሕይወትንና ኢመዋቲነትን ወደ ብርሃን ባወጣው በመድኃኒታችን በክርስቶስ ኢየሱስ

መምጣት ተገልጦአል" (2ጢሞቴ. 1፡10)፡፡ "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና" (ዮሐ. 3፡16)፡፡ ሰው ለዘላለም ሞቶ እንደማይቀር ይኸው አምላካዊ ተስፋ ያረጋግጥልናል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ቆሮ. 15፡51-54፣ 1ተሰ. 4፡13-18፡፡ ጥቅሶቹ ከሞት በኋላ ሕይወት ስለመኖሩና ሕያውነት ለሰብዓዊው ፍጡር ስለመሰጠቱ ምን ይነግሩናል?

---

---

እግዚአብሔር ሕያውነትን ለሕዝቡ የሚሰጠው ወዲያው እንደሞቱ ሳይሆን ነገር ግን የመጨረሻው የመለከት ድምፅ በሚሰማበት በዚያ የትንሣኤ ጠዋት መሆኑን ይነግረናል፡፡ አማኞች የሱስ ክርስቶስን የግል አዳኛቸው አድርገው እንደ ተቀበሉ የዘላለማዊውን ሕይወት ተስፋ ያገኙ ሲሆን ነገር ግን የሕያውነት ባለቤት የሚሆኑት በትንሣኤ ብቻ ነው፡፡ ሰዎች እንደ ሞቱ ነፍሳቸው ወደ ሰማይ ይሄዳል ስለሚባለው ጽንሰ ሃሳብ አዲስ ኪዳን የሚያውቀው አንዳች ነገር የለም፡፡ በአዲስ ኪዳንም ሆነ በብሉይ ኪዳን የማይገኘው ይህ የባዕድ አምልኮ አስተምህሮ ወደ ኋላ እስከ ጥንቱ የግሪክ ፍልስፍና የሚዘልቅ ታሪክ አለው፡፡

*ሞትን የምናስተውልበት መንገድ የዳግም ምጽአቱን ተስፋ አብልጠን እንድናደንቅ የሚረዳን እንዴት ነው? ይህ እምነታችን እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት አንድነታችንን ይበልጥ የሚያጠናክረው እንዴት ነው?*

## ዓርብ

## ኅዳር 14

ተጨማሪ ሀሳብ፡ Ellen G. White, "The Foundations, Pillars, and Landmarks," pp. 28-32, in Counsels to Writers and Editors. Read the article "Doctrines, Importance of," pp. 778, 779, in The Ellen G. White Encyclopedia.

እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስትነታችን ከአንዳንድ የክርስትና ድርጅቶች ጋር በአንድ የምንጋራቸው መሰረታዊ ኃይማኖታዊ አስተምህሮዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ መሃል አንዱና ዋንኛው በእኛ ምትክ በሞተውና ሥርየት ባመጣልን የሱስ ብቻ በማመን የሚገኝ ደኅንነት ወይም ጽድቅ በእምነት ነው፡፡ የጽድቃችን መሰረት የገዛ መልካም ሥራችን ሳይሆን ነገር ግን ለእኛ በማይገባ የጸጋ ስጦታው በእምነት በተቆጠረልን የክርስቶስ ጽድቅ ስለ መዳናችን እኛም ሆንን ሌሎች ክርስቲያኖች እናምናለን፡፡ "ለክርስቶስ የተገባው ለእኛ ይሆን ዘንድ፤ እነሆ በአመጻችን ምክንያት በእኛ ላይ ሊደርስ ይገባ የነበረው ሁሉ በእርሱ ላይ ደረሰ፡፡ ምንም ጥፋት ሳይኖርበት በእኛ ኃጢአት ተኮነነ፡፡ እኛም የማይገባንን በእርሱ ቅድስና ተዋጀን፡፡ የእርሱን ሕይወት እንቀበል ዘንድ ለእኛ ይገባ የነበረውን የሞት ሥቃይ ተቀበለ፡፡"—*The Desire of Ages, p. 25.* ከእነዚህ

እምነቶች የሚወጡ የአኗኗር ዘይቤና የሕይወት ስልቶቻችን በክርስትናው ዓለም ልዩ ያደርጉናል፡፡ ደግሞም እንዲህ መሆን ከሌለበት ታዲያ እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት መኖራችን ለምን አስፈለገ? ለየሱስ ያለን ፍቅርና የምናውጀው አስተምህሮ እርስ በርስ የሚያስተሳስረን ጠንካራ ገመድ ሊሆን ይገባል፡፡

## *የመወያያ ጥያቄዎች፡*

1. በክርስቶስ ይቅር ለመባላችንና ለመጽደቃችን የምንሰጠው አድናቆት ለክርስትና ኅብረታችን እንዲሁም ከማኅበረሰባችን ጋር ለሚኖረን ግንኙነት መሰረት የሚሆነው እንዴት ነው?

2. ኃይማኖታዊ አስተምህሮአችን ከቤተ ክርስቲያን አንድነት አኳያ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ያስቡ፡፡ በአንድ ላይ ከምንጋራቸው ኃይማኖታዊ አስተምህሮዎች ሌላ እነዚህን ከተለያዩ ብሔሮች፣ ኃይማኖቶች፣ የፖለቲካ አመለካከቶችና ባህላዊ ዳራዎች የመጡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወገኖች በአንድ ላይ ያሰባሰበው ምንድን ነው? ከተልዕኮና ከመልእክት አኳያ ሳይሆን ነገር ግን ለቤተ ክርስቲያን አንድነት ኃይማኖታዊ አስተምህሮ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ይህ ምን ይነግረናል?

3. “ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት” የተሰኘው ስማችን ሁለት ወሳኝ አስተምህሮዎችን ይጠቁማል--ሰባተኛ ቀን ሰንበት እና ዳግም ምጽአት፡፡ አንደኛው የስማችን ክፍል ፍጥረትን ሲያመላክት ሌላው መዋጀትን ያሳያል፡፡ ለመሆኑ እነዚህ ሁለት አስተምህሮዎች ባላቸው ዝምድና እንደ ሕዝብ ማንነታችንን በጥቂት ቃላት የሚገልጹት እንዴት ነው?

*ማጠቃለያ፡* ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች ከሌሎች የክርስትና ተቋማት ጋር የሚጋሯቸው ብዙ ኃይማኖታዊ አስተምህሮዎች እንዳሉ ሁሉ የሌሉም አሉ፡፡ እነዚህን አስተምህሮዎች እንደ ቤተ ክርስቲያን ከልዩ ማንነታችን አኳያ ጠቅለል አድርገን ስንወስድ በየሱስ የአንድነታችን መሰረት ናቸው፡፡

# ፱ኛ ትምህርት ኅዳር 15 - 21

## እጅግ የላቀው አሳማኝ ማስረጃ

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ዮሐ. 11:51-52፣ ኤፌ. 2:13-16፣ 2ቆሮ. 5:17-21፣ ኤፌ. 4:25-5:2፣ ሮሜ 14:1-6፣ 1:14፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ :-** “ይህን ያለው ከራሱ አልነበረም፤ ነገር ግን በዚያች ዓመት ሊቀ ካሕናት እንደ መሆኑ፣ ኢየሱስ ለአይሁድ ሕዝብ እንደሚሞት ትንቢት መናገሩ ነበር፡፡ ለዚያም ሕዝብ ብቻ ሳይሆን፣ የተበተኑትን የእግዚአብሔር ልጆች በአንድነት ለመሰብሰብ ነው” (ዮሐ. 11:51-52)፡፡

የሱስን አዳኝነት ማዕከል ባደረገና በመጨረሻው ዘመን ላይ አጽንኦት ሊሰጣቸው በሚገቡ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች የጋራ መልእክት አማካይነት አንድነት እንዴት መታየት እንደሚችል ባለፈው ሣምንት አጥንተናል፡፡ እግዚአብሔር የሰጠን መልእክት እና ለዓለም እንድናሰራጭ የቀረበልን ጥሪ የዛሬ ማንነታችንን ሰጥቶናል፡፡

በዚህ ሣምንት ከየዕለቱ የክርስቲያኖች ሕይወትና ከቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ አኳያ በገሃድ በሚታየው የቤተ ክርስቲያን አንድነት ላይ ትኩረት እናደርጋለን፡፡ የሱስ እንደ ተናገረው ቤተ ክርስቲያን አምላካዊውን የደኅንነትና የእርቅ መልእክት የማወጅ ሥራ ብቻ አትሠራም፡፡ የቤተ ክርስቲያን አንድነት ራሱ የዚያ እርቅ ወሳኝ መገለጫ ነው፡፡ በኃጢአትና በአመፃ በተከበበው በዚህ ዓለም፤ ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ አዳኝ ኃይል ሕያው ምስክር ሆና ትቆማለች፡፡ አንድነት በጎደለውና ኅብረት ባልጎበኘው የቤተ ክርስቲያን ምስክርነት--የመስቀሉ አዳኝ ኃይል በዚህ ዓለም ሊታይ አይችልም፡፡ “ከየሱስ ጋር የሚኖር ኅብረት አንዱ አማኝ ከሌላው ጋር ጠንካራ ትስስር እንዲፈጥር ያስችለዋል፡፡ ይህ አንድነት ኃጢአትን የማስወገድ ኃይል ላለው ለባለ ግርማውና በበጎነት ለተሞላው ክርስቶስ እጅግ አሳማኝ ማስረጃ ነው፡፡”—Ellen G. White Comments, The SDA Bible Commentary, vol. 5, p. 1148.

**እሁድ** **ኅዳር 16**

## በየሱስ መስቀል ስር

እንደ ሌሎች አያሌ መንፈሳዊ በረከቶች ሁሉ የቤተ ክርስቲያን አንድነትም እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚሰጠው ስጦታ ነው፡፡ አንድነት በሰብዓዊው ፍጡር ጥረት፣ መልካም ሥራና እቅድ የሚፈጠር ነገር አይደለም፡፡ በመሰረቱ የዚህ አንድነት ፈጣሪ የሱስ ክርስቶስ ሲሆን ይኸውም በሞቱና በትንሳዔው ነው፡፡ በጥምቀትና የኃጢአትን ይቅርታ በመቀበል ከሞቱና ከትንሳኤው ጋር በእምነት ገጣሚ ስንሆን፣ ከእምነት አጋሮቻችን ጋር የጋራ ጉዳይ ሲኖረን እና የሦስቱን መላእክት መልእክት ለዓለም ስናሰራጭ--ያን ጊዜ ከክርስቲያን ወገኖችም ሆነ ከእርሱ ጋር ሕብረት ይኖረናል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዮሐ. 11፡51-52፣ ኤፌ. 1፡7-10፡፡ እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስትነታችን በየሱስ ሕይወት የአንድነት መሰረት የሆነው የትኛው ክስተት ነው?

________________________________________________________

________________________________________________________

"(ቀያፋ) ይህን ያለው ከራሱ አልነበረም፤ ነገር ግን በዚያች ዓመት ሊቀ ካሕናት እንደ መሆኑ፣ ኢየሱስ ለአይሁድ ሕዝብ እንደሚሞት ትንቢት መናገሩ ነበር፡፡ ለዚያም ሕዝብ ብቻ ሳይሆን፣ የተበተኑትን የእግዚአብሔር ልጆች በአንድነት ለመሰብሰብ ነው" (ዮሐ. 11:51-52)፡፡ ምንም እንኳ ቀያፋ የሱስ እንዲሞት ሲፈርድበት ምን እያደረገ እንደነበር ባያውቅም እግዚአብሔር እርሱን ተጠቅሞ አስገራሚውን የየሱስ ሞት ፍቺ እንዲብራራ ማድረጉ እንግዳና ያልተለመደ አቀራረብ ነው፡፡ ካኅናቱም ቢሆኑ ቀያፋ የተናገረው ነገር ምን ያህል ጥልቀት እንደነበረው የሚያውቁት ነገር አልነበረም፡፡ ቀያፋ እንደሚያስበው ከፖለቲካ የዘለለ አባባል ከአንደበቱ አልወጣም፡፡ ዮሐንስ ስለ ሌሎች ምትክ እውን የሆነው የየሱስን ሞት አንድ ቀን "በአንድ ላይ ለሚሰበሰቡ" ታማኝ የእግዚአብሔር ልጆች ምን ማለት የመሆኑን መሰረታዊ እውነታ ለመግለጽ ይህን መልእክት እንደ ተጠቀመ ይታመናል፡፡

እንደ ሰባተኛ ቀን አደቬንቲስትነታችን የቱንም ዓይነት እምነት ወይም የምናውጀው መልእክት ቢኖረንም፤ የአንድነታችን መሰረት ስለ እኛ መሥዋእት የሆነውን የክርስቶስን ሞት መቀበላችን ነው፡፡

ከዚህ ባለፈ--በጥምቀት ይህን በክርስቶስ ያለንን ኅብረት እንለማመዳለን "ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ፤ ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁላችሁ ክርስቶስን ለብሳችሁታልና፡፡" (ገላ. 3፡26-27)፡፡ ሌላው

የእኛ የአድቬንቲስቶች በክርስቶስ ያለን እምነት ተምሳሌት እና በአንድ የሚያስተሳስረን ጥምቀት ነው፡፡ እኛ አንድ አባት ያለን እንደመሆኑ፤ ሁላችንም ወንዶችና ሴቶች ልጆቹ ነን፡፡ ደግሞም በሞቱና በትንሣኤው የተጠመቅን አንድ አዳኝ አለን (ሮሜ 6፡3-4)፡፡

*እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስትነታችን በባህል፣ በማኅበራዊ ሁኔታ፣ በብሔር ወይም በፖለቲካ አቋም ልንለያይ ብንችልም በየሱስ ያለን የጋራ እምነት ከእነዚህ ሁሉ ልዩነቶች ባሻገር መጓዝ የሚኖርበት ለምንድን ነው?*

**ሰኞ** **ኅዳር 17**

## የእርቅ አገልግሎት

ዓለማችን በስፋት ከምትታወቅባቸው ገጽታዎች መሃል--ቀውስ፣ ችግር፣ ጦርነት፣ ውዝግብ ዋንኞቹ ናቸው፡፡ እነዚህ ነገሮች በግል፣ በማኅበረሰብ ብሎም በብሔራዊ ደረጃ ሕይወታችንን ያቃውሳሉ፡፡ ችግሮቹ ብቅ ባሉ ቁጥር መላው ሕይወት ውዝግብ ውስጥ መግባቱ እሙን ነው፡፡ ሆኖም ይህ የአንድነት ጸርም ሆነ ቀውስ ለዘላለም እንደተንሰራፋ አይኖርም፡፡ እግዚአብሔር ዩኒቨርስ አቀፍ ኅብረት ለማምጣት በሚያስችለው ተልዕኮ ላይ ነው፡፡ ምንም እንኳ ኃጢአት መለያየት ቢያመጣም ነገር ግን ዘላለማዊው አምላካዊ የእርቅ ሂደት ሰላምና ፍጽምና ያመጣል፡፡

ጳውሎስ በኤፌ. 2፡13-16 መልእክቱ ክርስቶስ በአማኞች መካከል ሰላም ለማምጣት የሠራውን ሥራ የሚያሳዩ መርኅዎችን አስቀምጦአል፡ የሱስ በመስቀል ላይ ሞቱ አይሁዶችንም ሆነ አሕዛብን አንድ ሕዝብ በማድረግ ለያይቶአቸው የነበረውን የብሔርና የእምነት ግድግዳ አፈራርሶአል፡፡ ክርስቶስ ገና በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን በአይሁዶችና በአሕዛብ መካከል ይህን ካደረገ፤ ዛሬ የቤተ ክርስቲያናችንን ምዕመናን የከፋፈለውን የዘር፣ የብሔርና የባህል ግድግዳ ምን ያህል ይንድ?

እናም ከዚህ መነሻ ነጥብ ወደ ዓለም ሁሉ መድረስ እንችላለን፡፡

ጳውሎስ በ2ቆሮ. 5፡17-21 በክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር እርቅ የፈጠርን አዲስ ፍጥረቶች መሆናችንን ይናገራል፡፡ ታዲያ በዚህ ዓለም ያለን አገልግሎት ምንድን ነው? እንደ አንድ ኅብረት ያለው የቤተ ክርስቲያን አካል በማኅበረሰባችን ምን ልዩነቶች ማምጣት እንችላለን?

---

---

አማኞች እንደ እግዚአብሔር አዲስ ፍጥረትነታቸው ወሳኝ የሆነውን የእርቅ አገልግሎት ሦስት እጥፍ ተቀብለዋል፡፡ (1) ቤተ ክርስቲያናችን በአንድ ወቅት ከእግዚአብሔር የተነጠሉ--አሁን ግን በክርስቶስ መሥዋዕትነትና አዳኝ ጸጋ--በመንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት የፈጠሩ አማኞችን ይዛለች፡፡ እኛ የመጨረሻውን

ጊዜ መልእክት ለዓለም እንድናውጅ የተጠራን ትሩፋን ሕዝቦች ነን፡፡ አገልግሎታችን ዛሬም ከእግዚአብሔር የተነጠሉ ሕዝቦች ከእርሱ ጋር እርቅ ፈጥረው የተልዕኮአችን አካል እንዲሆኑ ነው፡፡ (2) ቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ እርስ በርሳቸው እርቅ የፈጠሩ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ናቸው፡፡ ከክርስቶስ ጋር አንድነት መፍጠር እርስ በርስ ስምሙ መሆን ማለት ነው፡፡ ይህ በእርግጥ ሞቅ ያለ አቀራረብ የያዘና ሀሳባዊ ሳይሆን በግልጽ የሚታይና የሚጨበጥ ሐቅ ሊሆን የተገባ ነው፡፡ አንዱ ከሌላው ጋር እርቅ ሲፈጥርና በወንድምና እህቶች መሃል ሰላምና ኅብር ሲሰፍን--ያኔ ለአዳኛችንና ቤዛችን የሱስ ክርስቶስ--ለዓለም የታወቅን ምስክሮቹ እንሆናለን፡፡ "'እርስ በርሳችሁ ብትዋደዱ፣ ሰዎች ሁሉ የእኔ ደቀ መዛሙርት እንደ ሆናችሁ በዚህ ያውቃሉ' " (ዮሐ. 13፡35)፡፡ (3) ቤተ ክርስቲያን አምላካዊው የማዳን እቅድ አውነተኛና ብርቱ መሆኑን በዚህ የእርቅ አገልግሎት አማካይነት ለመላው ዓለም ትነግራለች፡፡ በብርሃንና በጨለማ መሃል ያለው ታላቁ ውዝግብ እግዚአብሔርን እና የእርሱን ባህሪ ያማከለ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን በአንድነትና በእርቅ ዙሪያ በሠራች ቁጥር ዩኒቨርስ ዘላለማዊውን አምላካዊ ጥበብ በተግባር መመልከት ይችላል (ኤፌ. 3፡8-11)፡፡

**ማክሰኞ** **ኅዳር 18**

## በተግባር የሚገለጥ አንድነት

ኤለን ኋይን በ1902 ላይ የሚከተለውን ጽፋ ነበር፡ "እያንዳንዱ ክርስቲያን ክርስቶስ በዚህ ምድር የኖረው ዓይነት ህይወት እንዲኖር ተጠርቶአል፡፡ እርሱ ለእኛ ምሳሌ የሆነው በእንከን ዐልባ ንጽህናው ብቻ ሳይሆን በትዕግሥቱ፣ በተረጋጋና ልብ በሚማርክ ባህሪው ነው፡፡"—Ellen G. White, in Signs of the Times, July 16, 1902. እነዚህ ቃላት ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች ያቀረበውን ተማጽኖ የሚያስታውሱ ናቸው "በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረው ያ አስተሳሰብ በእናንተም ዘንድ ይሁን" (ፊልጵ. 2፡5)፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡና የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሱ፡ ኤፌ. 4፡25-5፡2፡፡ ለክርስቶስ ታማኝነታችንን እንድናሳይ ግብዣ የቀረበልን በተለይ በየትኞቹ የሕይወታችን ክፍል ነው? በአደባባይ ሕይወታችን ለየሱስ ወንጌል ምስክር መሆን የምንችለው እንዴት ነው?

---

---

ክርስቲያኖች የየሱስን ምሳሌ እንዲከተሉና የአምላካዊው ጸጋ ሕያው ምስክሮች እንዲሆኑ የሚጋብዙ አያሌ ጥቅሶች አሉ፡፡ በተመሳሳይ እኛም ስለ ሌሎች ደኅንነት

እንድንጥር ግብዣ ቀርቦልናል (ማቴ. 7፡12)፣ አንዱ የሌላውን ሸክም እንዲሸከም (ገላ. 6፡2)፣ በታይታ ከተሞላ የተካበደ ሕይወት በተቃራኒ ቀለል ባለውና ውስጣዊው መንፈሳዊነት ላይ ትኩረት ማድረግ (ማቴ. 16፡24-26፣ 1ጴጥ. 3፡3-4)፣ ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን መከተል ናቸው (1ቆሮ. 10፡31)፡፡

"ወዳጆች ሆይ፤ በዚህ ዓለም እንግዶችና መጻተኞች እንደ መሆናችሁ መጠን፣ ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት እንድትርቁ እለምናችኋለሁ፡፡ ምንም እንኳ ክፉ እንደምትሠሩ አድርገው ቢያሟችሁም ለፍርድ በሚመጣበት ጊዜ መልካሙን ሥራችሁን ዐይተው እግዚአብሔርን እንዲያከብሩ፣ በአሕዛብ መካከል በመልካም ሕይወት ኑሩ" (1ጴጥ. 2፡11-12)፡፡ እኛን በሚመለከቱ ላይ የክርስትና ባህሪ ሊያሳድር የሚችለውን ተጽእኖ ምን ያህል በተደጋጋሚ ዝቅ አድርገን እየተመለከትን ነው? በሚያውክና የሚያስቆጣ ሁናቴ ውስጥ የሚታይ ትዕግሥት፣ ውጥረትና ውዝግብ ባየለበት ድባብ የሚስተዋል ሥነ ሥርዓት መር ሕይወት፣ ለማይታገሥና ሻካራ ቃላት የሚቸር ገር ምላሽ--እነዚህ ሁሉ የበለጠ ለመሥራት እንድንሞክር የሚጋብዙን የየሱስ መንፈስ ምልክቶች ናቸው፡፡ እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስትነታችን ለመልካም ነገርና ለእግዚአብሔር ክብር ኃይል በመሆን አምላካዊውን ባህሪ በተሳሳተ መንገድ በሚተረጉመው ዓለም ላይ በአንድነት ምስክር እንሆናለን፡፡ አማኞች እንደ ክርስቶስ ወኪልነታቸው የሚታወቁት ለግብረገብ ታማኝ በመሆናው ብቻ ሳይሆን ስለ ሌሎች ደኅንነት በሚያሳዩት ተጨባጭ ፍላጎት ጭምር ነው፡፡ ኃይማኖታዊ ተሞክሮአችን ከልብ የመነጨ እስከሆነ ድረስ ለሌሎች ተገልጦ የሚታይና በዓለም ላይ ተጽእኖ የሚኖረው ይሆናል፡፡ የክርስቶስን ጸባይ ለዓለም የሚገልጽ በፍቅር የተሳሰረ የአማኞች ጥምረት በእርግጥ ብርቱ ኃይል መሆን ይችላል፡፡

*ምስክርነትዎ በሌሎች ዐይን ምን ይመስላል? አንድ ሰው የሱስን እንዲከተል ሊያደርገው የሚችል ምን ዓይነት ነገር በሕይወትዎ መመልከት ይችላል?*

## ረቡዕ ኅዳር 19

## አንድነት በብዝሐነት ውስጥ

ሐዋርያው ጳውሎስ በሮም የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን በጥልቅ ይከፋፍሉ ስለነበሩ ጉዳዮች በሮሜ. 14፡ እና 15 ይናገራል፡፡ አንዱ ለሌላው መቻቻልና ትዕግሥት እንዲያሳይ እንጂ በእነዚህ ጉዳዮች ሳቢያ ቤተ ክርስቲያንን እንዳይከፋፍሉ ሮማውያንን በመምከር ሀሳቡን አቅርቦአል፡፡ ከጳውሎስ ምክረ ሃሳብ ምን መማር እንችላለን?

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሮሜ 14፡1-6፡፡ በሮም በነበሩት የቤተ ክርስቲያን አባላት ላይ ከመፍረድ ውጪ እርስ በርሳቸው ኅብረት እንዳይኖራቸው መንስዔ የሆኑ ምን ዓይነት ከኀሊና ጋር ቁርኝት የነበራቸው ጉዳዮች ነበሩ?

---

---

እነዚህ ጉዳዮች ከአይሁድ ሜዳዊ ሥርዓት ጋር የመበረዝ ሁኔታ ሳይገጥማቸው እንዳልቀረ ይታመናል፡፡ ጳውሎስ እንደሚናገረው እነዚህ "አከራካሪ የሆኑ ጉዳዮች" (ሮሜ 14፡1) ደኅንነት የሚገኝባቸው ሳይሆኑ ለግለሰቡ የተተዉ የግል አመለካከቶችና ውሳኔዎች ናቸው (ሮሜ 14፡1)፡፡

በመጀመሪያ እነዚህ አከራካሪ ጉዳዮች የተነሱት ከምግብ ጋር በተያያዘ ነበር፡፡ በዘሌዋውያን ምዕራፍ 11 የቀረበው የእንስሳት ለምግብነት መዋል በዚህ በጳውሎስ መልእክት ግን ችግር ሆኖ አንመለከተውም፡፡ በጳውሎስ ዘመን የቀደሙት ክርስቲያኖች የዐሣማ ሥጋን ጨምሮ ሌሎች ንጹህ ያልሆኑ ምግቦችን መመገብ ስለ መጀመራቸው የምናገኘው መረጃ ባይኖርም ነገር ግን ጴጥሮስ እነዚህን ምግቦች አለመመገቡን እናውቃለን (ሐዋ. 10፡14)፡፡ ደግሞም በእምነቱ ያልጠነከረው አትክልት ብቻ መብላቱ (ሮሜ 14፡2) እና ውዝግቡ የአልኮል መጠጥንም ማካተቱ (ሮሜ 14፡17፣ 21) የጉዳዩ ትኩረት ከሜዳዊ ሥርዓቶች ጋር የተፈጠረውን መበረዝ ለማሳየት እንደሆነ ማስተዋል እንችላለን፡፡ ንጹህ ያልሆነ በሚል በሮሜ 14፡4 የቀረቡት ቃላት ተጨማሪ ማስረጃዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ጥንታዊ የግሪክ ቃላት ትርጓሜ በብሉይ ኪዳን ጥቅም ላይ የዋሉት ንጹህ ያልሆኑ እንስሳትን ለመጥቀስ እንጂ በዘሌዋውያን 11 የቀረቡትን ያልተፈቀዱ እንስሳት ለማመልከት አይደለም፡፡ የሮም ማኅረሰብ አካል የነበሩ አንዳንድ ሰዎች በጉባዔ ኅብረት የሚመጡ ምግቦችን አይመገቡም ነበር፡፡ ለዚህ መንስኤው ምግቡ በአግባቡ የተዘጋጀ ወይም ለጣኦታት ያልቀረበ ላለመሆኑ የሚያሳምናቸው ነገር ባለመኖሩ ነው፡፡

ጉዳዩ በተመሳሳይ ወደ ሣምንቱ ቀናትም ያመራል፡፡ ጳውሎስ ሰንበትን በመደበኛ መጠበቁን የምናውቅ እንደመሆኑ (ሐዋ. 13:14፣ 16:13፣ 17:2) ይህ አባባል የሣምንቱን ሰባተኛ ቀን አይጨምርም፡፡ ይልቁም ከተለያዩ የአይሁዳውያን የድግስ ወይም የጾም ቀናት ጋር ቁርኝት አለው፡፡ እነዚህን ሥርዓቶች በቅን ልቦና እና በታማኝነት የያዙ ሰዎች እንደ መዳኛ መንገድ እስካላሰቧቸው ድረስ እነርሱን በትዕግሥትና በመቻቻል ማለፍ የተገባ መሆኑን ለማመላከት ጳውሎስ መልእክቶቹን አስፍሮአል፡፡ አማኞች በተለይ ከመዳናችን ጋር ግንኙነት በሌላቸው ነጥቦች ሳንስማማ ስንቀር በክርስቲያኖች መካከል

የሚኖር ኅብረት ራሱን በትዕግሥት፣ በገርነትና በርኅራኄ ሊገልጥ የተገባ ነው፡፡

እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት የምናምናቸውንና በተግባር የምንገልጣቸውን አስተምህሮዎች አድቬንቲስት ነን የሚሉ ሁሉ ሊያምኑና አጥብቀው ሊይዙ አይገባም? በክፍል ውስጥ ተወያዩበት፡፡

ሐሙስ

ኅዳር 20

## አንድነት በተልዕኮ ውስጥ

በሉቃ. 22፡24 በጌታ ራት ወቅት የተስተዋለውን የደቀ መዛሙርቱን ስሜት ከጴንጤቆስጤ ተሞክሮአቸው ትንሽ ቀደም ብሎ ከነበረው ሁኔታ ጋር ለማስተያየት ይሞክሩ፡፡ እንዲህ ያለው ልዩነት በሕይወታቸው እንዲመጣ መንስዔው ምን ነበር?

____________________________________________

____________________________________________

አማኞች "በአንድ ልብ" እንደ ነበሩ በሐዋ. 1፡14 እና 2፡46 ተጠቅሶአል፡፡ ይህ ገቢራዊ መሆን የቻለው በአንድነትና በአንድ ቦታ ሆነው የሱስ አጽናኙን እንደሚልክላቸው የሰጣቸውን ተስፋ ፍጻሜ በመሻት በጸሎት በመትጋታቸው ነው፡፡

እነዚህ ወገኖች በአንድ ላይ ተሰባስበው የተሰጣቸውን ተስፋ እየተጠባበቁ በነበረበት ወቅት አንዱ በሌላው ላይ ሒስ የሚሰነዝርበት ዕድል ነበር፡፡ እንደውም አንዳንዶች የጴጥሮስን ክህደትና (ዮሐ. 18፡15-18፣ 25-27) የቶማስን ጥርጣሬ (ዮሐ. 20፡25) እያነሱ መጠቋቆሚያ ሊያደርጓቸው በቻሉ ነበር፡፡ በየሱስ ክርስቶስ መንግሥት ከፍ ያለውን ሥልጣንና ክብር ለማግኘት ዮሐንስ እና ያዕቆብ ያቀረቡትን ጥያቄ (ማር. 10፡ 35-41) ወይም የማቴዎስን የቀድሞ ቀረጥ ሰብሳቢነት እያስታወሱ አንዱ ሌላውን በተቸ ነበር (ማቴ. 9፡9)፡፡

ሆኖም ግን "እነዚህ የመዘጋጃ ቀናት ልቦቻቸውን በጥልቅ የሚፈልጉባቸው ጊዜያቶች ነበሩ፡፡ መንፈስ ቅዱስ አጥብቆ እንደሚያሻቸው በጥልቅ የተገነዘቡት ደቀ መዛሙርት ነፍሳትን ለማዳን ሥራቸው ገጣሚ የሚሆን መንፈስ እንዲፈስላቸው ወደ ጌታ አለቀሱ፡ ፡ ልመናቸው እንደው ጌታ እነርሱን እንዲባርክ ብቻ አልነበረም፡፡ ይልቁንም የነፍሳት መዳን ጫና ከፉኛ ይሰማቸው ነበር፡፡ ወንጌል ለዓለም መድረስ እንዳለበት አጥብቆ የተሰማቸው እነዚህ ወገኖች ክርስቶስ እንደሚልክላቸው ቃል የገባላቸው ኃይል እንደሚገባቸው ሆነው ተቀበሉ፡፡"—Ellen G. White, The Acts of the Apostles, p. 37.

በደቀመዛሙርቱ መካከል የነበረው ኅብረትና ጽኑ ጸሎት በጣም አስፈላጊ ለሆነው ለዚህ የጴንጤቆስጤ ተሞክሮ አዘጋጃቸው፡፡ ወደ እግዚአብሔር በቀረቡና የግል ልዩነቶቻቸውን ባስወገዱ ቁጥር የየሱስን ትንሳኤ ለመመስከር ፍርሀት ዐልባና ደፋር አድርጎ መንፈስ ቅዱስ አዘጋጃቸው፡፡ የቀድሞ ጉድለቶቻቸውና ውድቀቶቻቸው ይቅር መባላቸውን ያወቁት ደቀ መዛሙርት ሁኔታው ወደ ፊት የሚቀጥሉበትን ወኔ ሰጣቸው፡፡ የሱስ በሕይወታቸው ያደረገላቸውን ነገር ጠንቅቀው ይገነዘቡ ነበር፡፡ የመዳን ተስፋ ያለው በእርሱ ውስጥ መሆኑን ያውቁ የነበሩት እነዚህ አማኞች የክርስቶስን ባህሪ ገልጦ የማሳየት ጽኑ ምኞት ነበራቸው፡፡ ከዚህ አኳያ ጌታ በእነርሱ ውስጥ ብርቱ ነገሮችን ቢያደርግ ብዙም ላይደንቅ ይችላል፡፡ ይህ በእርግጥ ለእኛ ታላቅ ትምህርት ነው፡፡

*በሰዎች ሕይወት ውስጥ ስህተት ማግኘት ሁሌም ቀላል ነው፡፡ በውሁዷ ቤተ ክርስቲያን ለግዙፉ አምላካዊ ተልዕኮ ከመሥራት አኳያ የሌሎችን ስህተት ወደ ጎን ማለትን መማር የምንችለው እንዴት ነው?*

## ዓርብ ኅዳር 21

*ተጨማሪ ሀሳብ*፡ *Ellen G. White, "Unity in Diversity," pp. 98-103, in Evangelism.*

ምንም እንኳ በአማኞች መካከል ልዩነቶች ቢኖሩም የቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ራሷን ከክርስቶስ ጋር በማዋሃድ እንዴት ለዓለም ብርቱ ምስክር ለመሆን እንደበቃች--ይህ በትምህርተ ጥቅስ የቀረበው መልእክት እንድናስተውል ይረዳናል፡፡ "መንፈስ ቅዱስ ውሳኔ በመስጠቱ ሂደት የቀደመችውን ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደመራት አምላካዊው ቃል ይገልጽልናል፡፡ ይህ ደግሞ የቀረበ ትስስር ባላቸው ሦስት መንገዶች ገቢራዊ ለመሆን በቅቶአል፡ (1) ራእዮች፡ (ለምሳሌ፡ ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት በመንፈስ ቅዱስ ተነገረው፣ ቆርኔሌዎስ፣ አናንያስ፣ ፊልጶስ፣ እንዲሁም /ምናልባት/ የተጣለው ዕጣ)፣ (2) አምላካዊው ቃል፡ (3)፡ የጋራ መግባባት (መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ኅብረት መካከል ይሠራ ነበር)፡፡ አማኞች የባህል፣ ኃይማኖታዊ አስተምህሮና ሌሎች ልዩነቶች ሲገጥሟቸው መንፈስ ቅዱስ በጋራ የሚያግባቧቸውን ነጥቦች ተጠቅሞ ወደ ውሳኔ እንዲመጡ ይረዳቸው ነበር፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ የመሪዎቹን ብቻ ሳይሆን የክርስቲያን ማኅበረሰቡንም ንቁ ሚና እንመለከታለን፡፡ ነገሮችን ለመለየትና ለማስተዋል ጸሎት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነም እናያለን፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት--መላው ማኅበረሰብ በአምላካዊው ቃል ላይ በነበረው መረዳት፣

በማኅበረሰቡ ተሞክሮ እና ያሹዋቸው በነበሩ ነገሮች እንዲሁም አገልጋዮች ይሰጡ በነበረው አገልግሎት መታየት ችሎ ነበር፡፡ አምላካዊው ቃል፣ ጸሎትና ተሞክሮ የሥነ መለኮታዊው አስተምህሮ አላባ የሆኑባቸው አያሌ በመንፈስ ቅዱስ የተመሩ የውሳኔ ሂደቶች ገቢራዊ ለመሆን በቅተው ነበር፡፡””—Denis Fortin, “The Holy Spirit and the Church,” in Ángel Manuel Rodríguez, ed., Message, Mission, and Unity of the Church, pp. 321, 322.

## የመወያያ ጥያቄዎች፥

1. በረቡዕ ትምህርት መጨረሻ ላይ ለቀረበው ጥያቄ በተሰጡት መልሶች ላይ ተወያዩ፡፡

2. በየሱስ ሞትና ትንሣኤ ከሚያምኑ ሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ያለን ተዛምዶ ምን ይመስላል?

*ማጠቃለያ*፡ ለቤተ ክርስቲያን ኅብረት መኖር እጅግ አሳማኙ ማስረጃ የሱስ እንደ ወደደን እኛም እርስ በርሳችን መዋደዳችን ነው፡፡ የኃጢአት ይቅርታ ማግኘታችንና እንደ አድቬንቲስት የምንጋራው መዳናችን የኅብረታችን ምርጥ ማስተሳሰሪያዎች ናቸው፡፡ በክርስቶስ--አንድነታችንን ለዓለም ማሳየትና ሁላችንም በአንድ የምንጋራውን እምነት መመስከር እንችላለን፡፡ ከዚህ ውጪ እንድናደርግ አልተጠራንም፡፡

# 10ኛ ትምህርት ከኅዳር 22 - 28

## ሕብረት እና የፈረሱ ግንኙነቶች

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ 2ጢሞቴ. 4:11 ፊልሞ. 1–25፣ 2ቆሮ. 10:12–15፣ ሮሜ 5:8–11፣ ኤፌ. 4:26፣ ማቴ. 18:15–17፡፡

**<u>መታሰቢያ ጥቅስ :-</u>** "የእግዚአብሔር ጠላቶች ሳለን በልጁ ሞት ከእርሱ ጋር ከታረቅን፣ ዕርቅን ካገኘን በኋላ፣ በሕይወቱማ መዳናችን እንዴት የላቀ አይሆንም!" (ሮሜ 5፡10)፡፡

ቀደም ብለን እንደ ተመለከትነው ከጴንጤቆስጤ በኋላም እንኳ በአማኞች መካከል የነበረው ግንኙነት አልፎ አልፎ በውጥረት የተሞላ ነበር፡፡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አባላት ከእነዚህ ፈታኝ ጉዳዮች ጋር መጋፈጣቸውን የአዲስ ኪዳን ተደጋጋሚ ምሳሌዎች ይጠቁማሉ፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን መርኅዎች በመጠቀም ውዝግቦችን ለመፍታት ስንሞክርና ከክርስቶስ ጋር ያለንን አንድነት ስንጠብቅ አዎንታዊ ውጤቶች ተገልጠው መውጣት ይጀምራሉ፡፡ እነዚህ መርኅዎች ለዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን እጅግ የከበረ ዋጋ አላቸው፡፡

በዚህ ሣምንት ጥናታችን ወደ ቀደመ ንጽህናቸው የተመለሱ ግንኙነቶች ላይ ትኩረት እናደርጋለን፡፡ ደግሞም ሰብዓዊ ግንኙነቶቻችን ከክርስቶስ ጋር ያለን አንድነት ላይ እንዴት ተጽእኖ እንደሚያሳድር እንመለከታለን፡፡ መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር እንዲሁም እርስ በርስ የማቀራረብ ሥራ ይሠራል፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር እና እርስ በርስ ባለን ግንኙነት እንቅፋት የሆኑ የጥል ግድግዳዎችን ያፈራርሳል፡፡ በአጭሩ የወንጌል ኃይል ግዙፍ ማሳያ--ቤተ ክርስቲያን የምትለው ሳይሆን እየኖረችበት ያለው መንገድ ነው፡፡

"'እርስ በርሳችሁ ብትዋደዱ ሰዎች ሁሉ የእኔ ደቀ መዛሙርት እንደ ሆናችሁ በዚህ ያውቃሉ' " (ዮሐ. 13:35)፡፡ ያለዚህ ፍቅር ስለ ቤተ ክርስቲያን አንድነት የምናወራው ሁሉ ከንቱ ይሆናል፡፡

**እሁድ** **ኅዳር 23**

## ወደ ቀድሞ ንጽሕናው የተመለሰ ወዳጅነት

ጳውሎስ እና በርናባስ አብረው ለየሱስ የመመሥከር ሥራ ይሠሩ ነበር፡፡ ሆኖም ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ አብሮአቸው ይሂድ ወይም አይሂድ በሚለው ሃሳብ በመካከላቸው የከረረ አለመግባባት ተፈጠረ (ሐዋ. 15፡36-39)፡፡ ወንጌልን ከመስበክ ብርቱ አደጋዎችና ተግዳሮቶች አኳያ በአንድ ወቅት ዮሐንስ ጳውሎስንና በርናባስን ትቶ ወደ መኖሪያው የሩሳሌም ተመልሶ ነበር (ሐዋ. 13፡13)፡፡

"ይህ ውሳኔ ጳውሎስ ማርቆስን በተቃራኒ እንደውም ያለ ምኅረት እንዲመለከተው መንስዔ ሆነ፡፡ በሌላ በኩል በርናባስ ማርቆስ የነበረውን የልምድ ማነስና በአገልግሎት አለመብሰል በመመልከት ወደ ይቅርታው አመዘነ፡፡ ለክርስቶስ ጠቃሚ አገልጋይ የሚያደርገውን ብቃት በማርቆስ ውስጥ የተመለከተው በርናባስ አገልግሎቱን እንዳያቆም ውስጡን ሸብር ገባው፡፡""—Ellen G. White, The Acts of the Apostles, p. 170.

ምንም እንኳ እግዚአብሔር እነዚህን ሁሉ ሰዎች ቢጠቀምም በመካከላቸው የነበሩ አለመግባባቶች መፍትሔ ይሹ ነበር፡፡ ጸጋን የሰበከ ሐዋርያ ቅር ላሰኘው ለጋ ሰባኪ ተጨማሪ ጸጋ መቸር አስፈልጎት ነበር፡፡ የይቅርታው ሐዋርያ ይቅር ማለት አስፈልጎት ነበር፡፡ ዮሐንስ ማርቆስ በበርናባስ ጽኑ መካሪነት እየጎለበተ በመሄዱ (ሐዋ. 15፡39) ውሎ አድሮ ጳውሎስ በተመለከተው ለውጥ ልቡ ተነካ፡፡

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስና በቆለስያስ ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን የጻፈው ደብዳቤ ከዮሐንስ ማርቆስ ጋር የነበረውን ግንኙነት ማደሱንና በዚህ አዲስ ሰባኪ ላይ የነበረውን መተማመን የገለጠው እንዴት ነበር? ቆለ. 4:10-11፣ 2ጢሞቴ. 4:11፡፡

---

---

ምንም እንኳ ጳውሎስ ከዮሐንስ ማርቆስ ጋር የፈጠረው የእርቅ ዝርዝር ሃሳብ በግልጽ ባይሰፍርም መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሰፈረው ሃሳብ ግን ግልጽ ነው፡፡ ዮሐንስ ማርቆስ ለሐዋርያው ከታመኑ ባልደረቦች አንዱ ለመሆን በቃ፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ-- ዮሐንስ ማርቆስ ወደ ቆለስያስ ቤተ ክርስቲያን ሲመጣ እንዲቀበሉት ስለ እርሱ ከፍ ያለ አስተያየት ሰጥቶአል፡፡ ጳውሎስ "በአገልግሎቴ ስለሚረዳኝ" (2ጢሞቴ. 4፡11) በማለት በሕይወቱ መጨረሻ አካባቢ ጢሞቴዎስ ማርቆስን ወደ ሮም ይዞ እንዲመጣ አበክሮ ሲያደፋፍረው እናያለን፡፡ የጳውሎስ አገልግሎት ይቅር ባለው ወጣቱ ሰባኪ ዳብሮ ነበር፡፡ ቀደም ብሎ በሁለቱ መካከል የነበረው ጉዳይ ምንም ይሁን ምን፤ ግንኙነታቸው ወደ ቀድሞ ንጽህናው ተመልሶ የወንጌልን ሥራ አብረው ለመሥራት ቻሉ፡፡

*የጎዱንን ወይም ቅር ያሰኙንን ይቅር ማለት መማር የምንችለው እንዴት ነው? ብዙውን ጊዜ ይቅርታ የቀድሞውን ንጽና ፍጹም አድርጎ የማይመልሰው ለምንድን ነው? ይህ ሁሌም ላያስፈልግ የሚችለው ለምን ይሆን?*

ሰኞ

ኅዳር 24

## ከባርነት ወደ ልጅነት

ጳውሎስ በሮም ታስሮ በነበረበት ወቅት ከቆላስያስ ወደ ሮም ይኮበልል ከነበረ አናሲሞስ ከተባለ ባርያ ጋር ተገናኝቶ ነበር፡፡ ጳውሎስ የአናሲሞስ አሳዳሪ የነበረውን ጌታ በግል ያውቀው እንደ ነበር ለመገንዘብ ቻለ፡፡ ጳውሎስ ወደ ፊልሞና የጻፈው መልእክት ይህ ወዳጁ ከኮብላይ ባሪያው ጋር የነበረውን ግንኙነት ወደ ቀድሞው ሁኔታ እንዲመልስ የቀረበ የግል ተማጽኖ ነበር፡፡

ሰብዓዊ ግንኙነቶች ለጳውሎስ ትርጉም ነበራቸው፡፡ ነፋስ የገባቸው ግንኙነቶች ለመንፈሳዊው ዕድገትና ለቤተ ክርስቲያን አንድነት ጎጂ መሆኑን ሐዋርያው ያውቅ ነበር፡፡ ፊልሞና በቆላስያስ የቤተ ክርስቲያን መሪ ስለ ነበር በአናሲሞስ ላይ ቂም የሚይዝ ከሆነ በክርስትና ምስክርነቱ እና ገና ክርስቲያን ባልሆነው ማኅበረሰብ በሚኖረው አገልግሎት ላይ ጥላ ማጥላቱ አይቀሬ ነበር፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ፊልሞ. 1-25፡፡ ወደ ቀድሞው ሰላማዊ ሁኔታ ስለ ተመለሰ ግንኙነት ከዚህ ምን ዓይነት ጠቃሚ መርኅዎች እናገኛለን? እዚህ ላይ ቁልፉ ቃል መርኅዎች መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

________________________________________

________________________________________

በቅድሚያ ጳውሎስ ስለ አስከፊው የባርነት ቀንበር አንዳች ነገር ሳይል መቅረቱ ሊያስገርም ቢችልም ነገር ግን ሐዋርያው የተከተለው ሥልት ከዚህ በላቀ ውጤታማ ነበር፡፡ ሁሉንም ዓይነት የመደብ ልዩነቶች በማፈራረሱ ረገድ ወንጌል ተስማሚና የሰጠ ነው (ገላ. 3፡28፣ ቆለ. 3፡10-11)፡፡ አሁን ሐዋርያው አናሲሞስን መልሶ ወደ ፊልሞና የላከው እንደ ባሪያ ሳይሆን በየሱስ እንደ ልጁና በጌታ እንደ “ተወዳጅ ወንድም” (ቁ. 15) ነበር፡፡

የኮብላይ ባሮች የወደፊት ዕጣ ደብዛዛ መሆኑን ጳውሎስ ያውቅ ነበር፡፡ በማንኛውም ጊዜ ሊያዙ ከመቻላቸው በላይ በሰቆቃና በድኅነት የተሞላ ሕይወት እንዲገፉ የተፈረደባቸው ነበሩ፡፡ አሁን ግን አናሲሞስ በክርስቶስ የፊልሞን ወንድምና ፈቃደኛ ሠራተኛ እንደመሆኑ የተሻለ ተስፋ አለው፡፡ ምግቡ፣ መኖሪያውና ሥራው በፊልሞና አማካይነት አስተማማኝ ይደረግለታል፡፡ ተበላሽቶ የነበረው ግንኙነት ወደ ትክክለኛው

ስፍራ እንዲመለስ መደረጉ በአናሲሞስ ሕይወት ላይ አስደናቂ ልዩነት ምጣቱ እሙን ነው፡፡ አናሲሞስ “ታማኙና ተወዳጁ ወንድም” በሚል የሚጠራ የጳውሎስ የወንጌል አጋር ሠራተኛ ለመሆን በቃ (ቆላ. 4፡9)፡፡ በሁለቱ የየሱስ አማኞች መካከል እርቅ እንዲወርድ እጅግ የጋለ ቅንአትና ልበ ቀናነት የነበረው ጳውሎስ በገንዘብ የሚካካስ ነገር እንኳ ቢኖር ማንኛውንም መጠን ከገዛ ኪሱ ለመክፈል ዝግጁ ነበር፡፡

*በሰብዓዊ ግንኙነትዎ ሊከሰቱ ከሚችሉ ማናቸውም ዓይነት ጭንቀት፣ ውጥረት ብሎም ስብራት ከላይ ከተመለከቱት የወንጌል መርኅዎች ምን ዓይነት ጠቃሚ ነጥቦች መውሰድ ይችላሉ? እነዚህ መርኅዎች በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንዎ ሊከሰቱ የሚችሉ መሰነጣጠቆችን የሚገቱት እንዴት ነው?*

## ማክሰኞ ኅዳር 25

## መንፈሳዊ ስጦታዎች ለአንድነት

የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የነበሩባትን ጥልቅ ችግሮች ቀደም ባለው ትምህርታችን ተመልክተናል፡፡ ለቤተ ክርስቲያን ወሳኝ የሆኑትን እንደ ፈውስና ወደ ቀደመው ሰላም መመለስ--የሚከተሉት ጥቅሶች ምን ዓይነት መርኅ ይሰጡናል? 1ቆሮ. 3:5–11፣ 12:1–11፣ 2ቆሮ. 10:12–15፡፡

________________________________________

________________________________________

ሐዋርያው በእነዚህ ምንባቦች ለቤተ ክርስቲያን አንድነት ወሳኝ የሆኑ መርኅዎችን አብራርቶአል፡፡ ምንም እንኳ እያንዳንዱ ሰው ከሌሎች ጋር ተጣምሮ የእግዚአብሔርን መንግሥት በአንድነት ቢገነባም፤ የሱስ ለቤተ ክርስቲያን የተለያዩ አገልግሎቶች ልዩ ልዩ ሠራተኞችን መመደቡን በመልእክቱ ያሳያል (1ቆሮ. 3፡9)፡፡

እግዚአብሔር እንድንፎካከር ሳይሆን እንድንተባበር ጥሪ ያቀርብልናል፡፡ እያንዳንዱ አማኝ ለክርስቶስ አካል ብሎም ለማኅበረሰቡ ተባብሮ አገልግሎት የሚሰጥበት ጸጋ ከእግዚአብሔር ተሰጥቶታል (1ቆሮ. 12፡11)፡፡ የላቁ ወይም ያነሱ የሚባሉ ስጦታዎች የሉም፡፡ በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁሉም አስፈላጊ ናቸው (1ቆሮ. 12፡18-23)፡ ፡ በእግዚብሔር የተሰጡን ስጦታዎች ለራስ ወዳዱ ስብዕና ታይታ ሳይሆን ወንጌልን እንድናሰራጭ በመንፈስ ቅዱስ የተበረከቱልን ስጦታዎች ናቸው፡፡

ተስፋ ወደ ማስቆረጥ ወይም ወደ ግብዝነት የሚመራው ያንዱን ስጦታ ከሌላው ጋር ማወዳደር--ጥበብ የጎደለው አካሄድ ነው፡፡ ሌሎች እጅግ ከእኛ “የላቁ” ሆኖ የሚሰማንና የምናስብ ከሆነ በየትኛውም አገልግሎት ላይ ብንገኝም ራሳችንን ከእነርሱ ጋር እያወዳደርን በቀላሉ ተስፋ ወደ መቁረጥ ልናመራ እንችላለን፡፡ በሌላ በኩል እኛ

ለክርስቶስ የምንሠራውን ሥራ ከሌሎች በላቀ ውጤታማ አድርገን የምንመለከት ከሆነ በኩራት ስሜት መኮፈስ ይመጣል፡፡ እነዚህ ሁለቱም አመለካከቶች የእርስ በርስ ግንኙነታችንንና ለክርስቶስ የሚኖረንን ውጤታማነት ያሽመደምዳሉ፡፡ ክርስቶስ በሰጠን ተጽእኖ ዙሪያ ስንሠራ በምስክርነታችን ደስታና ፍስሐ እናገኛለን፡፡ አገልግሎታችን የሌሎች አባላትን ጥረት የተሟላ በማድረግ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አንድ እርምጃ ወደ ፊት እንድትራመድ ያስችላታል፡፡

*በአገልግሎት ስጦታው ቅናት ስላሳደረቦት የሆነ ሰው ማሰብ ይችላሉ? በተመሳሳይ እርስዎ ያሎትን ስጦታዎች ከሌሎች ጋር ሲያነጻጽሩ ምን ያህል የኩራት ስሜት ተሰምቶታል? ዋናው ነጥብ ጳውሎስን አሳስበው የነበሩ ነገሮች በኃጢአት በወደቀው ዓለም ውስጥ ሁሌም የሚኖሩ መሆናቸው ነው፡፡ በየትኛውም ወገን ልንወድቅ ብንችል፤ ከክርስቶስ ጋር ያለንን ግንኙነት ጠብቀን ለመጓዝ ወሳኝ የሆኑትን ራስ ወዳድ ያልሆኑ አመለካከቶች መማር የምንችለው እንዴት ነው?*

**ረቡዕ** **ኅዳር 26**

## ይቅር ማለት

ለመሆኑ ይቅርታ ማድረግ ወይም ይቅር ማለት ምንድን ነው? ይቅር ማለት አስከፊ በደል የፈጸመብንን ሰው ድርጊት ትክክለኛነት ማሳየት ይችላል? ይቅርታዬ በበደል ፈጻሚው ንስሐ ላይ የተመሰረተ ነው? ያዘንኩበት ሰው የእኔ ይቅርታ የማይገባው ቢሆንስ?

የሚከተሉት ጥቅሶች መጽሐፍ ቅዱሳዊውን የይቅርታ ተፈጥሮ ማስተዋል እንድንችል እንዴት ይረዱናል? ሮሜ 5:8–11፣ ሉቃ. 23:31–34፣ 2ቆሮ. 5:20-21፣ ኤፌ. 4:26፡፡

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ክርስቶስ እኛን ከራሱ ጋር ለማስታረቅ ተነሳሽነቱን ወሰደ፡፡ "የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ የሚመራ" ነው (ሮሜ 2፡4)፡፡ እኛ ኃጢአተኞች ሆነን ሳለ በክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቅን፡፡ የክርስቶስ የመስቀል ላይ ሞት እንጂ ንስሐ መግባታችንና ኃጢአታችንን መናዘዛችን እርቅ አይፈጥርም፡፡ የእኛ ድርሻ የተደረገልንን መቀበል ብቻ ነው፡፡

ኃጢአታችንን ሳንናዘዝ የይቅርታን በረከቶች መቀበል አለመቻላችን እሙን ነው፡፡ ይህ ማለት ኑዛዜአችን በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ ይቅርታን ይፈጥራል ማለት አይደለም፡፡ ይቅርታ ሁሌም ቢሆን በእርሱ ልብ ውስጥ አለ፡፡ ይልቁንም የኃጢአት ኑዛዜ የለመንነውን መቀበል እንድንችል ያደርገናል (1ዮሐ. 1፡9)፡፡ ኑዛዜ እጅግ ወሳኝ

የሆነበት ምክንያት እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን አመለካከት ስለሚለውጥ ሳይሆን እኛ በእርሱ ላይ ያለንን አመለካከት ስለሚለውጥልን ነው፡፡ ንስሐ በመግባትና የኃጢአት ኑዛዜ በማድረግ በደለኝነታችንን እንድንቀበል ለሚያደርገው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ራሳችንን ስናስገዛ የተለወጥን እንሆናለን፡፡

ይቅር ማለትም እንዲሁ ለገዛ መንፈሳዊ ደኅንነታችን በእጅጉ ወሳኝ ነው፡፡ በደል የፈጸመብን ግለሰብ ይቅርታ የማይገባው ሰው ቢሆን እንኳ ለይቅርታ ዳተኞች ስንሆን ከጎዳን ሰው ይበልጥ ተጎጂዎች እንሆናለን፡፡ አንድ ሰው ቢበድሎትና ይህን የበደሎትን ሰው ይቅር ባለማለትዎ ጉዳቱ በውስጥዎ እያመረቀዘ ቢሄድ፤ ግለሰቡ ከቀድሞው በበለጠ እንዲጎዳዎ እየፈቀዱለት ነው፡፡ እንደነዚህ ዓይነቶቹ አጉል ስሜቶችና ጉዳቶች ለቤተ ክርስቲያን መከፋፈልና ውጥረት ተደጋጋሚ መንስዔዎች ሲሆኑ ይስተዋላል፡፡ በቤተ ክርስቲያን አባላት መካከል መፍትሔ ማግኘት ያልቻለ ጉዳት የክርስቶስን አካል አንድነት ይጎዳል፡፡

ይቅርታ ክርስቶስ እኛን ከኩነኔ ይቅር እንዳለ በተመሳሳይ ከኩነኔአችን ነጻ ማድረግ ነው፡፡ ይቅር ማለት ለበደለን ሰው ባህሪ ትክክለኛነት ምክንያት መሆን አይችልም፡ ፡ እኛ በክርስቶስ ላይ በደል ፈጽመን ስናበቃ እርሱ ይቅር ብሎ እንደታረቀን ሁሉ በተመሳሳይ ከበደለን ሰው ጋር እርቅ መፍጠር እንችላለን፡፡ ይቅር የተባልን ሰዎች እንደመሆናችን እኛም ይቅር ማለት እንችላለን፡፡ የተወደድን እንደመሆናችን እኛም መውደድ እንችላለን፡፡ ይቅር ማለት ምርጫ ነው፡፡ የሌላው ሰው ድርጊት ወይም አመለካከት ምንም ሊሆን ቢችል እኛ ግን ይቅር ማለትን መምረጥ እንችላለን፡፡ ይህ እውነተኛው የየሱስ መንፈስ ነው፡፡

*በክርስቶስ ያገኘነው ይቅርታ ላይ ትኩረት ማድረጋችን ሌሎችን ይቅር ማለት መማር እንድንችል እንዴት ይረዳናል? ይህ ይቅርታ የክርስትና ተሞክሮአችን ወሳኝ ገጽታ የሆነው ለምንድን ነው?*

## ሐሙስ

**ሕዳር 27**

## ወደ ቀድሞው ሰላማዊ ሁኔታ መመለስ እና አንድነት

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ማቴ. 18፡15-17፡፡ በቤተ ክርስቲያን አባል በደል ሲደርስብን ውዝግቦችን ለማርገብና መፍትሔ ለማምጣት የሱስ የሰጠን ሦስቱ ቅደም ተከተሎች የትኞቹ ናቸው? እነዚህን የመፍትሔ ሃሳቦች ለዛሬው ሁኔታች ጥቅም ላይ ማዋል የምንችለው እንዴት ነው?

የሱስ በማቴ. 18 ለመስጠት የተመኘው ምክረ ሃሳብ በቤተ ክርስቲያን ሊነሱ የሚችሉ ግላዊ ግጭቶችን ለመፍታት ጉልህ ጠቀሜታ አለው፡፡ ሁለቱ የተጋጩ ሰዎች ችግራቸውን በራሳቸው እንዲፈቱ ማድረግ የእርሱ እቅድ የሆነው የሱስ "'ወንድምህ ቢበድልህ ሄደህ አንተ እና እርሱ ብቻ ሆናችሁ ጥፋቱን ንገረው' " (ማቴ. 18፡15) ሲል በይፋ ይናገራል፡፡ በሁለት ሰዎች ጥል መሃል ብዙዎች በገቡ ቁጥር ልዩነቶች ይበልጥ እየሰፉ ሊሄዱና የሌሎች ወገኖችም ኅብረት የዛኑ ያህል ቀውስ ውስጥ ሊገባ ይችላል፡፡ የገላጋዮችን ጎራ መለየት ተከትሎ ጉዳዩ ይበልጥ እየከረረ የሚሄድበት ዕድልም ሰፊ ነው፡፡ ነገር ግን ክርስቲያኖች ልዩነቶቻቸውን በግል ለማርገብ ሲሞክሩ፤ በክርስትና የፍቅር መንፈስና የጋራ መተሳሰብን ተከትሎ የእርቅ ድባብ ሊፈጠር ይችላል፡፡ ወገኖች ልዩነቶቻቸውን ለማስወገድ ጥረት ሲያደርጉ መንፈስ ቅዱስ አብሮአቸው ለመሥራት የሚያስችለው ሁናቴ ይፈጠርለታል፡፡

አንዳንዴ ግጭቶችን ለመፍታት የሚደረግ የአንድ ወገን ልመናና ተማጽኖ ውጤት ላያመጣ ይችላል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አጋጣሚ ሲፈጠር አንድ ወይም ሁለት ሰዎችን ይዞ የተጋጨነውን ሰው ማናገር ተገቢ እንደሆነ የሱስ ይነገረናል፡፡ ይህ ሁለተኛው ዓይነት የእርቅ ሂደት ሁሌም ቢሆን የመጀመሪያውን መከተሉ የግድ ይሆናል፡፡ ዓላማው ሰዎችን ማቀራረብ እንጂ ማራራቅ አለመሆኑ ላፍታም ቢሆን ሊዘነጋ አይገባም፡፡ በቅራኔ ውስጥ ያሉትን ግለሰቦች ለማግባባት የቀረበው አንድ ወይም ሁለት ሰዎች ዓላማ የአንዱን ወገን ትክክለኛነት ለማሳየት ወይም ሌላኛውን ጥፋቱ ያንተ ነው ለማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም እነዚህን ሁለት ባይተዋር ልቦች በክርስቲያን ፍቅር እና ርኅራኄ የተሞሉ ምክረ ሃሳቦችን በመለገስና በጸሎት አደራ ጭምር ለመሸምገል ሊመጡ ይገባል፡፡ በእርግጥ እነዚህን ሁሉ ቅራኔዎችን መፍቻ መንገዶች ውጤታማ የማይሆኑባቸው አጋጣሚዎች ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ ይህ ሲሆን ጉዳዩን ወደ ቤተ ክርስቲያን መውሰድ ተገቢ አድርጎ የሱስ ያዘናል፡፡ በእርግጥ ይህን ሲል ሰንበት ማለዳ የሚደረገውን የአምልኮ አገልግሎት ለግል ጸብና ውዝግብ ሽምገላ አውሉ አለማለቱ ግልጽ ነው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ቅደም ተከተሎች ሁለቱን ግለሰቦች ለማስታረቅ እገዛ ማድረግ ካልቻሉ ጉዳዩን ለመውሰድ ተገቢ የሚሆነው ስፍራ የቤተ ክርስቲያን ቦርድ ይሆናል፡፡ አሁንም ቢሆን የክርስቲያኖች ዓላማ በሻከሩ ልቦች መሃል እርቅ እንዲሰፍን ማድረግ እንጂ አንዱን አካል ጥፋተኛ አድርጎ ሌላውን በነፃ ለማሰናበት አለመሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡

"ቅሬታዎ ሥር ሰድዶ ወደ ጥላቻ እንዲያመራ አይፍቀዱ፡፡ የወንድምዎን ቁስል በመርዛማ ቃላት አያመርቅዙ፡፡ ይህ የሰሚውን አእምሮም ይበክላልና፡፡ የእርስዎንም ሆነ ያልተግባቡት ሰው አስተሳሰብ በመራር ቃላት እየሞላ እንዲቀጥል አይፍቀዱ፡፡ ይልቁንም ወደ ወንድምዎ ሄደው በትህትናና በቅንነት ስለ ጉዳዩ ያናግሩት፡፡"—Ellen G. White, Gospel Workers, p. 499.

*ተጨማሪ ሀሳብ፡* Read the article "Forgiveness," pp. 825, 826, in The Ellen G. White Encyclopedia.

"ሠራተኞች ከገዛ ነፍሳቸው የማይነጥሉት ክርስቶስ ሲኖራቸው፣ ሁሉም ዓይነት ራስ ወዳድነት ሲሞት፣ መፎካከር ሲከስም፣ በእኔ እበልጥ እሳቤ ጠብ ወይም ጥል ሲቀር፣ አንድነት ሲሰፍን፣ ራሳቸውን ሲቀድሱ፣ አንዱ ለሌላው ያለው ፍቅር ሲታይና በልብ ውስጥ ሲሰማ--ከተሰጠው አምላካዊው ተስፋ ቅንጣት ታክሏ ሳትጎድል የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በእርግጠኝነት በላያቸው ይፈሳል፡፡"—Ellen G. White, Selected Messages, book 1, p. 175.

"በታላቁ የጌታ ቀን ማማችንና መጠጊያችን አድርገን ከክርስቶስ ጋር የምንቆም ከሆነ ሁሉንም ዓይነት ቅናት፣ ምቀኝነትና እኔ እበልጥ ባይነት ከእኛ ማስወገዳችን የግድ ይሆናል፡፡ ቅድስና የጎደላቸው እነዚህ ነገሮች ዳግም እንዳያለመልሙና እንዳያፈሩ ከሥረ መሠረታቸው መንቀልና ማስወገድ አለብን፡፡ ራሳችንን በጌታ በኩል ቅዱስ አድርገን እናኑር፡፡"—Ellen G. White, Last Day Events, p. 190.

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

1. ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ቆለ. 3፡12-17፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ የቆላስያስ ቤተ ክርስቲያን አባላት እንዲኖራቸው በሚያበረታታቸው የክርስትና ብቃቶች ዙሪያ ተወያዩ፡፡ እነዚህ ብቃቶች ለግጭት አፈታቶች መሰረት የሆኑት ለምንድን ነው? የሱስ በማቴ. 18፡15-18 የሚሰጠንን መርኆዎች በማቀፍ ምሪት የሚሰጡን እንዴት ነው?

2. በቆለ. 3፡12-17 የቀረቡትን አስተምህሮዎች በድጋሚ ይመልከቱ፡፡ እነዚህ ነገሮች ለቤተ ክርስቲያን አንድነት ፍጹም አስፈላጊ የሆኑት ለምንድን ነው?

3. ጠቅለል አድርገን ወደ ቤተ ክርስቲያናችን ማለትም ወደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ስንመለከት--ወደ ዓለም ለመድረስ የሚያስፈልገው ዓይነት ኅብረት እንዳይኖረን ወደ ኋላ የሚጎትተን የገዘፈ ነገር ምንድን ነው? ኃይማኖታዊ አስተምህሮአችን ነው? በእርግጥ አይደለም፡፡ እነርሱማ ለዓለም እንድናውጃቸው በእግዚአብሔር የተሰጡን መልእክቶች ናቸው፡፡ ምናልባት ችግሩ በብቸኝነት ያለው

ራሳችን ላይ ነው፡፡ ከሰዎች ጋር ያሉን ግላዊ ግንኙነቶች፣ ምቀኝነት፣ ንትርክ፣ ራስ ወዳድነት፣ እኔ እበልጥ--እኔ እሻል ምኞት እና ሌሎች እልፍ ነገሮች፡፡ በሁሉም ቤተ ክርስቲያኖቻችን አንድነትን ከማየታችን አስቀድሞ በቅድሚያ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለውጥ እንዲያመጣ ለምን አብልጠው አይማጸኑትም?

*ማጠቃለያ፡* የየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ስለ ፈውስና ስለ መለወጥ ያወሳል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎች ጋር መልካምና የቀረበ ግንኙነት ሊኖረን እንደሚገባ አስመልክቶ ብርቱ መርኅዎችንና ምሳሌዎችን ይሰጠናል፡፡

# 11ኛ ትምህርት ኅዳር 29 - ታህሳስ 5

## አንድነት በአምልኮ ውስጥ

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ራእ. 4:8፣ 11፣ ማቴ. 4:8-9፣ ዳን. 3:8–18፣ ራእ. 14:9፣ ራእ. 14:6-7፣ ሐዋ. 4:23–31፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ :-** “ከዚያም ሌላ መልአክ በሰማይ መካከል ሲበር አየሁ፤ እርሱም በምድር ላይ ለሚኖሩ ለሕዝብ፣ ለነገድ፣ ለቋንቋና ለወገን ሁሉ የሚሰብከውን የዘላለም ወንጌል ይዞ ነበር፤ ባታላቅ ድምፅም፣ ‘እግዚአብሔርን ፍሩ፤ ክብርም ስጡት፤ ምክንያቱም የፍርዱ ሰዓት ደርሶአልና፣ ሰማይንና ምድርን ባሕርንም የውሃ ምንጮችን ለፈጠረው ስገዱ’ አለ” (ራእ. 14፡6-7)፡፡

የቀደሙት ክርስቲያኖች ከጴንጤቆስጤ በኋላ አብዛኛውን ጊዜያቸውን ያውሉ የነበረው ለአምልኮ ነበር፡፡ “እነርሱም በሐዋርያት ትምህርት በኅብረት፣ እንጀራውንም በመቁረስና በጸሎት ይተጉ ነበር” (ሐዋ. 2፡42)፡፡ የሱስን እንደ መሲህ በማወቃቸው ያገኙት ደስታና የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ፍጻሜ--ልባቸው በምስጋናና በውለታ እንዲሞላ አደረገ፡፡ ይህን አስደናቂ እውነት ማወቅ አብልጦ መታደል ነው፡፡ እነዚህ የቀደሙ ክርስቲያኖች በአንድነት ሆነው አምልኮ በማድረግ፣ ከቃሉ በማጥናትና በጸሎት በመትጋት በሕይወታቸው ላደረገላቸው ነገርና--የየሱስን ሕይወት፣ ሞትና ትንሣኤ የገለጠላቸውን አምላክ ለማመስገን ጊዜ ሊኖራቸው እንደሚገባ ተሰምቶአቸው ነበር፡፡

የየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የተሰኘው አባባል--አምልኮ የሚያደርግ ማኅበረሰብ የሚል ፍቺ ያለው ሲሆን፤ ይህ ማኅበረሰብ “ቅዱሳት ካኅናት በመሆን እንደ ሕያዋን ድንጋዮች መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ይሠራል” (1ጴጥ. 2፡5)፡፡ ለእግዚአብሔር ምስጋና የሚቀርብበት ማኅበረሰባዊ አምልኮ የሰዎችን ልብ እና አእምሮ ወደ አምላካዊው ባህሪ በመለወጥ ለአገልግሎት ያዘጋጃቸዋል፡፡ በዚህ ሣምንት ትምህርታችን በአምልኮ ፍቺ እና አምልኮ የየሱስ አማኞችን አንድነት እንዴት እንደሚያጸና እንመለከታለን፡፡

**እሁድ** **ኅዳር 30**

## ፈጣሪያችንን እና ቤዛችንን ማምለክ

ስለ አምልኮ ውይይት ሲደረግ ብዙውን ጊዜ መሰረታዊ ለሚባሉ አላባዎች አጽንኦት ይሰጣል፡፡ አምልኮ ምን ምን እንደሚያካትትና እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆንም ሳይጠቀስ አያልፍም፡፡ ሆኖም ግን የአምልኮ ጥልቅ ትርጉም ምንድን ነው? እግዚአብሔርን ማምለክ ስንል ምን ማለታችን ነው? ይህን የምናደርገው ለምንድን ነው? ዳዊት በመዝሙር 29፡2 እንዲህ ይላል፡ "ለስሙ የሚገባ ክብር ለእግዚአብሔር ስጡ፤ በቅድስናው ግርማ ለእግዚአብሔር ስገዱ፡፡" ይህ መልእክት የአምልኮን ትርጉም የምናስተውልበትን ትክክለኛውን አቅጣጫ ይሰጠናል፡፡ ጌታን ማምለክ ማለት ለእርሱ የሚባውን ምስጋናና ክብር መስጠትነው፡፡

የሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ እንዴት እንደ ከበረ በራእ. 4 እና 5 ተብራርቶ እንመለከታለን፡፡ የሰማይ ቅዱሳን እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔር በግ የሆነውን የሱስ ስለ ማምለካቸው የሚሰጡት ምክንያት ምንድን ነው? ጥቅሶቹን ይመልከቱ፡ ራእ. 4፡8፣ 11፡5፣ 9-13፡፡

________________________________________________________

________________________________________________________

ይህ የሱስ እንደ እግዚአብሔር በግ እና የዓለም አዳኝ ሆኖ የተዋወቀበት የሰማያዊው ዙፋን አምልኮ ገጽታ እጅግ ታላቅና በብርቱ አክብሮት የተሞላ ነው፡፡ እግዚአብሔር ላደረገው ነገር የእርሱ ፍጡር በአክብሮትና በፍቅር በተሞሉ ቃላት የሚያቀርበው የምስጋና ምላሽ ከአምልኮ ይመደባል፡፡ አምልኮ ለእግዚአብሔር የፍጥረትና የማዳን ሥራ የሚቸር የምስጋና ምላሽ ነው፡፡ በዘመን ፍጻሜ ላይ በበጉ ደም የተዋጁ ወገኖችም እንዲሁ ለአምላካዊው ማዳን በታላቅ ፍቅርና አክብሮት ምላሽ ይሰጣሉ፡፡ "ሁሉን ቻይ ጌታ ሆይ፤ ሥራህ ታላቅና አስደናቂ ነው፡፡ የዘመናት ንጉሥ ሆይ፤ መንገድህ ጽድቅና እውነት ነው፡፡ ጌታ ሆይ፤ አንተን የማይፈራ፣ ስምህን የማያከብርስ ማን ነው? አንተ ብቻ ቅዱስ ነህና፡፡ የጽድቅ ሥራህ ስለ ተገለጠ፣ ሕዝቦች ሁሉ ይመጣሉ፤ በፊትህም ይሰግዳሉ፡፡" ራእ. 15፡ 3-4)፡፡

ስለዚህ አምልኮ ለእግዚአብሔር ኃያል ሥራ የምንሰጠው የእምነታችን ምላሽ ሲሆን ይኸውም--በአንደኛ ደረጃ እኛን በመፍጠሩ፤ በሁለተኛ ደግሞ እኛን በማዳኑ ነው፡፡ ለእግዚአብሔር በምንሰጠው አምልኮ እርሱ አክብሮት፣ ውዳሴ፣ ምስጋና፣ ፍቅርና መታዘዝ እንደሚገባው እናምናለን፡፡ በእርግጥ እግዚአብሔር ፈጣሪያችንና አዳኛችን መሆኑን ማወቅ የቻልነው በመጽሐፍ ቅዱስ በገለጠልን እውነት መሰረት

ነው፡፡ በተጨማሪ የየሱስ በአካል መምጣትና አገልግሎቱ የእግዚአብሔርን ማንነት ለክርስቲያኖች በሙላት መግለጥ ቻለ፡፡ (ዮሐ. 14፡8-14)፡፡ የየሱስ የመሥዋዕት ሞትና ትንሣኤ የአምልኮ አስኳል ነው፡፡ ስለዚህ ክርስቲያኖች እርሱን እንደ አዳኝና ቤዛቸው ያመልኩታል፡፡

ክርስቲያኖች በአንድ ላይ ስንሰባሰብ አምልኮአችን በታላቅ አክብሮትና ውዳሴ መቀጠል የሚገባው በዚህ የተነሳ ነው፡፡

*ስለ እኛ ለመሞት ፈቃደኛ በመሆኑ የተነሳ ክርስቶስ እንደ ፈጣሪነቱና እንደ አዳኝነቱ ከምን እንዳዳነንና ምን እንደሰጠን ያስቡ፡፡ እነዚህ እውነቶች የአምልኮአችን መሰረት መሆን ያለባቸው ለምንድን ነው?*

**ሰኞ** **ታህሳስ 1**

## የሐሰት አምልኮ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ማቴ. 4፡8-9፡፡ የሱስ በምድረ በዳ የተፈተነው ሦስተኛው ፈተና ምን ነበር?

______________________________________________________

______________________________________________________

ሰይጣን ይህን ዓለም የፈጠረ ይመስል በውስጧ ያለው ሐብት፣ ክብርና ዝና ሕጋዊ ገዢና ባለቤት መሆኑን በትዕቢትና በግብዝነት እያወጀ በውስጧ የሚኖሩ ሁሉ ለእርሱ ክብር ሊሰጡ እንደሚገባ ተናገረ፡፡ ይህ መመጻደቁ የዚህ ዓለም ፈጣሪ ለሆነው ጌታ እንዴት ዓይነት ስድብ ነው! ሰይጣን በዚህ አነጋገሩ የአምልኮን ትክክለኛ ፍቺ አበጥሮ እንደሚያውቅ ገለጸ--ለሕጋዊው የዩነቨርስ ባለቤት ክብርና ምስጋና መስጠት፡፡

በዳንኤል ምዕ. 3 የቀረቡትን የሦስቱን ዕብራውያን ተሞክሮ (በተለይ ከቁ. 8-18) እና በራእ. 13፡4፣ 14፡9-11 ስለ መጨረሻው ጊዜ ኃይል የቀረበውን ያስተያዩ፡፡ በመጨረሻው ጊዜ ያለው አደጋ ምንድን ነው? በሁለቱም ታሪኮች የሚስተዋለው ፍሬ ነገርስ?

______________________________________________________

______________________________________________________

ሰይጣን ከአቤልና ቃየን እንዲሁም በባቢሎን ከነበሩት ሦስቱ ዕብራውያን ወጣቶች እስከ "የአውሬው ምልክት" (ራእ. 16፡2) ድረስ ያሉ ክስተቶችን በመጠቀም፤ ሰዎችን እጅግ በረቀቀ መንገድ ከእውነተኛው አምላክ ነጥሎና አምልኮን በቀጥታ ወደ ራሱ አዞሮ የሐሰት አምልኮ ሥርዓት ለማቋቋም ሲጥር ኖሮአል፡፡ ለነገሩ ሰይጣን ከውድቀቱ አስቀድሞም ቢሆን እንደ እግዚአብሔር መሆን ፈልጎ ነበር (ኢሳ. 14፡14)፡

ሦስቱ ወጣቶች “ለምስሉ” ካልሰገዱ በቀር እንደሚገደሉ የተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ በተመሳሳይ በመጨረሻዎቹ ቀናት የእግዚአብሔር ታማኝ ሕዝቦች “ለምስሉ” ካልሰገዱ እንደሚገደሉ ከሚወጣው ሕግ ጋር አንድ መሆኑ አጋጣሚ አይደለም፡፡ እውነተኛውን አምላክ እንድናመልክ ጥሪ ቀርቦልን እያለ በዚያ ፋንታ ለማንኛውም “ምስል” የምንሰግደው ለምን ይሆን?

“በዱራ ሜዳ ከነበሩ ዕብራውያን ወጣቶች ተሞክሮ እንድንማር የቀረቡልን ትምህርቶች ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው...

“በእግዚአብሔር ሕዝቦች ላይ የሚደርስ ከፍ ያለ የሥቃይ ወቅት የማያቅማማ የእምነት ባለቤት ያደርጋቸዋል፡፡ እርሱ ብቸኛው የአምልኮቸው አስኳል መሆኑን ልጆቹ ገልጠው ማሳየታቸው የግድ ነው፡፡ ራሷን ሕይወትን ጨምሮ የቱንም ዓይነት አስተሳሰብ በሐሰት አምልኮ ላይ ቅንጣት ታክል እምነት እንዲኖራቸው ሊያግባባቸው አይችልም፡፡ እሥር ወይም ግዞት ወይም ሞት ቢደርስባቸው እንኳ እውነትን ከመታዘዝ ወደ ኋላ አይሉም፡፡”—Ellen G. White, Prophets and Kings, pp. 4 512, 513.

ዛሬም ቢሆን አምልኮ ከሚገባው ብቸኛ አምላክ ውጪ አምልኮ እንድናቀርብ በተለያየ መንገድ ሊፈትኑን የሚችሉ ነገሮች ምንድን ናቸው? ሐሰተኛ አምልኮ ልንገነዘብ ከምንችለው በላይ ረቂቅ ስጋት መሆን የሚችለው እንዴት ነው? እንድናመልካቸው የምንፈተን አንዳንድ ነገሮች ምንድን ናቸው?

**ማክሰኞ** **ታህሳስ 2**

## የመጀመሪያው መልአክ መልእክት

ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች ከየሱስ ዳግም ምጽአት አስቀድሞ ገቢራዊ የሚሆነውን በራእ. 14፡6-12 የቀረበውን የሦስቱ መላእክት መልእክት የተልዕኮአቸው ገላጭና የመልእክታቸው እምቡጥ አድርገው ይመለከቱታል፡፡ የሦስቱ መላእክት መልእክት ለመላው የምድር ሕዝቦች “በታላቅ ድምጽ” መሰበክ ያለበት እጅግ ወሳኝ መልእት ነው፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 14፡6-7፡፡ የመጀመሪያው መልአክ መልእክት ምንድን ነው? ስለ እግዚአብሔር ምን ይናገራል? በዚህ መልእክት ሰለ አምልኮ የተጠቀሰው ለምንድን ነው?

ከሦስቱ መላእክት መልእክት የመጀመሪያው ለመላው የምድር ሕዝብ የታወጀውን መልእክት ይዞአል፡፡ ይህ የሱስ በማቴ. 24፡14 የተናገረው ትንቢት ፍጻሜ ነው፡፡ የሦስቱን መላእከት መልእት ገጽታና ተልእኮ ስንመለከት በአስቸኳይነትና በጥድፊያ የተሞላ ሁናቴ ይታይበታል፡፡ “ ‘የፍርዱ ሰዓት ደርሶአልና’ ” (ራእ. 14፡7) የሚለው የመጀመሪያው መልእክት ሰዎች ትኩረታቸውን በእግዚአብሔር ላይ እንዲያደርጉ ጥሪ ያደርጋል፡፡ ሁለተኛው የየሱስ ምጽአት የፍርድ ሂደቱ አቀጣጣይ ነው፡፡

“ ‘እግዚአብሔርን ፍሩ’ ” (ራእ. 14፡7) ሲል መልአኩ ያውጃል፡፡ አምላካዊውን ነገር እንደ ብርቱ ጉዳይ ለማይቆጥሩ ይህ መልእክትና የድርጊት ጥሪ በአእምሮአቸው ፍርሐት መፍጠሩ አይቀሬ ነው፡፡ የየሱስ ተከታዮች ሆነው ለዘለቁ ግን ልባቸው በታላቅ አክብሮትና ፍቅር እንዲሞላ ያደርጋል፡፡ ወደ እግዚአብሔር ቀና ብለው የአምላካዊውን ተስፋ ፍጻሜ ይመለከታሉ፡፡ ውስጣቸው ከበሬታ ባለው ብርቱ ውለታና ምስጋና ይሞላል፡፡

“‘ሰማይንና ምድርን፣ ባሕርንና የውሃ ምንጮችን ለፈጠረው ስገዱ’” (ራእ. 14፡ 7)፡፡ ይህ ፍጥረትን በማጣቀስ የቀረበ ቋንቋ ስለ ሰንበት ለተሰጠው ትእዛዝ ፍንትው ያለ ፍንጭ ይሰጠናል ( ዘፀ. 20፡8-11)፡፡ ሰንበትን ለፍጥረት ሥራው በመታሰቢያነት ያቋቋመው ይህ አምላክ ሊመለክና ሊፈራ የተገባው ነው፡፡

በምድር ታሪክ መደምደሚያ ላይ አምልኮ በታላቁ ተጋድሎ ቁልፍ የሰብዓዊው ዘር ታማኝነት መለኪያ ሆኖ መቅረቡን መገንዘባችን በእጅጉ መሳጭ ነው፡፡ ይህ መመለክ ያለበት ሰማይና ምድርን የፈጠረው አምላክ ብቻ መሆኑን ለመላው የምድር ነዋሪ ለማስታወቅ የቀረበ ጥሪ ነው፡፡

“በመጨረሻ ለሚነሳው ቀውስ የጉዳዩ ማዕከል አምልኮ ይሆናል፡፡ ፈተናው አምልኮ የመከልከል ሳይሆን በሚመለከው ኃይል ማንነት ላይ ያነጣጠረ እንደሚሆን የራእይ መጽሐፍ በግልጽ ያስቀምጥልናል፡፡ በመጨረሻ ሁለት ዓይነት ቡድኖች ብቻ በምድር ይኖራሉ፡ እውነተኛውን እግዚአብሔር የሚፈሩ፣ የሚያመልኩ (ራእ. 11፡1፣ 18፣ 14፡ 7) እና እውነትን ጠልተው ለዘንዶውና ለአውሬው የሚሰግዱ (13፡4-8፣ 14፡9-11)፡፡

“አምልኮ የመጨረሻው ቀውስ ዐቢይ ጉዳይ እስከ ሆነ ድረስ እግዚአብሔር የመጨረሻውን ጊዜ ወንጌል ልኮ የምድር ነዋሪዎች እንደ ፈጣሪነቱ እርሱን ብቻ እንዲያመልኩ ጥሪ ማድረጉ ብዙም ሊያስገርም አይችልም፡፡”—*Ranko Stefanovic, Revelation of Jesus Christ: Commentary on the Book of Revelation (Berrien Springs, Mich.: Andrews University Press, 2002), pp. 444, 445.*

ረቡዕ

ታህሳስ 3

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና የአማኞች ኅብረት

ጥቅሱን ያንብቡ፡ ሐዋ. 2፡42፡፡ የቀደመው ክርስትና አምልኮ አንዳንድ መሰረታዊ ባህሪያት ምን ነበሩ?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

"እነርሱም በሐዋርያት ትምህርትና በኅብረት.. ይተጉ ነበር" (ሐዋ. 2፡42)፡፡ አምልኮ ከእነዚያ የቀደሙ የቤተ ክርስቲያን ጊዜያቶች አንስቶ በሐዋርያት በተሰጠን የእግዚአብሔር ቃል ማዕከላዊነት ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ስለ መሲሁ የሱስ የሚናገረውን አምላካዊ ቃል በማጥናቱ ረገድ ታማኞች ነበሩ፡፡ እግዚአብሔር የሰጣቸውን በረከቶች ለሌሎች በማጋራት፣ አንዱ ሌላውን በማበረታታትና ከእርሱ ጋር በነበራቸው አረማመድ የማያቋርጥ ኅብረት የነበራቸው አማኞች፤ የመልእክቶቻቸው መሰረት የሆኑትን የአምላካዊውን ቃል የተቀደሱ እውነቶች በልባቸው ይጠብቁ ነበር፡፡

የሚከተሉት ጥቅሶች በዚህ ሣምንት እያጠናነው ስላለነው አስራ አንደኛ ትምህርት ማለትም ከሌሎች አማኞች ጋር ኅብረት ፈጥሮ የእግዚአብሔርን ቃል ስለ ማጥናት ምን ይላሉ?

2ነገሥ. 22:8–13__________________________________________

ሐዋ. 17:10-11 __________________________________________

2ጢሞቴ. 3:14–17__________________________________________

"ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ ከልባቸው የሚመኙ ወገኖች፤ የወንጌል እውነት ሲሰበክ ሲሰሙ መጽሐፍ ቅዱስን በትጋት የማንበብ ምኞት በውስጣቸው ያድራል፡፡ በምድር ታሪክ መዝጊያ ትዕይንት ላይ እነዚያ ፈታኝ እውነቶች የሚሰበኩላቸው ወገኖች የቤርያን ሰዎች ምሳሌ በመከተል ዕለት ዕለት መጽሐፍ ቅዱስን እየመረመሩ የመጡላቸውን መልእክቶች ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ያስተያያሉ፡፡"—Ellen G. White, The Acts of the Apostles, p. 232.

እኛ ከአምላካዊው ቃል ተነስተን ከምናውጃቸው እውነቶች አኳያ በአንድ የተዋሃድን ሕዝቦች ነን፡፡ ይህ በቀደመችው የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን እውነት እንደ ነበር በዛሬዋም ነው፡፡ የሦስቱን መላእክት መልእክት ለዓለም እንድናውጅ የተጠራንበትን

አምላካዊውን ቃል ማጥናት ከእግዚአብሔር ጋር እና እርስ በርስ ባለን ግንኙነት መሰረታዊውን የአምልኮአችንን ቅርጽ ይፈጥራል፡፡

ለአምልኮ ብሎም ከአማኞች ጋር ኅብረት ለመፍጠር እንደ አንድ ቤተሰብ ስንሰባሰብ ከእግዚአብሔር የተላከው አምላካዊ ቃል እኛን ለተልዕኮአችንና ለየሱስ ዳግም ምጽአት እያዘጋጀ ሕይወታችንን ይመራል፡፡

*የእምነታችን መሰረት በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያሉት ጽናት ምን ይመስላል? እምነትዎ በሞት ፊት ተጋፍጠው እንደ ቆሙት ሦስቱ ዕብራውያን ወጣቶች ምን ያህል ጥብቅ ነው?*

**ሐሙስ** **ታህሳስ 4**

## እንጀራ በመቁረስና በጸሎት

የቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ተግዳሮቶች የቱንም ያህል ብርቱ ቢሆኑም አማኞች በየሱስ ላይ የነበራቸው የጋራ እምነትና ለዓለም እንዲያሰራጩ የተሰጣቸው እውነት በአንድ አስተሳስሮአቸው ነበር፡፡ ጴጥሮስ ይህንን--ወቅታዊ እውነት በማለት ይጠራዋል (2ጴጥ. 1፡12)፡፡ የአማኞች የቤተ ክርስቲያን አንድነት በብዙ መንገዶች የተገለጸ ነበር፡፡

"እነርሱም... እንጀራውንም በመቁረስና በጸሎት ይተጉ ነበር" (ሐዋ. 2፡42)፡፡ ይህ እንጀራን አብሮ የመቁረስ ልምድ አማኞች የአምልኮ መርኀ ግብር ሲኖራቸው ወይም በመደበኞቹ ቀናት የሚተገብሩት ሊሆን ይችላል፡፡ አልፎ አልፎ በዚህ የኅብረት ማዕዳቸው ወቅት ከመካከላቸው አንዱ ዳግም ምጽአቱን ተስፋ በማድረግ ስለ የሱስ ሞትና ትንሣዔ መታሰቢያ እንዲሆን ለቀረበው ምግብና መጠጥ ልዩ ምስጋና ያቀርባል፡፡ የየሱስን ሕይወትና አገልግሎት እያስታወሱ ረዘም ያሉ ጊዜያቶችን ያጠፉ የነበሩት እነዚያ የቀደሙ ክርስቲያኖች በኅብረት ማዕድ ወቅትም ቢሆን ስለዚህ ጉዳይ አውርተው አይጠግቡትም ነበር፡፡ በመሆኑም በኅብረት እንጀራ የሚቆርሱበትም ቢሆን--የአምልኮአቸው ጊዜ ነበር፡፡ "በየዕለቱ በቤተመቅደስ በአንድነት እየተገናኙ፣ በቤታቸውም እንጀራ እየቆረሱ በደስታና በቀና ልብ ይመገቡ ነበር፤ እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ፣ በሕዝቡ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው፤ ጌታም የሚድኑትን በቁጥራቸው ላይ ዕለት ዕለት ይጨምር ነበር፡፡" (ሐዋ. 2፡46-47)፡፡ ይህ የኅብረት ጊዜያቸው በየሱስ የነበራቸውን የአንድነት ስሜት እንዲያጠነክሩ ለመርዳቱ ጥርጥር የለውም፡፡

የቀደሙት ክርስቲያኖች በአንድ ላይ በጸሎት ስለ መትጋታቸው በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የተሰጡን ምን ዓይነት ምሳሌዎች አሉን? የጸለዩት ስለ ምን ነበር?

ሐዋ. 1፡14________________________________________________

ሐዋ. 4:23–31________________________________________

ሐዋ. 12:12__________________________________________

አማኞች በአንድነት ለአምልኮ ሲሰባሰቡ ልመናዋን ለእርሱ ከማቅረብ ተሰናክላ የማታውቀው የቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ መገናኘት የመቻሏን ዕድል ጠብቃ ይዛ ነበር፡፡ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በላከው የመጀመሪያው ደብዳቤ ክርስቲያኖች በአንድነት ሲሰባሰቡ መጸለያቸው አስፈላጊ እንደሆነ ይጠቅሳል (1ጢሞቴ. 2፡1)፡፡ እንዲሁም ስለ ጸሎት አስፈላጊነት ለኤፌሶን ሰዎች በብርቱ ይናገራል "በሁሉ ዐይነት ጸሎትና ልመና፣ በማንኛውም ሁኔታ በመንፈስ ጸልዩ፤ ይህንም በማሰብ ንቁ፤ ስለ ቅዱሳንም ሁሉ በትጋት ልመና አቅርቡ፡፡" (ኤፌ. 6፡18-19)፡፡

*ለጋራ ጥቅም ለሆነ የምልጃ ጸሎት ኃይል--ጥልቀት ያለውን አንድነት መለማመድ የምንችልባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? እንደ ቤተ ክርስቲያን ይህ ጸሎት አንድ ሊያደርገን የሚችለው እንዴት ነው?*

## ዓርብ

## ታህሳስ 5

*ተጨማሪ ሃሳብ*፡ Read the articles "Prayer," pp. 1044–1046, and "Worship," pp. 1290, 1291, in The Ellen G. White Encyclopedia.

" 'ሰንበት የፍጥረት መታሰቢያ የሆነበት ዋንኛ ምክንያት እግዚአብሔር ሁሌም አምልኮ የሚገባው አምላክ የመሆኑን እውነተኛ ምክንያት ይኸውም--እርሱ ፈጣሪ እኛ ደግሞ የእርሱ ፍጥረቶች መሆናችንን ስለሚገልጥ ነው፡፡

"ሰንበት ከሌላ ከማንኛውም ተቋም ይልቅ እጅግ መሳጭ በሆነ መልኩ ይህን የመለኮታዊ አምልኮ መሰረት የሆነውን ታላቅ እውነት ያስተምራል፡፡ ሰባተኛው ቀን ሰንበት ለመለኮት አምልኮ የሚቀርብበት እውነተኛ መሰረት ብቻ ሳይሆን ነገር ግን በሁሉም አምልኮዎች--በፈጣሪና በፍጥረታቱ መካከል ልዩነት መኖሩንም ያሳያል፡፡ ይህ ታላቅ ሐቅ ፈጽሞ ሊሻርም ሆነ ሊዘነጋ አይችልም፡፡'—J. N. Andrews, History of the Sabbath, chapter 27. እግዚአብሔር ሰንበትን በኤደን የአትክልት ስፍራ ያቋቋመው ይህ እውነት ሁሌም በሰብዓዊው አእምሮ ተጠብቆ እንዲቆይ በማሰብ ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ፈጣሪነት እርሱን የምናመልክበት መንስዔ መሆኑ እስከ ቀጠለ ድረስ፤ ሰንበትም ምልክትና መታሰቢያ ሆኖ ይኖራል፡፡ ሰንበት በምድር ዳርቻ ተጠብቆ ቢሆን ኖሮ የሰው አስተሳሰብና ፍቅር በታላቅ አክብሮትና አምልኮ ወደ ፈጣሪው ባዘነበለና-ጣኦት አምልኮ፣ የዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሀሳብም ሆነ ኢ-አማኒነት ባልኖረ

ነበር፡፡ ሰንበትን መጠበቅ ‘ሰማይንና ምድርን፣ ባሕርንና የውሃ ምንጮችን ለፈጠረው’ እውነተኛ አምላክ ያለንን ታማኝነት የምናሳይበት ምልክት ነው፡፡ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያመልኩና ትእዛዛቱን እንዲጠብቁ በሚያዘው መልእክት አራተኛውን ትእዛዝ እንዲጠብቁ የተለየ ጥሪ ቀርቦላቸዋል፡፡”—Ellen G. White, The Great Controversy, pp. 437, 438.

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

1. መጽሐፍ ቅዱሳዊው የአምልኮ፣ የፍጥረትና የደኅንነት ጽንሰ ሃሳብ እጅግ በቅርብ የተሳሰሩ እንደመሆናቸው ሰንበት እንዴት አምላካዊ የሐሰት አምልኮ ማርከሻ መሆን የሚችል ይመስሎታል? በራእ. 14፡6-7 ስለ መጨረሻው ዘመን በቀረበው ትንቢት ሰንበት ምን ዓይነት ሚና ይኖረዋል? ሰንበት በአንደኛው መልአክ መልእክት የተጠቀሰው ለምንድን ነው?

2. ብዙውን ጊዜ በአምልኮ ወቅት መደረግ ስላለባቸውና ስለሌለባቸው ነገሮች ስናወራ እንደመጣን፡፡ ይህ ብቻውን በቂ ሊሆን ይችላል? ለመሆኑ አምልኮ ምንድን ነው? አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንዎ ትርጉም ያለውን አምልኮ እየተለማመደች የምትገኝበት መንገድ ምን ይመስላል?

3. የክርስትና ማኅበረሰባዊ አምልኮ ልማድ አድቬንቲስቶችን ጨምሮ በአንዳንድ ማኅበረሰቦች ቀስ በቀስ እየተረሳና እየተተወ የሄደ ይመስላል፡፡ ይህ ልማድ እንዲያንሰራራ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንዎ ምን ማድረግ ትችላለች?

**ማጠቃለያ**፡ አምልኮ እግዚአብሔር ለሰጠን የደኅንነት ስጦታ ክርስቲያኑ አማኝ የሚያቀርበው አመስጋኝ ምላሽ ነው፡፡ በተጨማሪ የክርስትናው ማኅበረሰብ አንድነትና ኅብረት ተሞክሮ መሰረታዊ አላባ ነው፡፡ ያለ ጸሎትና መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እግዚአብሔር ለእኛ ያዘጋጀውን እውነት ለማወቅ የምንጓጓ ከሆነ ማኅበረሰባችን በክርስቶስ አንድ የመሆንን ተሞክሮ ሳያገኝ ይቀራል፡፡

# 12ኛ ትምህርት ከታህሳስ 6 - 12

## የቤተ ክርስቲያን ድርጅትና አንድነት

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ኤፌ. 5:23-27፣ ማቴ. 20:25-28፣ ቲቶ 1:9፣ ማቴ. 16:19፣ ገላ. 6:1-2፣ ማቴ. 28:18-20፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ :-** " 'በእናንተ መካከል ግን እንዲህ መሆን የለበትም፡፡ ከእናንተ ትልቅ መሆን የሚፈልግ አገልጋያችሁ ይሁን፤ የበላይ ለመሆን የሚሻም የእናንተ የበታች ይሁን፡፡' " (ማቴ. 20፡26-27)፡፡

እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስትነታችን የሱስ ለሰብዓዊው ዘር የፈጸመውን በማመን ብቻ እንድናለን በሚለው እምነታችን ፕሮቴስታንት ክርስቲያኖች ነን፡፡ ክርስቶስ ለእኛ ያደረገውን ለመቀበልና ተጠቃሚ ለመሆን ቤተ ክርስቲያን ወይም የቤተ ክርስቲያን መዋቅር አያስፈልገንም፡፡ በእኛ ምትክ በመስቀል ላይ እንደ መሞቱና የሰማያዊው መቅደስ ሊቀ ካኅናትነቱ--ከክርስቶስ የምናገኘውን በቀጥታ ከእርሱ እንቀበላለን፡፡

ሆኖም ቤተ ክርስቲያን የተፈጠረችው በእግዚአብሔር ነው፡፡ እንደ መዳኛ ሳይሆን--ደኅንነትን ለዓለም የምንገልጽባትና የምናሳይባት መሣሪያ አድርጎ ስለ እኛ በመካከላችን አኖራት፡፡ ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን ለዓለም እንድታሰራጭ የሱስ የፈጠራት ድርጅት ናት፡፡ ድርጅት የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ እንዲጠናከር የሚፈቅድና የሚያመቻች እንደ መሆኑ አስፈላጊ ነው፡፡ የየሱስ አዳኝ መልእክት ያለ ቤተ ክርስቲያን ድርጅት ውጤታማ ሆኖ ከሌሎች ጋር አግባብ መፍጠር አይችልም፡፡ የየሱስን ምሳሌ በአርአያነት እያሳዩ አንድነት እንዲበረታታና እንዲስፋፋ የሚሠሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም እንዲሁ አስፈላጊ ናቸው፡፡ የቤተ ክርስቲያን ድርጅት ተልዕኮና አንድነት እንዲበረታታ ለማድረግ ወሳኝ የሆነበትን ምክንያት በዚህ ሣምንት እንመለከታለን፡፡

**እሁድ** **ታህሳስ 7**

## የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው - - ክርስቶስ

ቀደም ባለው ትምህርት እንደ ተመለከትነው የአዲስ ኪዳኗ ቤተ ክርስቲያን በምሳሌያዊ አካል ተወክላለች፡፡ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት፡፡ ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር አያሌ የቤተ ክርስቲያን ገጽታዎችን እንዲሁም በክርስቶስና በሕዝቡ መካከል ያለውን ግንኙነት ይጠቅሳል፡፡ እንደ ክርስቶስ አካልነቷ የቤተ ክርስቲያን ሕልውና የተመሰረተው በእርሱ ላይ ነው፡፡ እርሱ የቤተ ክርስቲያን ራስ (ቆሊ. 1፡18፣ ኤፌ. 1፡22) እና የሕይወቷ ምንጭ ነው፡፡

ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን እምነትና አስተምህሮ ምንጭ ብሎም ጠንሳሽ እንደመሆኑ አንድነቷን የምታገኘው ከእርሱ ነው፡፡ ምንም እንኳ እነዚህ አስተምህሮዎች አንገብጋቢ የማንነቷ መገለጫዎች ቢሆኑም ቤተ ክርስቲያን ከዚያም በላይ ናት፡፡ የቤተ ክርስቲያንን ማንነት የሚወስነው በክርስቶስና በመጽሐፍ ቅዱስ በተገለጠው ሕያው ቃል ነው፡፡ በዚህ የተነሳ ቤተ ክርስቲያን ማንነቷን እና ትርጉሟን ያገኘችው በእርሱ በክርስቶስ ነው፡፡

በክርስቶስ እና በቤተ ክርስቲያኑ መካከል ያለው ግንኙነት ለባልና ሚስት ግንኙነት ምሳሌ ሊሆን እንደሚገባ ጳውሎስ በኤፌ. 5፡23-27 ይናገራል፡፡ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያኑ መካከል ያለው ግኙነት ቁልፍ ጽንሰ ሃሳቦች ምንድን ናቸው?

---

---

ምንም እንኳ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ባለፉት ምዕተ ዓመታት ከሠሯቸው ከባድ ስህተቶች አኳያ ራስን ማስገዛት የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ይህችን ቤተ ክርስቲያን ይገልጻል የሚለውን አባባል ለመቀበል ብዙዎች ቢያመነቱም ነገር ግን ክርስቶስ ሁሌም የቤተ ክርስቲያን ራስ--ቤተ ክርስቲያንም የእርሱ ተጠሪ ናት፡፡ ክርስቶስን እንደ ቤተ ክርስቲያን ራስ መቀበላችን ታማኝነታችን ለማንም ሳይሆን ለራሱ ለጌታ መሆኑን እንድናስታውስ ይረዳናል፡፡ ቤተ ክርስቲያን ልትደራጅ የሚገባ ቢሆንም ነገር ግን ሁሌም ቢሆን ይህ ድርጅት ለእውነተኛው የቤተ ክርስቲያን መሪ፤ ይኸውም ለየሱስ ሥልጣን የተገዛ መሆን ይኖርበታል፡፡

“ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ መሰረቷ ስለሆነ በእርሱ ላይ ተገንብታለች፡፡ ራስዋም ስለሆነ ትታዘዘዋለች፡፡ በሰው ላይ አትተማመንም፤ በሰው ቁጥጥር ሥርም አይደለችም፡፡ ብዙ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን የአደራ ሥልጣን ሲሰጣቸው ሌሎች ሰዎች ምን ማመንና ምን

ማድረግ እንዳለባቸው የማዘዝ ሥልጣን ያላቸው ይመስላቸዋል፡፡ እግዚአብሔር ይህን ዓይነት ሥልጣን አይፈቅድም፡፡ አዳኛችን 'ሁላችሁም ወንድማማቾች ናችሁ' ነው ያለው፡፡ ሁላችንም ለፈተና የተጋለጥን ስንሆን ስህተት መሥራታችን የማይቀር ነው፡፡ ለመሪነት በማንም ውሱን ፍጡር ላይ መተማመን አንችልም፡፡ የእምነት ዋስትናው የክርስቶስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መገኘት ነው፡፡ ደካሞች በዚህ ጽኑ የእምነት መሰረት ላይ መተማመን ይችላሉ፤ ብርቱ ነን ባዮች ግን የብርታታቸው መሰረት ክርስቶስ እንዲሆን ካላደረጉ ደካሞች ይሆናሉ፡፡" (የዘመናት ምኞት ገጽ 426-427)፡፡

*በክርስቶስ እንጂ በሌላ በማንኛውም አካል መመካት እንደሌለብን መማር የምንችለው እንዴት ነው?*

ሰኞ

## ታህሳስ 8

## የአገልጋዩ አመራር

የሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በነበረው አገልግሎት በተደጋጋሚ ያይባቸው የነበረው ክፉ የሥልጣን ቅናት ይረብሸው ነበር፡፡ ደቀ መዛሙርቱ ብርቱ የየሱስ መሪዎች የመሆን ስጋት ይታይባቸው ነበር (ማር. 9፡33-34፣ ሉቃ. 9፡46)፡፡ ደቀ መዛሙርት የጌታ ራት አብረው ይበሉ በነበረት ወቅት እንኳ ይህ የበላይነት ስሜት ሳይሰማቸው እንዳልቀረ መመልከት ይቻላል (ሉቃ. 22፡24)፡፡

የሱስ በአንድ ወቅት ለሕዝቡ በመንፈሳዊ መሪነት ስለሚሰጥ አገልግሎት የነበረውን አስተሳሰብ በግልጽ አስቀምጦ ነበር፡፡ የሱስ በማቴ. 20፡25-28 ከሰጠው ልባዊ ምክር ምን ዓይነት የመሪነት መርኅዎችን እንማራለን? ይህን መርኅ በሕይወታችን፣ በተለይ በቤተ ክርስቲያናችን ገልጠን ማሳየት የምንችለው እንዴት ነው?

"የሱስ በዚህ እጥር ምጥን ያለ መልእክቱ ሁለቱን ዓይነት የመሪነት ምሳሌዎች ያቀርብልናል፡፡ የመጀመሪያው የሮማውያንን አገዛዝን ጽንሰ ሀሳብ የተከተለ ነበር፡፡ በዚህ አሠራር ልሒቃን እንደ ሥልጣን ተዋረዳቸው የበላይ ይሆናሉ፡፡ የበታቾቻቸው ሲጠሩት አቤት፣ ሲልኩት ወዴት ዓይነት የተገዢነት መንፈስ ይታዘዟቸዋል፡፡ በእነርሱ ላይ ውሳኔ የመወሰን ሙሉ ሥልጣን አላቸው፡፡ የሱስ 'በእናንተ መካከል ግን እንዲህ መሆን የለበትም' ሲል ይህን ዓይነቱን ገዢነት በግልጽ ተቃውሞአል፡፡ በዚህ ፋንታ የሱስ እነርሱ ከለመዱት ውጪ የሆነውን በዓይነቱ አዲስና አስደማሚ የኃላፊነት አርአያነትን በጥንቃቄ አቀረበላቸው፡፡"*Darius Jankiewicz, "Serving Like Jesus: Authority in God's Church," Adventist Review, March 13, 2014, p. 18.*

የሱስ በዚህ ታሪክ ያቀረበው የሥልጣን ጽንሰ ሃሳብ በሁለት ቁልፍ ቃላት ላይ የተመሰረተ ነው፡ አገልጋይ (ዲያኮኖስ) እና ባሪያ (ዱሎስ)፡፡ በአንዳንድ ትርጉሞች የመጀመሪያው ቃል “የወንጌል አገልጋይ” በሚል ተደጋግሞ የቀረበ ሲሆን ሁለተኛውም እንዲሁ “አገልጋይ” በሚል ይታወቃል፡፡ ሁለቱም ቃላት የሱስ ለማለት የፈለገውን በሚገባ የገለጹለት አይመስሉም፡፡ ምንም እንኳ እርሱ ማንኛውንም ምድራዊ የአገዛዝ መዋቅር የማስወገድ ምኞት ባይኖረውም፤ ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከሁሉም በፊት የእግዚአብሔር ሕዝቦች አገልጋይና ባሮች ሊሆኑ ይገባል ለሚለው ነጥብ አጽንኦት መስጠት ፈልጓል፡፡ የኃይማኖት መሪዎች የያዙት ኃላፊነት በሕዝቡ ላይ ገዥነታቸውን የሚለማመዱበት፣ ከሁሉም ከፍ ብለው የሚታዩበት ወይም ግላዊ ክብርና ዝና የሚሰጣቸው አይደለም፡፡ “ክርስቶስ በልዩ መርኅዎች ላይ የተመሰረተ መንግሥት በማቋቋም ላይ ነበር፡፡ ሰዎችን የጠራቸው ለሥልጣን ሳይሆን አገልግሎት እንዲሰጡና ብርቱዎቹ የደካሞቹን ችግር እንዲያቃልሉ ነው፡፡ ሥልጣን፣ ማዕረግ፣ ልዩ ችሎታ ወይም የትምህርት ዝግጅት የነበረው ሁሉ ሰዎችን የማገልገል ከፍተኛ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡” (የዘመናት ምኞት፡ ገጽ 566)፡፡

*ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዮሐ. 13፡1-20፡፡ የሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠው ምን ዓይነት የአመራር ምሳሌ ነበር? የሱስ በዚህ ጥቅስ በተጨማሪ ሊያስተምረን የፈለገው ነገር ምን ነበር? ከሌሎች ጋር በሚኖረን እያንዳንዱ ግንኙነት እነዚህን መርኅዎች ገልጠን ማሳየት የምንችለው እንዴት ነው?*

ማክሰኞ **ታህሳስ 9**

## የቤተ ክርስቲያንን ኅብረት ጠብቆ ማቆየት

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ 2ጢሞቴ. 2፡15፣ ቲቶ1፡9፡፡ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስና ለቲቶ በሰጠው ምክረ ሃሳብ ታማኝ የሆነው የቤተ ክርስቲያን መሪና ሽማግሌ ኃላፊነት ምንድን ነው?

________________________________________

________________________________________

መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ኃይማኖታዊ አስተምህሮ በንጽህና የመያዝን አስፈላጊነት አስመልክቶ ጳውሎስ የሚሰጠውን አጽንኦት ልብ ይሏል፡፡ ይህ ለአንድነት ወሳኝ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ የእኛ ኃይማኖታዊ አስተምህሮዎች ከማንኛውም ነገር በላይ ቤተ ክርስቲያናችን አንድነት እንዲኖራት የሚያደርጉ ለመሆናቸው ማንም ሊመሰክር ይችላል፡፡ ከተለያዩ የሕይወት መስመሮች፣ ባህሎችና ታሪካዊ ዳራዎች የመጣን እንደመሆኑ፤ በክርስቶስ ላይ ያለን አንድነት እንደ አድቬንቲስት ክርስቶስ በሰጠን እውነት ላይ ባለን መረዳት የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ነገር ግን በአስተምህሮዎቹ

ግራ የምንጋባ ከሆነ ውዥንብርና መለያየት መምጣቱ አይቀሬ ነው--በተለይ ወደ መጨረሻው በተቃረብን ቁጥር፡፡

“በእግዚአብሔር ፊት እንዲሁም በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ ባለው በክርስቶስ ኢየሱስ ፊት፣ መገለጡንና መንግሥቱን በማሰብ ይህን ዐደራ እልሃለሁ፤ ቃሉን ስበክ፤ ጊዜው ቢመችም ባይመችም ዝግጁ ሁን፤ በታላቅ ትዕግሥትና ማስተማር አቅና፤ ገሥጽ፤ አበረታታም፡፡ ምክንያቱም ሰዎች ትክክለኛ የሆነውን ትምህርት የማይቀበሉበት ጊዜ ይመጣል ከዚህ ይልቅ ለገዛ ምኞቶቻቸው የሚስማማውን፣ የሚያሳክክ ጆሮአቸው ሊሰማ የሚፈልገውን እንዲነግሯቸው በዙሪያቸው ብዙ አስተማሪዎችን ይሰበስባሉ፡፡ እውነትን ከመስማት ጆሮአቸውን ይመልሳሉ፤ ወደ ተረትም ዘወር ይላሉ፡፡” (2ጢሞቴ. 4፡1-4)፡፡

ጳውሎስ በእነዚህ ቃላት ትኩረቱን በየሱስ ዳግም ምጽአትና በፍርድ ቀን ላይ ያደርጋል፡፡ ሐዋርያው ይህን አስፈላጊ ምክረ ሀሳብ ለጢሞቴዎስ በመለገስ በእግዚአብሔር የተሰጠውን ሥልጣን በሙሉ (1ጢሞቴ. 1፡1) ጥቅም ላይ ሲያውል ይታያል፡፡ በመጨረሻዎቹ ቀናት የሐሰት አስተምህሮን ተከትሎ ቅንጡነትና የግብረገብ ውድቀት ቢነግሥም የጢሞቴዎስ ኃላፊነት የእግዚአብሔርን ቃል መስበክ ነው፡፡ እርሱ የተጠራበት አገልግሎት ይኸው ነውና፡፡

ጢሞቴዎስ የማስተማር የአገልግሎቱ አካል የሆነው ማቅናት፣ መገሰጽና ማበረታታት የኃላፊነት ድርሻው ነው፡፡ እነዚህ ገላጭ ግሦች በአምላካዊው ቃል የተሰጡ መመሪያዎች ናቸው (2ጢሞቴ. 3፡16)፡፡ የጢሞቴዎስ ሥራ በይቅርታና በትዕግሥት ክትትል ማድረግ፣ ማስተማርና በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚያገኘውን በተግባር መግለጽ ነው፡፡ ርኅራኄ የጎደለውና የከረረ ግሳጼ ኃጢአተኛውን ወደ ክርስቶስ የማምጣት ዕድሉ እምብዛም ነው፡፡ ጳውሎስ የጻፈውን መልእክት በመንፈስ ቅዱስ ምሪት በመከተልና የአገልጋዩን አመራር አተያይ በመያዝ--ጢሞቴዎስ ቤተ ክርስቲያንን በብርቱ ኃይል የሚያዋህድ አቅም ይሆናል፡፡

የቤተ ክርስቲያን መሪዎቻችን የቤተ ክርስቲያንን ኅብረት ጠብቀው ማቆየት እንዲችሉ በተጨባጭ እገዛ ልናደርግ የምንችልባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? በቤተ ክርስቲያን ጠብ እና አለመግባባት ቢኖርም እንኳ ከመለያየት በተቃራኒ የአንድነት ኃይል ለመሆናችን እርግጠኞች መሆን የምንችለው እንዴት ነው?

ረቡዕ

ታህሳስ 10

## የቤተ ክርስቲያን ደንብና ሥርዓት

ከቤተ ክርስቲያን ድርጅት አንገብጋቢ ጉዳዮች አንዱ ከደንብና ሥርዓት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ ደንብና ሥርዓት የቤተ ክርስቲያንን አንድነት አስጠብቆ የሚያቆይበት አካሄድ አንዳንዴ በቀላሉ በተሳሳተ መንገድ የሚስተዋልና የሚያስቆጣ ርዕሰ ጉዳይ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው አተያይ ቤተ ክርስቲያናዊው ደንብና ሥርዓት በሁለት አስፈላጊ ጉዳዮች ላይ ማዕከል ያደርጋል፡ --የኃይማኖታዊ አስተምህሮን ንጽህና ማስጠበቅ እና የቤተ ክርስቲያንን ሕይወት ንጽህና እና ተግባር ማስጠበቅ፡፡

በተለይ በመጨረሻው ጊዜ ሊቀሰቀስ ከሚችል ክህደትና የሐሰት አስተምህሮ አኳያ የመጽሐፍ ቅዱስን ንጽሕና ጠብቆ ስለ ማቆየት አስፈላጊነት--አዲስ ኪዳን የሚለንን ቀደም ባለው ትምህርት ተመልክተናል፡፡ በተመሳሳይ ማኅበረሰቡን ከብልሹ ግብረገብ፣ ታማኝ ካለመሆንና ከሕገወጥነት በመጠበቅ መልካም ስም እና ዝና እንደሰፈነ ማቆየት ይቻላል፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው እንደመሆናቸው "ለመገሰጽ፣ ለማቅናት፣ በጽድቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ" (2ጢሞቴ. 3፡16) በሚል ተነግሮናል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ማቴ. 16፡19፣ 18፡15-20፡፡ እንከን ያለባቸውን ወገኖች ደንብና ሥርዓት ስለ ማስያዝና ስለ መገሰጽ የሱስ ለቤተ ክርስቲያን የሰጣቸው መርኅዎች ምንድን ናቸው?

---

---

የደንብና ሥርዓት ጽንሰ ሃሳብን እንዲሁም በመንፈሳዊውና ሥነ ምግባራዊው ሕይወታችን አንዳችን የሌላችን ጠባቂ መሆናችንን መጽሐፍ ቅዱስ ይደግፋል፡፡ በእርግጥ ቤተ ክርስቲያን ተለይታ ከምትታወቅባቸው ምልክቶች አንዱ ቅድስናዋ ወይም ከዓለም መለየቷ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ግብረገብ በጎደላቸው አስቸጋሪ ባህሪያት ላይ እርምጃ እንድትወስድ የተገደደችባቸውን አያሌ ምሳሌዎች በመጽሐፍ ቅዱስ እናገኛለን፡፡ የሥነ ምግባር እሴቶች በቤተ ክርስቲያን ተጠብቀው መኖራቸው የግድ ነው፡፡

በቤተ ክርስቲያን አስቸጋሪ ሁኔታ ሲከሰት ልንከተላቸው የሚገቡ ምን ዓይነት መርኅዎችን ጥቅሶቹ ይዘዋል፡ ማቴ. 7፡1-5፣ ገላ. 6፡1-2፡፡

---

---

በቤተ ክርስቲያን ደንብና ሥርዓት ስለ ማስከበር አስፈላጊነት የተሰጠውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ መካድ አንችልም፡፡ ያለዚህ ለአምላካዊው ቃል ታማኝ መሆን አይቻለንም፡፡ አብዛኞቹ እነዚህ ግሳጼዎች በውስጣቸው የያዟቸውን ከጥፋት የመመለስ ብቃት ልብ ይሏል፡፡ ግሳጼ በተቻለ መጠን ከጥፋት የሚመልስ ሊሆን ይገባል፡፡ ደግሞም እኛ ሁላችን ኃጢአተኞች መሆናችንንና ጸጋው በተመሳሳይ ለሁላችንም እንደሚያስፈልግ ማስታወስ አለብን፡፡ ደንብና ሥርዓት ማስከበርን በኃላፊነት ስንመራ በትህትና ብቻ ሳይሆን የገዛ ስሜታችንንም በመቆጣጠር ሊሆን ይገባል፡፡

በስህተት ከወደቁ ወገኖች ጋር ባለን አግባብ ከቅጣት ይልቅ ከጥፋት የመመለስ መንፈስን መማር የምንችለው እንዴት ነው?

## ሐሙስ

## ታህሳስ 11

## ለተልዕኮ ማደራጀት

እንደ ቤተ ክርስቲያን ስለ መደራጀታችንና ወደ ሕዝቦች ለመድረስ የተልዕኮ ኅብረት ስለ መፍጠራችን በዚህ ሩብ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን ተመልክተናል፡፡ እኛ ቤተ ክርስቲያን እንጂ አንዳችን የምናምንበትን ለሌላው እያካፈልን ሀሳብ የምንለዋወጥበት የሰፈር ማኅበር ወይም እድር አካል አይደለንም (በእርግጥ ያ አስፈላጊ ቢሆንም)። እኛ ራሳችን እንድንወደው የተጠራንበትን እውነት ለዓለም እንድናካፍል እነሆ በአንድነት ተሰባስበናል፡፡

የሱስ ደቀ መዛሙርት ለዓለም ያላቸውን ተልዕኮ አስመልክቶ በማቴ. 28፡18-20 የመጨረሻውን መመሪያ ሰጥቶአል፡፡ የሱስ በትእዛዛቱ ጥቅም ላይ ያዋላቸውን ቁልፍ ቃላት ለይተው ለመገንዘብ ይሞክሩ፡፡ እነዚህ ቃላት ለዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን ምን ዓይነት አንደምታ አላቸው?

---

የሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠው ታላቁ ተልዕኮ አራት ቁልፍ ግሶችን አካትቷል፡--ሂዱ፣ ደቀ መዝሙሬ አድርጓቸው፣ አጥምቁ፣ አስተምሩ፡፡ መልእክቱ በተጻፈበት የግሪክ ሥርዓተ ቋንቋ ግስ መሰረት--ዋንኛው ግስ ደቀ መዝሙር ማድረግ ሲሆን ሌሎቹ ሦስት ግሶች ይህ እንዴት ተግባራዊ መሆን እንደሚችል ያሳያሉ፡፡ አማኞች ወደ ሕዝቦች

ሁሉ ሄደው ወንጌልን ሲሰብኩ፣ ሲያጠምቁና የሱስ የተናገረውን ሲያስተምሩ--ያኔ ደቀ መዛሙርት የማፍራት ሥራ ይሠራል፡፡

ቤተ ክርስቲያን ለዚህ ተልዕኮ ምላሽ ስትሰጥ የእግዚአብሔር መንግሥት እየተስፋፋ ይሄዳል፡፡ አያሌ ነገዶችና ቋንቋዎችም የሱስ ክርስቶስን አዳኛቸው አድርገው የተቀበሉ ወገኖችን ይቀላቀላሉ፡፡ ሕዝቦች የየሱስን ትእዛዛት በመጠበቅ ሲጠመቁና ትምህርቱ ላይ በቂ ትኩረት ሲያደርጉ በዓይነቱ አዲስና ዓለማቀፋዊ ይዘት ያለው ቤተሰብ ይፈጠራል፡ ፡ እነዚህ አዳዲስ ደቀ መዛሙርት ሌሎች ደቀ መዛሙርትን በማፍራት የሱስ በየቀኑ አብሯቸው የመሆኑን እውነታ ያረጋግጣሉ፡፡ የየሱስ አብሮነት የእግዚአብሔር መገኛ ተስፋ መገለጫ ነው፡፡ የማቴዎስ ወንጌል የየሱስ ክርስቶስን መወለድ "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር" (ማቴ. 1፡23) በማለት ይጀምርና የሱስ እስከ ዳግም ምጽአቱ አብሮን እንደሚሆን በሰጠን ተስፋ ይጨርሳል፡፡

*"ደቀ መዛሙርቱ ወደፊት የሚጠብቃቸውን ሥራ ቀላል አድርጎ ባይነግራቸውም... አብሮአቸው እንዲሚሆን ግን አረጋግጦላቸው ነበር፡፡ በእምነት እስከወጡ ድረስ በኃያሉ ጌታ ጥላ ስር መንቀሳቀስ ነበረባቸው፡፡ የመላእክት አለቃና የሰማይ ሰራዊት አዛዥ የሆነው ጌታ ጀግናና ብርቱ እንዲሆኑ አደፋፈራቸው፡፡ ለሥራቸው ግስጋሴ አስፈላጊውን ሁሉ በመስጠት የስኬታቸውን ኃላፊነት እርሱ ራሱ ወሰደ፡፡ የእርሱን ቃል እስከታዘዙና ከእርሱ ጋር ትስስር ፈጥረው እስከሠሩ ድረስ ውድቀት አያገኛቸውም"*— Ellen G. White, The Acts of the Apostles, p. 29.

የሱስ ዳግም እስኪገለጥ ከሕዝቡ ጋር አብሮ እንደሚሆን በሰጠው ተስፋ ትርጉም ላይ ጥልቅ ምልከታ ያድርጉ፡፡ በየሱስ የተሰጠንን ተልዕኮ ከግብ ለማድረስ ባለን መሻት የዚህ ተስፋ ሐቅ ተጽእኖ ሊያሳድርብን የሚችለው እንዴት ነው?

## ዓርብ — ታህሳስ 12

**ተጨማሪ ሀሳብ**፡ *Ellen G. White, "Individual Responsibility and Christian Unity," pp. 485-505, in Testimonies to Ministers and Gospel Workers; "Unity in Diversity," pp. 483-485, and "Church Discipline," pp. 498-503, in Gospel Workers. Read the articles "Church," pp. 707-710, and "Church Organization," pp. 712-714, in The Ellen G. White Encyclopedia.*

"የመልካም ግንኙነት መርኅዎች ቤተ ክርስቲያንን ጨምሮ በሁሉም ማኅበረሰባዊ ገጽታዎች ላይ ገጣሚ እንዲሆኑ ይደረጋሉ፡፡ ሆኖም የቤተ ክርስቲያን መሪ ግን ከመሪ በላይ ኃላፊነት ይጠበቅበታል፡፡ አገልጋይ መሆንም እንዲሁ ይጠበቅበታል፡፡

አንድ ሰው በተመሳሳይ ወቅት የመሪ እና አገልጋይ ባህሪ መላበስ የሚችለው እንዴት ነው? የመሪ ኃላፊነት ማዕረግና ከበሬታ የለውምን? ትእዛዝ አይሰጥም? ሌሎች እንዲታዘዙትስ አይጠብቅም? ነገሩ እንዲህ ከሆነ ትእዛዝ እየተቀበለና መሻታቸውን እያሟላ ዝቅ ያለውን የአገልጋይ ስፍራ መውሰድ የሚችለው እንዴት ነው?

"እርስ በርሳቸው የሚጻረሩ ለሚመስሉ ነጥቦች የመፍትሔ ሀሳብ ለማግኘት ወደ የሱስ መመልከታችን የግድ ይሆናል፡፡ እርሱ የአገልጋይነትን መርኅ በከፍተኛ ሁኔታ ወክሎአል፡፡ መላው የእርሱ ሕይወት የአገልጋይነት ነበር፡፡ በተመሳሳይ ዓለም አይታው የማታውቅ ታላቅ መሪም ነበር፡፡"—G. Arthur Keough, Our Church Today: What It Is and Can Be (Washington, D.C., and Nashville: Review and Herald, 1980), p. 106.

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

1. አገልጋይንና መሪን በአንድ ያቀፈው ጽንሰ ሀሳብ ላይ ጠለቅ ያለ ምልከታ አድርጉ፡፡ ለዚህ ጽንሰ ሃሳብ ምሳሌ መሆን የሚችል ነገር ከመንፈሳዊው ውጪ ከሆነው ዓለም ማግኘት ይቻላል?

2. ጥቅሱን በድጋሚ ያንብቡ፡ ማቴ. 20፡25-28፡፡ እግዚአብሔር ትልቅ (ማቴ. 20፡26) የሚለውን ቃል ትርጉም ከዓለማዊው ፍቺ በተቃራኒ እንዴት እንደሚያስተውለው ይህ ምን ይነግረናል?

3. ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ኃላፊነት አንዱ አንድነትን ጠብቆ ማቆየት ከሆነ፤ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሥጋ ለባሽነታቸው ፍጹም ምሳሌ ከመሆን ሲያግዳቸውና ይህን ማድረግ ሲሳናቸው ምን ማድረግ ይኖርብናል?

4. በስህተት የወደቁትን ወገኖች እንዲሁም የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓትና ደንብ የምናስከብረው በትህትና መንፈስና በፍቅር መሆኑን ማስተዋል በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? በእንዲህ ያለው ሂደት ማቴ. 7፡12 ሁሌም በአእምሮአችን ቀዳሚውን ስፍራ ሊይዝ የሚገባው ለምንድን ነው?

**ማጠቃለያ**፡ መልካም የቤተ ክርስቲያን አወቃቀር ለቤተ ክርስቲያን ተልዕኮና ለአማኞች አንድነት ወሳኝ ነው፡፡ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ መሆኑ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚመሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የእርሱን ምሳሌ መከተል ይኖርባቸዋል፡፡ አንድነት ተጠብቆ መቆየት የሚችለው የእግዚአብሔርን ቃል በታማኝነት በማስተማርና ለቃሉ ታማኝ ሆኖ በመኖር ነው፡፡

# 13ኛ ትምህርት ከታህሣሥ 13 - 19

## አንድነትን ወደ ቀደመ ንጽህናው መመለስ

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ዮሐ. 14፡1–3 ኢሳ. 11፡1–10፣ ራእ. 21፡1–5፣ 1ተሰ. 4፡13–18፣ ራእ. 22፡1–5፣ ኢሳ. 35፡4–10፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ :-** "እኛ ግን ጽድቅ የሚኖርበትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር በተስፋ ቃሉ መሰረት እንጠባበቃለን" (2ጴጥ. 3፡13)፡፡

አብልጠው ልብ ከሚያሞቁ የመጽሐፍ ቅዱስ ተስፋዎች አንዱ የየሱስ ዳግም ምጽአት ነው፡፡ የተስፋችን መሰረት ዳግም ምጽአቱ እንደመሆኑ ያለ እርሱ መና ሆነን በቀረን ነበር፡፡ ክርስቶስ በሰማያት ደመና ዳግም ሲገለጥ በአንድ ወቅት ትርጉም ይሰጥ የነበረው ምድራዊው፣ ሰው ሠራሹና ጊዜያዊው ሁሉ ተጠራርጎ ይነጉዳል፡፡ በሰማይ አንድ ሺህ ዓመት ከነገሥን በኋላ ይህች በጦርነት አረር፣ በረሃብ፣ በበሽታና በአሳዛኝ ሁኔታ ስትማቅቅ የኖረች ምድር በእሳት ትነጻለች፡፡ በመጨረሻ በበጉ ደም የተዋጁ ከጌታቸው ጋር እንዲሁም እርስ በርስ ዳግም ይገናኛሉ፡፡

የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ተስፋ የአዲስ ኪዳን አበይት ርዕሰ ጉዳይ እንደመሆኑ ክርስቲያኖች የዚህን ተስፋ ፍጻሜ ለማየት አብልጠው ሲጓጉ ኖረዋል፡፡ እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት እኛም ዳግም ምጽአቱን እንናፍቃን፡፡ ለነገሩ መጠሪያ ሰማችን በራሱ ይህን ተስፋ ያውጃል፡፡

በሩብ ዓመቱ የመጨረሻ ትምህርታችን ወደዚህ ተስፋ እንመለከታለን፤ ለክርስትና አንድነት ያለውን አንደምታም እንፈትሻለን፡፡ በክርስቶስ ያለን አንድነት በገዛ ራሳችን ሰብዓዊ ውሱንነትና ደካማነት ተደጋግሞ ፈተና ሲገጥመው ይስተዋላል፡፡ ያን ጊዜ ግን ለመከፋፈላችን መፍትሔ ፍለጋ መሮጥ አያስፈልገንም ምክንያቱም መከፋፈል አይኖርም፡፡ መጨረሻው ደርሶ ዳግም ምጽአቱ ገቢራዊ ሲሆን ከጌታ ጋር አንድ እንሆናለን፤ ዳግመኛ አንድነት ፈጥረን አንድ ቤተሰብ እንሆናለን፡፡

እሁድ

ታህሳስ 14

# የክርስቶስ ዳግም ምጽአት እውነታ

ስለ የሱስ ዳግም ምጽአት ከሚናገሩ ዝነኛ ጥቅሶች መካከል ዮሐ. 14፥1-3-- አንዱ ነው፡፡ የዳኑት ወገኖች በአዲሲቱ ምድር ስለሚኖሩት ሕይወት ተስፋው ምን ይነግሮታል?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

የቀደሙት ክርስቲያኖች የክርስቶስን ዳግም ምጽአት "የተባረከ ተስፋችን" (ቲቶ 2፥13) የሚል ከፍ ያለ ምልከታ ሰጥተውታል፡፡ ዳግም ምጽአቱ የክርስትና መንፈሳዊ ጉዞ ዓላማና ግብ በመሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ የተሰጡት ሁሉም ዓይነት ትንቢቶችና ተስፋዎች በዚህ ወቅት ፍጻሜ እንደሚያገኙ ጠብቀዋል፡፡ ክርስቶስን የሚወዱ ሁሉ ከእርሱ ጋር ፊት ለፊት ኅብረት የሚያደርጉባትን ያቺን ዕለት አሻግረው በተስፋ ይጠባበቃሉ፡፡ በጥቅሶቹ የቀረቡት ከእርሱ አንደበት የወጡ ቃላት ከየሱስ ጋር ብቻ ሳይሆን እርስ በርሳችን ጭምር የምንጋራቸውን የቅርብ ግንኙነቶችና ወዳጅነቶች ያመለክታሉ፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ትንቢቱ ፍጻሜ ማረጋገጫ ስለሚሰጠን ክርስቲያኖች በዚህ ተስፋ ያምናሉ፡፡ ማረጋገጫው ደግሞ የሱስ "ዳግመኛ እመጣለሁ" (ዮሐ. 14፥3) ብሎ የነገረን እኛም አምነን የምንቀበለው ነው፡፡ የክርስቶስ የመጀመሪያ ምጽአት ትንቢት አስቀድሞ እንደተነገረ ሁሉ ዳግም ምጽአቱም በራሱ በብሉይ ኪዳን ጭምር ተነግሮአል፡፡ በክብር የሚገለጠው መሲህ ለኃጢአት ፍጻሜ ያመጣል ሲል በምድር ላይ የውሃ ጥፋት ከመድረሱ አስቀድሞ እግዚአብሔር ከእምነት አባቶች አንዱ ለነበረው ሄኖክ ነግሮት ነበር፡፡ "'እነሆ፤ ጌታ ከእልፍ አእላፋት ቅዱሳኑ ጋር ይመጣል፤ ይህም በሰው ሁሉ ላይ ለመፍረድ እንዲሁም ዐመጻኞችን ሁሉ በክፋት መንገድ በሠሩት የዐመጽ ሥራና በክፋት በእርሱ ላይ ስለ ተናገሩት የስድብ ቃል ሁሉ አጥፊነታቸውን ይፋ ለማድረግ ነው' " (ይሁዳ 14-15)፡፡

የሱስ ወደዚህ ምድር ከመምጣቱ ከአንድ ሺ ዓመት በፊት መሲህ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በአንድነት ለመሰብሰብ እንደሚመጣ ንጉሥ ዳዊት በትንቢት ተናግሮ ነበር፡ "አምላካችን ይመጣል፤ ዝም አይልም፤ የሚባላ እሳት በፊቱ፣ የሚያስፈራ ዐውሎ ነፋስም በዙሪያው አለ፡፡ በሕዝቡ ይፈርድ ዘንድ፣ በላይ ያለውን ሰማይንና ምድርን እንዲህ ብሎ ይጠራል፤ 'በመሥዋዕት ከእኔ ጋር ኪዳን የገቡትን፣ ቅዱሳኔን ወደ እኔ ሰበሰብኳው' " (መዝ 50፥3-5)፡፡

የየሱስ ሁለተኛው ምጽአት ከመጀመሪያው ጋር በቅርብ የተሳሰረ ነው፡፡ በውልደቱና ምድራዊ አገልግሎቱ ዙሪያ የተሰጡ ትንቢቶች (ዘፍ. 3:15፣ ሚክ. 5:2፣ ኢሳ. 11:1፣ ዳን. 9:25-26) የዳግም ምጽአቱ ተስፋችንና የመታመናችን መሰረት ናቸው፡፡ ክርስቶስ "ኃጢአትን ለማስወገድ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተገልጦአል... ክርስቶስ የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ለመሸከም፤ እንዲሁ አንድ ጊዜ መሥዋዕት ሆኖአል፤ ሁለተኛ ጊዜም ይገለጣል፤ ይህም ለሚጠባበቁት ድነትን ለማምጣት እንጂ ኃጢአትን ለመሸከም አይደለም" (ዕብ. 9፡26፣28)፡፡

ከዳግም ምጽአቱ የተስፋ ቃል ዛሬም ቢሆን ተስፋና መጽናናት ማግኘት የሚችሉባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው?

## ሰኞ

## ታህሳስ 15

## ወደ ቀደመው ንጽህና ስለ መመለስ የተሰጠ የተስፋ ቃል

ጥቅሱን ያንብቡ፡ ኢሳ. 11፡1-10፡፡ ለእስራኤል የተሰጠው የተስፋ ቃል ምንድን ነው? ስለ ዳኑት ዘላለማዊ መኖሪያስ ምን ይላል?

---

---

መጽሐፍ ቅዱስ የምድርን አፈጣጠር ትርክት በመንገር ይጀምራል (ዘፍ. 1፣2)፡፡ ትርክቱ ለመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን አዳምና ሔዋን በዐደራ ስለ ተሰጠችው ውብ እና ስምሙ ዓለም በቂ መግለጫ ይሰጣል፡፡ ምድር ለሰብዓዊው ዘር መኖሪያ እንድትሆን በእግዚአብሔር የተፈጠረች ፍጹም ስፍራ ነበረች፡፡ ሁለቱ የመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻ ምዕራፎችም እንዲሁ እግዚአብሔር ለተቤዠው ሰብዓዊ ዘር ፍጹም የሆነ መኖሪያ እያዘጋጀ መሆኑን ቢናገሩም (ራእ. 21-22) ነገር ግን በዚህ ወቅት ገቢራዊ የሚሆነው ምድርን ከኃጢአት ውድመት ወደ ቀደመ ንጽህናዋ የመመለስና ዳግመኛ የመፍጠር ዓይነት ሥራ ይሆናል፡፡

ይህ ለዳኑ ወገኖች የተጋጀ ዘላለማዊ መኖሪያ በተጨባጭ ገቢራዊ እንደሚሆን አያሌ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በይፋ ይናገራሉ፡፡ የዳኑት በሚኖራቸው አዲስ ሕይወት፣ የሚያዩ፣ የሚሰሙ፣ የሚያሸቱ፣ የሚዳስሱ እንዲሁም ስሜት የሚኖራቸውና የአዳዲስ ተሞክሮዎች ባለቤት ይሆናሉ፡፡ ትንቢተ ኢሳይያስ የመሲህን ምጽአት ተከትሎ ገቢራዊ ስለሚሆነው የአዲስ ዘመን ጅማሮ ውብ የሆኑ መልእክቶችን አስፍሯል፡፡ ለአመጻ ፍጻሜ በማምጣት ዘላለማዊ ሰላም ያሰፍናል፡፡ የእግዚአብሔር በአዲሲቱ ምድር መንገሥ ዩኒቨርስ አቀፍ ለዛና መዋሃድ ያመጣል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 21፡1-5፡፡ ይህን አዲስ ውህደት ተከትሎ ለዘላለም የሚወገደው ምንድን ነው?

የዳኑት ምን እንደሚጠብቃቸው አስመልክቶ ኤለን ኋይት የሚከተለውን ጽፋለች፡ “ዘላለማዊዎቹ ዓመታት በተዟዟሩ ቁጥር ስለ እግዚአብሔርና ስለ ክርስቶስ ታላቅና የከበረ ማንነት በጥልቅ መግለጣቸውን ይቀጥላሉ፡፡ ዕውቀት ታዳጊ እንደመሆኑ ፍቅር፣ አክብሮትና ደስታም በተመሳሳይ እየተስፋፉና እየበለጸጉ የሚሄዱ ናቸው፡፡ ሰዎች አብልጠው ስለ እግዚአብሔር በተማሩ ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ የባህሪው አድናቂ ይሆናሉ፡፡ የሱስ የቤዛነቱን ምስጢርና ከሰይጣን ጋር የተደረገውን ታላቅ ውዝግብ ውጤት በሙላት ሲገልጥላቸው--የተዋጁት ወገኖች ልብ በብርቱ አምልኮና ስግደት መምታት ይጀምራል፤ ከዚያም የወርቅ በገናቸውን አንስተው በእነዚያ ጽኑ እጆቻቸው መጫወት ይጀምራሉ፡፡ የበገናዎቹን ድምጸት ተከትሎ አሥር ሺ ጊዜ አሥር ሺ ኅብረ ድምጾች ይደጣሉ፡፡”—Ellen G. White, The Story of Redemption, pp. 432, 433.

*ዛሬም በዚህ ምድር የእግዚአብሔርን ጸባይ የምናስተውልባቸው መንገዶች የተኞቹ ናቸው? ከሌሎች ጋር ለዛ ያለው ስምምነትና አንድነት መፍጠር ዛሬም ቢሆን አምላካዊውን ጸባይና ተፈጥሮ የሚገልጠው እንዴት ነው?*

## ማክሰኞ ታህሳስ 16

## ትንሳኤ እና ወደ ቀድሞ ንጽህና የተመለሱ ግንኙነቶች

የክርስቶስ ዳግም ምጽአት የተስፋ ቃል ከቤተ ክርስቲያን የቀደሙ ቀናት አንስቶ ምናልባትም ከማንኛውም ነገር በላቀ የእግዚአብሔር ታማኝ ሕዝቦች ልብ መጽናኛ ሆኖ ኖሮአል--በተለይ በፈተና ወቅት፡፡ አማኞች የትኛውንም ዓይነት አስፈሪ ትግል፣ መራር ሐዘንና ሥቃይ ቢጋፈጡም--የክርስቶስ ዳግም ምጽአት የተስፋ ቃል እና መገለጡ የያዛቸው አስደናቂ ተውህቦዎች ነበሯቸው፡፡
በሚከተሉት ጥቅሶች ምን ዓይነት የተስፋ ቃሎች ተካተዋል--1ተሰ. 4፡13-18? ወደ ቀድሞ ንጽሕናቸው ስለ ተመለሱ ግንኙነቶችስ ምን ይላል?

የክርስቶስ ዳግም ምጽአት መላውን ሰብዓዊ ዘር በጥልቅ ይነካል፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መቋቋም አንዱ አስፈላጊ ገጽታ የተመረጡትን በአንድ መሰብሰብ ነው፡

"'መላእክቱንም ከታላቅ የመለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፤ እነርሱም ምርጦቹን ከአራቱም ነፋሳት፣ ከሰማያት ከአንዱ ዳርቻ ወደ ሌላው ዳርቻ ይሰበስባሉ።' " ማቴ. 24፡31)። በዚህ የመሰብሰብ ወቅት የሞቱ ጻድቃን በትንሣኤ የማይሞተውን አካል ይወስዳሉ (1ቆሮ. 15፡52-53)፤ "በክርስቶስ የሞቱም አስቀድመው ይነሳሉ" (1ተሰ. 4፡16)። ይህ ሁላችንም ስንጠባበቀው የኖርነው ክስተት ነው። የትንሣኤ ባለቤት የሆኑ ሁሉ የእነርሱን መገኘትና ፍቅራቸውን ሲናፍቁ ከቆዩ ወገኖች ጋር ዳግም ይገናኛሉ። ጳውሎስ ይህን አስደናቂ ሁኔታ እንዲህ በሚሉ ቃላት ያወድሰዋል፡ " 'ሞት ሆይ፤ ድል መንሳትህ የት አለ? ሞት ሆይ፤ መንደፊያህስ የት አለ?' " (1ቆሮ. 15፡55)።

በበሽታ ማቅቆና መንምኖ፣ በዕድሜ ብዛት ገርጅፎና ጃጅቶ ወይም ትክክለኛ ገጽታውን አጥቶ ወደ መቃብር የወረደ ሁሉ ያን የቀድሞ ሁኔታ እንደ ያዘ አይነሳም፡ ፡ ይልቁንም የኃጢአት ነቁጥ የሌለው አዲስ፣ የማይሞትና የማይበሰብስ ፍጹም አካል ለብሶ ይነሳል። የትንሣኤ ባለቤት የሆኑት ጻድቃን በፍጥረት ወቅት ታቅዶ የነበረውን ፍጹም አምላካዊ አምሳል እያንጸባረቁ የክርስቶስን ሥራ ፍጻሜ ይለማመዳሉ።

የየሱስ ዳግም ምጽአት ገቢራዊ ሲሆን የተዋጁት ጻድቃን በትንሣኤ ከመቃብር ሲነሱ፤ በምድር ላይ በሕይወት ያለነው የዳንን ወገኖች ደግሞ እንለወጥና ፍጹም የሆነውን አካል እንወስዳለን፡ "የሚጠፋው የማይጠፋውን፣ የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና" (1ቆሮ. 15፡53)። በመሆኑም እነዚህ ሁለት ቡድኖች--በትንሣኤ የተነሱት እና በሕይወት እያለን የተለወጥነው--"ጌታን በአየር ለመቀበል ከእርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ በዚህም መሠረት ለዘላለም ከጌታ ጋር እንኖራለን" (1ተሰ. 4፡17)።

*በምንኖርበት በሣይንስና ቴክኖሎጂ የረቀቀ ዘመን አንዳንድ ክርስቲያኖች ለማንኛውም ነገር ተፈጥሮአዊ ማብራሪያ ለማግኘት ይሞክራሉ--ታምራትን ጨምሮ። እኛን ሊያድን የሚችለው ከተፈጥሮ ውጪ ብቻ ያለው አምላካዊ ኃይል ስለ መሆኑ የትንሣኤው የተስፋ ቃል ምን ያስተምረናል?*

**ረቡዕ** **ታህሳስ 17**

## አዲስ ምድር ለተዋጁት

"'እነሆ፤ እኔ፣ አዲስ ሰማያትንና አዲስ ምድርን እፈጥራለሁ፤ ያፉት ነገሮች አይታሰቡም፤ አይታወሱም' " (ኢሳ. 65፡17)። ኢሳይያስ እና ዮሐንስ ተስፋ የተገባችውን የአዲሲቱን ምድር በራእይ አይተው ነበር።

ዮሐንስ የዳኑት ከተማ የሆነችውን አስገራሚዋን አዲሲቱን የሩሳሌም እንዴት እንደ ገለጻት ልብ ብለው ይመልከቱ--(ራእ. 21፡2፣ 9-12)። በዚህች ከተማ ስለሚሰፍነው

አንድነትና ውህደት ጥቅሶቹ በተዘዋዋሪ ምን ይላሉ?

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 22፡1-5፡፡ ከእግዚአብሔርና ከበጉ ዙፋን የሚወጣው የሕይወት ወንዝ ከሕይወት ዛፍ ጋር ተደምሮ--ሌሎቹ ሁለት የአዲሲቱ ከተማ አስፈላጊ ገጽታዎች ናቸው፡፡ በአዲሲቱ ምድር የሚኖራቸው ጥቅም ምን ይሆናል?

---

---

አዳም አምላካዊውን ሕግ በመጣሱ ወደ ሕይወት ዛፍ እንዳይደርስ ተከልክሎ የነበረ ቢሆንም (ዘፍ. 3፡22-24) አሁን ግን አጥቶት የነበረውን በክርስቶስ አማካይነት በአዲሲቱ የሩሳሌም ያገኛል፡፡ ድል ለሚነሱ ከተገባው ቃል አንዱ ወደ ሕይወት ዛፍ መድረስ ነው (ራእ. 2፡7)፡፡ ይህ ዛፍ በየወሩ እያፈራ ዐሥራ ሁለት ጊዜ ፍሬ መስጠቱ በአዲሲቱ ምድር “ ‘ከአንዱ ወር መባቻ እስከ ሌላው፣ እንዲሁም ከአንዱ ሰንበት እስከ ሌላው፣ የሰው ልጅ ሁሉ በፊቴ ሊሰግድ ይመጣል’” (ኢሳ. 66፡23) በማለት እግዚአብሔር የተናገረበትን ምክንያት የሚጠቁም ሊሆን ይችላል፡፡ “ሕዝቦች የሚፈወሱባቸው” በሚል የቀረበው ማመሳከሪያ በህዝቦች መካከል ያለውን ግድግዳ የማፍረስና ሰብዓዊውን ዘር ወደ ቀደመው ዓላማ የመመለስ አምላካዊ እቅድ የሚያሳይ ሲሆን ይኸውም--ለእግዚአብሔር ክብር በመስጠት ኅብረት የፈጠሩ ሕዝቦችን፣ ነገዶችንና ብሔሮችን ወደ አንድ የማይከፋፈል የቀደመ ቤተሰብ በመመለስ በአንድ ልብ እና በሰላም መኖር ነው፡፡

“ ‘ሕዝቦች የሚፈወሱባቸው’ የሚሉት ቃላት በሕዝቦች መካከል ያለውን የብሔርና ቋንቋ ግድግዳና መለያየት መወገድ የሚወክል ምሳሌያዊ አነጋገር ነው. . . የሕይወት ዛፍ ቅጠሎች በሕዝቦች መካከል ያሉ ቅሬታዎችን ይፈውሳሉ፡፡ ሕዝቦች እንደ እውነተኛ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አንድ ይሆናሉ እንጂ ‘አሕዛብ’ ተብለው አይጠሩም (21፡24-26)፡፡ ከአያሌ መቶ ዓመታት አስቀድሞ ሚክያስ የተነበየው አሁን ፍጻሜ ያገኛል፡ ‘እያንዳንዱ ሰው በገዛ ወይኑ ሥር፣ ከገዛ በለሱም ሥር ይቀመጣል፣ የሚያስፈራቸው አይኖርም’ (ሚክ. 4፡3-4፣ ኢሳ. 2፡4)፡፡ የተዋጀው ወገን በሕይወት ወንዝ ዳርቻ ከተከለው ወይንና በለስ ‘ባልንጀራውን ይጋብዛል’ (ዘካ. 3፡10)፡፡ የዛፉ ቅጠሎች ሰብዓዊውን ዘር ለዘመናት ሲከፋፍሉ የኖሩትን ሁሉንም ዓይነት የዘር፣ የብሔር፣ የነገድ ወይም የቋንቋ ደዌዎች የመፈወስ ኃይል አላቸው፡፡”—Ranko Stefanovic, Revelation of Jesus Christ: Commentary on the Book of Revelation, p. 593.

ሐሙስ

## ታህሳስ 18

# ሕይወት በአዲሲቱ ምድር

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ኢሳ. 35፡4-10፤ 65፡21-25፡፡ በዚያን ወቅት ሕይወት ከአሁኑ ተሞክሮ ምን ዓይነት የተለየ ገጽታ ይኖረዋል?

---

---

በኢሳይያስ መጽሐፍ አዲስ የሚሉ ቃላትን በተደጋጋሚ እናነባለን፡ "አዲስ ነገር" (ኢሳ. 42፡9፤ 48፡6)፤ "አዲስ መዝሙር" (42፡10)፤ "አዲስ ነገር" (ኢሳ. 43፡19)፤ "አዲስ ስም" (62፡2)፡፡ በኢሳይያስ 65 የምናገኘው አዲስ ነገር--አዲስ የሥርዓት አደረጃጀት ነው፡፡ በመላው የእግዚአብሔር ሕዝቦች መሀል ሰላምና አንድነት ሰፍኖአል፡፡ ከእንግዲህ ኃጢአት ስለሌለ በዐመጻዋና ባለመታዘዟ ምድሪቱን ይረግም የነበረው ኪዳን (ዘሌዋ. 26:14–17፤ ዘዳ. 28:30) ለዘላለም ይወገዳል፡፡ በዚያ ፋንታ  የምንኖትበት ቤት እና የምንበላው ምግብን ጨምሮ የተትረፈረፉ በረከቶች ባለቤት እንሆናለን፡፡

ሕይወት በእንዲህ ያለ ውብ ስፍራ ምን ትመስል ይሆን? የማይሞተውን አካል ከለበስንና ሙሉ ለሙሉ አምላካዊን አምሳል ከወሰድን በኋላ አንዳንዶች ቤተሰቦቻችንንና ወዳጆቻችንን ለይተን ማወቅ እንችል ይሆን--ሲሉ ያስባሉ፡፡ ክርስቶስ ካረገ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ እርሱን ለመገንዘብ አልተቸገሩም፡፡ ማርያም የለየችው በድምፁ ነበር (ዮሐ. 20፡11-16)፡፡ ቶማስ የየሱስን አካል ሲያይ እርሱ መሆኑን ተገንዝቦአል (ዮሐ. 20፡27-28)፡፡ ሁለቱ የኤማሁስ መንገደኛ ደቀ መዛሙርት ከየሱስ ጋር በገበታ ሲቀርቡ በአኳኋኑ አውቀውት ነበር (ሉቃ. 24፡30-31፤35)፡፡ ስለዚህ በትንሣኤ የእኛም አካል ከየሱስ ጋር ተመሳሳይ እስከሆነና አንዳችን ሌላችንን ለይተን ማወቃችንና መገንዘብ መቻላችን እውነት እስከሆነ ድረስ--ወደ ፍጹም ንጽህናና ዘላማዊነት የሚመለሰውን ግንኙነት ከወዲሁ አሻግረን ለመመልከት እንጣር፡፡ በዚያ ስፍራ አብረውን ከሚሆኑ ከምንወዳቸው ቤተሰቦቻችንና ጓደኞቻችን ጋር የሚኖረን ግንኙነት እንደሚቀጥል ተስፋ ማድረግ እንችላለን፡፡

"በዚያን ወቅት የዳኑት ሌሎችን ያውቃሉ፤ እነርሱም ይታወቃሉ፡፡ ራሱ እግዚአብሔር በነፍስ ውስጥ የተከለው ፍቅርና ርኅራኄ--በዚያ ስፍራ መታንና ጣፋጭ ልምምድ ያገኛል፡፡ ቅዱስ ከሆኑ ነገሮች ጋር የሚኖር ንጹህ መንፈሳዊ አንድነት፣ በዘመናት ታማኝ ሆነውና ልብሶቻውን በበጉ ደም አጥበው እንደ በረዶ ያነጹ ጻድቃን ከእግዚአብሔር

የተባረኩ መላእክት ጋር የሚኖራቸው ስምሙ የአብሮነት ሕይወት፣ 'በሰማይና በምድር ያለ ቤተሰብ ሁሉ' (ኤፌ. 3፡15) ቅዱስ በሆነ ኅብረት ይተሳሰራል፡፡ ይህ ለዳኑት የደስታ ምንጭ ይሆናል"—Ellen G. White, The Great Controversy, p. 677.

"ስለዚህ ተስፋ አንቆርጥም፤ ውጫዊው ሰውነታችን እየጠፋ ቢሄድም እንኳ ውስጣዊው ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል፤ ምክንያቱም ቀላልና ጊዜያዊ የሆነው መከራችን ወደር የማይገኝለት ዘላለማዊ ክብር ያስገኝልናል፡፡ ስለዚህ ዐይናችን የሚያተኩረው በሚታየው ነገር ላይ ሳይሆን በማይታየው ላይ ነው፤ የሚታየው ጊዜያዊ ነውና፤ የማይታየው ግን ዘላለማዊ ነው፡፡"

## ዓርብ

## ታህሳስ 19

*ተጨማሪ ሃሳብ*፡ Ellen G. White, " 'Behold, I Come Quickly,' " pp. 355–359, in Counsels for the Church. Read the articles "Resurrection," pp. 1082–1084, and "Heaven and New Earth," pp. 863, 864, in The Ellen G. White Encyclopedia.

የጌታችን ትንሣኤና ዕርገት ቅዱሳን በሞትና በመቃብር ላይ ባለ ድል መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ነው፡፡ የባህሪያቸው መገለጫ የሆነውን ልብሶቻቸውን በበጉ ደም አጥበው ለሚያነጹ ሰማይ ክፍት መሆኑን የሚያሳይ የተስፋ ቃል ነው፡፡ የሱስ ሰብዓዊውን ዘር በመወከል ወደ አብ አረገ፡፡ አምላካዊውን አምሳል የሚያንጸባርቁ ክብሩን ይጋሩ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፡፡

"ለምድር መናኞች የተዘጋጀ ሰማያዊ ቤት አለ፡፡ ለዳኑት የጽድቅ ልብስ፣ አክሊልና የድላቸው ማብሰሪያ የዘንባባ ዝንጣፊ ተዘጋጅቶአል፡፡ በዚህ ዓለም ግራ አጋብተውን የነበሩ ነገሮች ሁሉ በእግዚአብሔር ቸርነት በአዲሲቱ ምድር ግለጽ ይሆኑልናል፡፡ ለማስተዋል አስቸጋሪ የነበሩ ነገሮች ሁሉ ማብራሪያ ያገኛሉ፡፡ የጸጋ ምስጢር ወለል ብሎ በፊታችን ይገለጣል፡፡ ግራ መጋባት፣ የታጠፉ ቃሎችንና ተስፋዎችን ብቻ ያውቅ የነበረው ውሱኑ አእምሮአችን እጅግ ፍጹምና ውቡ የሆነውን ኅብር ይመለከታል፡ ፡ ከዉሱን ባሻገር--መጨረሻ የሌለውን ፍቅር ተሞክሮ በዚያን ጊዜ እናውቃን፡፡ ነገሮች ለእኛ በጎ እንዲሰለጥኑ የሚሠራውን፣ በርኅረኄ የተሞላ ጥንቃቄውን መገንዘብ ስንጀምር በቃላት ሊገለጽ በማይችል ሐሴትና ክብር እንሞላለን፡፡"—Ellen G. White, Counsels for the Church, p. 358.

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

1. ምንም እንኳ ክርስቲያኖች (ሁሉም ባይኑም) በየሱስ ዳግም ምጽአት ብናምንም፤ ነገር ግን በዚህ ዙሪያ ለየት ያለው የአድቬንቲስቶች ተስፋ ምንድን ነው?

2. በአንድ ወቅት ሁሉት ዓሣዎች እየዋኙ እያለ አንደኛው “ውሃው እንዴት ነው?” ብሎ ቢጠይቅ ሌላው “ለመሆኑ ውሃ ምንድን ነው?” በማለት ጥያቄውን በጥያቄ መለሰ ይባላል፡፡ ለምሳሌ እኛ በኃጢአት የተወለድን፣ በኃጢአት የተሞላንና በኃጢአተኛ ዓለም ውስጥ የምንኖር እንደመሆናችን በዚያ ግሩም አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር የሚኖረንን ሕልውና ማስተዋል የምንችለው እንዴት ነው? የቱንም ዓይነት ዉሱንነት ቢኖረንም--ምን ሊመስል እንደሚችል በዐይነ ኅሊናችን መመልከት አንችል ይሆን?

3. በአዲሲቱ ምድር የሚኖረን ሕልውና የቱንም ዓይነት ሊሆን ቢችል ከእያንዳንዱ ጋር በኅብር መኖራችን ጥያቄ ውስጥ አይገባም፡፡ ራሳችንን ለዚያ ጊዜ ለማዘጋጀት አሁን ምን ማድረግ እንችላለን?

**ማጠቃለያ**፡ ይህች ምድር ዳግም እንደምትፈጠርና ለዘላለም ከኃጢአት ሥር እንደምትነጻ መጽሐፍ ቅዱስ በይፋ ይናገራል፡፡ በመጨረሻ ሰብዓዊው ዘር አስቀድሞ ወደ ታለመለት የቀደመ ንጽህናው ይመለሳል፡፡ ሰው ሁሉ ስምሙ ሆኖ በአንድ ላይ ይኖራል፡፡ ምንም እንኳ ዛሬ ከክርስቶስ ጋር ያለን መንፈሳዊ አንድነት ፍንትው ብሎ የሚታይ ባይሆንም፤ የዚያን ጊዜ ግን ሕያውና ዘላለማዊ ሐቅ ይሆናል፡፡

# የትንቢት መንፈስ መጻሕፍትን ተርጉሞና አሳትሞ ማሰራጨት ለሚፈልጉ ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች የተሠጠ

# ማሳሰቢያ

የትንቢት መንፈስ *(Spirit of Prophecy - SOP)* መጻሕፍት በሙሉ የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት አለም አቀፍ ቤተክርስቲያን ንብረት ናቸው፡፡

እነዚህን ጽሁፎች በከፊልም ሆነ በሙሉ ወደ አማርኛም ሆነ ወደ ተለያዩ የአገሪቱ ቋንቋዎች በማስተርጎምና በማሳተም ለማዳረስ የሚፈልግ ግለስብም ሆነ ድርጅት፣ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት ለኢትዮጵያ ዩኒየን ሚሽን የጽሁፍ ክፍል ጥያቄውን በጽሑፍ በማቅረብና በአካልም ቀርቦ በመወያየት ወደ ሰምምነት ከተደረሰ በኋላ ትርጉሙ፣ ህትመቱና ስርጭቱ በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ተከናውኖ ሥራውን መፈፀም ይቻላል፡፡

በዚሁ መሠረት የትንቢት መንፈስ ጽሁፎችን በማሳተም ወንጌልን ለማዳረስ የሚጥሩ ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች በእጅጉ ይበረታታሉ፡፡

ሆኖም ግን ይህንን በመተላለፍ ያለ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን ፈቃድ በቤተክርስቲያኗ ስም የትንቢት መንፈስ ጽሁፎችን አሳትሞ ማስራጨት፣ በአገሪቱም ሆነ በዓለም ዓቀፍ የሥነ ጽሁፍ ህግ ያስጠይቃል፡፡ በተጨማሪም ድርጅቱ እያስተረጎመ ያለውን መጽሐፍ ሌላ አካል ተመሳሳዩን መጽሐፍ በመተርጎም ላልተፈለገ የጊዜ፣ የጉልበትና የገንዘብ ወጪም ይዳርጋል፡፡

ስለሆነም የቤተክርስቲያኗ ህግና መተዳደሪያ ደንብ በሚፈቅደው መሠረት ሁላችንም ጽሁፎችን በማሳተምም ሆነ በማሰራጨት የሶስቱን መላዕክት መልዕክት ለማዳረስ እንድንችል ጌታ ይርዳን፡፡

***ድርጅቱ***

# ዓለም አቀፍ አድቬንቲስት ሬዲዮ
# የተስፋ ድምፅ

## ትግርኛ

ጠዋት 12:00 - 12:30
**9530 Khz 31** ሜ.ባንድ
ማታ 1:30 - 2:00
**15130Khz 19** ሜ.ባንድ
አየር ሞገድ

**አድራሻ**

ስልክ **+251 115 511199**
የውስጥ መስመር **205**
ወይም
**+251 910 145105**

## አማርኛ

ጠዋት 12:30 - 1:00
**15500 Khz 19** ሜ.ባንድ
ማታ 2:00 - 2:30
**17570Khz 16** ሜ.ባንድ
አየር ሞገድ

**አድራሻ**

ስልክ **+251 115 511199**
የውስጥ መስመር **242**
ወይም
**+251 911 137222**

ፖ.ሳ.ቁ **145** አዲስ አበባ

## ኦሮምኛ

ጠዋት 12:00 - 12:30
**15500 Khz 19** ሜ.ባንድ
ማታ 2:30 - 3:00
**15155 Khz 19** ሜ.ባንድ አየር ሞገድ

**አድራሻ**

ስልክ **+251 115 511199**
የውስጥ መስመር **237**
ወይም **+251 921 600938**

---

የተላለፉ ፕሮግራሞችን እንደገና ለማዳመጥ ከመረጃ መረባችን www.awr.org ላይ በመግባት እንደገና ማግኘት ይችላሉ፡፡

---

የዓለም አቀፍ አድቬንቲስት ሬዲዮ የ24 ሰዓት
የአማርኛ ቋንቋ ስርጭትን በክርስቲያን ቻናል ጣቢያ
ውስጥ ከዚህ በታች በተቀመጠው መሰረት ያገኙታል

HC The Voice of Hope
Frequency: 12574
Symbol Rate: 09700
Polarity: Horizontal
Satellite: Intel Sat 68.5E
LNB: KU BAND

በተጨማሪም
በአሜሪካ ያሉ አድማጮቻችን 712 432 9970
በመደወል እንዲሁም
በእንግሊዝ ያሉ 033 001 03890 በመደወል
ፕሮግራሞቻችንን በማንኛውም ሰዓት
ማዳመጥ ይችላሉ

**የዓለም አቀፍ አድቬንቲስት ሬዲዮ የተስፋን ድምፅ ያዳምጡ**
**ለወዳጆችዎ በማስተዋወቅና በመጋበዝ የበረከቱ ተካፋይ ይሁኑ**